

# መንትያዎቹ ክስተቶች



ሩሂ ተቋም





መጽሐፍ 4

# መንትያዎቹ ክስተቶች

ሩሂ ተቋም

## ተከታታዮቹ መፃሕፍት፡–

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በሩሂ ተቋም ታቅደው እና ተዘጋጅተው በተከታታይ የቀረቡ መጽሐፎች ናቸው። መፃሕፍቱ በስልታዊ ጥረት ማህበረሰባቸውን እንዲያገለግሉ የሚያስችሏቸውን ችሎታዎች እንዲያዳብሩ ወጣቶች እና አዋቂዎች እንዲጠቀሙባቸው የቀረቡ የዋናው ተከታታይ ኮርሶች አካል ናቸው። የሩሂ ተቋም የባሃኢ ሕፃናት ክፍሎች አስተማሪዎችን ለማሰልጠን ከተዘጋጁት ከሦስተኛው መፅሐፍ በቅርን ጫፍ በተከታታይ መልክ የወጡትን እያበለፀገ፣ በተጨማሪ ከአምስተኛው መፅሐፍ ለታዳጊ ወጣቶች ቡድኖች አነቃቂዎች ለማፍራት የሚያገለግል ተከታታይ ፅሑፎችን እያዘጋጀ ይገኛል። እነዚህም ከዚህ በታች በተቀመጡት ዝርዝሮች ስር ይገኛሉ። በመስኩ የሚገኘው ተሞክሮ እያደገ መጥቶ ለውጥ ሲገኝ ሊለወጥ ይችላል፣ እና እየዳበሩ ያሉት የስርዓተ ትምህርት ቁምነገሮች እየተደመሩ ሄደው በስፋት መጠ ቀም የመጀመር ደረጃ ላይ ሲደረስ፣ ሌሎች ተጨማሪ አርዕስቶች እየተጨማመሩ የመጽሐፉ ዝርዝር እየተለወጠ ሊመጣ እንደሚችል ሊሰመርበት ይገባል።

መጽሐፍ 1 *በመንፈሳዊ ህይወት ላይ እሰብታዎች*

መጽሐፍ 2 *ለአገልግሎት መነሳት*

መጽሐፍ 3 *የሕፃናት ትምህርት፤ አንደኛ ክፍል*

*የሕፃናት ትምህርት፤ ሁለተኛ ክፍል (ቅርንጫፍ ኮርስ)*

*የሕፃናት ትምህርት፤ ሦስተኛ ክፍል (ቅርንጫፍ ኮርስ)*

*የሕፃናት ትምህርት፤ አራተኛ ክፍል (ቅርንጫፍ ኮርስ)*

መጽሐፍ 4 *መንትያዎቹ ክስተቶች*

መጽሐፍ 5 *የታዳጊ ወጣቶች ችሎታዎች እንዲወጣ ማድረግ*

*የመነሻ ግፊት፡– የመፅሐፍ 5 የመጀመሪያው ቅርንጫፍ ኮርስ*

*ምህዳሩን ማስፋት፡– የመፅሐፍ 5 ሁለተኛው ቅርንጫፍ ኮርስ*

መጽሐፍ 6 *እምነቱን ማስተማር*

መጽሐፍ 7 *በአገልግሎት መንገድ ላይ አብሮ መጓዝ*

መጽሐፍ 8 *የባሃኡላህ ቃል ኪዳን*

መጽሐፍ 9 *ታሪካዊ እይታ ማግኘት*

መጽሐፍ 10 *ህይወታማ ማህበረሰብን መገንባት*

መጽሐፍ 11 *ቁሣዊ ሁኔታዎች*

መጽሐፍ 12 *ቤተሰብ እና ማህበረሠብ*

መጽሐፍ 13 *በማህበራዊ ሥራ መጠመድ*

መጽሐፍ 14 *በህዝባዊ ውይይቶች ላይ መሣተፍ።*

የመጀመሪያው እትም 1990፣ 1996፣ 2021 በሩሂ ተቋም፣ ኮሎምቢያ

© የአዘጋጁ መብት በህግ የተጠበቀ ነው 1.1.1. PE published December 1996

ህትመት 2.1.1.PE December 2021

ISBN 978-958-53332-3-9

© 2007, 2023 by Ruhi Foundation, Colombia

All rights reserved. 2.1.1.PE in Amharic in May 2023

Ruhi Institute

Cali, colombia

Email: inistituto@ruhi.org

Website: www.ruhi.org

# ማውጫ


ለአስጠኚው ጥቂት ሐሳቦች……………………..v

የዚህ ቀን ታላቅነት…………………………….1

የባብ ህይወት………………………………….15

የባሃኡላህ ህይወት……………………………..45

## ለአስጠኚው ጥቂት ሐሳቦች

የሩሂ ተቋም በሚሰጠው አራተኛው ኮርስ ላይ ተሳታፊዎቹ ሲደርሱ፣ በዋናዎቹ ተከታታይ ጥናቶች በተከፈተው የግልጋሎት መስክ ያለጥርጥር እየተራመዱ እንደሆነ እሙን ነው። ወደ መጽሐፍ 1 ሲገቡ የትኛውም ዓይነት ቀደምት ሁናቴዎች ይኑራቸው፣ በባሃኡላህ ፅሑፎች ውስጥ ለተዘረዘሩት ግለሰባዊ ሆነ የጋራ እድገት ራዕዮችን ለመተግበር ቁርጠኞች ናቸው። ይህንን በማድረግ፣ የእርሱን (ባሃኡላህን) ቃላቶች በየዕለቱ የማንበብ ልማድ ጀምረዋል እናም እርሱ በገለፃቸው ፀሎቶች እና ምክሮች በፀሎተ ሱታፌ ሆነ በጥሞና በማሰላሰል ጊዜ፣ መንፈሳዊ ጤናማነትን መጤን እየቻሉ ነው። ከጓደኞ ቻቸው እና ከሚያውቋቸው ጋር እርሱ በገለፃቸው መንፈሳዊ መርሆዎች ላይ በመንደራቸው ወይም በጎረቤቶቻቸው ያሉ ቤቶች በመጎብኘት እርሱ ዓለምን እንደ አዲስ ለማነፅ የተነሳው ያስቀመጣቸውን ምክሮች ለመወያየት በንግግር መጠመድን እየተማሩ ነው። አንዳንዶች የሕፃናት መንፈሳዊ ትምህርት ክፍሎችን እያስተማሩ ነው። እርግጥ ነው እነዚያ በግልጋሎት መንገድ የሚጓዙት፣ የእርሱ ህይወትም ሆነ ትምህርቱ እጅግ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሮባቸው እና የእርሱ ግልፀትን የቀስ በቀስ መገለፅ እና ውልደት ታሪካዊ ሁኔታዎችን ጠለቅ ያለ ዋጋ ሰጥተው ለማድነቅ የሚፈልጉት ዝግጁነትና፣ ጉጉት ይኖራቸዋል። መጽሐፍ 4[ትን] ያዋቀሩት የሦስቱ ምዕራፎች ትልም ለተሳታፊዎች ይህንን እድል ለመስ ጠት ነው።

የእግዚአብሔር ክስተት ሕይወት በመሠረቱ ከሌሎች ሰዎች ሕይወት የተለየ ሲሆን፣ ታላቅነቱም በእርሱ ዙሪያ የተካሄዱትን ክንውኖችን በማጥናት ብቻ ለመረዳት አይቻልም። በምድር ላይ በሚኖርባቸው ዓመታት ወቅት የእርሱ ለየት ያሉ ኃይሎች በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ እውነታ ውስጥ ጥልቅ ለውጥ በማምጣት እና የሰውን ልጅን ወደ አዲስ የእድገት ደረጃ በማስወንጨፍ፣ በጠቅላላው ዓለም ላይ ያሰርፃሉ። በውጫዊ ዓይኖች ሲታይ የእርሱ ሕይወት በመከራ የተሞላ ቢመስልም፣ በመንፈሳዊ ዓይኖች ሲታይ ግን በእያንዳንዱ ድርጊት ውስጥ የክብሩና የግርማውን ምልክቶች ይስተ ዋላሉ። በተከታታይ ባሉት በሁለተኛው እና በሦስተኛው ርዕሰ-ምዕራፎች ውስጥ የተብራሩትን፣ የባብ እና የባሃኡላህን የሕይወት ታሪኮች እንዲያጠኑ ተሳታፊዎችን ለማዘጋጀት፣ የመጀመሪያው ርዕሰ- ምዕራፍ እየኖርንበት ያለውን የቀኑን ታላቅነት፣ ማለትም የሁለቱን የአምላክ ክስተቶች የተገለፁበትን ቀን፣ እንዲያጤኑ ይጠይቃቸዋል።

ርዕሰ-ምዕራፉ እጅግ በጣም አጭር ነው። ከባሃኢ ፅሁፎች ስለዚህ ቀን ታላቅነት የሚናገሩ ጠቀም ያሉ ምንባቦችን እና ጥቂት ቀላል መልመጃዎችን ይጠቀልላል። ከሌሎቹ ርዕሰ ምዕራፎች ጋር በአንድ ላይ፣ ተሳታፊዎቹ በታሪክ ውስጥ የዚህን ጊዜ ሁኔታ ላይ እንዲያሰላስሉ ብቻ ሳይሆን፣ ከረዥም ጊዜ በኋላ የሰው ልጅ አንድነት እውን ሲሆን፣ የዚህ እውቀት ኃላፊነት በእያንዳንዳችን ላይ የሚጥለውን ጫና ለመረዳት ያስችላቸዋል። የመፅሐፍ 4 አስጠኚ በመሆን እያገለገሉ ላሉት አስጠኚዎች መገንዘብ ያለባቸው፡ ተሳታፊዎቹ ከበፊቱ ኮርሶች ካካበቷቸው ጥናቶች እና በየማህበረሰቦቻቸው ሕይወት ተሳትፎ ልምዶች፣ የእምነቱ መሠረታዊ አንዳንድ ጭብጦች ላይ ግንዛቤ አላቸው ተብሎ ይገመታል። ሁሉም የቀድሞ ሃይማኖቶች መፃሕፍት ቃል ስለተገባለት የአምላክ ቀን፣ በምድር ላይ ሰላም እና ፍትሕ የሚመሠረትበትን ቀን ጠቅሰዋል፣ ባሃኡላህ የዓለም ዓቀፋዊ ሰላም ሰንደቅ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ እና ለሰው ልጅ መሠረታዊ አንድነት እውቅና እንዲሰጥ ጥሪ አድርጓል፣ የእርሱ ማህበረሰብ ተከታዮች በአዲሱ የዓለም ስርዓት በሆኑት "የዚህ ቀን ታላቅነት" በሚለው ምዕራፍ ውስጥ በተካተቱት— ላይ የእይታ ትኩረታቸውን እንዲያደርጉ ጥሪ አስተላልፏል።

የሚቀጥሉት ሁለት ርዕሰ-ምዕራፎች፣ ባብ እምነቱን ሲያውጅ በዚያች የሁኔታዎች ገድል እምነ ቱን ወደፊት ባራመደው፣ የመጪው እድል ወሳኝ በሆነው፣ እ.ኤ.አ. ከ1844 ምሽት ጀምሮ ከሃምሳ ዓመት በኋላ ጠዋት ጎህ ሳይቀድ በነበረው ሰዓት የባሃኡላህ መንፈስ ከምድራዊ ኑሮ ተላቅቆ ወደ ሰማይ ያረገበትን ጊዜ ይተርካሉ። ይህ የባሃኡላህ ታሪክ ቅደም ተከተላዊ አወራረድ ትረካ፣ በተለይ በባሃኡላህ ህይወት ላይ በሦስተኛው ምዕራፍ፣ በአንዳንድ መንፈሳዊ ጭብጦች ከክስተቱ ማንነት ጋር በተያያዘ ከቅዱሳን ፅሑፎቹ ምንባቦች ጋር የሚመጋገቡ ናቸው። ከአብዛኛዎቹ ምንባቦች በኋላ መልመጃዎች ይከተላሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ በግል ለማሰላሰል እና በድጋሚ ለማንበብ ሲባል ተቀምጠዋል። አስጠኚው ደግሞ ተሳታፊዎቹ ምዕራፎቹን ሲያጠኑ በባብ እና በባሃኡላህ ሕይወት ዙሪያ ጠለቅ ያለ እና ስልታዊ እውቀትን፣ እንደ ዋነኛ ጠቀሜታ ደግሞ የተብራሩት ከኩነቶቹ ጋር ከፍተኛ እና ጥልቅ ጥምረት ያላቸውን መንፈሳዊ እውነታዎችን ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

ቡድኑን ለሁለተኛው እና ለሦስተኛ ርዕሰ-ምዕራፎች ለማዘጋጀት፣ አስጠኚው መንፈሳዊ ጭብጦች ላይ ጥንቃቄ የተሞላው እሳቤዎችን ማድረግ አለበት። ከእነዚህም መካከል፣ ለምሳሌ፣ እያንዳንዱ መለኮታዊ ብርሃን ሰጪ ለሰብዓዊው ዓለም እንዲከሰት የተደረገው በእራሱ ምርጫ ሳይሆን ነገር ግን በአምላክ ፈቃድ እንደሆነ፣ አምላክም ተፈጥሯዊ በሆነ እውቀት እንደአደላቸው፣ እርሱን ለመገንዘብ የመጀመሪያዎቹ የሆኑትም ታላላቅ ጀግንነትንና የእምነቱን የመለወጥ ኃይል የሚመሰክሩ ሥራዎችን ለመሥራት እንደታጩ ሲሆን፣ ክስተቶቹም የሰውን ዘር ወደ እውነት እንዲመሩ እና የአምላክን ፈቃድ እና ዓላማ ለፍጡራኑ እንዲያሳውቁ በሕይወታቸው ስቃይን እንዲቀበሉ እና እንዲችሉ፤ የትኛውም ኃይል ቢኖረው፣ በምድር ላይ ያለ ምንም ዓይነት ኃይል፣ እርሱ በአደራ የተሰጠውን ተልዕኮውን ከማሳካት፣ የእርሱን ተፅዕኖ ሊያኮስስ ወይም ሊከላከል እንደማይቻላቸው መሆኑን ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በሦስተኛው ርዕሰ- ምዕራፍ ውስጥ የሚስተናገደው አንድ አስፈላጊ ጽንሰ-ሐሳብ ቀውስ እና ድል ነው። ይህንን ጭብጥ መረዳት—ማለትም በአምላክ ሃይማኖት እያንዳንዱ ቀውስ የሚያገለግለው በውስጡ የታጨቀውን አብሮ ያለውን ኃይል ለመልቀቅ ነው—ለእነዚያ በአገልግሎት ጎዳና ለመጓዝ ለሚሹት ለሁላቸውም በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምናልባትም የእምነቱን ታሪክ ተገቢውን ቦታ እንዲሰጡት ብቻ ሳይሆን፣ ሳይቋረጥ እየተገለጠ እየመጣ ያለውን በተከታታይ ቀውስ እና ድል እያለፈ ያለውን እምነት ለጎረቤቶቻቸውንና ለመንደራቸው እያበረከቱት ካለው አስተዋፅዖ አኳያ አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

በእንደነዚህ ዓይነቶቹ ጭብጦች ላይ ማሰላሰሉ፣ ተሳታፊዎች በባብ እና ባሃኡላህ ሕይወት ላይ ከተያያዙት ኩነቶች ጋር በማዛመድ ለሰው ልጅ ያላቸውን የጋለ ፍቅር እና የተከታታይ ግልፀታቸው ተልዕኮ ባህርይ ጠልቀው እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል። ልቦቻቸውን ወደ አምላክ ክስተቶች እንዲሳብ እና በእርሱ እምነት ግልጋሎት ጎዳና እርምጃዎቻቸውን እንዲያጠናክሩም ያገለግላል። በመፅሐፍ ሁለት ውስጥ የእርሱን ሕይወት ታሪክ በማጥናት እያሳደጉ የመጡትን ችሎታ፣ ስለባሃኡላህ ሰብዕና እና ስለ እርሱ ግልፀት ከሌሎች ጋር ለመወያየት የሚያስችላቸውን ዓቅም እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል። የእርሱን ሕይወት ታሪክ እና የእርሱን ብሥራት ነጋሪ ሕይወት የአድማጩን ልብ እስኪነካ ድረስ የመተረክ ችሎታ ከሁሉም በላይ የሚንተራሰው፣ በተተረኩት ታሪኮች መንፈሳዊ ጠቀሜታን በመረዳት ላይ ነው። አዎን፣ ከፍተኛ የሆነ የተግባር ልምምድ ይጠይቃል፣ አስጠኚውም ተሳታፊዎቹ የመንትያዎቹን ክስተቶች የሕይወት ኩነቶች ክፍል እርስ በእርሳቸው እንዲወያዩ በቂ አጋጣሚ እና እድል ስለማግኘታ ቸው እርግጠኛ መሆን አለበት። አንዳንድ ተሳታፊዎች ቤቶችን በተከታታይ በሚደረጉት ጉብኝት ወቅት ከጓደኞቻቸው እና ከጎረቤቶቻቸው ጋር በሚደረጉት ጭውውት ውስጥ የተማሩትን ለማስተዋወቅ ይችሉ ይሆናል። ለእነዚህ እና ለሌሎች አጋጣሚዎች የሚረዳ፣ በሁለቱም የታሪክ ምዕራፎች ላይ የሚያጠነጥኑ፣ አጫጭር ማብራሪያ የታከሉበቸው ስዕላዊ

መግለጨዎች ተጨምረዋል። ከተፈለገ፣ ማስታዎሻዎቹ ሊባዙ ይችላሉ፣ ወይም ከሩሂ ተቋም የህዝብ ድረ ገፅ ላይ ለማውረድ ይቻላል።

እዚህ ላይ ከመንትያ ክስተቶች ህይወት ጋር የተያያዙ ኩነቶች የተመዘገቡት በጎርጎሪዮሳዊው ቀን አቆጣጠር መሠረት እንደሆነ መጥቀስ አስፈላጊ ነው። አሁን ግን የባዲ የቀን መቁጠሪያ የተደነገገውን ደንብ በመከተል እጅግ አስፈላጊዎቹ በዓላት የሚከበሩት በባሃኢ ቀናት አቆጣጠር ነው። የግሪጎሪያን አቻው ከዓመት ዓመት ይለያይ ይሆናል። አስጠኚው በዚህ ጉዳይ ላይ ከቡድኑ አባላት ጋር ወደ እዚህ ውይይት ውስጥ መግባት የለበትም፤ በየማህበረሰባቸው የበዓል ቀናትን እያከበሩ ሲመጡ፣ ቀስ በቀስ ለእነርሱ ግልፅ እየሆነ ይመጣል። እርግጥ ነው በእነዚህ እና ሌሎች የጋራ እንቅስቃሴዎች፣ የክስተቶቹ ሕይወት ኩነቶች እና የእምነቱ የመጀመሪያዎቹ ቀናት አብዛኛውን ጊዜ ሲዘረዘሩ፣ ይህ ተሳታፊዎቹን ታሪካዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ ተጨማሪ እይታዎች በመስጠት በመንደሮቻቸው ወይም በሠፈሮቻቸው ዛሬ እያራመዷቸው ባሉት ሂደቶች ተጨማሪ ግፊት ይሰጣሉ።



# የዚህ ቀን ታላቅነት

## ዓላማ

ስለዚህ ቀን ታላቅነትና ለሰው ልጅ ስለሰነቀው ተስፋ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ለማግኘት።

## ምዕራፍ 1

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እኛ ልዩ በሆነ ክፍለ ዘመን እንድንኖር ተባርከናል—በባሃኡላህ እና በእርሱ ብስራት ነጋሪ፣ በባብ፣ ሁሉንም የተፈጠሩ ነገሮች ለማደስ በመጡ፣በሁለት የአምላክ ክስተቶች የተዋጀ ቀን ነው:: እነርሱ በለቀቋቸው ኃይሎች እንዴት ህብረተሰቡን እየቀየሩ እንደሆነ፣ እንዴት አሮጌው ዓለም እያለፈ በምትኩ አዲስ ዓለም እየተመሠረተ እንደሆነ፣ በእራሳችን ዓይኖች እየተመለከትን ነው:: አዎን፣ እውነት ነው፣ እየሞተ ያለው አሮጌው ሥርዓት ሊነገሩ በማይቻሉ መከራዎች የታጀበ ነው:: ነገር ግን፣ በዚህ በሚካሄደው ውድመት እና ስቃይ ሳንነካ እና በጥልቅ ሳናዝን አልቀረንም:: ነገር ግን፣ ዓለም ባሃኡላህ ወደ ተነበየላት ክቡራማው ስልጣኔ ያለማቋረጥ እየተጓዘች እንደሆነ ስለምናውቅ፣ በሁኔታዎቹ አንወናበድም::

ይህ የአምላክ ቀን ነው:: በአምላክ ቀን መኖር ከግምት በላይ የሆነ ፀጋ ነው፤ በዚያው ልክ ከፍተኛ ኃላፊነትን ያስከትላል:: የዚህን ፀጋ ይዘት በትክክል ለመረዳት እና ለማወቅ እና ግዴታዎቻችንን በወጤታማነት ለመወጣት፣ በዚህ ቀን ጠቀሜታ እና ታላቅነት ላይ አዘውትረን ማሰላሰል እና አምላክ ለሰው ልጅ ባለው ዓላማ ላይ ያለማሰለስ መመርመር ይኖርብናል:: በአንፃራዊነቱ አጭር ቢሆንም፣ የዚህ ምዕራፍ ዓላማ እየኖርንበት ባለነው የዚህ ዘመን ጠቀሜታ ላይ ከባሃኢ ፅሑፎች ጥቂት ምንባቦችን በማጣቀስ እናንተን ለማስተዋወቅ ነው:: እነዚህን ምንባቦች ከማጥናታችሁ በፊት እና በትርጉሞቹ ላይ ከማሰላሰላችሁ በፊት፣ ከቡድናችሁ አባላት ጋር ዛሬ አምላክ ለሰው ልጆች አልሞ እንዲያከናውኑ ካዘዛቸው አንዳንዶቹን ጉዳዮች መወያየቱ ጠቃሚ ይሆናል:: እንደምናውቀው፣ የዓለም ህዝቦችን እንደ አንድ ዓለም ዓቀፍ ቤተሰብ መዋሃድ፣ በዚህ ዘመን ልናሳካው ከተነሳንበት ዋነኛው ግብ አንዱ ነው:: ሌሎቹስ ጥቂቶቹ ምን ምን ናቸው?

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

## ምዕራፍ 2

ባሃኡላህ እንዲህ ይላል :–

> **"በእውነት እላችኋለሁ ይህ ቀን የሰው ዘር በተስፋ ሲጠብቅ የነበረውን ፊት ለማየት፣ ድምፁንም ለመስማት የሚችልበት ቀን ነው:: የእግዚአብሔር ጥሪ ቀርቧል፣ የእርሱም ገፅታ ብርሃን በሰዎች ላይ አብርቷል:: እያንዳንዱ ሰው የእያንዳንዱን ከንቱ ቃል ቅሪት ከልቡ ፅላት ማንፃት እና በቀናና እና በማያወላውል አእምሮ ወደ እርሱ ግልፀት ምልክቶች፣ ወደ እርሱ መልዕክት ማስረጃዎች እና ወደ እርሱ ክብር መገለጫዎች አትኩሮ ማየት አለበት::"[1]**

1. ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች ያሟሉ:–

ሀ. በዚህ ቀን ያ ቃል የተገባለትን_______________ ማየት፣ እና __________ መስማት እንችላለን፡፡

ለ. ___________________ቀርቧል__________________በሰዎች ላይ አብርቷል፡፡

ሐ. እያንዳንዱ ሰው ________________ ቅሪት ________________ ማንፃት እና ______________________________ አእምሮ ወደ እርሱ _______________ ምልክቶች እና ወደ እርሱ __________________ አትኩሮ ማየት አለበት፡፡

2. ከሚከተሉት ውስጥ ሰዎች የባሃኡላህን እውነታ እንዳያውቁ የሚያደርጋቸው አስተሳሰቦች የትኞቹ ናቸው?

—— “ለእኔ የቤተሰቦቼ እምነት ይበቃኛል፡፡”

—— “የሰው ልጅ የመንፈሳዊ የፀደይ ወቅት ፍለጋ ላይ ነው፡፡”

—— “ሃይማኖት ለእነዚያ ለሚፈልጉት መልካም ነገር ነው፡፡”

—— “ሃይማኖት የግጭት መንስዔ በመሆኑ ብቻ፣ መወገድ አለበት፡፡”

—— “እኔ እንደሚታየኝ ሁሉም ሃይማኖቶች ከሞላ ጎደል አንድ ስለሆኑ የትኛውንም ብንከተል ለውጥ አናመጣም፡፡”

—— “አምላክ የሰውን ልጅ እርግፍ አድርጎ ትቶታል፡፡”

—— “ሁሉም ነገሮች ሃይማኖትም ጭምር መታደስ አለባቸው፡፡”

—— “ሣይንስ እግዚአብሔር እንደሌለ አረጋግጧል፡፡ የማመዛዘን ችሎታችንን ከተጠቀምን ችግሮቻችን ሁሉ ሊፈቱ ይችላሉ፡፡”

—— “እራሴን በማንኛውም ሃይማኖት ማስገዛት አልፈልግም፡፡”

—— “መንፈሳዊ ለመሆን ሃይማኖት አያስፈልገኝም፡፡”

—— “እያንዳንዱ ግለሰብ አምላኩን በራሱ መንገድ እንዲያውቅ ሊፈቀድለት ይገባል፡፡” ለምን መልዕክተኛ ስፈልገዋል፡፡

—— “የራሳችን ሃይማኖት ቅዱሳን ፅሑፎች አሉን፡፡ አዲስ ክስተት የሚያስፈልግበት ምክንያት የለም፡፡”

3. ከሚከተሉት መካከል የትኞቹ የባሃኡላህ ክብር ምልክቶች ናቸው?

—— አንደበተ ርዕቱእነቱ፡፡

—— የቃላቶቹ ስርስሮ የመግባት ኃይል፡፡

—— ከእርሱ ፅሁፎች ጋር የተገናኙ ልቦች ውስጥ የተከናወነው መለወጥ፡፡

—— የእርሱ ትምህርቶች በሰዎች አስተሳሰብ እና ተግባራቸው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ፡፡

—— የእርሱ ትምህርቶች በታሪክ አቅጣጫ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ፡፡

—— ለሰው ልጅ የወደፊት እጣ ፈንታ የእርሱ ልብ የሚማርከው ራዕዩ፡፡

—— ለሰው ልጅ ሲል የተቀበላቸው መከራዎች እና ስቃዮች፡፡

—— የምድራዊ ኃይሎች ጭቆና ቢወርድበትም የተቀዳጀው የእርሱ ሉዓላዊነት፡፡

—— የሁሉንም ዓይነት ሃይማኖት እና የመደብ ጀርባ ያላቸውን ህዝቦች አንድ የማድረግ የአስተምህሮቱ ኃይል፡፡

—— የእርሱ ተከታዮች ማህበረሰብ ያላሰለሰ እድገት፡፡

—— እያንዳንዱን እንቅፋት በመቋቋም የእርሱን ሃይማኖት አንድነት ማስጠበቅ የቻለው የቃል ኪዳኑ ኃይል፡፡

—— የአስተዳደር ሥርዓቱ እፁብነት፡፡

—— እርሱ በራዕዩ በተለመው መንገድ የዓለም ጉዞ፡፡

## ምዕራፍ 3

ባሃኡላህ እንዲህ ይላል:–

**"ይህ ቀን በእርግጥ ታላቅ ቀን ነው! በሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቀን ተብሎ መወሳቱ ታላቅነቱን ያረጋግጣል፡፡ የእያንዳንዱ የእግዚአብሔር ነቢይ፣ የእያንዳንዱም መለኮታዊ መልዕክተኛ ነፍስ ለዚሁ ድንቅ ቀን ተጠምቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ልዩ ልዩ የምድር ወገኖች ሁሉ ሊደርሱበት ናፍቀዋል፡፡ ሆኖም ወዲያው የግልፀት የቀኑ ኮከብ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሰማይ ራሱን እንደከሰተ፣ ፍፁም ኃያሉ ሊመራቸው ከፈቀደው በስተቀር ሌሎች ሁሉም ፈዘው እና ግዴለሽ ሆነው ተገኙ፡፡"[2]**

1. ከዚህ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሟሉ :–

ሀ. ይህ ቀን በእርግጥ ነው! በሁሉም____________________ የ ____________________

____________________ ተብሎ መወሳቱ ታላቅነቱን ያረጋግጣል፡፡

ለ. የእያንዳንዱ ____________________________፣ የእያንዳንዱም ______________________________
ነፍስ ለዚሁ _____________ ቀን _____________________ ።

ሐ. በተመሳሳይ ሁኔታ _____________ የምድር _______________ ሁሉ _______________________።

መ. ሆኖም ወዲያው የግልፀቱ ቀን ኮከብ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሰማይ __________________________
ፍፁም ______________________________________________ ሌሎቹ ሁሉም ___________________
እና ____________________________ሆነው ተገኙ።።

2. ከላይ ከተጠቀሰው ምንባብ፣ ይህ የፍፃሜው ቀን እንደሆነ ግልፅ ነው። ሁሉም የእግዚአብሔር ነቢያት እና መልዕክተኞች በምድር ላይ ሰላም እና ስምሙነት የሚመጣበት ቀን እንደሆነ አስቀድመው ተንብየዋል። ባሃኡላህ በጥቅሱ የሚለው እነዚያ የእርሱ ተስፋ የተገባለትን ቀን በጉጉት የጠበቁት፣ እርሱ ምፅዓቱን ሲያውጅ አልተቀበሉትም። ባሃኡላህን አንዲት ነፍስ ስታውቅ ብዙ እይታዎች በአእምሮዋ ውስጥ ይመጣሉ። ከዚህ በታች ባሉት ቃላት በእያንዳንዱ ባዶ ቦታዎች ተገቢ የሆኑትን ቃላት ሙሉ፦ ንቃት፣ እርግጠኝነት፣ ግንዛቤ፣ መታመን፣ ተስፋ።

ሀ. ከግዴለሽነት ወደ _____________________________

ለ. ከቸልተኝነት ወደ _____________________________

ሐ. ከትካዜ ወደ _____________________________

መ ካለመታመን ወደ _____________________________

ሠ. ከጥርጣሬ ወደ _____________________________

## ምዕራፍ 4.

ባሃኡላህ እንዲህ ይላል፦

**“ይህ ቀን የእግዚአብሔር እጅግ በጣም የላቁ ችሮታዎች በሰዎች ላይ የፈሰሱበት የእርሱ ከሁሉም በላይ ታላቅ ፀጋ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ውስጥ እንዲሰርፅ የተደረገበት ቀን ነው። የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ልዩነቶቻቸውን በመፍታት፣ በእርሱ እንክብካቤ እና ፍቅራዊ ደግነት ዛፍ ጥላ ሥር በፍፁም አንድነት እና ሰላም መኖር አለባቸው። በዚህ ቀን ደረጃዎቻቸውን ከፍ ለማድረግ እና ከሁሉ የበለጠውን ጥቅማቸውን ለማራመድ አመቺ የሆነውን ማንኛውም ነገር አጥብቀው መያዝ ይገባቸዋል።”**[3]

1. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ያሟሉ፦

ሀ. በዚህ ቀን የእግዚአብሔር እጅግ በጣም የላቁ ___________________________ በሰዎች ላይ ___________________________ ቀን ነው።

ለ. በዚህ ቀን የእግዚአብሔር እጅግ በጣም ታላቅ ___________________________ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ውስጥ ___________________________ የተደረገበት ቀን ነው።

ሐ. የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ልዩነቶቻቸውን ___________________፣ በእርሱ እና _____________ ጥላ ሥር _____________________ በ ___________ እና ___________ መኖር አለባቸው::

መ. የዓለም ሕዝቦች _____________ን ከፍ የሚያደርገውንና ከሁሉ _____________________ ማንኛውንም ነገር አጥብቀው መያዝ አለባቸው::

2. በዚህ ቀን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ከሰጣቸው "እጅግ በጣም የላቁ ችሮታዎች" መካከል አንዳንዶቹ ምን ምን ናቸው::

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

3. "ተስማሚ" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?___________________________________________

4. የሰው ልጆችን እጅግ የላቁ ጥቅሞችን ለማራመድ እርሰዎ ሊያደርጉ የሚችሏቸውን ነገሮች ይዘርዝሩ፡

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

## ምዕራፍ 5

ባሃኡላህ እንዲህ ይላል :–

> **"ይህ ቀን፣ የእግዚአብሔር ምህረት ውቅያኖስ በሰዎች ላይ የተገለፀበት፣ የፍቅራዊ ደግነቱ የቀኑ ኮከብ ጮራውን በእነርሱ ላይ የፈነጠቀበት፤ የእርሱ በረከት የተመላበት ችሮታ ደመናዎች በመላው የሰው ዘር ላይ ጥላቸውን ያጠሉበት ቀን ነው:: በሚያነቃቁ የፍቅር እና**

***የወንድማማችነት ልዝብ ነፋሶች፣ የወዳጅነትና የበጎ አድራጎት የሕይወት ውሃዎች አማካኝነት ያዘኑትን ለማስደሰት እና ለማፅናናት ጊዜው አሁን ነው፡፡”*** [4]

1. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ያሟሉ፡—

   ሀ. ይህ ቀን የእግዚአብሔር ________________________ ውቅያኖስ _____________ ___________ ለ________________________ ቀን ነው፡፡

   ለ. በዚህ ቀን የ ________________________ የቀኑ________________________ከኮብ ________________________በእነርሱ ላይ ________________________ ፡፡

   ሐ. በዚህ ቀን የእርሱ ________________________ደመናዎች በመላው የሰው ዘር ላይ ________________________፡፡

   መ. በሚያነቃቁ የ_______________እና የ_______________ ፣ የ_______________ እና _______________እና _______________ የሕይወት ውኃዎች ያዘኑትን ለ _______________ እና _______________ አሁን ነው፡፡

2. ከሚከተሉት ውስጥ ሰዎችን የሚያስደስቱ እና ስሜታቸውን ከፍ የሚያደርጉት የትኞቹ ናቸው?

   —— የትምህርት እድል ማግኘት

   —— የምክክር ችሎታቸውን ማሳደግ

   —— በአዘኔታ ዓይን መመልከት

   —— ከሳይንሳዊ የእድገት ለውጥ መጠቀም

   —— አንድ ወይም ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ቡድን ለመደገፍ መነሳሳት

   —— ከሌሎች ጋር የአምላክን ቃላት ማንበብ ወይም መካፈል

   —— በብድር የማያስፈልጋቸውን እቃዎችን ለመግዛት መወያየት

   —— ስለ ፀሎት ጥቅም የላቀን እውቀት ማግኘት፡፡

—— በጥረታቸው ላይ መበረታታትን መቀበል

—— ቅሬታዎቻቸውን በህጋዊ መንገድ በጥሩ ሁኔታ ለባለስልጣናት ለማቅረብ መብቃት

—— በተቃውሞ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ

—— ችግሮቻቸውን ለመርሳት አልኮሆል መጠጣት

—— የጤና ክብካቤ መርሐግብር ድጎማዎችን መቀበል

—— ለመደሰቻ በአቅራቢያቸው የምሽት ቤት እንዲኖር መፈለግ

—— የአሁኑን የአምላክ ክስተት ማወቅ

—— በመለኮታዊ እርዳታ ኃይል መመካት

## ምዕራፍ 6

ባሃኡላህ እንዲህ ይላል :–

> **"በዚህ እጅግ በጣም ታላቅ፣ በዚህ አዲስ የዓለም ሥርዓት ንዝረት ኃይል የተነሳ የዓለም ሚዛን ተናግቷል። በሥርዓት የነበረው የሰው ዘር አኗኗር መሰሉን ሚች ዓይኖች አይተውት ከቶ በማያውቁት በዚህ ልዩ፣ በዚህ ድንቅ ሥርዓት ኃይል አማካኝነት ተለውጧል።"[5]**
>
> **"ምስጢራቱን ትገልፁ እና በጥልቀቱ ውስጥ ተደብቀው የሚገኙትን የጥበብ እንቁዎች ሁሉ ታገኙ ዘንድ፣ ራሳችሁን በቃላቴ ውቅያኖስ ውስጥ አስጥሙ። የአምላክ ኃያልነት እምቅ ኃይሎች የተገለፁበትንና ሉዓላዊነቱም የተሰመረበትን እምነት፣ የዚህን እምነት እውነትነት ለመቀበል ከውሳኔያችሁ እንዳታወላውሉ ተጠንቀቁ"[6]**

1. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ያሟሉ :–

   ሀ. በዚህ እጅግ በጣም ታላቅ፣ በዚህ ________________________________ ተናግቷል።

   ለ. በ______________ የሰው ዘር______________ ሚች ዓይኖች አይተውት ከቶ በማያውቁት በዚህ______________ ፣ በዚህ ______________ ኃይል አማካኝነት ______________።

   ሐ. በጥልቀቱ ውስጥ ተደብቀው የሚገኙትን የ ______________እንቁዎች ሁሉ ______________ ዘንድ፣ራሳችንን በቃላቱ ውቅያኖስ ውስጥ______________ አለብን።

መ. የዚህን እምነት ________________ ለመቀበል ከ________________ተጠንቀቁ።

ሠ. ይህ የአምላክ ________________እና________________የተመሠረተበት እምነት ነው።

2. “ሚዛን” የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው? ______________________________________

3. የዓለምን ሚዛን ያናጋው ነገር ምንድን ነው? ________________________________________:

4. ዓለም ሚዛኗን እንዳጣች የሚጠቁሙ አንዳንድ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

________________________________________________________

5. የሰው ልጅ ሕይወት እየተለወጠ ለመሆኑ የሚጠቁሙ አንዳንድ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

________________________________________________________

6. ባሃኡላህ “ድንቅ ሥርዓት” ብሎ የጠቀሰው ምንድን ነው?

______________________________________________________________________

________________________________________________________________

7. በባሃኡላህ ቃላት ውቅያኖስ ውስጥ እራሳችንን የምናሰጥመው እንዴት ነው?

______________________________________________________________________

________________________________________________________________

8. በእርሱ ቃላት ውቅያኖስ ውስጥ እራሳችንን ስናሰጥም ተግባሮቻችን የሚለወጡት እንዴት ነው?

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_________________________________________________________________

9. በእርሱ ቃላት ውስጥ ራሳችንን ስናሰጥም ተግባሮቻችን ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ያሳድራሉ?

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_________________________________________________________________

10. የባሃኡላህን የዓለም ሥርዓት እንዲመሠረት ለመሥራት መንፈሳዊ ጉልበት የምናገኘው ከየት ነው?

_____________________________________________________________________________

_________________________________________________________________________

11. "ማወላወል" የሚለው ቃል ማለት ምን ማለት ነው?

_______________________________________________________________________________

_______________________________

12. የእርሱን እምነት እውነታ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ካወላወልን በመንፈሳዊ ጉልበታችን ላይ ምን ተፅእኖ ይደርስበታል?

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

___________________________________________________

## ምዕራፍ 7

አብዱል-ባሃ እንዲህ ሲል ተናግሯል :–

> **“እናንተ የጌታ ተወዳጆች ሆይ! ይህ ቀን የውህደት ቀን ነው፣ የሰው ዘር ሁሉ የሚሰበሰቡበት ቀን ነው። በእውነቱ እግዚአብሔር ልክ እንደማይደፈር ግድግዳ በተሰተረ መስመር ለእምነቱ የሚዋጉትን ይወዳል። በተሰተረ መስመር እንደሚል አስተውሉ :– ይህ ማለት በአንድ ላይ ተቀራርበው እና አንዱ ከሌላው ተያይዞ እያንዳንዱ ጓደኞቹን ይደግፋል ማለት ነው። በቅዱስ ጥቅሱ ውስጥ የተጠቀሰው ውጊያ ማድረግ በዚህ ከሁሉም የሃይማኖት ግልፀቶች ይበልጥ እጅግ በጣም ታላቅ በሆነው የሃይማኖት ግልፀት ሰይፍንና ጦርን፣ ሾተልንና ሹል ቀስትን ይዞ መውጣት ማለት አይደለም፤ ነገር ግን በንፁህ ፍላጎት፣ በመልካም ዓላማ፣ በሚጠቅሙ እና ውጤታማ ምክሮች፣ በአምላካዊ ባህርዮች፣ ፍፁም ኃያሉን በሚያስደስቱ ተግባሮች፣ በሰማያዊ ባህርያት ታጥቆ ማለት ነው። ለመላው የሰው ዘር ትምህርትን ለሰዎች ሁሉ መመሪያ፣ የመንፈስ ጣፋጭ ጣዕም ከዳር እስከ ዳር ማሰራጨት፣ የእግዚአብሔርን ማረጋገጫዎች ማወጅ፣ አሳማኝ እና መለኮታዊ የሆኑ ክርክሮችን ማቅረብ፣ የበጎ አድራጎት (የግብረ ሰናይ) ሥራዎችን መሥራት ያመለክታል።”[6]**

1. የሚከተሉትን መልመጃዎች ያሚሉ :–

   ሀ. አብዱል-ባሃ እንደሚነግረን ይህ ቀን የ________________ ቀን ________________የ ________________ ሁሉ________________ ቀን ነው።

   ለ. እግዚአብሔር ልክ ________________ በ________________ ለእምነቱ የ__________ ________ እንደሚወድ ________________ ያብራራል።

   ሐ. “የተሰተረ መስመር” የሚለው ሐረግ በ________________አንዱ ________________ እያንዳንዱ ጓደኞቹን ________________ ማለት እንደሆነ አብዱል-ባሃ ያብራራል።

   መ. በዚህ ከሁሉም የ_____________፣ ________________ እጅግ በጣም ታላቅ በሆነው የሃይማኖት ግልፀት ውጊያ ማድረግ ________________ እና ________________ ፣________________ እና ________________ ይዞ

መውጣት ማለት አይደለም:: ነገር ግን በ____________________ በ____________________
እና____________________በሆኑ በ___ _________________ታጥቆ ማለት ነው::

ሠ.በተመሳሳይ መንገድ በዚህ ታላቅ የሃይማኖት ዘመን ውጊያ ማድረግ ለመላው የሰው ዘር _________________ለሰዎች ሁሉ_________________ የ _________________ከዳር እስከ ዳር ማሰራጨት፣ የ _________________፣ _________________እና_________________ የሆኑ___________፣ የ _________________ ያመለክታል::

2. ይህ የሰው ልጅ አንድ የሚሆንበት ቀን ነው:: ይህ ሥራ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ለመገንዘብ የሰው ልጆች ራሳቸውን ያለያዩባቸው፣ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ልዩ ልዩ ክፍሎችን ያስቡ:: የሚችሉትን ያህል ዝርዝር ይፃፉ::

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

3. እነዚህን ሁሉ መከፋፈሎች ለመቋቋም ምን ዓይነት ኃይል ያስፈልጋል?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

4. የተያያዝነው ውጊያ ምን ዓይነት ነው?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

5. ከሚከተሉትመሣሪያዎች መካከል የትኞቹን በዚህ ውጊያ እንጠቀማለን?

—— ንፁህ ፍላጎት
—— ንዴት
—— አምላካዊ ባህርያት
—— ልግስና
—— መልካም ዓላማ
—— የፀሎት ኃይል
—— መሪ የመሆን ፍላጎት
—— አስመስጋኝ ሥራዎች
—— ትዕቢት እና ኩራት
—— የአምላክ ፍቅር
—— ለፍትህ ጥልቅ ስሜት
—— ለሰው ልጅ ፍቅር
—— መመፃደቅ
—— በአምላክ መተማመን
—— ጠመንጃ
—— ጠቃሚ እና ውጤታማ ምክር
—— ቢላዋዎች
—— የአንድነት ኃይል
—— የአምላክ ቃላት ኃይል
—— ገንዘብ
—— በእራስ መርካት
—— እምነት
—— እራስን መቆለል (ማግነን)
—— ትህትና

6. ፍትህን ለመመስረት ሲባል በሌሎች ላይ የበላይነትን መሳየት ተገቢ ነውን? ________________

7. ከሚከተሉት ውስጥ የሰው ልጅን አንድ ለማድረግ በምናከናወነው መንፈሳዊ ውጊያ የምንጠቀ ምባቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

—— ትምህርትን ማስፋፋት

—— እኛ ለምንፈልገው ሥራ ሌሎችን ማስገደድ

—— እምነቱን ማስተማር

—— የአምላክን እምነት ማወጅ

—— በእራሳችን ፍላጎት መሰረት በአንጃዎች መከፋፈል

—— የራሳችን ለሆነው ቡድን ፍላጎት መታገል

—— ምግባረ ሰናይ ሥራዎችን መሥራት

—— የባሃኡላህን ግልፅት እውነታ የሚያረጋግጡ አሳማኝ ክርክሮችን ማቅረብ

—— በቃላቱ ውቅያኖስ ውስጥ ራሳችንን ማስጠም

—— ደካሞችንና የተገፉትን መጨቆን

—— በጋለ ስሜት መፀለይ

—— የሕዝቦችን ንብረት መዝረፍ

—— ከሌሎች በመስረቅ ሐብትን ማከማቸት

## ምዕራፍ 8

ለዚህ ቀን ታላቅነት ያለን ግንዛቤ በመጨመሩ በሁላችንም ዘንድ፣ ለማስተማር፣ ለማገልገል፣ እና መስዋዕትነት የተሞሉ ሥራዎችን ለማከናወን፣ የመነሳሳትን ሁኔታ ፈጥሯል። ከጉዳዩ አጣዳፊነት አኳያ እምነቱን የማገልገል መንፈስ ላይ ትኩረታችንን ሳንነቅል፣ ከዚህ የሚከተለውን፣ በሞግዚቱ ከተ ፃፈ ደብዳቤ የተወሰደውን ምንባብ በቃልዎ ያጥኑ፡—

**"ሊባክን የሚችል ጊዜ የለም። ለማወላወልም ቦታ የለም። አያሌ ሕዝቦች የሕይወትን ዳቦ እየተ ራቡ ነው። መድረኩ ተዘጋጅቷል። ፅኑው የማይናወጠው ቃል ተገብቷል። የራሱ የእግዚአብ ሔር እቅድ መፈፀም ጀምሯል። በእያንዳንዱ አላፊ ቀን ኃይል እየሰበሰበ ነው። የሰማይ እና የምድር ኃይሎች በምስጥራዊ መንገድ ለአፈፃፀሙ እርዳታ ያደርጋሉ። እንደዚህ ዓይነቱ እድል የማይተካ ነው። የእነኝህ ዓይነቶችን አባባሎች እውነተኝነት ተጠራጣሪ ካለ ይነሳና ራሱ ያረጋ ግጥ። መሞከር፣ መፅናት፣ የመጨረሻውንና የተሟላ ድልን ማረጋገጥ ነው።"[7]**

## ማጣቀሻዎች


1. ከባሃኡላህ ፅሑፎች ቅስማት (ዊልሜት፣ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 1994) ቁጥር 7፣ ገፅ፡10-11

2. ከባሃኡላህ ፅሑፎች ቅስማት፣ ቁጥር 7፣ ገፅ 11

3. ከባሃኡላህ ፅሑፎች ቅስማት፣ ቁጥር 4፣ ገፅ 6

4. ከባሃኡላህ ፅሑፎች ቅስማት፣ ቁጥር 5፣ ገፅ 7

5. ከባሃኡላህ ፅሑፎች ቅስማት፣ ቁጥር 70፣ ገፅ 136

6. ከአብዱል-ባሃ ፅሑፎች የተውጣጡ (ሃይፋ፣ የዓለም ባሃኢዎች ማዕከል 1982) ቁጥር 207፣ ገፅ 260

7. ለአሜሪካ የተላኩ መልዕክቶች፣ ለሰሜን አሜሪካ ባሃኢዎች ከተላኩ የተመረጡ ደብዳቤዎች እና የቴሌግራም መልዕክቶች፣ 1932-1946 (ዊልሜት፣ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 1974) ገፅ 17



# የባብ ሕይወት

## ዓላማ

**የባብን አጭር እና በትዕይንት የተሞላ የሕይወት ታሪኩን ተገቢውን አድናቆት መስጠት እና የእርሱን የሕይወት ታሪክ መተረክን መማር።**

# ምዕራፍ 1

የባብ ግልፀት እ.ኤ.አ በ1844 የተጀመረ ሲሆን የቆየውም ለዘጠኝ ዓመት ብቻ ነበር። ተቀዳሚ ዓላማው ለባሃኡላህ መምጣት መንገዱን ማዘጋጀት ነበር። ምንም እንኳ የባብ የግልፀት ዘመን አጭር ቢሆንም፣ የለቀቀው መንፈሳዊ ኃይል ግን እጅግ በጣም የተጋጋመ ከመሆኑ የተነሳ የቀጣዩ መቶ ዓመ ታቶች ትውልዶች ውጤቱን ያዩታል።

ስሙ ሰዒድ ዓሊ ሙሐመድ በመባል የሚታወቀው ባብ፣ በኦክቶበር 20 1819፣ በቀድሞ ፋርስ አሁን በደቡብ ኢራን በምትገኘው በሺራዝ ከተማ ተወለደ። አብዛኛዎቹ የፋርስ ሰዎች ቃይም የሚባል በአምላክ ቃል የተገባለት መልዕክተኛ የሚጠባበቁ የእስልምና ቅርንጫፍ ተከታዮች ናቸው። "ቃይም" "እርሱ የሚነሳው" ማለት ነው።

ባብ የተወለደው የዘር ግንዳቸውን ከእስልምናው ነብይ ከሙሐመድ የሚሳብ ከታወቀ እና ከተከበረ ቤተሰብ ነው። ገና በልጅነቱ፣ ወላጅ አባቱ ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ፣ ያሳደጉት የእናቱ ወንድም አጎቱ ናቸው። ባብ አብሮት የተፈጠረ እወቀት ስለነበረው ሰብዓዊ ትምህርት ባያስፈልገውም፣ የአጎቱን ፍላጎት ለሟሟላት ገና በለጋ እድሜው ትምህርት ቤት ገባ። ነገር ግን፣ ወዲያው አስተማሪው የባብን ታላቅ ችሎታ በመረዳታቸው እና ይህንን ልዩ የሆነ ችሎታ ያለውን ልጅ ምንም ነገር ሊያስተምሩት አለመቻላቸውን ተገነዘቡ። ስለ ባብ የትምህርት ቀናትን አስመልክቶ ከዚህ የሚከተለውን ታሪክ ተናገሩ፦

> "አንድ ቀን ቀን የመክፈቻ ምዕራፍ በቃሉ እንዲያዜም ጠየቅሁት። . . .አመነታና፣ የቃለቱ ፍቺ ምን እንደሆነ ካልተነገረው በስተቀር ለማዜም ፈፅሞ እንደማይሞክር ተናገረ። ትርጉማቸውን እንደማላውቅ ዓይነት አስመሰልሁ። 'የእነኝህን ቃላት ትርጉም አውቃለሁ። ፈቃድዎ ከሆነ ላብራራቸው፣' አለ ተማሪዬ። ሲናገር በአንደበቱ ርቱዕነት እና በእውቀቱ በከፍተኛ አድናቆት ተዋጥሁ። . . .የንግግሩ ጥዑምነት አሁንም በትውስታዬ (አእምሮዬ) ጓዳ ይንሸራሸራል። አጎቱ እንድንከባከብው የሰጡኝን አደራ እጃቸው ላይ ለመጣል እና ለመመለስ ተገፋፋሁ። ይህን ዓይነቱን ድንቅ ልጅ ለማስተማር እንደማይገባኝ ልነግራቸው ወሰንሁ። አጎቱ በቢሯቸው ለብቻቸው አገኘኋቸው። 'መልሼ ወደ እርስዎ ይዤው መጥቼአለሁ፣' አልኳቸው፣ 'በንቃት ጥበቃ እንዲያደርጉለት አደራ እልዎታለሁ። ይህ ልጅ እንደማንኛውም ልጅ መታየት የለበትም፣ የቃይሙ ግልፀት ብቻ ሊያሳየው የሚችለውን ምስጢራዊ ኃይል ምልክቶች አሁን በእርሱ ላይ ማየት ችያለሁ። እጅግ በጣም ታላቅ ፍቅራዊ እንክብካቤ ሊያደርጉለት ይገባል። በቤትዎ ይቆይ፣ ምክንያቱም እርሱ በእርግጥ እንደ እኔ ያሉ አስተማሪዎች አያስፈልጉትምና።' አጎትየው ባብን አጥብቀው ወቀሱት። 'ያዘዝኩህን ረሳኸውን?' አሉት 'የሌሎቹን ተማሪዎች ምሳሌ እንደትከተል፣ ፀጥ ብለህ፣ አስተማሪህ የሚናገሩትን ቃላት ሁሉ በጥሞና እንድትከታተል አልመከርኩህምን?' አሉ። ትዕዛዛቸውን በታማኝነት እንዲጠበቅ ቃል ካስገቡት በኋላ ባብ ወደ ትምህርት ቤቱ እንዲመለስ አደረጉ። ሆኖም ግን የዚያ ልጅ ነፍስ በአጎቱ ኃይለኛ ወቀሳ ሊገታ አልቻለም። ከአምላክ የተሰጠው እውቀት እንዳይፈስ ሊገድብ የሚችል ዓለማዊ ሥርዓት የለምና። 'በየቀኑ ያሳያቸው የነበሩትን ከሰብዓዊ ፍጡር አቅም በላይ የሆኑ አስደናቂ የጥበብ ማስረጃዎችን ልገልፃቸው ኃይል የለኝም።' "[1]

በመጨረሻም ባብ ከትምህርት ቤት እንዲወጣ ተፈቀደለት። ከዚያም ከሺራዝ በደቡብ ምዕራብ በምትገኘው ቡሺር ከተማ ከአጎቱ ጋር መነገድ ጀመረ። ከዚያም በኋላ ባብ ሚስት አገባ። አህመድ የሚባል ልጅም ወለዱ፣ ነገር ግን ባብ ቃል የተገባለት ቃይም መሆኑን ከማወጁ አንድ ዓመት በፊት ልጁ በጨቅላነቱ ሞተ።

ባብ፣ ወጣት እያለ፣ ማንም ሊወዳደረው የማይችል ዓይነት ኃይል እና ታላቅነትነት ይታይበት ነበር። በእነዚያ አጭር እና በሐዘን የተሞሉ ዓመታት ውስጥ የእርሱ ብቻ የሆኑና ልዩ የሚያደርጉት ባህርያት አስቀድመው ይታዩበት ነበር። ተወዳጁ ሞግዚት እርሱን "ጨዋ እና ቁምነገረኛ፣ ወጣት እና ሊገታ የማይቻለው የባብ ሰብዕና፣ በትህትናው ተወዳዳሪ የሌለው፣ በእርጋታው የማይናወጥ፣ በንግግሩ የሚስብ" ነበር ሲል ገልጾታል። የሚቀጥሉት ምዕራፎች በተሟላ መልኩ ባይሆንም የሕይወቱን በአግራሞት የተሞላ ኩነቶች ይገልፃሉ። ይህ የህይወቱ ዘመን አጭር ቢሆንም በብዙ ሺህ ፋርሲያኖች እና ከዚያም ውጪ በነበሩ ተከተዮቹ ልብ ውስጥ ተቀጣጥሎ ይገኛል።

1. የባብ ስም ማን ነበር? ______________

2. ባብ የተወለደው የት እና መቼ ነበር? ___________________

3. "ቃይም" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? _____________

4. የባብ ቤተሰቦች የዘር ግንድ የሚሳበው ከማን ነው? _____________

5. አባቱ ከሞቱ በኋላ ኃላፊነትን ወስዶ ባብን ያሳደገው ማን ነው? __________________

6. አምላክ፣ ለባብ፣ ከትምህርት ያልተገኘ እውቀት አድሎት ነበር የሚለው ዓረፍተ ነገር ምን ማለት ነው? ___________________________

7. የእርሱን ታላቅ ችሎታ ሲገነዘብ የባብ አስተማሪ ምን አሰበ? _____________

8. "ከሰብዓዊ ፍጡር አቅም በላይ ጥበብ" የሚለው ሐረግ ምን ማለት ነው? _______________ _________________________________________

9. ከትምህርት ቤት ከወጣ በኋላ ባብ ምን ይሠራ ነበር? _________________________________

10. ተወዳጁ ሞግዚት ባብን በምን ዓይነት ቃላት ገልፆታል? _______________________________ ___________________________________________________

11. ባብ ትምህርት ቤት በነበረበት ወቅት የነበረበትን ሁኔታ የሚያወሳ ታሪክ በራስዎ አባባል ይፃፉ።

_______________________________________________________________________

_______________________________________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

## ምዕራፍ 2

ባብ መልዕክቱን ከማወጁ በፊት በዓለም ዙሪያ የነበሩ ብዙ ሰዎች በጥልቅ ልቦናቸው አዲስ የአምላክ ቀን ሊነጋ እንደሆነ አውቀው ነበር። ከእነዚህ ቅዱሳን ሰዎች መካከል አንዱ፣ በኢራቅ ውስጥ ባለችው ካርቢላ ከተማ የኖሩት ሰዒድ ቃዚም ነበሩ። ሰዒድ ቃዚም ብዙ ተማሪዎች ነበሩዋቸው፣ ለተ ማሪዎቻቸውም መምጣቱ ለብዙ ዘመናት ሲጠበቅ የነበረውን ቃይም እንዲቀበሉት ለማዘጋጀት ሕይወታ ቸውን ሰጡ። እሳቸው ከሞቱ በኋላ ልቦቻቸውን ከምድራዊ ፍላጎቶች በማንፃት ቤታቸውን ጥለው የተስፋ ቃል የተነገረለትን ተወዳጁን ለመፈለግ በሰፊው መሰራጨት እንዳለባቸው ተማሪዎቻቸውን በተደ ጋጋሚ ነግረዋቸው ነበር።

ሰዒድ ቃዚም ካረፉ በኋላ በጣም የታወቀው ሙላ ሁሴይን የሚባለው የእርሳቸው ተማሪ አርባ ቀናትን በፀሎት እና በሱባዔ አሳለፈ። በዚህን ወቅት እግዚአብሔር መለኮታዊ መነቃቃትን እንዲሰጠው ልቡን ወደ እርሱ አቀና። ከዚያም ከሁለት ባልደረባዎቹ ጋር ኢራቅን ለቅቆ ፍለጋውን ቀጠለ። በመጀመሪያ ወደ ቡሺር ሄደ። እዚያም ብዙ አልቆየም። ነገር ግን፣ አንዳች ሊቋቋመው ያልቻለው ኃይል ወደ ሰሜን፣ ወደ ሺራዝ ሲስበው ተሰማው። ወደ ከተማው እየተቃረበ ሲመጣ፣ ሁለቱን ባልደረባዎቹን ወደ አንድ መስጊድ በመሄድ በእዚያ እንዲቆዩት እና እርሱም እዚያው እንደሚያገኛቸው ነገራቸው።

ፀሐይ ከመጥለቋ ከጥቂት ሰዓታት በፊት፣ ከሺራዝ ከተማ መግቢያ ወጣ ብሎ፣ ከአንድ ወጣት ሰው ጋር ተገናኘ። ወጣቱም እንኳን ደህና መጣህ ብሎ ተቀብሎ ረዥም እና አድካሚው ጉዞው በኋላ እረፍት እንዲያደርግ ወደ ቤቱ ጋበዘው። ሙላ ሁሴይን በዚህ አስደናቂ ወጣት እርጋታ የተሞላ ሆኖም አስገዳጅ በሆነው ንግግር በጥልቅ ተነካ። አብረው ሄደውም አንድ መጠነኛ ቤት ደጃፍ ላይ ደረሱ። ወደ ውስጥ በመዝለቅ ወደ ላይኛው የቤቱ ክፍል አመሩ። ደጉ አስተናጋጅ እንግዳው አቧራውን እንዲታጠብ ውኃ እንዲመጣ አዘዘ። ከዚያም እራሱ ሻይ አፍልቶ አቀረበለት። ከዚህ መስተንግዶ በኋላ፣ መናገር ጀመረ። የዚያ ታሪካዊ ንግግር ዝርዝር በሙላ ሁሴይን አንደበት በእንዲህ ዓይነት መልኩ ተተርኳል ፦

> "ወጣቱ አስተናጋጄ ሊያነጋግረኝ ሲጀምር ከፀሐይ መጥለቅ በኋላ አንድ ሰዓት ገደማ አልፎ ነበር። 'ከሰዒድ ቃዚም በኋላ የእርሳቸው ተተኪ እና መሪያችሁ ማን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?' በማለት ጠየቀኝ። እኔም እንዲህ ስል መለስሁ፦ 'የተለዩን አስተማሪያችን፣ በመሞቻቸው ሰዓት

ቤቶቻችንን ጥለን የተስፋ ቃል የተነገረለትን ተወዳጅ ለመፈለግ በሁሉም ቦታዎች እንድንሰራጭ በጥብቅ መክረውን ነበር። ስለዚህም ወደ ፋርስ መጥቼያለሁ፣ ፈቃዳቸውን ለመፈፀም ተነስቼያለሁ፣ እናም እስካሁን በፍለጋ ላይ ነው ያለሁት።' በመቀጠልም እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ:– 'አስተማሪያችሁ፣ ያ የተስፋ ቃል የተነገረለት ልዩ የሚያደርጉትን ዝርዝር ምልክቶች ሰጥተዋች ኋልን?' 'አዎን' በማለት መልስ ሰጠሁ፣ 'ከንፁህ እና ታዋቂ የትውልድ ሐረግ፣ እንዲሁም ከፋጡማ ዘር ነው። ዕድሜው ከሃያ ያላነሰ ከሠላሳ ያልበለጠ፣ በትምህርት ያልተገኘ የተፈጥሮ እውቀት ያለው። መካከለኛ ቁመት ያለው። ሲጃራ የማያጨስ፣ ከአካል ጉዳት ነፃ የሆነ ነው።' አልኩ። ጥቂት ዝም ብሎ ቆየት አለና፣ በሚያስገመግም ድምፅ፣ 'ተመልከት፣ እነኝህ ሁሉ ምልክቶች በእኔ ላይ ይታያሉ!' አለ። ከዚያም ከላይ የተጠቀሱትን ምልክቶች እያንዳንዳቸውን በማንሳት ሁሉም በእርሱ ላይ ያሉ ምልክቶች እንደሆኑ ጥርጥር በሌለው መንገድ አረጋገጠ።"[2]

በዚያን ሌሊት፣ የተስፋ ቃል የተነገረለት ቃይም እርሱ እራሱ እንደሆነ ባብ ለሙላ ሁሴይን በግልፅ እና በማያሳስት ማስረጃዎች አረጋገጠለት። ከዚያም በሚያስደንቅ ፍጥነት በቁርዓን ውስጥ ከፍተኛ ግምት ከሚሰጣቸው ምዕራፎች አንዱ የሆነውን የዮሴፍን ምዕራፍ ማብራሪያ የመጀመሪያ ክፍል ገለፀለት። ከዚያም ለሙላ ሑሴይን እንዲህ በማለት ተናገረ :–

"አንተ በእኔ ለማመን የመጀመሪያው የሆንከው ሆይ! በእውነቱ እላለሁ፣ እኔ የእግዚአብሔር በር ባብ ነኝ፣ አንተ ደግሞ የዚያ በር መግቢያ ደጃፍ ባቡል–ባብ ነህ። በመጀመሪያ አስራ ስምንት ነፍሶች ያለማንም ግፊት በራሳቸው ተነሳሽነት እኔን መቀበል እና የግልፀቴን እውነታ ማወቅ አለባቸው። እነኝህ እያንዳንዳቸው ማንም ሳያስጠነቅቃቸው እና ሳይጋብዛቸው እኔን ለማግኘት በራሳቸው መፈለግ አለባቸው። ቁጥራቸው ሲሟላም ከመካከላቸው አንዱ ወደ መካና መዲና በማደርገው ጉዞ አብሮኝ እንዲሄድ መመረጥ አለበት። እዚያም የእግዚአብሔርን መልዕክት ለመካው ሸሪፍ አስተላልፋሁ። ከዚያም እንደገና የእርሱን እምነት በዚያች ቅድስት ከተማ መስጊድ ውስጥ ወደምገልፅበት ወደ ኪፊህ እመለሳለሁ። ያየኸውንና የሰማኸውን ለጓደኞችህም ሆነ ለሌላ ለማንም ነፍስ አለመግለፅ ይጠበቅብሃል።"[3]

ይህ ክቡር ግልፀት የሙላ ሁሴይንን ነፍስ በደስታ እና በሐሴት፣ በአክብሮት እና በአድናቆት ሞላው። እንዲህም አለ፡-

"ከዚህ በፊት ምን ያህል ደካማ እና ዓቅመ-ቢስ፣ ምን ያህል ሐዘን የጎዳኝ እና ፈሪ እንደነበርኩ ተሰማኝ! በዚያን ጊዜ እጆቼ እና እግሮቼ በጣም ይንቀጠቀጡ ስለነበር መፃፍም ሆነ መንቀሳቀስ አልችልም። አሁን ግን የግልፀቱ እውቀት ሰውነቴን አነቃው። ይሰማኝ የነበረው ወኔ እና ኃይል ዓለም ከመላ ሕዝቦቿ እና ገዢዎቿ ጋር በእኔ ላይ ቢነሱብኝም እንኳ ሳልፈራ ብቻዬን ጥቃቱን ለመቋቋም የሚያስችለኝ ነበር። ሁለንተም ዓለም በሙሉ በመዳፌ ውስጥ ያለ የአቧራ ጭብጥ መሰለኝ። የሰውን ልጅ ሁሉ እንዲህ እያለ የሚጣራውን የገብርኤልን ድምፅ የሆንኩ መሰለኝ።:– 'ንቁ! እነሆ ጎህ ቀዷል እና። ተነሱ እምነቱ ተገልጿልና። የዓለም ሕዝቦች ሆይ! የፀጋው ደጃፍ በሰፊው ተከፍቷል፣ እዚያ ግቡ፣ለእናንተ ቃል የተገባው መጥቷል።!'"[4]

ባብ ማንነቱን ያወጀው ሜይ 23 1844 ምሽት ላይ ነበር። በዚያን ጊዜ ሃያ አምስት ዓመቱ ነበር። ከአስርተ ዓመታት በኋላ አብዱል-ባሃ የባብ እምነቱን ያወጀበት ዐውደ ዓመት ክብረ-ባዓል ላይ ለተገኙ ባሃኢዎች እንዲህ ብሎ ነበር:–

**“ይህ የባብ መልዕክት እና እወጃ ዓውደ ዓመት ሜይ 23 ነው። የባብ መምጣት የእውነተኛው ንጋት የመጀመሪያው ብርሃን እንደመሆኑ የተባረከ ቀንና የግልፀት ጎህ ነው፣ . . . የመንግስተ ሰማያዊ በረከት መፀነስ፣ የአምላካዊ ፀዳል መጀመሪያ ስለሆነ የተባረከ ቀን ነው። ባብ በዚህ ዕለት እ.ኤ.አ. በ1844 ስለ እግዚአብሔር መንግስት ምፅዓት ለማብሰር እና ለማወጅ ተላከ፣ የመላውንም ፋርስ ግዛት ተቃውሞ ተቋቁሞ ስለባሃኡላህ መምጣትም አስደሳች ዜና አበሰረ።”[5]**

1. ሰዒድ ቃዚም በመሞቻቸው ሰዓት ለተማሪዎቻቸው ምን ተናገሩ? ______________________

______________________________________________________

2. ሰዒድ ቃዚም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ሙላ ሁሴይን ምን አደረገ? ________

______________________________________________________________________________

_______________________________________

3. ሙላ ሁሴይን ሺራዝ መድረሱን ባብ እንዴት አወቀ? __________________________

______________________________________________________________________________

4. እርሱ ቤት ከደረሱ በኋላ ባብ ሙላ ሁሴይንን ምን ምን ጥያቄዎች ጠየቀው?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

5. ሰዒድ ካዚም የቃይሙን ሰብዕና በተመለከተ ምን ዓይነት ምልክት ለተማሪዎቹ ሰጣቸው?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

6. ፋጢሚህ የማን ልጅ ናት? "የእርሷ ዘር" ማለትስ ምን ማለት ነው?

_______________________________________________________________

7. ሙላ ሁሴይን እየፈለገ የነበረውን መለያዎች ባብ ይዞ ነበርን? ____________________

8. "ባብ" የሚለው ማዕረግ ምን ማለት ነው?____________________

9. ባብ ለሙላ ሁሴይን ምን የሚል ማዕረግ ሰጠው?____________________

10. ይህ ማዕረግ ምን ማለት ነው? ____________________

11. ባብ ሃይማኖቱን በግልፅ ከማወጁ በፊት ምን መካሄድ ነበረበት?

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

12. በእራስዎ ቃላት በዚያ ታሪካዊ ምሽት ሙላ ሁሴይን ያ የተስፋ ቃል የተገባለትን ቃይም እያወቀው ሲመጣ ስለሆነው ሁኔታ ግለፁ።

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

13. የባብ ግልፀቱን ያወጀው መቼ ነበር? ________________________

14. ባብ አዋጁን ሲያውጅ ዕድሜው ስንት ነበር? ____________

## ምዕራፍ 3

ከሙላ ሁሴይን በኋላ ሌሎች አስራ ሰባት ግለሰቦች የልባቸውን እሾት የሆነውን ባብን በእየራሳቸው መንገድ ፈልገው አገኙት። አንዳንዶቹ በራዕይ ወይንም በህልም፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በፀሎት እንዲሁም ሌሎቹ በተመስጦ በነበሩበት ጊዜ፣ አዲስ የተወለደውን ግልፀት እውነታ ለማወቅ እንዲችሉ እያንዳንዳቸውን እግዚአብሔር መራቸው። ከአንዷ በስተቀር እነኝህን ሁሉ የተባረኩ ነፍሶች ሁሉም በሺራዝ ከተማ ባብ ፊት መቅረብ ችለው ነበር። እርሱን ያላገኘችው የብሩህ አእምሮ ባለቤት የሆነችው እና ገጣሚ የነበረችው ታሂሬ ነበረች። ባብን የማወቅ እድል ያገኘችው በህልሟ ሲሆን፣ የተስፋ ቃል የተነገረለት ተወዳጅ እርሱ መሆኑን ካወቀች በኋላ ደፋር የሃይማኖቱ አራማጅ ሆነች። የእርሱን ተከታዮች ደረጃ ለመቀላቀል፣ አስራ ስምንተኛው ሰው የሃያ ሁለት ዓመቱ ወጣት ቅዱስ ነበር። ምንም እንኳ ቅዱስ ወጣት የነበረ ቢሆንም፣ ጥቂቶቹ ብቻ ሊስተካከሉት የሚችሉት አርአያ ሊሆን የሚችል ባህርይ ያለው፣ ጥቂቶች ብቻ አቻ ሊሆኑት የሚችል፣ ወኔና እምነት ነበረው። ሙላ ሁሴይንን ጨምሮ እነኝህን አስራ ስምንቱን አማኞች "ሕያዋን ፊደላት" ተብለው በባብ ተሰየሙ።

የሕያዋኑ ፊደላት ቁጥር ከተሟላ በኋላ ብዙ ሳይቆይ ባብ ሙላ ሁሴይንን ወደ እርሱ ጠርቶ የሚከተለውን ትዕዛዝ ሰጠው :–

> **"በአብሮነት የነበርንባቸው ቀናት ወደ ማብቂያቸው ናቸው። ከአንተ ጋር የገባነው ቃል ኪዳን አሁን ተሟልቷል። የጥረትህን ሽንጦች አጥብቅና ሃይማኖቴን ለማስራጨት ተነሳ። የዚህን ትውልድ ብልሹነት እና ጠማማነት በመመልከት ተስፋ አትቁረጥ፣ የቃል ኪዳኑ ጌታ ያለጥርጥር ያግዝሃልና። በእውነቱ እርሱ ፍቅራዊ ጥበቃው ይከብሃል፣ ከድል ወደ ድልም ይመራሃል። በምድር ላይ በረከቱን እንደሚዘንበው ደመና ሁሉ መሬትን ከአንድ ጫፍ ወደ ሌላው ጫፍ አቋርጥ፣ እናም ሁሉን ቻዩ ከምህረቱ የተነሳ የለገሰህን ቡራኬዎች በሕዝቦቿ ላይ አዝንብ። . . . በቅርቡ በምናደርገው መንፈሳዊ ጉዞ ቅዱስ አጅቦን እንዲጓዝ መርጠነዋል። ኃይለኛና ምህረት የሌለውን የጠላት ጥቃት እንድትጋፈጥ ትተንሃል። ሆኖም ሊነገር ከሚቻል በላይ የከበረ በረከት እንደሚለገስህ እርግጠኛ ሁን። ወደ ሰሜን የምታደርገውን ጉዞ ቀጥል፣ እግረ መንገድህንም ኢስፋሃንን፣ ካሻንን፣ ቁምን፣ እና ቴህራንን ጎብኝ። በእዚያ ዋና ከተማ የእውነተኛ ልዕልና መንበር ፊት ለመቅረብ እና የተወዳጁ እልፍኝ ውስጥ ለመግባት በልግስናው እንዲያስችልህ የእርሱን ሁሉን ቻዩን ፈቃድ ተማፀን። በዚያች ከተማ ውስጥ ምስጢር ተደብቋል። ይህ ምስጢር ሲገለጥ ምድርን ወደ ገነት ይለውጣታል። ከፀጋውም እንደምትካፈል እና ብሩህነቱንም እንደምትገነዘብ ተስፋ አደርጋለሁ።"**[6]

ሙላ ሁሴይንን ወደ ቴህራን እንዲሄድ ካዘዘው በኋላ ባብ ሌሎቹን ሕያዋን ፊደላት ወደ እርሱ ጠርቶ ለእያንዳንዳቸው ልዩ የሆነ ተልዕኮ ሰጣቸው። በመሰናበቻ ንግግሩ እያንዳንዳቸው ምድራዊ ፍላጎቶቻቸውን ወደ ጎን በመተው፣ የእርሱን ሃይማኖት ለማወጅ በርቀት እና በስፋት እንዲበተኑ ጥሪ አቀረበላቸው። እንዲህ በማለት ነገራቸው:–

> **"የማፈቅራችሁ ወዳጆቼ ሆይ! እናንተ በዚህ ቀን የእግዚአብሔር ስም ተሸካሚዎች ናችሁ። የእርሱ ምስጢር ማስቀመጫ ምህደሮች ሆናችሁ ተመርጣችኋል። እያንዳንዳችሁ የእግዚአ ብሔርን ባህርያት ለማሳየት እና በድርጊታችሁ እና በቃላችሁ፣ የእርሱ ቅድስና ምልክቶች፣ የኃያሉ እና የክቡሩ ምሳሌዎች የመሆን ኃላፊነት አለባችሁ። የአካላችሁ መለያልዮች በእራሳቸው ስለ ዓላማችሁ ከፍተኛነት፣ ስለሕይወታችሁ ሐቀኝነት፣ ስለ እምነታችሁ እውነታ፣ እና ስለ ፅናታችሁ ባህርይ ልዕልና መመስከር አለባቸው። ስለ እውነት እላችኋለሁ፣ ይህ አምላክ በእርሱ**

መፅሐፍ ውስጥ የተናገረበት ቀን ነው :– 'በዚያን ቀን በአፎቻቸው ላይ ማህተምን እናደርጋለን፤ ነገር ግን በእጆቻቸው እኛን ያናግሩናል፣ እናም ስለ ሠሩት ድርጊት እግሮቻቸው ይመሠክራሉ፣ የተባለበት ቀን ነው' የአምላክን ሃይማኖት ለማወጅ በላካቸው ጊዜ፣ እየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በተናገረው ላይ አሰላስሉ። ተልዕኳቸውን ለማሳካት እንዲነሱ በእንዲህ በሚሉ ቃላት ጠራቸው :– 'እናንተ የሌሊቱን ጨለማ እንድታበሩ በተራራው ጫፍ ላይ እንደተለኮሳችሁ የእሳት ነበልባሎች ናችሁ። በሰዎች ፊት ብርሐናችሁ በመታየት የደመቀ ይሁን። በእናንተ አማካኝነት የምድር ህዝቦች እርሱ የንፅህና እና የፀጋ ምንጭ የሆነውን ሰማያዊ አባታቸውን እንዲያውቁ እና እንዲቀርቡ ይሆን ዘንድ፣ የፀባያችሁ ንፅህና እና የመላቀቃችሁ ደረጃ ይህ መሆን አለበት። እርሱ በሰማይ ያለውን አባት ያየው የለም። እናንተ የእርሱ መንፈሳዊ ልጆች የሆናችሁ በተግባሮቻችሁ የእርሱን ሰናያት ማሳየት፣ እና የእርሱ ክብር ምስክሮች መሆን አለባችሁ። እናንተ የዓለም ጨው ናችሁ፣ ነገር ግን ጨዉ ማጣፈጡን ካጣ፣ ታዲያ ለምን ይሆናል? የመላቀቃችሁ ልክ በዚህ ደረጃ መሆን አለበት፣ የአምላክን ሃይማኖት ለማወጅ እና ለማስተማር የትኛውም ከተማ ብትገቡ፣ ከነዋሪዎቹ ሰዎች ሥጋም ሆነ ሽልማት መጠበቅ የለባችሁም። በፍፁም፣ ከከተማው ለቅቃችሁ ስትወጡ፣ ከእግሮቻችሁ ላይ ያለውን አቧራውን እንኳ ማራገፍ ይገባችኋል። ንፁህ እና ሳትበከሉ እንደገባችሁ፣ ከከተማውም ስትወጡ እንደዚያ መሆን ይገባችኋል። ስለ እውነት እላችኋለሁ፣ ሰማያዊው አባታችሁ ሁሌም ከእናንተ ጋር ነውና ይጠብቃችኋል። ለእርሱ ታማኝ ከሆናችሁ፣ ሁሉንም የምድር ፀጋዎች እጆቻችሁ ላይ እንደሚያስቀምጥላችሁ፣ ከዓለም መሪዎች እና ነገሥታት በላይ ከፍ እንደሚደርጋችሁ ጥርጥር የለም።' የእኔ ሕያዋን ፊደላት ሆይ! እውነት እላችኋለሁ፣ ከቀድሞቹ የሐዋርያት ቀናት ይህ ቀን እጅግ በጣም የላቀ ቀን ነው። በፍፁም፣ እንዲያውም ልዩነቱ ሊለካ አይችልም! እናንተ ያ የተስፋ የተገባለት የአምላክ ቀን ንጋት ምስክሮች ናችሁ። እናንተ የእርሱ ግልፀት ምስጢራዊ ዋንጫ ተካፋዮች ናችሁ። የጥረቶቻችሁን ሽንጦችን አጥብቁ፣ እናም በእርሱ መፅሐፍ ውስጥ ለተገለፁት የአምላክ ቃላትን ልብ በሉ :– 'አቤቱ፣ አምላካችሁ ጌታ መጥቷል፣ ከእርሱም ጋር የእርሱ መላዕክት አጀብ በሠልፍ አብረውት አሉ።' ከዓለማዊ እሾት ልቦቻችሁን በማፅዳት፣ እናም በምግባሮቻችሁ የእነዚህ የአምላክ ቃላት ምስክሮች ትሆኑ ዘንድ፣ መላዕክታዊ ሰናያት ጌጣችሁ ይሆኑ ዘንድ ጥረት አድርጉ፣ 'ወደ ኋላ' በመመለስ 'እንደ እናንተ ዓይነት ባልሆኑ፣ እና የአምላክ መንግስትን ከእናንተ ላይ በሚነጥቁ' 'በሌሎች ሕዝቦች እንዳይቀይራችሁ፣' ተጠንቀቁ። ከንቱ አምልኮት በቂ የነበረበት ጊዜ አብቅቷል። እጅግ ንፁህ ተነሳሽነት፣ ባልተበከሉ ንፁህ ምግባራት ካልተደገፈ በቀር፣ ወደ እጅግ ከፍተኛው ዙፋን እና በእርሱ ዘንድ ተቀባይነትን ወደ ማግኘት አያርጉም። 'መልካም ቃላት ወደ እርሱ ያርጋሉ፣ ቀጥተኛ ድርጊቶችም በእርሱ ዘንድ ከፍ እንዲሉ ምክንያት ይሆናሉ፣' እናንተ እርሱ አምላክ በመፅሐፉ የተናገራችሁ፣ ዝቅ ያላችሁ ናችሁ :– 'በምድር ላይ ዝቅ ለተደረጉት ሰዎች ሞገስን ልናደርግላቸው እና በሰዎች መካከልም መንፈሳዊ መሪዎች ልናደርጋቸው እና የእኛ ወራሾች ልናደርጋቸው ወደድን።' ለዚህ ማዕረግ ተጠርታችኋል፤ እያንዳንዱን ምድራዊ ፍላጎት ከእግራችሁ ስር ረግጣችሁ ከተነሳችሁ ብቻ፣ እናም እንደ እነዚያ 'እርሱ እስኪናገር ድረስ ጠብቀው ካልሆነ የማይናገሩት፣ እርሱ ያዘዘውን ከሚያደርጉት የተከበሩ አገልጋዮች ከሆናችሁ፣ ልትደርሱበት ትችላላችሁ።' እናንተ ከቀዳማዊ ነቁጥ የፈለቃችሁ የመጀመሪያዎቹ ፊደላት፣ ከዚህ ግልፀት ምንጭ ኩልል ብላችሁ የፈለቃችሁ የመጀመሪያዎቹ ምንጮች ናችሁ። ምድራዊ ቁራኛዎች፣ ዓለማዊ መቅሰፍቶች፣ ኃላፊ ጠፊ ጉጉቶች ንፅህናችሁን እንዳይበክል፣ ወይም በውስጣችሁ እየፈሰሰ ያለውን ፀጋ ጣፋጭነት እንዳያጎመዝዝ፣ አምላካችሁን ጌታችሁን ተማፀኑ። እየመጣ ላለው እጅግ በጣም

***ታላቅ ቀን እያዘጋጀኋችሁ ነው:: ምናልባት፣ እኔ አሁን እያዘዝኳችሁ ያለሁት፣ በአምላክ ርህራሄ መቀመጫ ፊት ተቀምጬ፣ በድርጊቶቻችሁ እደሰት ዘንድ፣ እናም በስኬታችሁ ክብረት ይሰማኝ ዘንድ፣ ለሚመጣው ዓለም ያለ የሌለ ጥረታችሁን አውሉ:: ሊመጣ ያለው የቀኑ ምስጢር ለአሁን ተደብቋል:: ሊገለፅም ሆነ ሊገመት አይችልም:: በዚያን ጊዜ የተወለደ አራስ ህፃን የዚህን ጊዜ ጠቢብ እና አዋቂ የተባለውን ይበልጠዋል፣ እጅግ ዝቅተኛው እና በጭራሽ ምንም ትምህርት ያልተማረው የዚያን ጊዜ ሰው፣ የዚህን ጊዜ እጅግ የተራቀቁትን እና የበቁትን ቀሣውስት በመረዳት ችሎታው ያጥፋቸዋል:: በዚህ ምድር ስፋት እና ርቀት ተሰራጩ፣ እናም በፅናት እግሮች እና በነፁ ልቦች፣ ለእርሱ መምጣት መንገዱን አዘጋጁ:: ለድክመቶቻችሁ እና ለዓቅመቢስነታችሁ ትኩረት አትስጡ:: እይታዎቻችሁን በጌታ፣ በአምላካችሁ፣ በእጅግ በጣም ኃያሉ ሊገታ በማይቻለው ኃይሉ ላይ አኑሩ:: ባለፉት ጊዜያት፣ ምንም እንኳ ረዳት የለሽ ደካማ ቢመስልም፣ አብርሐምን፣ በኒምሮድ ኃይሎች ላይ ድልን እንዲጎናፀፍ አላስቻለውምን? ብቸኛው ወዳጁ በትሩ የነበረውን ሙሴን የፈርዖንና ሠራዊቱን ኃይል እንዲያጨናገፍ አላስቻለውምን? በሰዎች ዓይኖች ደሃ እና ደካማ የሚመስለውን እየሱስን በተባበረው የአይሁዶች ሕዝቦች ኃይሎች ላይ ታላቅነቱን አልመሠረተምን? አረመኔዎች እና ውጊያ ናፋቂ የሆኑ የአረቢያ ጎሣዎችን ለእርሱ ነብይ ለሙሐመድ ቅዱስ እና ለዋጭ ስነምግባር እንዲገዙ አላደረገምን? በስሙ ተነሱ፣ መመካታችሁንም በእርሱ ላይ አኑሩ፣ ለማያዳግም ድልም እርግጠኛ ሁኑ::”[7]***

1. የተስፋ ቃል የተነገረለት ቃይም እርሱ መሆኑን ያወቁትን የመጀመሪያ አማኞች ባብ ማን ብሎ ሰየማቸው? ______________________________________

2. ስንት ህያዋን ፊደላት ነበሩ? __________________

3. ባብን ለማወቅ የመጀመሪያው ማን ነበር? _______________

4. ከሕያዋን ፊደላት የመጨረሻዋ ማን ነች? _______________

5. የባብን ግልፀት እውነታ እንዲያውቁ ሕያዋን ፊደላት የተመሩት እንዴት ነበር? _____________

_________________________________________________________________________

_________________________________________________________________________

6. ከህያዋን ፊደላት መካከል ባብ ፊት ለመቅረብ እድል ያላገኘችው ማንኛዋ ነበረች?___________

7. የሕያዋን ፊደላት ቁጥር ከተሟላ በኋላ፣ ባብ ሙላ ሁሴይንን ወደ እርሱ ጠርቶ ከዚህ የሚከተለውን ትዕዛዝ ሰጠው :– “_________________________ የነበርንባቸው ቀናት ወደ

____________________ ናቸው:: ከአንተ ጋር _________________________ አሁን ________________________:: የ_________________ ሽንጦች አጥብቅና ___________________________ ለማሰራጨት ተነሳ:: የዚህን _____________________________ እና ________________________________ በመመልከት _________________________፣ የ___________________________ጌታ ያለጥርጥር __________________________:: በእውነቱ በእርሱ ፍቅራዊ __________________________ ይከብሃል፣ ከ____________ወደ_______________________ይመራሃል:: በምድር ላይ ___________________________________ ሁሉ መሬትን ከአንድ ጫፍ ወደ ሌላው ጫፍ አቋርጥ፣ እናም ___________________________ ከምህረቱ የተነሳ የለገሰህን ቡራኬዎች በሕዝቦቿ ላይ _________________________::

8. ባብ ለስግደትና ለመሳለም ጉዞ ሲሄድ አጅቦት እንዲሄድ የመረጠው ማንን ነበር? ___________

9. ሙላ ሑሴይንን ወደ የት እንዲሄድ ጠየቀው?_________________________________

10. ለሙላ ሑሴይን ምን ዓይነት ተስፋ ሰጠው?____________________________________

_______________________________________________________________________

11. ባብ ለሕያዋን ፊደላት ከሰጣቸው ትዕዛዛት አንዳንድ ክፍሎቹን በቃላችሁ ልትይዙት ትፈልጉት ይሆናል::

## ምዕራፍ 4

በ1844 ኦክቶበር ወር፣ ባብ በቅዱስ ታጅቦ፣ ለስግደት እና ለመሳለም ጉዞ ወደ መካ እና መዲና አቀና:: በሳዑዲ አረቢያ የሚገኙ፣ እነዚህ ሁለት ከተሞች፣ በእስልምና ተከታዮች ዘንድ ቅዱስ ተደርገው ይወሰዳሉ:: ባብ እና አብሮት የነበረው አጋሩ፣ ከቡሺር በመርከብ ተሳፍረው፣ በአረቢያ ሰላጤ አድርገው መካ ለመድረስ ወደ ሁለት ወር ፈጀባቸው:: መካ እያሉ፣ ባብ የቅዱስ መካነ መቃብሩ የበላይ ጠባቂ እና

ለከተማው ከንቲባ ሻሪፍ፣ ደብዳቤ ፃፈ:: በዚያ ደብዳቤ፣ የእርሱን ተልዕኮ በመዘርዘር ሻሪፉ የእርሱን እምነት እንዲቀበል አሳሰበው:: ነገር ግን ሻሪፉ፣ በእራሱ ጉዳይ እጅግ ከመጠመዱ የተነሳ፣ ለመለኮታዊው መልዕክት ምላሽ ከመስጠት ተሰናከለ:: ከዚያም ባብ ከቅዱስ ጋር፣ የነብዩ ሙሐመድ መካነ መቃብር ወደሚገኝበት፣ ከመካ ወደ መዲና ተጓዘ:: ቅድስቲቱን ከተማ ከጎበኙ በኋላ፣ በመርከብ ወደ ፋርስ ተመለሱ:: ቡሺር እንደደረሱ፣ ባብ ቅዱስን ወደ ሺራዝ ጉዞውን እንዲቀጥል አዘዘው::

> **“ከእኔ ጋር የነበረህ አብሮነት ወደ ማብቃቱ እየደረሰ ነው:: የመለያያችን ሰዓት ደርሷል፣ በእግዚአብሔር መንግስት በቀር በሌላ መገናኘት የማይከተለው መለያየት . . . በሺራዝ መንገዶች ላይ ቁጣዎቻቸውን እና ንዴቶቻቸውን ይወርዱብሃል፣ እጅግ አሰቃቂ ጥቃቶች በአካልህ ላይ ያደርሱብሃል:: የጠላቶችህን ቅጥ ያጣ ባህርይን ሁሉ ትቋቋማለህ፣ እርሱ የእኛ ተመላኪው ተወዳጅ እና ተፈቃሪ ምክንያት የሆነው ዘንድ መቅረብን ትቀዳጃለህ:: በእርሱ ቅር በት የወረደብህን ጉዳትና ውርደትን ትረሳለህ:: የማይታዩት ሠራዊቶች አንተን ለመርዳት ይጣደፋሉ፣ ለዓለም ሁሉ የአንተን ጀግንነት እና ክብር ያውጃሉ:: በቃላት ሊነገር የማይቻል፣ ለእርሱ ሲባል የመስዋዕትነት ፅዋን የመጎነጨት ደስታ የአንተ ይሆናል:: እኔም ደግሞ፣ የመስዋዕትነትን መንገድ ተከትዬህ እጓዛለሁ፣ ከዚያም በዘለዓለማዊው መንግስት ውስጥ ከአንተ ጋር እሆናለሁ::”[8]**

1. ባብ ወደ ስግደት እና መሳለም ጉዞ ለመጓዝ የተነሳው መቼ ነው? ______________________

2. ባብ ለስግደት እና ለመሳለሙ ጉዞ ወዴት ከተሞች ሄደ? ___________________________

3. በመካ ደብዳቤ የፃፈው ለማን ነው?_______________________

4. መዲና ለሙስሊሞች ቅድስት ከተማ ለምን ሆነች? _______________________

5. ከዚህ በታች በሚገኘው ባዶ ቦታ፣ ባብ ቡሺር ሲደርሱ ለቅዱስ የነገረውን በእራስዎ ቃላት ያስፍሩ::

   ________________________________________________________________________

   ________________________________________________________________________

   ________________________________________________________________________

   ________________________________________________________________________

   ________________________________________________________________________

6. ባብ ለቅዱስ ቃል የገባለት ማንን እንደሚያገኝ ነው?______________________________

## ምዕራፍ 5

በሺራዝ ቅዱስ እምነቱን በጋለ ስሜት ማስተማር ጀመረ፡፡ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ከእስልምና ቀሳውስት እና ከአውራጃው ገዢ ከፍተኛ ተቃውሞ ደረሰበት፣ ከዚያም እርሱ እና ሁለቱ ባልደረባዎቹ እንዲታሰሩ ትዕዛዝ ወጣ፡፡ ጨካኝ እና እኩይ የሆነው አገረ-ገዢ፣ በሕዝብ ፊት እንዲቀጡ አዘዘ፡፡ ጢማቸው እንዲቃጠል፣ አፍንጫቸው ተበስቶ በቀዳዳው ገመድ ታስሮ በገመዱ ጫፍ በመንገድ ላይ እየተጎተቱ ሁሉም እንዲያያቸው ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ የአገረ-ገዢው ትዕዛዝ ዓላማ "መናፍቅ መሆን ቅጣቱ ምን እንደሆነ የሺራዝ ሕዝብ ትምህርት እንዲወስዱ ነበር፡፡"[9] ያንን ሁሉ ውርደት ከተቀበሉ በኋላ፣ ቅዱስ እና ባልደረቦቹ ወደ ከተማው ከተመለሱ የከፋ ቅጣት እንደሚደርስባቸው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው፣ ከከተማው ተባረሩ፡፡ እነዚህ ሁለት ጀግና ነፍሶች ለአዲሱ እምነታቸው ሲሉ በፋርስ ውስጥ የመሰቃየትን ክብር በቀደምትነት ተጎናፀፉ፡፡ በኋላ ላይ፣ አብዱል-ባሃ በሺህዎች ለሚቆጠሩት ለእጅግ ተወዳጃቸው፣ ለባብ ሲሉ ስለተሰቃዩት እንዲህ ብሏል፦

> **" . . . እጅግ አሳዛኝ ችግሮችን እና አስከፊ ፍዳዎችን ተቀብለዋል፡፡ ፈተናዎቹን በአስገራሚ ኃይል እና ልብ በሚነካ ጀግንነት ተቋቁመዋቸዋል፡፡ በሺህዎች የሚቆጠሩ ወህኒ ወርደዋል፣ ተቀጥተዋል፣ ተሰቃይተዋል፣ እንዲሁም ሰማዕት ሆነዋል፡፡ ቤቶቻቸው ተዘርፈዋል እንዲሁም ወድመዋል፣ ይዞታዎቻቸውም ተወርሰዋል፡፡ በእምነታቸው እስከመጨረሻው ፍንክች ሳይሉ ሕይወታቸውን በሙሉ ፈቃደኝነት አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡ እነዚያ አስገራሚ ነፍሶች፣ የእግዚአብሔር መቅረዞች፣ ከዘለዓለማዊው የእግዚአብሔር ፈቃድ አድማስ በክብር የሚያንፀባርቁ የንፅህና ክዋክብት ናቸው፡፡"[10]**

በቅዱስ እና በባልንጀሮቹ ላይ ኢፍትሐዊ ቅጣቱን ካዘዘ በኋላ፣ አገረ ገዢው ንዴቱን ወደ ባብ አዞረ፡፡ ወታደሮቹን ወደ ቡሺር በፈረስ ጋልበው ሄደው ባብን በቁጥጥር ስር እንዲያውሉት እና በሠንሠለት አስረው እንዲያመጡለት ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ በዚያን ወቅት ባብ፣ ቡሺርን ለቅቆ ወደ ሺራዝ በፈረስ እየተጓዘ ነበር፡፡ ከብዙ ጊዜ በኋላ፣ የፈረሰኞቹ ቡድን መሪ አጋጥሞት የነበረውን በእንዲህ ዓይነት መልኩ ተርኮታል፡፡

> **"በቀረብነው ጊዜ ሠላምታ አቀረበልንና ወዴት እየተጓዝን እንደሆነ ጠየቀን፡፡ እውነቱን ከእርሱ መደበቁ የተሻለ ስለመሰለኝ፣ በዚህ አካባቢ የሆነ ጉዳይ እንድናጣራ በአገረ-ገዢው ታዘናል በማለት መለስኩለት፡፡ እሱም በፈገግታ 'አገረ-ገዢው እኔን በቁጥጥር ስር እንድታውሉኝ ልኳችኋል፡፡ ይኸው አግኝታሁኛል፣ እንዳሻችሁ አድርጉ፡፡ ላገኛችሁ በመውጣቴ የጉዟችሁንም ርቀት ላሳጥርላችሁ፣ በቀላሉም እንድታገኙኝ አድርጌላችኋለሁ፡፡' አለኝ፡፡ በዚህ አስተያየቱ ስደነግጥ በግልፅነቱ እና በቀጥተኛነቱ ተገረምኩ፡፡ ሆኖም እራሱን ለማሳሰር እና በገዛ ፈቃዱ በመንግስት ባለስልጣን ጭካኔ ቅጣት ስር በመውደቅ ሕይወቱን እና ደህንነቱን ለአደጋ ለማጋለጥ የነበረውን ዝግጁነት ለመገንዘብ አልቻልኩም ነበር፡፡ እንዳልሰማሁ በመምሰል ለመሄድ ስዘጋጅ ተጠግቶኝ 'በእርሱ ሰውን በፈጠረው፣ ከተቀሩት ፍጡራን ሁሉ በለየው፣ ልብንም የልዕልናው እና የእውቀቱ መቀመጫ ባደረገው ታላቅነት፣ ሕይወቴን ሙሉ ከእውነት ውጪ አለመናገሬን፣ ከወገኖቼ ደህንነት መሻሻል በስተቀር ሌላ ምንም ዓይነት ፍላጎት እንደሌለኝ እምላለሁ፡፡ የግሌን ምቾት ትቼያለሁ፣ በማንም ላይ የጉዳት እና የሐዘን መንስዔ ከመሆን ርቄአለሁ፡፡ እኔን**

እየፈለጋችሁ እንደሆነ አውቄአለሁ አንተን እና ባልደረቦችህን ለእኔ ስትሉ አላስፈላጊ ለሆነ ብስጭት ከምዳርጋችሁ በገዛ ራሴ እጄን ብሰጣችሁ እመርጣለሁ፣' አለኝ። እነዚህ ቃላት እጅግ በስሜት ቀሰቀሱኝ። በደመ-ነፍስ ከፈረስ ወርጄ የእግሮቹ መረገጫ እርካብን ስሜ እንዲህ አልኩት :– 'አቤቱ የአምላክ ነብይ ዓይኖች ብርሃን ሆይ! በፈጠረህ እና እንዲህ ያለ የበላይነት እና ኃይል ባደለህ ይሁንብህ እያልኩ፣ ጥያቄዬን እንድታሟላልኝ እና ፀሎቴን እንድትመልስልኝ እማፀንሃለሁ። ከዚህ ቦታ ጠፍተህ በመሄድ ከምህረት የለሹ እና ከዚህ ከተናቀው አውራጃ ገዢ እንድታመልጥ እለምንሃለሁ። ይህ በአንተ ላይ የተጠነሰሰው ሴራ ያስበረግገኛል፣ እንዲህ ንፁህ እና ጨዋ በሆነ የእግዚአብሔር ነብይ ተወላጅ ላይ ለሚያቅደው ተንኮል መሣሪያ የመሆኔን ሐሳብ እቃወማለሁ። . . . ' ለዚህ ከልብ ለመነጨ ጥያቄዬ የሚከተለውን መልስ ሰጠኝ:– 'ፍቅር ለተመላው እና ለበጎ ዓላማህ ጌታ አምላክ ምላሹን ይስጥህ። የእምነቴን ምስጢር የሚያውቀውም ሆነ ጥልቅ ነገሮቹን የሚደርስበት ማንም የለም። ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ መቼም ቢሆን ፊቴን አላዞርም። እርግጠኛ እና ጠንካራ ምሽጌ፣ ደጋፊዬ እና መጠለያዬ እርሱ ብቻ ነው። የመጨረሻዋ ሰዓት እስክትደርስ ማንም ሊያጠቃኝ፣ ማንም የሁሉን ቻዩን እቅድ ሊያደናቅፍ አይችልም። ሰዓቴ ቀርባለች (ደርሳለች)፣ በእርሱ ስም የሰማዕትነትን ፅዋ ስጨልጥ ደስታዬ ምን ያህል ታላቅ ይሆን! ይኸው በፊትህ እገኛለሁ! ለጌታህ እጆች አስረክበኝ፤ የሚወቅስህ ስለሌለ ፍርሐት አይግባህ' ሲለኝ በመስማማት እጅ ነስቼ ፍላጎቱን ፈፀምኩ።"[11]

ባብ ወዲያውኑ ታጅቦ ጉዞውን ወደ ሺራዝ ቀጠለ። ምንም ዓይነት ሠንሠለት በእጆቹ ላይ ሳይጠልቁ፣ በነፃነት በአክብሮት ከሚከተሉት ከፈረሰኞቹ ዘቦች ቡድን ፊት ለፊት ይሄድ ነበር። ሺራዝ ሲደርሱ፣ ባብ በከፍተኛ ማዋረድ እና ጭካኔ አያያዝ በተቀበለው አገረ-ገዢ ፊት ቀረበ። በሕዝቡ ፊት ባብን በመንቀፍ ተቸው። በአጎቱ ጥበቃ ስር ሆኖ እንዲቆይ ለቀቀው። ምንም እንኳ ባብ በገዛ ቤቱ እንዲቆይ ቢፈቀድለትም ነፃነቱ የተገደበ ነበር። ሊያገኙት የሚችሉት የቤተሰቡ አባላት እና ሌሎች ጥቂቶች ብቻ ነበሩ። ምንም እንኳ አገረ-ገዢው እና ቀሳውስቱ የእርሱን ተፅዕኖ ለመግታት ቢጥሩም፣ የተከታዮቹ ቁጥር ግን በፍጥነት እየጨመረ ሄደ።

የባብ ከፍተኛው እና የማይረሳው አዋጅ እጅግ ከመሰራጨቱ የተነሳ የፋርሱ ንጉስ ሁኔታውን እንዲመረምር እጅግ ታማኙንና ዓዋቂውን ሊቅ ወደ ሺራዝ ለመላክ ወሰነ። ይህ የተማረ ሰው፣ ሺራዝ አገረ-ገዢው ቤት በእንግድነት ተቀምጦ ከባብ ጋር ሦስት ጊዜ የመገናኘት አጋጣሚ አገኘ። የባብን ማስረጃዎች ለማስተባበል በቆራጥነት ወስኖ ነበር፣ ነገር ግን በእያንዳንዱ ግንኙነት በእርሱ(በባብ) እውቀት፣ አንደበተ-ርቱዕነት እና ጥበብ እየተመሰጠ ሄደ። በሦስተኛው ግንኙነት ወቅት፣ ቫሂድ የተባ ለው ሊቅ፣ በወጣቱ መለኮታዊ ደረጃ ሙሉ ለሙሉ እያመነ መጣ። ቫሂድ ከባብ ጋር ስለነበረው ግንኙነትን በኋላ ላይ እንዳብራራው "ከእርሱ እግር ስር እንዳለው አቧራ፣" እንደሆነ ተሰማው። ከዚያም በፍጥነት ለንጉሡ ችሎት ዘገባ ከፃፈ በኋላ በባብ መመሪያ መሠረት ሺራዝን ለቆ ሄደ። ከዚያን ቀን በኋላ፣ መላውን ጉልበቱን የእርሱን (የባብን) እምነት ለማስተማር አዋለው፣ በመጨረሻም በእርሱ ተወዳጅ መንገድ ሕይወቱን ሰዋ።

በባብ ታዋቂነት እና ዝነኝነት የተነሳ የአገረ-ገዢው ቁጣ እያየለ መጣ። እንደገና እንዲታሰር አዘዘ። በዚህን ጊዜ ባብ እንዲገደል ፍላጎት ነበረው፣ በአጎቱ ቤት ያለውን ባብ፣ በቁጥጥር ስር ለማዋል የፖሊስ መኮንኑን በእኩለ ሌሊት ላከ። ነገር ግን፣ በዚያ ምሽት ሌሊቱን፣ በአጠቃላይ በሺራዝ ከተማ ውስጥ ወረርሺኝ ተነስቶ ጠቅላላው ሀገር ተሸበረ። በጥቂት ሰዓታት ውስጥ በዚህ አስከፊ በሽታ ከአንድ መቶ በላይ ሰዎች አለቁ። በየመንገዶቹ የሕመም እና የስቃይ ድምፅ ይሰሙ ጀመር፣ የከተማው ነዋሪዎችም ግራ በመጋባት ሀገር ለቀው ሸሹ። ምን ማድረግ እንዳለበት መወሰን የተሳነው፣ መኮንኑ ባብን ወደ

እራሱ ቤት ይዞት መጣ:: እርሱ ቤት እንደደረሱ መኮንኑ የእራሱ ልጅ ከበሽታው የተነሳ ሊሞት መሆኑን አወቀ:: በከፍተኛ ሐዘን እራሱን ባብ እግር ስር ከጣለ በኋላ ይቅር እንዲለው አጥብቆ ለመነው:: ልጁ በተዓምር መዳኑን ሲያይ፣ መኮንኑ ወረርሽኙ የአምላክ እጅ መሆኑን አውቆ፣ ባብን እንዲለቀው አገረ-ገዢውን ተማፀነ:: አገረ-ገዢው ለእራሱ እና ለቤተሰቡ ሕይወት ስለፈራ፣ ባብ ሺራዝን ለቅቆ እንዲሄድ በጉዳዩ ተስማማ::

በ1846 የክረምት ወቅት ባብ፣ ከሺራዝ በስተደቡብ ወደ ሚገኘው፣ ወደ ኢስፋሃን ከተማ ተጓዘ:: አጎቱን እየተሰናበተ ሳለ እንዲህ አለው:– "በድጋሚ የማገኝህ በአዘርባይጃን ተራሮች መካከል ሲሆን ከዚያም የሰማዕትነት አክሊል ወደ ምትጎናፀፍበት ቦታ እልክሃለሁ:: እኔም ከታማኝ ደቀመዛሙርቴ መካከል ከአንዱ ጋር በመሆን ተከትዬህ በዘለዓለማዊው ግዛት አብረን እንሆናለን::"[12]

1. ቅዱስ ሺራዝ ሲደርስ ምን አደረገ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

2. ቅዱስ የባብን መልዕክት በሺራዝ ማስተማር ሲጀምር ማን ተቃወመው? ____________________

3. "ቀሣውስት" ቃል ትርጉም ምን ማለት ነው? ____________________________________

4. የሺራዙን አገረ-ገዢ ባህርይ በምን ዓይነት ቃላት ይገልፁታል?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

5. አገረ-ገዢው በቅዱስ እና በሁለቱ ጓዶቹ ላይ ምን ዓይነት ቅጣት አዘዘ? ____________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

6. "መናፍቅ" ማለት ምን ማለት ነው? ____________________________________________

7. ቅዱስ እና ሁለቱን ባልደረባዎቹ ከሺራዝ እንዲባረሩ ካደረገ በኋላ፣ አገረ-ገዢው የእርሱ ጠባቂዎች ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

8. ወታደሮቹ ሲያገኙት ባብ ምን እያደረገ

ነበር?_________________________________________________________________

________________________________________

9. ባብ እርሱን እንዲያስሩ ተልኮ ለመጣው የዘቦቹ ቡድን መሪ እንዲህ አለው፣

'____________________ እኔን __________________________ ልኳችኋል። ይኸው

አግኝታሁኛል፣ _____________________። ላገኛችሁ በመውጣቴ ____________________

ላሳጥርላችሁ፣ በቀላሉም ___________________አድርጌላችኋለሁ።' አለኝ። እንዳልሰማሁ

በመምሰል ለመሄድ ስዘጋጅ ተጠግቶኝ _____________________፣

__________________________________፣ ______________________ እና

_________________________ ባደረገው ___________________፣

________________________ሙሉ ________________________ አለመናገሬን፣

_____________________________________ ___________________ በስተቀር ሌላ

______________________ ________________________ እንደሌለኝ እምላለሁ።

________________________ ትቼያለሁ፣ በማንም ላይ ______________________ እና

______________________መንስዔ ከመሆን ርቄአለሁ። እኔን

____________________________ እንደሆነ አውቄአለሁ ______________________

እና _____________________ ለእኔ ስትሉ _________________________ ለሆነ

____________________ ከምዳርጋችሁ _________________________ እጄን ብሰጣችሁ

እመርጣለሁ፣' አለኝ።

10. ባብ የወታደሮቹን ጥላቻ እንዴት አስወገደ? ______________________________________

11. ባብ ሺራዝ የደረሰው በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነበር?

______________________________________________________________________

_________________________________

12. አገረ-ገዢው በባብ ላይ የወሰደው እርምጃዎች ምን ነበሩ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

13. በተከታዮቹ ወራቶች የእርሱን ተፅዕኖ መቋጫ ለመስጠት፣ በአገረ-ገዢው እና በቀሳውስቱ የተሞከሩ ሙከራዎች ውጤቶች ምንድን ናቸው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

14. ቫሂድ ማን ነው?

__________________________________________________________

15. እያደገ ለመጣው የባብ ዝና የአገረ-ገዢው ምላሽ ምን ነበር?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

16. አገረ-ገዢው በስተመጨረሻ ባብን እንዲለቀው እና ሺራዝን ለቅቆ እንዲወጣ ያደረገው ምን ነበር?

______________________________________________________________________

17. ባብ ሺራዝን ለቅቆ ከወጣ በኋላ ወደ የት ሄደ? ____________________________________

18. ይሄንን ጉዞ ያደረገው መቼ ነው? ______________________________________________

19. ባብ አጎቱን ተሰናብቶ ሲሄድ ምን አለው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

20. ከቡድኖ አባላት ጋር በመጣመር ተራ በተራ በቡሺር እና በሺራዝ መካከል ባለው ዱር ውስጥ ባብ ከፈረሰኞች አጃቢዎቹ ጋር ያጋጠመው ትዕይንትን እርስ በእርሳችሁ በመተረክ ተወያዩበት።

## ምዕራፍ 6

ባብ ወደ ኢስፋሃን ከተማ እየተቃረበ ሲመጣ፣ ለአውራጃው አገረ-ገዢ የሚያርፍበትን ቦታ ያስታውቀው ዘንድ ደብዳቤ ፃፈለት። ልበ ንፁህ የሆነው አገረ-ገዢ በባብ ደብዳቤ አፃፃፍ እጅግ ስሜቱ ተነክቶ የአውራጃው ከፍተኛው የሃይማኖት ባለሟል ባብን በእርሱ ቤት እንዲያስተናግደው እና ሞቅ ያለ እና ልግስና የተሞላበት አቀባበል እንዲያደርግለት አዘዘ።

ባብ በኢስፋሃን ቆይታው የእርሱን ንግግሮች ለመስማት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በየቀኑ ይመጡ ነበር። ነገር ግን፣ እያደገ የመጣው የእርሱ ዝና፣ ለዘመናት ተቆጣጥረውት የነበረውን ኃይል እና ሥልጣን ልናጣ ይሆናል ከሚል ስጋት፣ የአካባቢውን ቀሳውስት ቅናት አነሳሳ። በእርሱ ላይ ጥርጣሬን ለመዝራት በባብ ላይ የሐሰት ወሬዎችን መንዛት ጀመሩ። ይህ አልሳካ ሲል፣ እርሱን ለማስወገድ እቅድ ጠነሰሱ። ይህንን የቀሳውስቱን ውጥን ሴራ የተረዳው አገረ-ገዢ፣ ባብን በእራሱ ቤት እንዲቆይ ጋበዘው። እዚያም፣ በውይይት በቆዩባቸው ሰዓታት፣ አገረ-ገዢው የእርሱን ግልፀት ታላቅነት መረዳት ቻለ። አንድ ቀን፣ በእርሱ ቤት በሚገኘው የአትክልት ስፍራ ከባብ ጋር ተቀምጠው ሳለ፣ አገረ-ገዢው እንዲህ አለው፦

> ***"እጅግ ኃያሉ ሰጪ ከፍተኛ ሐብት ለግሶኛል። እንዴት በአግባቡ እንኳን እንደምጠቀምበት አላውቅም ነበር። አሁን በእግዚአብሔር እርዳታ ይህንን ግልፀት ለማወቅ በመቻሌ፣ ንብረቴን ሁሉ የእምነቱን ጉዳዮች ለማራመድ እና ዝናውን ለማግነን እንዲውል ለማድረግ ፍላጎቴ የጋለ ነው። ከፈቀድክልኝ ደግሞ ወደ ቴህራን መሄድ እና በእኔ ያለው እምነት ፅኑ እና የማይነቃነቅ የሆነውን ንጉሡን የዚህ እምነት ተከታይ ለማድረግ ፍላጎት አለኝ።"[13]***

ለዚህ የፍቅር እና የፅኑነት ጎርፍ የባብ ምላሽ እንዲህ ያለ ነበር፦

> ***"ልትተገብራቸው ላሰብካቸው የተከበሩ ሐሳቦች ወሮታውን አምላክ ይክፈልህ። ለእኔ እንደዚህ ዓይነቱ የላቀ ዓላማ ከተግባሩ ከእራሱ የበለጠ ውድ ነው። ሆኖም የአንተ እና የእኔ ቀናት አጭር ናቸው፤ እነዚህን ተስፋዎችህን ለመፈፀም እኔም ፍፃሜያቸውን ለማየት የሚበቁ አይደሉም። ሁሉን ቻዩ አምላክ የእምነቱን ድል የሚያመጣው አንተ ተስፋ ባደረግከው መንገድ አይደለም። ምንም የማይሳነው ንጉሥ የእምነቱን መሠረት የሚያፀናው፣ የሚያጠናክረው እና የሚረጋግጠው በዚህ ምድር ድሆችን እና ዝቅተኞች፣ እነርሱ በእርሱ መንገድ በሚያፈሱት ደም***

**አማካኝነት ነው። አምላክ ራሱ፣ በሚመጣው ዓለም በራስህ ላይ የዘለዓለማዊ ክብር ዘውድ ያጎናፅፍሃል፣ እንዲሁም በዋጋ የማይታመኑ ቡራኬዎቹን ያዘንብልሃል። ከምድራዊ ህይወትህ ሦስት ወራት እና ዘጠኝ ቀናት ብቻ ቀርተውሃል፣ ከዚያ በኋላ በእምነት እና በእርግጠኝነት ወደ ዘለዓለማዊ መኖሪያህ ትገሰግሳለህ።"[14]**

ባብ እንደተነበየው ከሦስት ወራት እና ከዘጠኝ ቀናት በኋላ አገረ-ገዢው አረፈ። እርሱ ከሞተ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ የእርሱ ተተኪ የሆነው ባብን ምን ላድርገው፣ ሲል ቴህራን ለሚገኘው ንጉሥ መልዕክት ላከ። ንጉሡ ባብን ሊያገኘው ወደ አሰበበት ዋና ከተማ በድብቅ እንዲልከው አዘዘው። ስለሆነም ባብ በፈረሰኞች ታጅቦ ወደ ቴህራን የሚያደርገውን ጉዞ ጀመረ።

1. ባብ ኢስፋሃን ከተማ እየተቃረበ ሲመጣ ደብዳቤ የፃፈው ለማን ነበር?

______________________________________________

2. የኢስፋሃኑን አገረ-ገዢን ባህርይ ምን ቃላት ሊገልፁት ይችላሉ?

______________________________________________

______________________________________________

3. ለአውራጃው ከፍተኛ የሃይማኖት ባለሟል አገረ-ገዢው የሰጠው ትዕዛዝ ምን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

4. የኢስፋሃን ቀሳውስትን ያስቀናቸው ጉዳይ ምንድን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

5. ባብ እምነቱን ማወጁን ከቀጠለ ቀሳውስቱ ምን ልናጣ እንችላለን ብለው ሰጉ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

6. ከቀሳውስቱ ሴራ ባብን ለመታደግ የኢስፋሃን አገረ-ገዢ ያደረገው ነገር ምንድን ነው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

7. አገረ-ገዢው ለባብ እምነት ያቀረበው ልግስና ምን ነበር?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

8. አገረ-ገዢው ለሰጠው ልግስና የባብ ምላሽ ምን ነበር?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

9. የአምላክ ሃይማኖት እድገትን በተመለከተ ባብ ለአገረ-ገዢው በሰጠው ምላሽ ምን ዓይነት ፍፁም ጥልቅ እውነታን ተናገረ?

________________________________________________________________

__________________________________________________________

10. ለአገረ-ገዢው ተተኪ ወራሽ ንጉሡ ምን ዓይነት ትዕዛዝ አስተላለፈ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

## ምዕራፍ 7

በዚያን ጊዜ የፋርሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ራስ ወዳድ እና ለቦታው ብቃት የሌለው ሰው ነበር፡፡ ባብ ወደ ቴህራን መጥቶ ከንጉሡ ጋር ቢገናኝ ቦታውንና ሥልጣኑን አጣለሁ በማለት ፈራ፡፡ ስለዚህ ንጉሡን አሳምኖ ትዕዛዙን በማስለወጥ ባብን ከአገሪቱ ሰሜን ምዕራብ ወደሚገኘው አዘርባይጃን አውራጃ እንዲላክ አስደረገው፡፡

በጁን ወር 1847፣ የአውራጃው ዋና ከተማ ወደ ሆነው፣ ወደ ታብሪዝ ባብ በፈረሰኞች ታጅቦ ከደረሰ በኋላ፣ ወደ አንድ ቤት ተወስዶ በእስራት እንዲቀመጥ ተደረገ፡፡ ቤቱም በተወሰኑ ወታደሮች ይጠበቅ ነበር፡፡ ከሁለቱ የእርሱ ተከታዮች በስተቀር፣ ማንም እንዲያየው አይፈቀድም ነበር፡፡ ማንም ባብን

ለማየት የሞከረ ሰው ወደ እስር ቤት እንደሚወረወር እና ጠቅላላ ሐብቱ እንደሚወረስ ለከተማው ሕዝብ ማስጠንቀቂያ ተላልፎ ነበር።

ባብ በታብሪዝ ለአጭር ጊዜ ከቆየ በኂላ ከትልቅ ከተሞች እና መንደሮች እርቆ በሚገኝ በአዘርባይጃን ተራሮች ስር ባለ ማህኩ በተባለ ምሽግ ውስጥ እንዲቆይ ተደረገ። በዚህ የዳር አገር እና ምቹ ያልሆነ ጥግ ስር በግዞት ማስቀመጥ፣ የባብን ተፅዕኖ ያመናምነው እና የኂላ የኂላ እንዲረሳ ያድርጋል በማለት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገምቶ ነበር። ነገር ግን እርሱ ያልተገነዘበው ነገር ቢኖር፣ የእግዚአብሔር ሃይማኖት መብራት አንዴ ከበራ፣ የትኛውም የሰው ልጅ እጅ ሊያጠፋው አለመቻሉን ነበር። ባብም በግርማው እና በፍቅራዊ ደግነቱ ወዲያውኑ ምሽጉን የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠው ባለስልጣን እና የአካባቢውን ሕዝብ አክብሮት እና አድናቆትን ማትረፍ ቻለ።

ከዚያም በባብ ላይ ተጥሎ የነበሩት ጥብቅ እገዳዎች ቀስ በቀስ እየላሉ ሄዱ፣ እርሱን ለመጎብኘት ከተለያዩ የፋርስ ክፍሎች ቁጥራቸው በየጊዜው እየጨመረ ለመጣው ተከታዮቹም የምሽጉ በሮች ተከፈቱ። ባብ በማህኩ በእስር ላይ በነበረበት ጊዜ ከሥራዎቹ ሁሉ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነውን የፋርስኛውን ባያንን ገለፀ። በዚህ መፅሐፉ የእርሱን ህግጋቶቹን መሠረተ፤ ከዚህም ሌላ ከእርሱ የግልፀት ሌላ የላቀ (ግልፀት) የሚመጣ መሆኑን በግልፅ እና በቀጥታ አስታወቀ፤ ተከታዮቹንም "እርሱ አምላክ የሚከስተውን" ፈልገው እንዲያገኙት አሳሰባቸው (አስጠነቀቃቸው)። በዚያን ጊዜ በማህኩ ይኖር የነበረ ከተከታዮቹ አንዱ ስለ ፋርስኛ ባያን ግልፀት እነዚህን በመሰሉ ዓይነት ቃላት አብራርቷቸው ነበር።

> **"የእምነቱን ትምህርት እና መሠረተ ሃሳቦች ለጽሐፊው በሚናገርበት ጊዜ፣ ለእነዚያ በተራራው ግርጌ ለሚኖሩት ሰዎች በግልፅ ይሰማ ነበር። የዝማሬው ቃና፣ ከከናፍሮቹ የሚፈሱት የጥቅሶቹ ዜማ አወራረድ ጆሮአችንን ይስቡ በነፍሶቻችንም ውስጥ ጠልቀው ይገቡ ነበር። ተራራው እና ሸለቆው የእርሱን ድምፅ ግርማ ሞገስ አስተጋብተዋል። እርሱም በሚያስተላልፈው ንግግሩ ልቦች በጥልቅ ተርገበገቡ።"[15]**

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ባብ የማህኩን ሕዝብ አድናቆት ማግኘቱንና እምነቱንም በአገሩ ውስጥ መስፋፋት መቀጠሉን ሲሰማ ወደ ቺህሪክ ምሽግ እንዲዛወር ትዕዛዝ አወጣ። ነገር ግን እዚያም በምሽጉ አካባቢ የሚገኙ ከተሞች ሕዝቦች እና ባለሥልጣናት በባብ መግነጢሳዊ ስብዕና ተማረኩ። እንዲያውም እጅግ በጣም ከታወቁት የአካባቢው ቀሳወውስት ጥቂቶቹ አዲሱን ዕምነት ተቀብለው ከእርሱ ተከታዮች ጋር በመሆን ጥቅም የሚያስገኝላቸውን ሥልጣነቸውን ተዉ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቺህሪክ እየሆነ ያለውን ዜና ሲሰማ፣ ባብ ወደ ታብሪዝ እንዲዛወር ትዕዛዝ አስተላለፈ። እዚያም፣ የእርሱን ተፅዕኖ በአሉታዊ መልኩ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማጠናቀቅ፣ የባብን ጉዳይ የሚመረምር የሃይማኖት ባለሥልጣናት ስብሰባ ተጠራ። ጁላይ 1848 ነበር፣ በስብሰባው ላይ ቀሳውስቱ እና የመንግስት ባለሥልጣናት ባብን ለማዋረድ ሞክረው በእርሱ ግርማ ሞገስ እና በታላቅነቱ ተሸነፉ። "አንተ እኔ ማን ነኝ ትላለህ፣ ያመጣኸውስ መልዕክት ምንድን ነው?" ተብሎ ለተጠየቀው መልስ እንዲህ ሲል አወጀ :–

> **"እኔ! እኔ ነኝ! ያ በተስፋ ስጠበቅ የነበረው እኔ ነኝ! ያ ለሺህ ዓመታት ስሙን ስትጠሩ የነበራችሁት፣ ስሙም ሲነሳ (ከመቀመጫችሁ) ብድግ የምትሉት፣ ምፅዓቱንም ለማየት የናፈቃችሁት፣ የግልፀቱንም ሰዓት እንዲያፋጥን ለአምላክ የፀለያችሁት እኔ ነኝ። በእውነት እላችኋለሁ የምስራ**

**ቅም የምዕራብም ሕዝቦች ለቃሌ መታዘዝን እና ለእኔ ሰብዕና ታማኝ ለመሆን ቃል መግባት ይገባቸዋል።"[16]**

ከዚያ ስብሰባ ጥቂት ቀናት በኋላ ባብ ወደ ቺህሪክ ተመልሶ ተወሰደ። ጠላቶቹም ባብን ወደ ቺህሪክ በማምጣት ተልዕኮውን እንዲተው ለማስገደድ ተስፋ አድርገው ነበር። ነገር ግን በመጨረሻ ባብ በሕይወት እስካለ ድረስ፣ በፋርስ ሕዝቦች መካከል የእርሱን እያደገ የሚሄድ ተፅዕኖ ማዕበል ለማስቆም እንደማይቻል ተገነዘቡ።

1. በጊዜው የነበረውን የፋርሱን ጠቅላይ ምኒስትር ባህርይ ምን ቃላት ሊገልፁት ይችላሉ?

____________________________________________________________

2. ባብ ከንጉሡ ጋር መገናኘትን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምን አስፈራው?

____________________________________________________________

3. ባብ ከንጉሡ ጋር እንዳይገናኝ ለመከላከል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምን አደረገ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

4. ባብ በታብሪዝ በቆየበት ጊዜ የመግቢያ በሩን ወታደሮቹ የጠበቁ የነበረው ለምንድን ነው?

____________________________________________________________

5. ለከተማው ሕዝብ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነበር?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

6. ባብ በታብሪዝ ከነበረው የአጭር ጊዜ ቆይታ በኋላ የተዛወረው ወዴት ነው?________________

7. በማህኩ ከታሰረ በኋላ የባብ እምነት ምን ይሆናል ብሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገመተ?

____________________________________________________________

8. የጠቅላይ ሚኒስትሩ አስተሳሰብ እንዴት የተሳሳተ ሆነ?

________________________________________________________________

_______________________________________________________________

9. በማህኩ የባብ እስር ቤት በሮች ለእርሱ ተከታዮች እንዴት ሊከፈቱ ቻሉ?

________________________________________________________________

_______________________________________________________________

10. ባብ በማህኩ ምሽግ በእስር በቆየበት ጊዜ የገለፀው እጅግ ጠቃሚ መፅሐፍ ምን ነበር?

__________________________________________________

11. የፋርስኛው ባያን አንዳንድ ጭብጦች ምን ነበሩ?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

12. በባያን ውስጥ፣ ባብ ማንን እንዲፈልጉ እና እንዲያገኙ አስጠነቀቃቸው?

___________________________________________

13. የባብ እምነት መስፋፋቱን በመቀጠሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምን አደረገ?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

14. ባብ ወደ ቺህሪክ ከተዛወረ በኋላ የእርሱ እምነት ምን አጋጠመው?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

15. የባብ ጠላቶች ባብን ከቺህሪክ ወደ ታብሪዝ በማምጣታቸው ምን ማሳካት ፈልገው ነበር?

________________________________________________________________

16. ባለሥልጣናቱ ባብን በምርመራቸው ወቅት ምን ዓይነት ጥያቄ ጠየቁት?

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

17. ለጥያቄዎቻቸው የባብ ምላሽ አዋጅ ምን ነበር?

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 8

ባብን በሚመለከት፣ አብዱል-ባሃ እንዲህ አለ :–

> *"ነፍሴ ስለእርሱ መስዋዕት ትሁንና! — ባብን በተመለከተ፣ እምነቱን ለማወጅ የተነሳው የተባረከው ሕይወቱ ሃያ አምስተኛው ዓመቱ ሲደርስ፣ ገና በወጣትነት እድሜው ነበር። . . . ብቻውን፣ ሊታሰብ ከሚቻል በላይ፣ በሃይማኖት አክራሪነታቸው በዓለም ሁሉ በታወቁት የፋርስ ሕዝቦች ተልዕኮውን ለማወጅ ተነሳ። ይህ አንፀባራቂ ህልውና የፋርስ ሕዝቦችን የሃይማኖ ቶቻቸውን ሕግጋቶች መሠረቶቻቸውን፣ ወጎቻቸውን፣ ስነ-ምግባራዊ አኗኗናቸውን፣ ግብረገብነ ታቸውን፣ እና ልማዶቻቸውን በሚያናውጥ ኃይል ተነስቶ አዲስ ሕግ፣ እምነት እና ሃይማኖት አቋቋመ። ምንም እንኳ የአገሩ ታላላቅ ሰዎች፣ የሕዝቡ አብዛኛው ክፍል፣ እና የሃይማኖት መሪዎች በአንድ ላይ ተባብረው ሊያጠፉት እና ሊያወድሙት ቢነሱም፣ እርሱ ያለምንም አጋዥ ብቻውን ተቋቁሟቸው ጠቅላላውን ፋርስ አነቃነቀ። እነዚህ በፍፁም ደስታ እና ፈቃደኝነት በእርሱ መንገድ ሕይወታቸውን በመስዋዕትነት መስክ ለመስጠት የተጣደፉት፣ የሃይማኖት ብፁዓኖች፣ መሪዎች፣ እና የአገሪቷ ነዋሪዎች እንዴት ብዙ ነበሩ።*
>
> *መንግስቱ፣ ሕዝቡ፣ ቀሳውስቱ፣ እና የታወቁ ታላቅ ሰዎች፣ የእርሱ ብርሃን የሚጠፋ መስሏ ቸው ተመኝተዋል፣ ነገር ግን ሙከራቸው ከንቱ ነበር። በስተመጨረሻ የእርሱ ጨረቃ ከፍ አለች፣ የእርሱም ኮከብ አበራች፣ መሠረቱም የማይነቃነቅ ሆኖ ፀና፣ አድማሱም በብርሃን ጅረት ተጥለቀለቀ። እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸውን በመለኮታዊ ትምህርት አሠለጠነ እና በፋርሳውያን፣ አስተሳሰቦች፣ ባህሎች፣ ስነምግባራት፣ እና ግብረገባዊ አኗኗኖች ላይ አስደናቂ ተፅዕኖ አሳረፈ። ለጠቅላላው የእርሱ ወዳጆች፣ የባሃን ፀሐይ ክስተት ብስራትን አውጆ ለእምነት እና ለእርግጠኝ ነት አዘጋጅቷቸዋል።*
>
> *አንድ ወጣት ነጋዴ፣ አስደናቂ ምልክቶች እና ታላላቅ ውጥኖች በመከሰቱ፣ በሕዝቡ አስተሳሰብ ሆነ አእምሮ ውስጥ ተፅዕኖ ያሳደሩትን፣ የእድገት መሠረቶችን በመዘርጋቱ፣ እና ለስኬት እና ለብልፅግና ቅድመ-ሁኔታዎችን የነበሩትን መመሥረቱ እና ዓለም-ዓቀፋዊ መምህር ለመሆኑ— የትኛውም ሚዛናዊ አእምሮ ያለው ሰው ለመመስከር የማያወላውልበት ሐቅ ነው።"* [17]

ከላይ በተጠቀሰው የአብዱል-ባሃ ቃላት እና እስካሁን ድረስ ባጠኑት ታሪክ በመመስረት ስለ ባብ ሕይወት አንድ አጭር ንግግር እንዲያዘጋጁ ይበረታታሉ።

## ምዕራፍ 9

በ1850፣ እንደፈተኛው ደም እንደተጠማው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ባብ ላይ የሞት ትዕዛዝ ደነገገ። እንደገና ባብ ከቺህሪክ ወደ ታብሪዝ ተወስዶ፣ የእርሱ መሥዋዕትነት ከሚፈፀምበት አደባባይ ከሚታይበት የእስር ቤት ክፍል ውስጥ እንዲቀመጥ ተደረገ።

ባብ ወደ እስር ቤቱ ክፍል በግዳጅ ሲወሰድ፣ ከሕዝቡ መካከል አንድ ወጣት እየተጋፋ በመዝለቅ በባብ እግሮቹ ፊት ተደፋ። ወጣቱም "ጌታ ሆይ! ከአጠገብህ አታርቀኝ" ብሎ ተማፀነው። ባብ ወደሚ ሄድበት ቦታ ሁሉ እንዲከተለው እንዲፈቀድለት ለመነው። ባብም "ተነስ ከእኔም ጋር እንደምትሆን እርግጠኛ ሁን። በነገው ዕለት አምላክ የሚደነግገውን ታያለህ" አለው። ወጣቱም ወዲያውኑ ባብ እና የእርሱ ፀሐፊ በታሰሩበት ክፍል ውስጥ እንዲገባ ተደረገ። ይህም ወጣት አኒስ በመባል ይታወቃል።

አኒስ ስለ አዲሱ መልዕክት የሰማው፣ በጊዜው ምንም እንኳ ባብ ከከተማው ነዋሪዎች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዳያደርግ ከፍተኛ ጫና በተደረገበት በታብሪዝ ባደረገው አጭር የጉብኝት ቆይታ ነበር። በአኒስ ልብ ውስጥ የሚነደው የእግዚአብሔር ፍቅር እሳት በጣም ጠንካራ ስለነበረ ብቸኛ ፍላጎቱ ለአዲሱ እምነቱ እራሱን መስዋዕት ማድረግ ነበር። ነገር ግን የእንጀራ አባቱ በልጁ እንግዳ ባሕርይ በመስጋት አኒስን በቤት ውስጥ በጥብቅ ክትትል እንዲቀመጥ አደረገው። እዚያም አኒስ እግዚአብሔር በተወዳጁ ፊት ለመቅረብ እንዲፈቀድለት በፀሎት እና በሱባዔ ሣምንታትን አሳለፈ። አንድ ቀን በጸሎት ተመስጦ ላይ እያለ ከነባራዊው ሁኔታ ልዩ የሆነ ራዕይ ታየው። ባብ ከፊት ለፊቱ ቆሞ ሲጠራው አየ። አኒስም ከእግሮቹ ስር እራሱን ወረወረ። ባብም **"ደስ ይበልህ፣ በዚህች ከተማ ውስጥ በብዙ ሕዝቦች ዓይኖች ፊት በገመድ ተንጠልጥዬ በጠላቶች ተኩስ መስዋዕት የምሆንበት ሰዓት እየተ ቃረበ ነው። ከእኔ ጋር የሰማዕትነትን ፅዋ የሚካፈል ከአንተ በስተቀር ማንንም አልመርጥም። ይህ እኔ የምሰጥህ ተስፋ እንደሚፈፀም እርግጠኛ ሁን።"**[19] አለው። ስለዚህ አኒስም ከተወዳጁ ጋር የሚገናኝበት ቀን እንደሚመጣ በማወቅ በትዕግስት መጠባበቅ ጀመረ። ከዚያም በስተመጨረሻ የልቡን ምኞት ተቀዳጀ።

በዚያ ምሽት ባብ በደስታ ፈክቶ ነበር። ደስታ በተመላበትም ሁኔታ አኒስንና ሌሎቹን ከእርሱ ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ታስረው የነበሩትን ሦስቱን ታማኝ ተከታዮቹን እንዲህ ሲል አነጋገራቸው። "ነገ የሰማዕትነቴ ቀን ነው። ከእናንተ መካከል አንዱ ተነስቶ በራሱ እጆች ለሕይወቴ ፍፃሜ ያድርግ። እኔ ከጠላት እጅ ይልቅ በወዳጄ እጅ መሰየፍን እመርጣሁ።" ከመካከላቸው እንዲህ ያለውን ውድ ሕይወት ለማጥፋት ለማሰብ የሚችል ስላልነበረ እንባ ከዓይኖቻቸው እየጎረፈ ፀጥ ብለው ቀሩ። ከዚያም በኋላ፣ አኒስ ድንገት ፈንጠር ብሎ በመነሳት፣ ባብ የሚያዘውን ማንኛውንም ነገር ለመተግበር ዝግጁ እንደሆነ ተናገረ። **"ይኸው ምኞቴን ለመፈፀም በፈቃደኝነት የተነሣው ወጣት ከእኔ ጋር የሰማዕትነትን ፅዋ ይቀዳጃል። የሰማዕትነቱንም ዘውድ ከእኔ ጋር እንዲካፈል እርሱን እመርጣለሁ።"**[20]

በሚቀጥለው ቀን ጁላይ 9፣ 1850 በማለዳ አንድ ባለሥልጣን ድንገት ንግግራቸውን በሚያቋ ርጥበት ጊዜ ባብ ከፀሐፊው ጋር እየተነጋገረ ነበር። ባብም **"እኔ ልናገረው የምፈልገውን ማንኛውንም ነገር**

**እስካልነገርኩት ድረስ ምንም የምድር ኃይል ሊያቆመኝ አይችልም። መላው ዓለም ጦርነት ሊያደርግብኝ ቢነሳም እንኳን፣ ሐሳቤን እስከመጨረሻው ቃል ድረስ ከመፈፀም ሊያግዱኝ ኃይል አልባ ናቸው።"**[21] አለው። ነገር ግን፣ ባለስልጣኑ የባብ ቃላትን ምንነት አልተረዳም ነበር። ከዚያም ባብን ከእስር ቤቱ ክፍል አውጥቶ፣ ያለማመንታት፣ የእርሱን ግድያ እንዲፈፀምበት ትዕዛዝ በፊርማቸው ወደ አፀደቁት፣ በከተማው ውስጥ ወደሚገኙ ሦስት ታላላቅ ቀሳውስት መኖሪያ ቤቶች ወሰደ።

ያን ጠዋት ረፋዱ ላይ ባብ፣ በየጣሪያው ላይ በመንጠላጠል፣ ወደ አስር ሺህ የሚጠጋ ህዝብ ወደ ተሰበሰበበት ግቢ እንደገና እየተመራ ተወሰደ። እርሱን ለመግደል ትዕዛዝ ወደተቀበለው፣ የወታደሮች ጦር አዛዥ ለሆነው ለሳም ካሃን እጁን ተሰጠ። ነገር ግን ሳም ካሃን ሁኔታው አላምር አለው። ድርጊቱ የአምላክን ቁጣ ያስከትልብኛል በማለት በፍርሃት ተያዘ። እርሱም ለባብ እንዲህ አለው ፦ "እኔ የክርስቲያን እምነት ተከታይ ነኝ፣ በአንተም ላይ ምንም ዓይነት ክፉ ምኞት የለኝም። የአንተ እምነት የእውነት እምነት ከሆነ፤ የአንተን ደም ከማፍሰስ ግዳጅ ነፃ አድርገኝ።" ባብም **"የታዘዝከውን ፈፅም፣ ሐሳብህ ቅን ከሆነ ኃያሉ አምላክ በእርግጥ ከጭንቀትህ ይገላግልሃል።"**[22] አለው።

ሳም ካሃን ወታደሮቹን አንድ የብረት ምስማር በግድግዳው ላይ እንዲመቱ እና ሁለት ገመዶች እንዲያስሩበት አዘዘ። በእነዚህ ገመዶች ላይ ባብ እና አኒስ ተንጠለጠሉ። ከዚያም እያንዳንዱ ቡድን ሁለት መቶ ሃምሳ ሰዎችን የያዘ፣ በሦስት ረድፍ ወታደሮቹ ተሰልፈው ተዘጋጁ። አንዱ ከሌላው በመቀጠል እያንዳንዱ ረድፍ ተኮሰ። የሰባት መቶ ሃምሳ ጠመንጃዎች ጭስ ከጠራ በኋላ፣ የተደነቀው ሕዝብ በዓይኑ ለማመን የሚያስቸግረውን ትዕይንትን ተመለከተ። አኒስ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት እና በሕይወት ከፊት ለፊታቸው ቆሟል፣ ነገር ግን ባብ ከእይታቸው ውጪ ነበር። ጥይቶቹ በጣጥሰው የጣሉት ተንጠልጥለውበት የነበሩበትን ገመድ ብቻ ነበር። በመደናበር ባብን መፈለግ ጀመሩ ። በስተመ ጨረሻም ታስሮ በነበረበት ክፍል ውስጥ ከጸሐፊው ጋር ተቋርጦበት የነበረውን ንግግሩን ጨርሶ ተቀ ምጦ ተገኘ። ባብም **"አሁን ንግግሬን ፈፅሜአለሁ፣ ሐሳባችሁን ለመፈፀም ትችላላችሁ።"**[23] አለ።

በተፈጠረው ሁኔታ የደነዘዘው፣ ሳም ካሃን የእርሱ ሰዎች እንደገና እንዲተኩሱ አልፈቀደም እናም ግቢውን ለቀው እንዲወጡ ትዕዛዝ ሰጠ። ግድያውን እንዲፈፅም ሌላ ግብረ-ኃይል ተጠራ። እንደገና ባብ እና አኒስ በግቢው ውስጥ በገመድ እንዲንጠለጠሉ ተደረገ፣ ወታደሮቹም ተኩስ ከፈቱ። በዚህን ጊዜ ጥይቶቹ ዒላማቸውን መቱ። የባብ እና የአኒስ አካላት በጥይቶቹ ሙሉ ለሙሉ ተበሳሱ፤ ፊቶቻቸው ግን ይህን ያህል አልተነኩም ነበር። ወታደሮቹ ተኩሱን ለመክፈት ዝግጅት በማድረግ ላይ እያሉ ባብ ሁኔታውን ይመለከት ለነበረው ብዙሐን ከዚህ የሚከተለውን የመጨረሻ ቃላት ተናገረ ፦

> **"አመፀኛ ትውልድ ሆይ፤ ብታምኑኝ ኖሮ እያንዳንዳችሁ ይህንን በማዕረግ ከአብዛኛዎቻችሁ በልጦ የተገኘውን፣ በመንገዱ በፈቃደኝነት እራሱን መስዋዕት ያደረገውን የዚህን ወጣት ምሳሌ ትከተሉ ነበር። እኔን የምታውቁበት ጊዜ ይመጣል፣ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ከእናንተ ጋር አል ሆንም።"**[24]

1. ባብ መስዋዕት የሆነው የትኛው ከተማ ውስጥ ነበር?________________

2. በባብ ላይ የሞት ፍርድ እንዲፈፀም ያዘዘው ማን ነው?________________

3. አኒስ የተባለው ወጣት ከባብ ጋር እንዴት ለስማዕትነት እንደበቃ በራስዎ ቃላት ይተርኩ::

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

4. አኒስ ከባብ ጋር የሰማዕትነትን ዘውድ እንዲቀዳጅ በባብ የተመረጠው ለምን ነበር?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

5. ባብ ግድያ በተፈፀመበት ጠዋት ከፀሐፊው ጋር እየተነጋገረ ሳለ በባለሥልጣኑ በተቋረጠበት ጊዜ ለዘቡ እንዲህ ብሎ ተናገረው :– "እኔ ልናገረው የምፈልገውን

________________________ ____________________________________

ድረስ ምንም ______________________ ኃይል _________________________

አይችልም::

6. የባብን ግድያ እንዲያስፈፅም የታዘዘው ኃይል አዛዥ ስም ማን ነበር? __________________

7. ሳም ካሃን ባብ ምን እንዲያደርግለት ጠየቀው?

_______________________________________________________

8. ባብ ሳም ካሃን ምን እንዲያደርግ ነገረው? ____________________________________

9. በባብ እና በባልደረባው በአኒስ ላይ ተኩስ የከፈቱት ወታደሮች ብዛት ስንት ነበር? __________

10. በተኩሱ ምክንያት ተፈጥሮ የነበረው ጭስ ከጠፋ በኋላ የተደነቀው ሕዝብ ያየው ምን ነበር?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

11. ባብ በተገኘበት ጊዜ ምን እያደረገ ነበር? ______________________________________

12. በኋላ ላይ ባብ በተገኘበት ጊዜ ምን አለ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

13. የባብ ሰማዕትነት የተፈፀመው በምን ዕለት ነበር? ___________________________________

14. ባብ ሰማዕት ሲሆን እድሜው ስንት ነበር? ___________________

15. ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ ባብ፣ የእርሱን ግድያ አፈፃፀም ለመመልከት ለተሰበሰበው ሕዝብ የተናገራቸውን የመጨረሻ ቃላት ይፃፉ?

_____________________________________________________________________________


_____________________________________________________________________________

_____________________________________________________________________________

______________________________________________________________________

## ምዕራፍ 10

የባብን ጉዞዎች እና ግዞቶች ከዚህ በታች በሚገኘው ካርታ ላይ እንድታሰምሩ ይጠበቃል። ይህ ንን በምታደርጉበት ጊዜ፣ በእያንዳንዱ ቦታ ላይ ምን እንደተፈፀመ እና ጠቀሜታውንም አሰላስሉ።



## ምዕራፍ 11

በዚህ ርዕሰ-ምዕራፍ ውስጥ፣ የዚህ ዘመን የአምላክ መንትያዎቹ ክስተቶች ከሆኑት የአንዱን የህይወት ታሪክ ተምራችኋል። በአጭር የሕይወቱ ዘመን ግልፀት፣ ባብ በፋርስ መንፈሳዊ አብዮትን ፈጥሯል። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ንፁህ ነፍሳት መልዕክቱን በመቀበል ባብ "እርሱ እግዚአብሔር የሚከስተው" በማለት ላመላከተው የእግዚአብሔር ክስተት መምጣት እራሳቸውን ማዘጋጀት ጀመሩ። እንደምታውቁት፣ የእግዚአብሔር ክስተት በምድር ላይ በሚታይበት ጊዜ፣ እነዚያ ለሥልጣን እና ለመሪነት ከፍተኛ ጥማት ያላቸው በእርሱ ላይ በመነሳት የእርሱን ግልፀት ብርሃን ለማጥፋት ሞክረዋል። በዚህ ምክንያት በፋርስ ደናቁርት መሪዎች ሰማዕት የሆነው ባብ ብቻ ሳይሆን በሺህዎች የሚቆጠሩ ተከታዮቹም ላይ የሞት ፍርድ ተፈፅሟል። በመጪዎቹ ዓመታት የእነዚህ አዲስ የተወለደውን ግልፀት ዛፍን በደማቸው ያጠጡትን የመጀመሪያዎቹን ባቢዎች የጀግንነት ሕይወት ማጥናት የወደፊ ርዕሳችሁ ይሆናል። እንደ ሙላ ሁሴይን፣ ቅዱስ፣ ታሂሬህ፣ እና ቫሂድ ስለመሳሰሉት ስለዋና ዋናዎቹ ስብዕነዎች፣ ስለ ባሃኢ ዘመን የመጀመሪያ አመታት አስደናቂ ታሪክ መማር በምትቀጥሉበት ጊዜ በህይወታችሁ ሁሉ ለእናንተ የመነሳሳት እና የድፍረት ምንጭ ይሆናሉ። ለአሁን ግን፣ አንዱ መሠረታዊ ጥያቄ ላይ እናሰላስላለን:— በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ፣ በከንቱ አስተሳሰብ በተዘፈቁ፣ እና በሙሰኛ መሪዎች እንደባርያ በሚታዘዙ ምዕላተ ሕዝብ መካከል፣ ቁጥራቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ እንዲህ ዓይነት ነፍሶች ሙሉ ለሙሉ ተለውጠው፣ ይህንን የተለየ ሥራ ልዩ በሆነ ጀግንነት ሊሰሩ ቻሉ? ይህ መልስ ሊገኝ የሚችለው በዓሊ ሙሐመድ በባብ ሰብዕና አማካይነት ብቻ ነው። ስለዚህም፣ ስለቅዱሱ ህላዌ(ባብ)፣ ከባሃኡላህ፣ ከአብዱል-ባሃ፣ እና ከሞግዚቱ ፅሑፎች አንዳንድ ምንባቦችን እንድታጠኑ እና እንድታሰላስሉ ይመከራል።

አብዱል-ባሃ በኑዛዜው እና በቃልኪዳኑ ውስጥ እንዲህ ይላል :—

> ***"(ሕይወቴ ለእነርሱ ቤዛ ይሁንና") የባሃ ሕዝቦች እምነት መሠረቱ ይህ ነው :— 'እርሱ የተከበረው ብፁዕነቱ (ባብ) የእግዚአብሔር አንድነት እና አሐዱነት ክስተት እና የጥንታዊው ውበት አዋጅ ነጋሪ ነው። ብፁዕነቱ የአብሃ ውበት(ባሃኡላህ) ለፅኑ ወዳጆቹ ሕይወቴ መስዋዕት ይሁንና የእግዚአብሔር ከሁሉ የላቀ ክስተት እና የእርሱም እጅግ ከፍተኛ መለኮታዊ ህላዌ የቀኑ ምንጭ ነው። ሌሎች ሁሉ የእርሱ አገልጋዮች እና የእርሱ ትዛዝ ፈፃሚዎች ናቸው።'"***[25]

በሞግዚቱ በተፃፈው አምላክ በአጠገባችን ሲያልፍ ( God Passes By) በተባለው መፅሐፉ የሚከተለውን አንቀፅ እናነባለን :—

> ***"በባሃኡላህ የ'ሕላዌዎች ህላዌ' የ'ባህሮች ባህር፣' የነብያት እና የመልዕክተኞቹ እውነታ በዙሪያው የሚሽከረከሩበት ነጥብ፣ 'የነበረው እና ወደፊትም የሚኖረው እውቀት ሁሉ ከእርሱ እንዲመነጩ እግዚአብሔር ያደረገው፣' 'ማዕረጉ ከሁሉ ነብያት የሚልቀው፣' 'ግልፀቱ ከምርጦቻቸው ሁሉ ግንዛቤ እና የመረዳት ችሎታ በላይ የሆነው፣' ብሎ ያረጋገጠለት ባብ መልዕክቱን አቅርቧል፣ ተልዕኮውንም ፈፅሟል። እርሱ በአብዱል-ባሃ አባባል :— 'የእውነት ንጋት' እና 'ከሁሉም በላይ ታላቅ ብርሃን አብሣሪ' መምጣቱም በአንዱ 'የትንቢቶች ዑደት' ማብቃቱን እና 'የፍፃሜው ዑደት' መጀመሩን ሲያመለክት፣ ወዲያውም በግልፀቱ አማካይነት***

**በአገሩ ያንዣበበውን የጭለማ ጥላ አስወግዶ የዚያ ብርሐኑ መላውን የሰው ዘር የሚሸፍነውን፣ ያ ወደር የሌለውን ሉል በፍጥነት የሚያነሳ መሆኑን አወጀ።"[27]**

ባሃኡላህ ራሱ እንዲህ በማለት ገልፆታል :–

**"ይህንን ከሁሉም በላይ ታላቅ እና አስደናቂ ግልፀት ከእኔ ከራሴ... እንዲለይ ያደረገውን ያንን አጭር ጊዜ፣ የማንም አእምሮ ሊለካው የማይችል ምስጢር እና ማንም ሰው ሊፈታው የማይችል ስውር ነገር ነው። "[28]**

አብዱል-ባሃ እንዲህ ይላል :–

**"የባብ መምጣት ከንጋት ጋር ይመሳሰላል፣ ምክንያቱም ንጋት የፀሐይ ተስፋ አለውና። የባብ ንጋት መላውን ዓለም ስለሚሸፍነው የእውነት ፀሐይ መውጣት ተስፋ ሰጥቷል።"[28]**

## ምዕራፍ 12

በምድር ላይ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ሆኖ ባሳለፈው አጭር ህይወቱ፣ ባብ እጅግ በጣም ብዙ መጽሃፎችን እና ጽላቶችን ገልጿል። አሁን የእርሱን ሕይወት ጥናት የፈፀማችሁ በመሆኑ ከፀሎቶቹ ውስጥ ከዚህ በታች ሁለቱን በቃላችሁ እንድታጠኑ ትመከራላችሁ።

**"ከእግዚአብሔር በስተቀር ችግርን የሚያስወግድ አለ ወይ? በል:– ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው! እርሱ አምላክ ነው! ሁሉም አገልጋዮቹ ናቸው፣ ሁሉም በትዕዛዙ ይኖራሉ።"[29]**


**"በል:– እግዚአብሔር ሁሉን ነገሮች ከሁሉም በላይ ያረካል፤ በሰማይ እና በምድር ከእግዚአብ ሔር በስተቀር የሚያረካ የለም፤ በእውነቱ እርሱ በራሱ የሚያውቅ፣ ሕይወት የሚሰጥ፣ ምንም የማይሳነው ነው።"[30]**

## ምዕራፍ 13

በመፅሐፍ ሁለት ክፍል ሦስት ውስጥ፣ በተከታታይ በማህበረሰቦቻችሁ ቤቶችን ስትጎበኙ፣ በተለይ እንዴት በብዙ ጭብጦች ላይ መነጋገር እንደምትችሉ ለመማር ትኩረት ሰጥታችኋል። አሁን ደግሞ ይህንን ክፍል አጠናቃችኋል፣ ከጭብጦቻችሁ መዝገብ ውስጥ የባብን የህይወት ታሪክ ለመወያየት ልታካትቱት ትችላላችሁ። በየትኛውም አጋጣሚ ምን ያህል ዝርዝር ሁኔታን ለመሸፈን እንደምትሹ፣ በብዙ ምክንያቶች ላይ ይመረኮዛል። ነገር ግን፣ የትኛውንም አጋጣሚዎች ባልተመለከተ፣ የባሃኡላህ አዋጅ ነጋሪነውን እና የአዲሱ ዘመን አብሳሪውን የእርሱን ዋና ዋና የሕይወት ታሪክ ኩነቶች ለመጋራት ተስፋ ልታደርጉ ይገባል። አንዳንዴ ከዚህ ቀጥለው ያሉት ገጾች ጠቃሚ ሆነው ታገኙዋቸው ይሆናል።

# ባብ

## የአዲሱ ዘመን አብሳሪ




ባብ የተወለደው ኦክቶበር 20 ቀን 1819 በኢራን ደቡባዊ ክፍል በምትገኝ ሺራዝ በምትባል ከተማ ነበር። አባቱ ሲሞት ገና ልጅ ነበር። ያደገው በአጎቱ ሲሆን በለጋነቱ ትምህርት ቤት አስገብቶታል።




የባብ መምህር ታላቅ ችሎታውን በፍጥነት ተገንዝቦ እንደዚህ ዓይነት ልዩ የሆነ ልጅ ማስተማር እንደማይችል ተገነዘበ። ባብ የተፈጥሮ እውቀት በእግዚአብሔር ተሰጥቶታል።



በዚያን ጊዜ የኢራን ሰዎች አዲሱን የእግዚአብሔር መልእክተኛ መምጣት ይጠባበቁ ነበር። በምድር ላይ ሰላምና ፍትህ እንዲመጣ በቅርቡ እንዲከሰተ ጸለዩ። ብዙዎች ተስፋ የተገባለትን መልዕክተኛ ፍለጋ ቤታቸውን ፍለጋ ተሰማሩ።




ሜይ 23 1844 ዋዜማ አንድ ወጣት ቃል የተገባውን ለመፈለግ ሺራዝ ደረሰ፡፡ ባብ ከከተማው በር ውጭ አገኘው እና ከረጅም ጉዞው በኋላ እረፍት እንዲያደርግ ወደ ቤቱ ጋበዘው፡፡ ከዛም ባብ በጉጉት ሲጠባበቅ የነበረው እርሱ መሆኑን አወጀ፡፡



“ባብ” የሚለው ቃል “መግቢያ” ወይም “በር” ማለት ነው። ባብ ሁሉንም የዓለም ህዝቦች በማሰባሰብ
አንድ ቤተሰብ የሚያደርግ ሌላ የእግዚአብሄር መልእክተኛ እንደሚመጣ አውጇል።
ባብ የሰውን ልጅ ወደ አዲስ እና የከበር መጪው ዘመን እንደሚመራ በር ነው።



የባብ ተከታዮች ቁጥር በፍጥነት አደገ። በመላው ኢራን ውስጥ እርሱ የከሰተውን መለኮታዊ ትምህርቶች ማሰራጨት ጀመሩ።



ብዙም ሳይቆይ በሕዝብ ላይ ሥልጣናቸውን እንዳያጡ የፈሩት የመንግሥት ባለሥልጣናትና ቀሳውስቱ በአዲሱ የአምላክ እምነት ላይ ተነሱ። ባብን ከተከታዮቹ አርቅው በሀገሪቱ ጫፍ በሚገኝ የምሽግ እስር ቤት ውስጥ አሰሩት።



የባብ ተከታዮች እጅግ በጣም የከፋ ስቃይ ደረሰባቸው። ተጠቁ፣ ተደበደቡ፣ ለእስራትም ተዳረጉ። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተገድለዋል፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር እምነት መስፋፋቱን ቀጠለ።



በ1850 ባብ ሰማዕት ሆነ። በመንግስት ትእዛዝ መሠረት ከአንድ ተከታዮ ጋር በአንድ ግቢ ውስጥ በገመድ ከግንድ ጋር ታሰረ እናም በወታደሮች ስልፈኛ ተረሸነ። ባብ ሲሰዋ 31 ዓመቱ ነበር።



ባብ ህይወቱን የሰጠው "የእግዚአብሔር ክብር" የሆነው ባሃኡላህ፣ የእምነቱ ሰንደቅ በሁሉም የፕላኔቷ ማዕዘናት ላይ እንደሚውለበለብ አይቀሬ ለሆነው መምጣት መንገድ ለማዘጋጀት ነው ።

**ማጣቀሻዎች**

1. ዘዶውን ብሬከርስ፣ የመጀመሪያው የባሃኢ ግልፅት የናቢል ትረካዎች (ዊልሜት የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 1974) ገፅ 75—76

2. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 57

3. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 63

4. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 65

5. ዘ ፕሮሙልጌሽን ኦፍ ዩኒቨርሳል ፒስ፣ አብዱል-ባሃ በ1912 እ.ኤ.አ አሜሪካን እና ካናዳን ሲጎበኝ የሰጣቸው ንግግሮች (ዊልሜት፣ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 1995) ገፅ 138

6. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 85—86

7. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 92—94

8. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 142—143

9. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 146

10. ዘ ፕሮሙልጌሽን ኦፍ ዩኒቨርሳል ፒስ፣ ገፅ 138

11. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 148—150

12. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 198

13. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 212

14. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 213

15. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 249

16. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 315—316

17. ሳም አንሰርድ ኩዌስችንስ (ዊልሜት፣ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 1994) ገፅ 25—26

18. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 507

19. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 307—308

20. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 508

21. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 509

22. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 512

23. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 513

24. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ 514

25. ዊል ኤንድ ቴስታሜንት ኦፍ አብዱል-ባሃ (ዊልሜት፣ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 1991) ገፅ 19

26. ጎድ ፓስስ ባ፣ ገፅ 57

27. በሃኡላህ፣ በባሃኢ የዓለም ስርዓት ላይ የተጠቀሰ፣ የተመረጡ ደብዳቤዎች (ዊልሜት፣ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት1991) ገፅ 124

28. ሾጊ ኤፌንዲ፣ ኢንተሮዳክሽን ቱ ዘ ዶውን ብሬከርስ፤ ገፅ 33

29. ባብ፣ የባሃኢ ፀሎቶች፣ ከባሃኡላህ፣ ከባብ፣ እና አብዱል-ባሃ ፀሎቶች የተውጣጡ (ዊልሜት የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 1993) ገፅ 28

30. ባብ፣ የባሃኢ ፀሎቶች፣ ገፅ 29



# የባሃኡላህ ሕይወት

### ዓላማ

በባሃኡላህ የተለቀቁትን መንፈሳዊ ኃይሎች ጥንካሬን
ተገቢውን አድናቆት የመስጠት ችሎታን
ለማዳበር እና የእርሱን ሕይወት ታሪክ
መተረክን ለመማር፡፡

## ምዕራፍ 1

ሚርዛ ሁሴን ዓሊ በሚባል ስም ይታወቅ የነበረው ባሃኡላህ፣ እ.ኤ.አ. በኖቬምበር 12 ቀን 1817 በፋርስ ዋና ከተማ በቴህራን ተወለደ። አባቱ ሚርዛ ቡዝሩግ የፋርሱ ንጉሥ ከፍተኛ ባለሥልጣንና ታዋቂ መኮንን ነበሩ። ባሃኡላህ ገና በህፃንነቱ የታቅነት ምልክቶች ይታዩበት የነበረ ሲሆን፣ እጅግ የሚያስደነቅ ዓይነት እውቀት እና ጥበብም ነበረው። መደበኛ ትምህርት ቤት ገብቶ አያውቅም፣ ነገር ግን በቤት ውስጥ በጥቂቱ ትምህርት ተሰጥቶታል። ልጅነቱን በተመለከተ አብዱል-ባሃ እንዲህ ይላል:—

> **"የተባረከው ውበት፣ ባሃኡላህ ከፋርስ መኳንንት ወገን ነበር። ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ከዘመዶቹ እና ከጓደኞቹ መካከል የተለየ ነበር። እንዲህ ይሉ ነበር:— 'ይህ ልጅ የተለየ ኃይል አለው። በጥ በብም፣ በአእምሮ ንቃት እና የአዲስ እውቀት ምንጭ በመሆን ከእድሜው በላይ የተራቀቀ እና በአካበቢው ሁሉ የበላይ ነበር።' የሚያውቁት ሁሉ የልጅ አዋቂነቱ መጠን ያስደንቃቸው ነበር። ሁልጊዜ እንዲህ የማለት ልማድ ነበር :— 'እንደዚህ ዓይነቱ ልጅ እድሜ የለውም፣ ምክንያቱም የልጅ አዋቂ የሆኑ ልጆች የጎልማሳነት እድሜን አይደርሱም' በሚል ይታመን ስለነበር ነው።"[4]**

በአንድ ፅላት ውስጥ ባሃኡላህ ራሱ በልጅነቱ ከወንድሞቹ አንዱ በቴህራን ከተማ የጋብቻውን በዓል በፈጸመበት ወቅት የተገኘበትን አንድ ትዕይንት ይናገራል። በዚያን ጊዜ በቴህራን እንደተለመደው ሁሉ ለሰባት ቀናትና ሌሊቶች ታላቅ ፌስታ ተደረገ። በመጨረሻው ቀን እንግዶቹን ለማዝናናት ስለ አንድ የታወቀ ንጉሥ፣ የአሻንጉሊት (የፓፔት) ጨዋታ ይታይ ነበር፣፤ ባሃኡላህም ለትዕይንቱ ተብሎ በተተከለው ድንኳን ትይዩ ከፍ ብሎ በሚገኝ አንድ ክፍል ውስጥ ተቀምጦ ነበር።

ትዕይንቱ ሲጀመር፣ ጥቂት፣ ሰው የሚመስሉ የአሻንጉሊት ቅርፆች ገብተው "ንጉሡ እየመጡ ናቸው" ብለው በማስታወቅ ትዕይንቱን ይጀምራሉ። ከዚያም ሌሎች አሻንጉሊቶች ታዩ። ለንጉሡ መምጣት ዝግጅት ለማድረግ አንዳንዶቹ ጽዳት ያካሂዱ ነበር፣ ሌሎቹ ደግሞ ውኃ ያርከፈክፉሉ። ከዚያም ብዙ ሳይቆይ የከተማው ለፋፊ ወደ ትዕይንቱ ገባ፣ ሕዝቡንም ንጉሡን ለማግኘት እንዲሰበሰቡ ነገራ ቸው። ብዙ ሰዎችም መጡ፣ ተገቢ ቦታቸውንም ያዙ። በመጨረሸም ንጉሡ ግርማ ሞገስ ተላብሶ ገባ። በራሱ ላይ ዘውድ ነበር። ግርማ ሞገስ በተላበሰ ሁኔታ እየተራመደ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ። ተኩስ ተተኮሰ መለከት ተነፋ፣ ድንኳኑም በጭስ ተሞላ።

ጭሱ ሲለቅ ንጉሡ በዙፋን ላይ ተቀመጠ፣ በተጠንቀቅ በፊቱ በቆሙ ምኒስትሮች፣ ልዑላንና የመንግስት ሹማምንት ተከቦ ይታይ ነበር። ከዚያም አንድን ሌባ ንጉሡ ፊት አቀረቡ፤ እርሱም ጭንቅላቱ እንዲቀላ አዘዘ። የቅጣት ፈፃሚዎቹም አለቃ የንጉሡን ትዕዛዝ ወዲያውኑ ፈፀመ። የሞት ቅጣቱ ከተፈፀመ በኂላ ከሚኒስተሮቹ እና ከሹማምንቱ ጋር ማውጋት ጀመረ። ይሁንና ወዲያው ከሀገሪቱ ጠረፎች በአንዱ አመፅ እንደተነሳ የሚያወሳ ዜና ደረሰ። አመፁን ለማንበርከክ ወታደሮች ወዲያውን ተላኩ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኂላ በስተጀርባ በኩል የመድፍ ድምፅ ተሰማ፣ የንጉሡ ወታደሮችም ከአመፀኞቹ ጋር እየተዋጉ መሆናቸው ተነገረ።

በዚህ መንገድ ትዕይነቱ ቀጠለ። ባሃኡላህ በትዕይንቱ እጅጉን ተገረመ። ትዕይነቱ ካለቀ እና መጋረጃው ከተዘጋ በኂላ አንድ ሰው ከድንኳኑ በስተጀርባ አንዲት ሻጥን በክንዱ ስር ይዞ ሲወጣ አየው። "ይህ ሳጥን ምንድነው? ትዕይንቱስ ምን ማለት ነው?" ብሎ ባሃኡላህ ጠየቀው። "እነኚህ ሁሉ የተንቆጠቆጡት ጌጣ ጌጦች፣ ንጉሡ፣ ልዑላኑ፣ እና ሚንስትሮቹ ለእይታ የቀረበው ብልጭልጩ እና ክብራቸው፣ ኃያልነታቸው እና ሥልጣናቸው፤ ያየኸው እያንዳንዱ ነገር ሁሉም አሁን በዚህች ሳጥን ውስጥ ናቸው።"[2] ብሎ መለሰለት። ይህ አባባል በባሃኡላህ ላይ ከፍተኛ ስሜት ስላሳደረበት እንዲህ ሲል ተናገረ:—

**“. . . ከዚያን ቀን ጀምሮ፣ የዚህ ዓለም ወጥመዶች ሁሉ በዚህ ወጣት ዓይን ሲታዩ ያንኑ ዓይነት ትዕይንት ይመስሉታል። የሠናፍጭ ቅንጣት ታክል እንኳ ፈፅሞ፣ በጭራሽ ዋጋ እና ተፅዕኖ አሳድረውበት አያውቁም . . .**

**“ለወደፊቱም እንዲሁ። . . . ብዙ ሳይቆዩ እዚያ ሳጥን ውስጥ እንደገቡ ሁሉ እነኝህ ውጫዊ ወጥመዶች፣ እነኝህ የብርና የወርቅ ክምሮች፣ እነኝህ ምድራዊ ከንቱ ውዳሴዎች፣ እነኝህ የብርና ወርቅ ክምሮች፣ እነኝህ ምድራዊ ከንቱ ውዳሴዎች፣ እነኝህ ብዛት ያላቸው ክፍለ-ጦሮች፣ እነኝህ ባለ ሕብረቀለም የሚያምሩ ልብሶች፣ እነኝህ በኩራት የተሞሉ እና ሐኬተኛ ነፍሶች፣ ሁሉም ወደ ጠባብ መቃብር ውስጥ ይወርዳሉ። የማስተዋል ባለቤት በሆኑት ዓይን ሲታይ ይህ ሁሉ ግጭት፣ ጥልና ሐኬት፣ እንደ ልጆች ጨዋታ ነበር፣ ለወደፊቱም እንዲህ ይሆናል።”[3]**

ሌላው ከባሃኡላህ የልጅነት ታሪክ ጋር የተያያዘው ደግሞ አባቱ ስለ እርሱ ያዩት ህልም ነው:–

*“ . . . በአንድ እጅግ ሰፊ ወሰን አልባ በሆነ ውቅያኖስ ውስጥ ይዋኝ ነበር። አካሉ በውኃው ላይ ያበራ ነበር፤ ይኸም ነፀብራቅ ባህሩን በብርሃን ሞላው። በግልፅ ከውኃው በላይ ይታይ የነበረው ረዥም፣ እጅግ ጥቁር የነበረው፣ ዠርጋጋ ፀጉሩ፣ በማዕበሉ ላይ በብዛት ተንሳፍፎ በሁሉም አቅጣጫዎች ላይ ተንሰራፍቶ ነበር። . . . ብዛት ያለቸው ዓሣዎች ዙሪያው ከበውት ነበር፣ እያ ንዳንዲ (ዓሣ) በእያንዳንዱ ፀጉር ጫፍ ላይ በመጣበቅ፣ እጅግ በርካታ ዓሣዎች በዙሪያው ተሰበሰቡ። በገፁ ብሩህነት በመሳብ በሚዋኝበት በየትኛውም አቅጣጫ ይከተሉታል። ቁጥራቸው ቢበዛም፣ ምንም እንኳ በዞማ ፀጉሩ ላይ በጥብቅ ቢጣበቁበትም፣ ከራሱ ላይ አንዲት ፀጉር ስንኳ አልተነቀለችም፣ በእርሱ ላይም ምንም ጉዳት አልደረሰበትም። ነፃና ያልተገታ ሆኖ ከውኃው በላይ ይንቀሳቀስ ነበር፣ እነርሱም ሁላቸውም ተከተሉት።”[4]*

በህልማቸው እጅግ ስለተደነቁ፣ የባሃኡላህ አባት አንድ በአስታዋይነታቸው ተደናቂ የነበሩን ሰው ህል ሙን እንዲፈታላቸው ጠየቁት። ይህ ሰው፣ የባሃኡላህ የወደፊት ክብር በጨረፍታ እንደታየው ሁሉ፣ እንዲህ አለ:–

*“በህልምዎ ያዩት ወሰን አልባው ውቅያኖስ ሌላ ሳይሆን የፍጥረት ዓለም ነው። ያለማንም እር ዳታ እና ብቻውን ልጅዎ በፍጥረት ዓለም ላይ ከፍተኛ የበላይነትን ይቀዳጃል። ወደ ፈለገው ቦታ ማንም ሳያግደው ይሄዳል። ማንም ጉዞውን ሊቋቋም አይችልም፣ ማንም እርምጃውን አያስተጓጉልም። በርካታ ዓሣዎች የሚያመለክቱት በምድር ሕዝቦች እና ዘሮች መካከል የሚቀሰቅሰውን ነውጥ ነው። በዙሪያው ይሰበሰባሉ፣ በእርሱም ላይ ይጣበቃሉ። የሁሉን ቻዩ የማይነጥፍ ጥበቃ ስለተረጋገጠለት ይህ ሁሉ ነውጥ እርሱን አይጎዳውም፣ በሕይወት ባህር ላይ ብቸኛ መሆኑም ጉዳት ላይ አይጥለውም።”[5]*

1. የባሃኡላህ ስም ማን ነበር? ____________________

2. የተወለደው መቼ ነበር? ____________________

3. የተወለደውስ የት ነበር? ____________________

4. ዛሬ ጊዜ ፋርስ ማን በሚል ስም ትታወቃለች? ____________________

5. የባሃኡላህ አባት ስም ማን ነበር? ____________________

6. የባሃኡላህ አባት ምን ዓይነት ሥልጣን ነበራቸው? ____________________

7. ባሃኡላህ በልጅነቱ ምን ዓይነት ምልክቶች ይታዩበት ነበር?

________________________________________________________________

8. ባሃኡላህ ምን ዓይነት ትምህርት አግኝቶአል?

________________________________________

9. ባሃኡላህ በልጅነቱ ያየውን የአሻንጉሊት ጨዋታ ይግለፁ።

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________

10. ንጉሡ፣ ሚንስትሮቹ፣ ወታደሮቹ፣ እና ዙፋኑ ተሰብስበው በሳጥኑ ውስጥ መከተታቸውን ካየ በኋላ ባሃኡላህ ምን አሰበ?

________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

_____።

11. ንጉሡ፣ ምኒስትሮቹ፣ ወታደሮቹ እና ዙፋኑ በአንዲት ሳጥን ውስጥ መከተታቸውን ካየበት ቀን ጀምሮ ባሃኡላህ ይህን ብሏል፦ "…የዚህ________________ሁሉ በዚህ____________ ሲታዩ ያንኑ _________________ይመስሉታል። የ_________________ያህልም እንኳል ቢሆን_________________ውስጥ_________________አያውቁም፤ ለወደፊቱም እንዲሁ። . . . ብዙ ሳይቆይ እዚያ ሳጥን ውስጥ እንደገቡ ሁሉ እነኝህ ውጫዊ

____________፣_______እነኚህ የ____________ እና የ ____________፣ ____________ ፣

እነኚህ____________ ፣ እነ ኚህ____________እነኚህ፣ ሁሉም ወደ

ጠባብ____________ውስጥ ይወርዳሉ። የ____________ ባለቤት በሆኑት ዓይን ሲታይ ይህ

ሁሉ ____________፣____________ እና____________እንደ ____________ ነበረ፣

ለወደፊቱም እንዲሁ ይሆናል።"

12. የሚርዛ ቡዝሩግን ህልም በራስዎ አባባል ይተርኩ።

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

____________________

13. በህልሙ ውስጥ የውቅያኖሱ ትርጉም ምን ነበር? ____________________

14. በህልሙ ውስጥ በባሃኡላህ ዙሪያ የተሰበሰቡት ቁጥራቸው የበዙት ዓሦች ትርጉም ምን ነበር?

______________________________________________________________________________

___

15. ባሃኡላህ ነፃ እና ያልተገታ ሆኖ ይንቀሳቀስ ነበር ሲባል ምን ማለት ነው?

______________________________________________________________________________

___

## ምዕራፍ 2

መለኮታዊ ክስተቶች በትምህርት ያልተገኘ እውቀት ስላላቸው (ስለተለገሳቸው)፣ ከትምህርት ቤቶች እና ከዩኒቨርስቲዎች እውቀት መቅሰም አያስፈልጋቸውም። አስተማሪዎች እንጂ ተማሪዎች አይ ደሉም፣ ባሃኡላህ እንዲህ ይላል :–

> **"ይህ፣ የተገፋው ምንም ትምህርት ቤት አዘውትሮ አያውቅም። የምሁራንን ውዝግቦች ተካፍሎ አያውቅም። በሕይወቴ! በራሴ ፈቃድ ራሴን አልገለፅኩም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በራሱ ምርጫ ከስቶኛል።"[6]**

የባሃኡላህን በትምህርት ያልተገኘ እውቀት በተመለከተ አብዱል-ባሃ እንዲህ ብሏል:–

> **"ማንም በእርሱ ፊት የቀረቡ ሁሉ በእርሱ ኃያልነት በአድናቆት ሳይዋጡ አይመለሱም። እርሱ ዘንድ የቀረቡ ምሁራን በእርሱ እውቀት እጅግ ይደነቁ ነበር፤ ነገር ግን እርሱ ትምህርት ቤት ገብቶ ወይም ከሰዎች ተምሮ አያውቅም። ወዳጆቹ እና ቤተሰቡ ይህንን ይመሠክራሉ፣ እንዲህም ሆኖ የእርሱ ትምህርቶች የዘመኑ መንፈስ ናቸው።**
>
> **ፀሐይ ከራሷ ብርሐኗን ታመነጫለች እንጂ ከሌሎች ምንጮች አትወስድም (አትቀበልም)። መለኮታዊ አስተማሪዎች የራሳቸው (ከሌላ ያልተገኘ) ብርሃን አላቸው፤ በፍጥረት ዓለም ውስጥ ስላሉት ነገሮች ሁሉ እውቀት እና ግንዛቤ አላቸው። የተቀረው ዓለም ብርሐኑን ከእነርሱ ይቀበላል፤ በእነርሱም አማካኝነት ኪነ-ጥበባትንና ሣይንሶች በእያንዳንዱ ዘመን ያብባሉ።"[7]**

1. ከዚህ የሚቀጥሉትን ዓረፍተ ነገሮች ያሟሉ :–

    ሀ. ፀሐይ_______________ታመነጫለች፤ ___________ __________ አትወስድም (አትቀበልም)።

    ለ. መለኮታዊ አስተማሪዎች________________________________ አላቸው።

    ሐ. መለኮታዊ መምህራን በፍጥረተ ዓለም ውስጥ ስላሉት ነገሮች ሁሉ__________ እና ___________ አላቸው።

    መ. በመለኮታዊ አስተማሪዎች አማካኝነት፣ የተቀረው ዓለም______________________ይቀበላል።

    ሠ. በመለኮታዊ አስተማሪዎች አማካኝነት፣ ኪነ-ጥበባት እና ሣይንሶች____________________።

2. በቡድናችሁ ካሉት አባላት ጋር "ከትምህርት ያልተገኘ፣ በተፈጥሮ የተገኘ እውቀት"፣ በትምህርት ከሚገኝ እውቀት ጋር እንዴት እንደሚለያይ ተወያዩ።

3. ከላይ የተጠቀሰውን ከባሃኡላህ ፅሑፎች የተገኘውን ጥቅስ በቃላችሁ ያዙ።

## ምዕራፍ 3

ባሃኡላህ እያደገ ሲሄድ ታላቅ የመሆኑ ምልክቶች ይበልጥ ግልፅ እየሆኑ መጡ። ወጣትነት ላይ በደረሰ ጊዜ፣ በሰላ የአእምሮው ንቃት፤ እጅግ በጣም መልካም በሆነው ባህሪው፣ በልግስናው እና በርህራሄው የታወቀ ሆነ። እጅግ በጣም ከባድ ለሆኑ ችግሮች መፍትሔ የመስጠት እና እጅግ የተወሳሰቡ እና ጥልቅ ለሆኑ ጥያቄዎች መልስ የመስጠት ችሎታው ጨመረ። ሆኖም ይህ ሁሉ የተለየ ኃይል የነበረው ቢሆንም ሥልጣንና እውቅናን ፈፅሞ አይፈልግም ነበር። አባቱ ሲሞቱ ባሃኡላህ በእርሳቸው እግር እንዲተካ እና በንጉሡ ችሎት ውስጥ የአባቱን ሥልጣን እንዲይዝ ተጠይቆ ነበር። ነገር ግን እርሱ አልተቀበለውም። ለዚህ ዓለም ማዕረጎች እና ከበሬታዎች ፍላጎት አልነበረውም። የእርሱ ፍላጎት ለድሆች መሟገት እና ነዳያንን መንከባከብ ነበር። በ18 ዓመቱ ባሃኡላህ አሲይህ ካህኑምን የተባለች ሴትን አገባ። ቤታቸውም የሁሉም መጠለያ ሆነ። የእነርሱን መስተንግዶ ማንም ተከልክሎ አያውቅም ነበር።

እ.ኤ.አ ሜይ 23 ቀን 1844 ባብ ተልዕኮውን ለሙላ ሑሴይን በሺራዝ ከተማ በገለፀበት ጊዜ ባሃኡላህ 27 ዓመቱ ነበር። ያ ታሪካዊ ክንውን ሦስት ወራት እንኳን ሳይሆነው ባሃኡላህ ከባብ አንዳንድ ፅሑፎቹን የያዘ የብራና ጥቅል ደረሰው። ስለ ባብ ግልፀት እውነተኝነት ወዲያው መሰከረ፤ ትምህርቶቹንም ለማራመድ ተነሳ። ለባሃኡላህ ያ ጥቅል እንዴት እንደደረሰው የሚያወሳው ታሪክ ከዚህ የሚከተ ለው ነው።

ባብ የእርሱን፣ አስራ ስምንቱን፣ የተመረጡ ደቀ-መዛሙርት ሕያዋን ፊደላት ብሎ ከሰየማቸው በኂላ፣ ብዙም ሳይቆይ ወደ እርሱ ዘንድ ጠርቶ በየቦታው ተሠራጭተው መልእክቱን እንዲያውጁ አዘዛቸው። ለእያንዳንዳቸው የተለየ ሥራ ሰጣቸው። ለአንዳንዶቹ የትውልድ ቀዬቸው የጥረታቸው መስክ አድርጎ መደበላቸው። ከእነኝህ ከተባረኩ አስራ ስምንት ነፍሶች መካከል፣ ተልዕኮውን ለማወጅ፣ ለስግደት እና የመሳለም ጉዞ ወደ መካ አብሮት እንዲሄድ ቅዱስን መረጠው። በእርሱ ለማመን የመጀመሪያው ለሆነው ሙላ ሑሴይን ደግሞ እነኝህን ቃላት በመናገር ሸኘው፦ **"ወደ ሂጃዝ በማደርገው ጉዞ አብረኸኝ ለመጓዝ ባለመመረጥህ አትዘን። በዚያ ፋንታ ሂጃዝም ሆነ ሺራዝ ሊወዳደሩት ተስፋ የማያደርጉትን የላቀ ቅድስና ያለው ምሥጢር ወደ ደበቀችው ከተማ እርምጃዎችህን እመራቸዋለሁ።"**[8] ካለው በኂላ፣ ለሙላ ሑሴይን አንድ የብራና ጥቅል ሰጠው እና ወደ ቴህራን እንዲሄድ አዘዘው። በዚያች ከተማ የተደበቀውን ምሥጢር ብርሃን እንዲገነዘብ እና ተወዳጁ ዘንድ ለመቅረብ እንዲያስችለው አምላ ክን እንዲማፀን ነገረው።

ሙላ ሑሴይን ተልዕኮውን ለማሟላት ጉዞውን ቀጠለ፤ በብዙ ከተሞች መካከል ካለፈ በኂላ ቴህራን ደረሰ። እዚያም በአንድ የሃይማኖት ትምህርት ቤት አንድ ክፍል ውስጥ ተቀመጠ። መጀመሪያ ካደረጋቸው ነገሮች አንዱ የባብን መልዕክት ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ማወጅ ነበር። እርሱም በትዕቢት ተሞልቶ አልተቀበለውም ። ሆኖም ግን አንድ የትምህርት ቤቱ ወጣት ተማሪ ሲነጋገሩ ሰምቶ በሙላ ሁሴይን ንግግር በጥልቅ ተነካ። እኩለ ሌሊት ሲሆን ሙላ ሁሴይንን ለመግኘት እና እንደዚህ በጋለ ስሜት የሚያስተምረውን መልዕክት የበለጠ ለማወቅ ወሰነ። ሙላ ሑሴይን ወጣቱን ልጅ ከተቀበለ በኂላ በታላቅ አክብሮት እና ደግነት አናገረው። ለምን ወደ እዚህ እንደመጣ አሁን እንደተረዳ ለወጣቱ ነገረው። የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ግን መልዕክቱን በመናቅ አልተቀበለውም ነበር። ሙላ ሑሴይንም እንዲህ አለ፦ "እንደ አስተማሪው ሳይሆን ተማሪው እውነቱን እንደሚገነዘብ ተስፋ አደርጋለሁ።"[9]

በንግግራቸው መካከል ሙላ ሑሴይን ተማሪውን ከየት እንደሆነ ጠየቀው። እርሱም በማዚንዳራን ክፍለ ሀገር ውስጥ ከምትገኝ ኑር ከምትባል ወረዳ እንደመጣ ነገረው። "እስቲ ንገረኝ" ብሎ ሙላ ሑሴይን ጠየቀው፣ "በአሁኑ ጊዜ ከሟቹ ሚርዛ ቡዝሩግ ኑሪ ቤተሰብ መካከል በባህርይው ሰዎችን የመሳብ ችሎታው፣ በሚያስደስት ለዛው፣ በስነ-ጥበቡ እና በአእምሯዊ ውጤቱ የታወቀ፣ የዚያን ታዋቂ ቤት ከፍተኛ ባህላዊ እሴቶች ጠብቆ በመኖር ችሎታውን ያረጋገጠ ሰው ይገኛልን?"[10]

"አዎን" ብሎ መለሰ፣ "አሁን በሕይወት ካሉት ወንድ ልጆቹ መካከል አንዱ አባቱ ተላብሰውት በነበሩት ባህሪዎች ራሱን አሳውቋል። ፅድቅ በተሞላው ሕይወቱ፣ በተጎናፀፋቸው ከፍተኛ ስኬት፣ ፍቅር በተሞላው ደግነቱ እና ለጋስነቱ የትልቅ ሰው ትልቅ ልጅ መሆኑን አረጋግጧል።" "ሥራው ምንድነው?" ሲል ሙላ ሑሴይን ጠየቀ። "ያዘኑትን ያፅናናል እንዲሁም የተራቡትን ይመግባል።" "ሹመቱ እና ሥልጣኑስ?" በማለት ሙላ ሑሴይን በድጋሚ ጠየቀ፣ "ድሆችን እና እንግዶችን ከመወዳጀት በቀር ምንም ሌላ ስልጣን የለውም።" "ስሙ ማን ነው?" "ሑሴይን ዓሊ"[11]

በእያንዳንዱ መልስ ሙላ ሑሴይን ይበልጥ በደስታ ተሞላ። "ጊዜውን እንዴት ያሳልፋል?" በመቀጠል ጠየቀ። "ደኖች ውስጥ ይዘዋወራል፣ በገጠርም ውበት ይደሰታል።" "እድሜው ስንት ነው?" "ሃያ ስምንት"፣ "ብዙ ጊዜ ታገኘዋለህ?" ብሎ ያንን ወጣት በሚጠይቅበት ጊዜ የሙላ ሑሴይን ገፅ በእርካታ እና በደስታ ፈክቶ ነበር። "አዘውትሬ ቤቱን እጎበኛለሁ።" ብሎ መለሰ። "አንድ አደራ ብሰጥህ በእጁ ታስረክብልኛለህ?" "ያለ ምንም ጥርጥር" ነበር መልሱ። ከዚያም ሙላ ሑሴይን በጨርቅ የተሸፈነችውን ጥቅል ሰጠውና በሚቀጥለው ቀን ጎህ ሲቀድ ለባሃኡላህ እንዲያቀርበው ጠየቀው። "መልስ ሊሰጠኝ ፈቃዱ ከሆነ እባክህን ምላሹን ታሳውቀኛለህ?"[12] አለው። ተማሪው ጥቅል ፅሑፉን ወሰደ፣ የሙላ ሑሴይንን ፈቃድ ለማሟላት ጎህ ሲቀድ ተነስቶ ሄደ።

ወደ ባሃኡላህ ቤት ሲቃረብ ወንድሙ ሚርዛ ሙሳ ከውጪው በር ላይ ቆሞ አየው፣ የጉብኝቱንም ምክንያት አብራራለት። ሚርዛ ሙሳ ወጣቱን ወደ ባሃኡላህ ወሰደው፣ ጥቅል ፅሑፉንም እፊቱ አቀረበ። ባሃኡላህ እንዲቀመጡ ጋበዛቸው። ጥቅል ፅሑፉን ገለጠና ከምንባባቦቹ አንዳንዶቹን ድምፁን ከፍ አድርጎ ማንበብ ጀመረ። አንድ ገፅ ካነበበ በኋላ ወደ ወንድሙ ዞር ብሎ እንዲህ አለ፦ **"ሙሳ፣ ምን የምትለው ነገር አለህ? በእውነት እላለሁ በቁርዓን የሚያምንና ምንጩ መለኮታዊ መሆኑን የሚያውቅ ማንም ሰው እነኝህን ነፍስ የሚቀሰቅሱ ቃላት (ልክ እንደ ቁርዓን) ያንኑ ሕይወትን እንደገና የመዝራት ኃይል ያላቸው መሆኑን ለመቀበል ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ቢያመነታ በጣም በእርግጠኝነት በፍርዱ እጅግ ተሳስቷል፤ እንዲሁም ከፍትህ መንገድ ርቆ ባዝኗል።"[13]** ባሃኡላህ ወጣቱን ሲሸኝ ለሙላ ሁሴይን እንደ ስጦታ አድርጎ ስኳርና ሻይ ቅጠል እንዲወስድለትና አድናቆቱንና ፍቅሩን እንዲያስተላልፍ ለት ጠየቀው።

ወጣቱ በደስታ ተሞልቶ ወደ ሙላ ሑሴይን በፍጥነት ሄደ። የባሃኡላህን ስጦታ እና መልዕክትም ሰጠው። ስጦታውን ሲቀበል ሙላ ሑሴይን ያሳየው ደስታ በቃላት የሚገለፅ አልነበረም። ራሱን ዝቅ አድርጎ ስጦታውን ተቀበለና በታላቅ ስሜት ሳመው። ከዚያም ወጣቱን አቀፈው። ዓይኑንም ሳመው እና እንዲህ አለው፦ "እጅግ የተወደድህ ወዳጄ ሆይ! ልቤን እንዳስደሰትከው ሁሉ፣ አምላክ ዘለዓለማዊ ሐሴት እንዲሰጥህ እና ልብህን በማይጠፋ ደስታ እንዲሞላው እፀልያለሁ።"[14] ወጣቱ በሙላ ሑሴይን ሁኔታ ግራ ተጋባ። እነኝህን ሁለት ነፍሶች ያስተሳሰረው ገመድ ምን ሊሆን ይችላል? በሚል ተገረመ። በሁለቱ መካከል ያለው ወዳጅነት መንስዔው ምን ይሆን? ከባሃኡላህ አንዲት ትንሽ ስጦታ በመቀበሉ ሙላ ሑሴይን እንደዚህ ዓይነት ደስታ ለምን ተሰማው? ወጣቱ ሊፈታው ከማይችለው እንቆ ቅልሽ ጋር ተጋፈጠ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ሙላ ሑሴይን በኢራን ሰሜን ምስራቅ ወደ ሚገኘው ኮህራሳን አውራጃ ተጓዘ። የኑሩን ወጣት ተማሪ ሲሰናበተው እንዲህ ብሎ ተናገረው፦ "ያየኸውንና የሰማኸውን ለማንም እንዳትተነፍስ (እንዳትናገር)። ይህ በልብህ ውስጥ የተደበቀ ምስጢር ይሁን። ስሙን አትግለፅ፣ ምክንያቱም በእርሱ ላይ የሚቀኑት ሊገድሉት ይነሳሉና። በተመስጦህ ጊዜ ፍፁም ኃያሉ እንዲጠብቀው በእርሱም አማካኝነት የተጨቆኑትን ከፍ እንዲያደርግ፣ ድኾችን እንዲያበለፅግ እና የወደቁትን እንዲታደግ ሁሉን ቻዩ እንዲጠብቀው፣ ፀልይ። የነገሮች ምስጢር ከዓይኖቻችን ተሰውረዋል። የእኛ ኃላፊነት የአዲሱን ቀን ጥሪ ማሰማት እና ለሁሉም ሕዝቦች ይህን መለኮታዊ መልዕክት ማወጅ ነው። በዚህች ከተማ ብዙ ነፍሶች በዚህ መንገድ ደማቸውን ያፈሳሉ። ያም ደም የእግዚአብሔርን ዛፍ ያጠጣል ፣ እንዲያድግ እና የሰውን ልጅ እንዲጠለል ያደርገዋል።"[15]

1. አስራ ስምንቱን የሕያዋን ፊደላት ከሰየመ በኂላ ባብ ምን አደረገ?

________________________________________________________________

___

2. ወደ መካ ባደረገው መንፈሳዊ ጉዞ አብሮት እንዲሄድ ባብ የመረጠው ማንን ነው?

____________

3. ሂጃዝ የትኛውን አገር ያመላክታል? ____________________

4. ባብ እርሱ ለማመን የመጀመሪያው ለሆነው ሙላ ሑሴይን እነኝህን ቃላት በመናገር ሸኘው:–

"ወደ____________________________ በማደርገው ______________________

አብረኸኝ ለመጓዝ ባለመመረጥህ ________________:: በዚያ ፋንታ

_______________________ ሆነ ___________________ ________________

ተስፋ _________________________ የላቀ ቅድስና ያለው ምሥጢር

__________________ ከተማ እርምጃዎችህን እመራቸዋለሁ::"

5. ባብ ለሙላ ሁሴይን ምን ሰጠው?

_____________________________________________

6. ቴህራን ሲደርስ ሙላ ሑሴይን በአንድ የሃይማኖት ትምህርት ቤት ውስጥ ተቀመጠ::

የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ለባብ መልዕክት ምላሽ የሰጠው እንዴት ነበር?

________________________________________________________________

___

7. አምላክ ሙላ ሑሴይንን ወደ ትምህርት ቤቱ የመራው ለምን ነበር?

________________________________________________________________

___

8. ለባብ መልዕክት ምላሽ የሰጠው ተማሪ ትውልዱ ከየት ነበር?

______________________________________________

9. የባሃኡላህ የትውልድ ስፍራ ከየት ነው?

______________________________________________

10. ለሙላ ሑሴይን ጥያቄዎች ሲመልስ፣ ከኑር የመጣው ተማሪ ባብራራው መሠረት:–

- የባሃኡላህ አባት የታወቁበት ባህርያት ምን ነበሩ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______

- ባሃኡላህ ትኩረት ወደምን ያዘነበለ ነበር?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______

- የእርሱ ሹመት እና ሥልጣን ምን ነበር?

______________________________________________________________________

___

- ጊዜውን የሚያሳልፈው እንዴት ነበር?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

___

11. ከኑር የመጣውን ተማሪ ሙላ ሁሴይን ምን እንዲያደርግለት ጠየቀው?

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

______

12. ከባብ ተልኮ የመጣውን የጥቅሉን አንድ ገፅ ካነበበ በኋላ፣ ባሃኡላህ እንዲህ አለ:–

"በእውነት እላለሁ በ________________________ የሚያምንና

__________________________ መሆኑን የሚያውቅ __________________________

እነኝህን ነፍስ የሚቀሰቅሱ ቃላት (ልክ እንደ ቁርዓን) ያንኑ ____________________እንደገና

________________________ ያላቸው መሆኑን ለመቀበል

____________________________ በጣም በእርግጠኝነት _______________________

እንዲሁም _______________________መንገድ ርቆ ባዝኗል::"

13. ሙላ ሁሴይን የባሃኡላህን ስጦታ የተቀበለው እንዴት ነበር?

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

_____

14. ሙላ ሁሴይን ስጦታውን ሲቀበል፣ ወጣቱን ተማሪ የአስገረመው እና እንቆቅልሽ የሆነበት ነገር ምን ነበር?

___________________________________________________________________

15. ሙላ ሁሴይን ከኑር የመጣውን ተማሪ ሲሰናበተው የተናገረውን በእራሳችሁ ቃላት ተርኩ።

## ምዕራፍ 4

ባብ፣ ባሃኡላህን "እርሱ አምላክ የሚከስተው" በማለት ይገልፀው ነበር:: እጅግ በጣም ቅዱስ መፅሐፉን ባያንን ጨምሮ፣ የባብ ፅሑፎች እርሱን አምላክ የሚከስተውን አስመልክተው ስፍር ቁጥር የሌላቸው ውዳሴዎችን ይዘዋል:: የባሃኡላህን ማንነት እና (ደረጃ) እንዲሁም በመንትያ ክስተቶቹ መካከል ያለውን ዝምድናን በጨልቅታ (በጨረፍታ) ማየት ይችሉ ዘንድ ከዚህ በታች ከባብ ፅሑፎች ውስጥ ጥቂት ጥቅሶች ቀርበዋል::

> **"ገነት ማለት እርሱ አምላክ የሚከስተውን ማወቅ እና ራስን ለእርሱ ማስገዛት መሆኑንም በእርግጥ እወቁ፤ እንዲሁም እሳት (ማለት) ራሳቸውን ለእርሱ ለማስገዛት ያልቻሉ ወይም እር ሱን የሚያስደስተውን ነገር መቀበል ያልቻሉ ሰዎች ስብስብ ማለት ነው::"[16]**

> **". . . አምላክን ከማውሳት በስተቀር ምንም እንዳትሰማ ጆሮህን አፅዳ፣ ከአምላክም በስተቀር ምንም እንዳያዩ ዓይኖችህን አንፃ፣ እንዲሁም ሕሊናህ ከአምላክ ሌላ እንዳያስተውል፤ ልሳንህም አምላክን እንጂ ሌላ እንዳያውጅ፤ በእጅህ ከአምላክ ቃላት እንጂ ሌላ ምንም እንዳይፅፍ፣ እውቀትህም ከአምላክ በስተቀር ምንም እንዳይገነዘብ፤ ልብህም ከአምላክ በስተቀር ምንም ምኞት እንዳያስተናግድ፤ እንዲሁም በተመሳሳይ መንገድ በንፁህ ፍቅር ገነት ውስጥ ታድግ፣ ምናል ባትም እርሱ አምላክ የሚከስተው ዘንድ መቅረብን እንድትቀዳጅ፣**

**እርሱ በከፍተኛ ሁኔታ በሚያ ከብረው ንፅህና አጊጠህ፣ እንዲሁም ፊቱን ከእርሱ ካዞረና እርሱን ከማይደግፍ ከማንኛውም ሰው ትነፃ ዘንድ ተግባሮችህንና ሥራዎችህን ሁሉ አንፃ። ”**[17]

**“በእውነቱ እንዲህ በል፣ እርሱ፣ አምላክ የሚከስተውን፣ የሚያስደስት አምላክን የሚያስደስት ሲሆን፣ እንዲሁም እርሱ፣ አምላክ የሚከስተውን የሚያስከፋ ይህ ሌላ ሳይሆን አምላክን የሚያስ ከፋ ነው።።”**[18]

1. “እርሱ አምላክ የሚከስተው” የሚለው የሚያመለክተው ማንን ነው?______________________

2. በእርሱ አምላክ በሚከስተው ፊት ለመቅረብ እንዲፈቀድላቸው ተከታዮቹ እራሳቸውን እንዲያዘ

   ጋጁ ባብ በጥብቅ አስጠንቅቋቸዋል። ምን እንዲያደርጉ ነበር የነገራቸው?

   ___________________________________________________________________________

   ___________________________________________________________________________

   ___________________________________________________________________________

   ___________________________________________________________________________

   ___________________________________________________________________________

   _______________

3. ከላይ ከተሰጡት ጥቅሶች አንዱን ይምረጡ እና በቃልዎ ይያዙ።

## ምዕራፍ 5

ባሃኡላህ፣ ስለባብ እውነተኝነት ከመሠከረበት ጊዜ ጀምሮ እምነቱን ለማወጅ ተነሳ። አዲሱን እምነት ለማስተማር በመጀመሪያ የተጓዘው በማዚንዳራን አውራጃ ውስጥ ወደምትገኘው፣ የእርሱ የዘር ሐረግ መኖሪያ ወደ ነበረችው ኑር ከተማ ነበር። እዚያም እንደደረሰ የቤተሰቡ ቤት ወደሚገኝበት ታኩር ወደሚባል መንደር ሄደ።

ባሃኡላህ ታኩር የመድረሱ ዜና በአካባቢው በፍጥነት ተሠራጨ። የአካባቢው ሹማምንት እና ባለሥልጣናት፣ “እንኳን ደህና መጣህ” ሊሉት እና በዚያውም ስለ ንጉሡ፣ በንጉሡ ዙሪያ ስላሉ መኳን ንት እና ስለመንግሥት ጉዳዮች ሊሰሙ መጡ። ነገር ግን ባሃኡላህ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልሰው እምብዛም ባለመደሰት ነበር። ርዕሱን በፍጥነት ይቀይርና እጅግ በተዋበ ቋንቋ ባብ ያወጀውን መልዕክት ያቀርብ ነበር። በቃላቱ አሳማኝነት እና በክርክሩ ተቀባይነት ሁሉም ይገረሙ ነበር። በአብዛኛው ካህናት እና የሃይማኖት መሪዎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ እንደዚህ ዓይነት ከፍተኛ ቦታ ላይ ያለ ሰው ጠንካራ ፍላጎት ማሳየቱ አዳማጮቹ የጠበቁት አልነበረም። የጋለ ስሜቱ እና የእውቀቱ ጥልቀት የእራሱን ቤተሰብ ጨምሮ ብዙ ታዋቂ ሰዎችን እና ብዛት ያላቸውን ሰዎች ወደ አዲሱ እምነት በፍጥነት ሊስብ ቻለ። ከእራሱ አጎት በስተቀር እፊቱ የቀረበ ማንም ሰው በጣፋጭ ቃላቱ ፍሰት ያልተደመመ ወይንም የንግግሩን እውነተኝነት ለመቃወም የደፈረ አልነበረም።

ይህ አጎቱ ባሃኡላህን እና ይዞት የመጣውን መልዕክት ዋጋ ለማሳጣት የተቻለውን ሁሉ አደረገ። ይህን ለማድረግ ዓቅሙ እንደማይፈቅድ ሲረዳ ወደ አንድ የታወቀ የሙስሊም ካህን በመሄድ እርዳታውን ተማፀነ። ባሃኡላህ ወደ ኑር መምጣቱንና ምንም እንኳን ክህነት ባይኖረውም ስለ ሃይማኖት የውስጥ ጉዳዮች እየተናገረ ስለመሆኑ ቅሬታውን አሰማ። ባሃኡላህ ፊት የቀረበ ማንኛውም ሰው በእርሱ ምትሃት እንደሚወድቅ እና በቃላቱ ኃይል እየተሸነፈ እንደሆነ የሃይማኖቱን ሊቅ አስጠነቀቀው። "አስማተኛ ይሁን ወይንም በሻዩ ውስጥ ምስጢራዊ የሆነ ንጥረ ነገር ይቀላቅል፣ እኔ አላውቅም፣ ብቻ ሻዩን የጠጡ ሁሉ እያንዳንዱ ሰው የአስማቱ (ተጠቂ) ምርኮኛ ይሆናል።"[19]አለ።

ባሃኡላህን መቋቋም እንደማይሳካለት የተረዳው የሃይማኖቱ ካህን የአጎትየውን ውትወታ ችል አለው። ነገር ግን የባብ መልዕክት በወረዳው ውስጥ ሁሉ እንደ ሰደድ እሳት መሠራጨቱን ቀጠለ። የሃይማኖቱ ካህን የእርሱ ተከታዮች እየተደናገጡበት ስለተቸገረ አንድ እርምጃ እንዲወስድ ግፊት ያደርጉበት ጀመር፣ በመጨረሻም ከተማሪዎቹ መካከል በችሎታቸው በጣም ተደናቂ የሆኑትን ባሃኡላህን እንዲጎበኙ እና እያስፋፋው የሚገኘውን መልዕክት ሁኔታ እንዲመረምሩ ለመላክ ወሰነ። እነዚያ ሁለት ተወካዮች ባሃኡላህ ፊት እንደቀረቡ ምን እንደተፈጠረ የሚያወሳው ታሪክ ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

ታኩር ሲደርሱ፣ ባሃኡላህ ክረምቱን ወደ ሚያሳልፍበት ቤት መሄዱ ስለተነገራቸው ሁለቱ የሃይማኖቱ የካህናቱ ተወካዮች እርሱ ወደሄደበት ለመሄድ ወሰኑ። እዚያ ሲደርሱ ባሃኡላህ ከቁርዓን ምዕራፎች የአንዱን ማብራሪያ እየገለፀ አገኙት። ተቀምጥውም ሲያዳምጡ፣ በአቀራረቡ፣ በአንደበተ ርቱዕነቱ፣ እና በአነጋገሩ አስደናቂነት በእጅጉ በጥልቅ ተነኩ። ከተወካዮቹ አንዱ እራሱን መቆጣጠር ተስኖት ከመቀመጫው ተነስቶ፣ ወደ ክፍሉ መጨረሻ በመሄድ ከበሩ አጠገብ በአክብሮት እና ራሱን በማስገዛት ሁኔታ በትህትና በፀጥታ ቆመ። እየተንቀጠቀጠ ዓይኑ በዕንባ ተሞልቶ አብሮት ለመጣው ጓደኛው እንዲህ አለው፡– "ለባሃኡላህ ጥያቄ ለማቅረብ አልችልም ኃይል አልባ ሆኛለሁ። ልጠይቀው አቅጄ የነበሩት ጥያቄዎች በድንገት ከትውስታዬ ጠፉ። በምርምርህ ለመቀጠል ወይንም ወደ አስተማሪያችን ለብቻህ በመመለስ ያለሁበትን ሁኔታ ልታስረዳው ትችላለህ። ወደ አስተማሪያችን ፈፅሞ እንደገና ለመመለስ እንደማልችል ንገረው። ይህንን ደጃፍ ከእንግዲህ ትቼው የትም አልሄድም።" ሌላኛውም ተወካይ በባሃኡላህ ሁኔታ እጅግ ከመማረኩ የተነሳ የጓደኛውን ፈለግ ተከተለ። "ለአስተ ማሪያችን የነበረኝን እውቅና ከእንግዲህ መስጠት አቁሚያለሁ። ከሕይወቴ የቀሩት ቀናት እውነተኛና ብቸኛ ለሆነው ጌታዬ፣ ለባሃኡላህ አገልግሎት አሳልፌ ለመስጠት በዚህች ደቂቃ ለአምላክ ቃል ገብቼ አለሁ።"[20] አለ።

የሃይማኖት ሊቁ ተማሪዎች ሃይማኖታቸውን የመቀየራቸው ዜና በኑር ሕዝብ መካከል በፍጥ ነት ተሠራጨ። የተከበሩ ሰዎች፣ የመንግሥት ባለሥልጣነት፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ነጋዴዎች እና ገበሬዎች በብዛት በባሃኡላህ ፊት ተሰባሰቡ። በባብ ሃይማኖት ጥላ ሥር በመቶዎች የሚቆጠሩ ተጠ ለሉ። ሆኖም ግን ከባሃኡላህ በስተቀር ከእነኚህ መካከል፣ አዲስ የተወለደው እና ገና ለጋ የሆነውን እፅ ዋት ከስሩ ለመንቀል በሚደረግ እጅግ በጣም ዘግናኝ የሆነ ጭፍጨፋ እንደሚደርስባቸው የተረዱ አልነበ ሩም።

1. ስለ ባብ ግልፀት እውነተኝነት ከመሰከረ በኋላ ባሃኡላህ ምን አደረገ? ______________________

2. የኑር ነዋሪዎች ባሃኡላህን የተቀበሉት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነበር?

______________________________________________

3. ባሃኡላህ ጥያቄዎቻቸውን በመለሰበት መንገድ አንዳንድ ሰዎች የተደነቁት እንዴት ነው?

4. ባሃኡላህ የባብን እምነት ሲያውጅ የባሃኡላህ አጎት ምን አደረገ?

5. ታዋቂው የእስልምናው ካህን የባሃኡላህን አጎት ልመና ችል ያለው ለምንድነው?

6. ከተከታዮቹ ግፊት ሲበዛበት የሃይማኖቱ ሊቅ በመጨረሻ ምን ለማድረግ ወሰነ?

7. ባሃኡላህ ፊት የቀረቡትን፣ ሁለቱን የሃይማኖቱ ሊቅ ተወካዮቹን ታሪክ በራስዎ ቃላት ይተርኩ።

________________________________________________________________

_______________

8. የእነዚህ ሁለት ተወካዮች ሃይማኖታቸውን መቀየር በኑር ከተማ ውስጥ በባብ ሃይማኖት እድገት ላይ ምን ውጤት አመጣ?

_______________________________________________

## ምዕራፍ 6

ባሃኡላህ እንድናደርገው የጠየቀን እርሱ በኑር ወረዳ ያደረገውን–ማለትም ጊዜ ሳናጠፋ ተነስተን የአምላክን እምነት እንድናስተምር ነው። እርሱ የባብን ግልፀት ከተቀበለ በኋላ ያደረገው የመጀመሪያው ነገር በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ነፍሶችን ማስተማር እንደነበር በማስታዎስ፣ የሚከተሉትን የባሃኡላህ ቃላት እናጥናና እናሰላስልባቸው።

> **"በአምላክ መንገድ ተጓዥ ሆይ! ከእርሱ የፀጋ ውቅያኖስ ድርሻህን ውሰድ፣ በጥልቀቱም ውስጥ ተሸሽገው ከሚገኙት ነገሮች ራስህን አትንፈግ። ከዚህ ሃብት ከተካፈሉትም ሁን። ከዚህ ውቅያኖስ አንድ የጤዛ ጠብታ በሰማያት እና በምድር በሚገኙት ላይ ጠብ ቢል በፍፁም ኃያሉ፣ በሁሉን አዋቂው፣ በፍፁም ጠቢቡ፣ አምላክ በረከት ሊያበለፅጋቸው ይችላል። ከሰው ሰራሹ ውስንነት ሁሉ እንዲነፁ እና የኃያሉን አምላክ መቀመጫ ወደ ሆነው ወደ እዚህ የተቀደሰ እና አንፀባራቂ ነጥብ እንዲቀርቡ በመላቀቅ እጆች ከሕይወት ሰጪ ውኃዎች ቀድተህ፣ ይህንን በተፈጠሩት ነገሮች ላይ አርከፍክፍ።"**

> **"አንተ ብቻህን የምታከናውነው ቢሆንም እንኳን አትዘን። አምላክ ፍፁም አርኪህ ይሁን። ከመንፈሱ ጋር ተቋረብ፤ ከአመስጋኞቹም ሁን። የጌታህን እምነት በሰማያት እና በምድር ለሚገኙት ሁሉ አውጅ። ማንም ጥሪህን ቢሰማ የጌታ፣ የአምላክህ፣ የእርሱ መንፈስ ወደ አንተ የላካቸውን የጥበብ እንቁዎች በፊቱ በግልፅ ዘርጋለት፣ ከእነዚያም በእውነት ከሚያምኑት ሁን። ማንም ስጦታህን ባይቀበል ደግሞ ከእርሱ ዞር በል፣ አደራህንና እምነትህን የዓለማት ሁሉ ጌታ በሆነው አምላክህ ላይ አድርግ።"[21]**

1. ከዚህ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ያሟሉ:–

ሀ. ባሃኡላህ ከ____________________ድርሻችንን እንድንወስድ ይጠይቀናል።

ለ. በ_______________ውስጥ_______________ ራሳችንን መንፈግ የለብንም።

ሐ. ከዚህ ውቅያኖስ አንድ የጤዛ ጠብታ በሰማያት እና በምድር በሚገኙት ሁሉ ላይ ጠብ ቢል _______________ይችላል።

መ. በ______________ከ ______________እንድንቀዳ እና ይህንንም በ______________

______________እንድናርከፈክፍ ተጠይቀናል።

ሠ. __________________________________________ማዘን የለብንም።

ረ. ከ______________የተቋረብን መሆን አለብን።

ሰ. የ____________በ____________________________ማወጅ አለብን።

ሸ. ማንም ጥሪያችንን ቢሰማ____________፣የ________________________፣የ______

_________፣ወደ____________በ____________፣____________በ____________።

ባሃኡላህ ይነግረናል።

ቀ. ማንም ስጦታችንን ባይቀበል ደግሞ ከ_______________________ማለት አለብን።

## ምዕራፍ 7

መለኮታዊ ግልፀት ቀጣይ እና ታዳጊ ነው። አምላክ የሰው ልጅ ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላኛው እያደገ በሚሄድበት ወቅት በእርሱ መልዕክተኞች አማካኝነት የእራሱን ፈቃድ ይገልፃል። አንዳንድ አስ ፈላጊ እውነታዎችን እያጠናከሩ፣ እያንዳንዱ መልዕክተኛ ለሰው ልጅ ችሎታ ተመጣጣኝ የሆኑ አዳዲስ ህግጋቶችንና ትዕዛዞችን ይደነግጋሉ። ከእነርሱ በፊት የመጡትን ለጊዜው የማያስፈልጉትን ደግሞ ይሽራሉ። ይሁን እንጂ ሰዎች ያለፈውን ትተው መሄድ አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል፣ ሌላው ቀርቶ የቅርብ ደቀ-መዛሙርቶች እንኳን መጀመሪያ ላይ የግልፀቱን ሙሉ እውነታ መጨበጥ አይችሉም ነበር። ትውል ዶችም ለብዙ መቶ ዓመታት የተከተሉትን ሃይማኖታዊ ልማዶችና ወጎች አጥብቀው መከተልን ይቀጥ ላሉ። ከጊዜ በኂላ ግን አዲሱ መልዕክተኛ ለሰው ልጅ ሂደታዊ ለውጥ የዘረጋውን አዳዲስ ህግጋትን መረዳት ይጀምራሉ።

በባብ ግልፀት ጊዜም የሆነው እንዲሁ ነበር። ከመካከላቸው ባብ የተገኘው፣ ሙስሊሞችም፣ ከነ ብዩ ሙሐመድ ትምህርቶች አንዲት "ፊደል" እንኳን ብትሆን እስከ ዓለም መጨረሻ ልትለወጥ እንደማትችል ያምኑ ነበር። ስለዚህም ባብ ሙሉ መልዕክቱ ቀስ በቀስ ብቻ እንዲታወቅ ፈቀደ። በእርሱ ግልፀት የመጀመሪያ ዓመት፣ በእስልምና ህግጋት ላይ የተደረገ ለውጥ አልነበረም። ነገር ግን፣ እንደም ታውቁት በማህኩ ምሽግ እስር ቤት፣ በእስራት ላይ እያለ፣ ባብ በፋርሱ ባያን ውስጥ አዳዲስ ህግጋቶችን ገልጿ። በዚህን ጊዜ ነበር የእርሱ ተከታዮች ከበፊቱ ቁርጥ ያለ መለያየት የኖራቸው እናም የእርሱን የአ ምላክ ክስተትነት እውነተኛ ደረጃ እንዲያውጅ የተደረገው። ይህ የተደረገው ደግሞ በባዳሽት ጉባዔ ወቅት ነበር።

ባዳሽት ከቴህራን ራቅ ያለች በሀገሪቱ ሰሜን ምሥራቅ የምትገኝ መንደር ነች። የባዳሽት ጉባዔ እ.ኤ.አ. በጁላይ ወር 1848 ተካሄደ። በዚህ ጉባዔ ሰማንያ አንድ እጅግ ታዋቂ የሆኑ የባብ ተከታዮች ተገኝተዋል። ዋነኛ ተሳታፊዎቹ ባሃኡላህ፣ ቅዱስ እና ታሂሬ ነበሩ።

ምንም እንኳ ባሃኡላህ፣ የእርሱን እውቀት እና ጥበብ በተረዱ እና የእርሱን መርህ በሚሹ ዘንድ፣ ከእርሱ መሰል ባቢዎች፣ ከፍተኛ ግምት እየተሰጠው ቢሆንም፣ የእርሱ ታላቅነት እና ግርማ ግን በጉባዔው ላይ ይበልጥ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እየደረሰ መጣ። እርግጥ ነው፣ የእርሱ ሚና ወሳኝ ነበር። ጉባዔው የተካሄደበትን የአትክልት ስፍራዎች ተከራይቶ፣ ለሃያ ሁለት ቀናት፣ በዚያ የተሰባሰቡት ሁሉ በእርሱ ልግስናና እንግዳ አቀባበል መስተንግዶው አስደስቷቸው ነበር። ለተሰባሰቡት አማኞች እንዲነበብ ባሃኡላህ በየቀኑ አንድ ፅላት ይገልፅ ነበር። ለእያንዳንዳቸውም አንዳንድ አዳዲስ ስም ሰጣቸው። ለታሂሬ እና ለቅዱስ ለሁልጊዜም በታሪክ የሚጠሩባቸውን የማዕረግ ስም ተሰጣቸው። ታሂሬ የሚለው የማዕረግ ስም "ንፅሂቷ" ማለት ሲሆን፣ ቅዱስ ማለት ደግሞ "የተቀደሰ" ማለት ነው። ከዚያን ጊዜም ጀምሮ እርሱ ራሱ "ባሃ" በሚለው ስም እንዲታወቅ ሆነ። ከጊዜ በኋላ ባብ ጉባዔውን ለተካፈለ ለእያንዳንዱ አማኝ በዚያን ጊዜ በተቀበለው ስም እየጠራ ልዩ የሆነ ፅላት ገለፀላቸው።

አንድ ቀን ባሃኡላህ ታሞ አልጋው ላይ ተኛ። ሁሉም በእርሱ ዙሪያ ተሰባስበው ነበር። በኢራን ሙስሊሞች ዘንድ ሁሉም ሴቶች በአደባባይ (በሕዝብ ፊት) መከናነብ እንዳለባቸው ይታመናል፣ ነገር ግን፣ ሳይታሰብ በድንገት፣ የንፅህናና የግብረ ቅድስና መገለጫ ተደርጋ የምትታወቀው ታሂሬ፣ በእነርሱ ፊት ያለ ዓይነ እርግቧን ተገልጣ ብቅ አለች። እዚያ ከነበሩት ባቢዎች አንዳንዶቹ ይህቺ ሴት በራሷና በአዲሱ እምነት ላይ አሳፋሪ ተግባር እንደፈፀመች አድርገው ተሰማቸው። የቅዱስ ቁጣ በግልፅ ይታይ ነበር። ነገር ግን፣ ታሂሬ ሳትረበሽ እና በደስታ እያበራች፣ በአንደበተ ርቱዕነት ለጓዶቿ ንግግር አደረገች። ከባለፉት ዘመናት ሃይማኖታዊ ቀኖናዎች፣ ከባህሉ እና ከስርዓቶቹ ራሳቸውን እንዲያላቅቁ ጥሪ አቀረበችላቸው። በቅዱስ እና በታሂሬ መካከል የተነሳው ውጥረት በባሃኡላህ አስታራቂነት ረገበ። ከዚህ እወጃ የተነሳ ጥቂት ባቢዎች እምነቱን ትተው ቢሄዱም አብዛኞቹ በፅናታቸው በመቀጠል፣ በአዲስ የመነቃቃት ስሜት ተሞሉ። ባሃኡላህ የአዲሱን ቀን ንጋት ለማብሰር ያንን ጊዜ ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ተጠቅሞበታል። ታሂሬ ድፍረት በተሞላበት ተግባሯ የአሮጌውን መፈፀም እና የአዲሱን እምነት መጀመር የሚያበስረውን መልዕክት አሰማች።

በተጨማሪም የባዳሽት ጉባዔ የባቢ እምነት እጅግ ነውጥ የተሞላበት የእድገት ደረጃ ላይ ለመድረሱ ያመላከተበት ሁኔታ ነው። ብዙ ሳይቆይ በተከታዮቹ ላይ የደረሰው ሊገመት የማይችል የጭ ቆናው ግፍ፣ ብዙዎቹን ለሰማዕትነት ጠራ። ጉባዔው ከዚያ ወጥተው ታላቅ ጀግንነት የተሞላበት ተግባ ራትን ለመፈፀም የሚሄዱ፣ በአብሐ መንግሥት ብቻ እንደገና የሚገናኙበት፣ የስንብት ስብሰባ ይመስል ነበር።

በጉባዔው ላይ የተካፈሉት ሁሉ በአንድ ላይ ወደ ማዚንዳራን ሄዱ። ነገር ግን፣ ከመንደሩ ወጣ ብለው አረፍ ባሉበት፣ ስለ እውነተኛ ዓላማቸው ባልተረዱ በመንደሩ ነዋሪዎች ጥቃት ደረሰባቸው። ባቢዎቹም እንዲሸሹና በተለያየ አቅጣጫ እንዲጓዙ ተገደዱ። ባሃኡላህ በማዚንዳራን ወደምትገኘው ኑር ጉዞውን ቀጠለ።

ብዙ ሳይቆይ የባዳሽቱ ጉባዔ ዜና ቴህራን ደረሰ፣ ንጉሡ እና ምኒስትሮቹም የተደረጉትን ነገሮች እና በጉባዔውም ባሃኡላህ የተጫወተውን ሚና አወቁ። በአጭር ጊዜ ሕይወቱን በሚያጣው በሽታ የተዳከመው ንጉሥ፣ ባሃኡላህ እንዲያዝ ትዕዛዝ እንዲሰጥ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተመከረ። በዚሁም መሠረት በማዚንዳራን ከሚገኙት ሹማምንት መካከል ለአንዱ ባሃኡላህን በቁጥጥር ሥር እንዲያውል እና ወደ ዋናው ከተማ እንዲያመጣው ትዕዛዝ ተላለፈለት። ይህ የሆነውም፣ ባሃኡላህን በጣም የሚወድ የነበረ ሹም እርሱን ለማስተናገድ ቀጠሮ ከያዘበት አንድ ቀን አስቀድሞ ትዕዛዙ ደረሰው። በጣም ስለተጨነቀ፣ ለማንም ላለመናገር መረጠ። በሚቀጥለውም ቀን የንጉሡ መሞት ዜና ማዚንዳራን ደረሰ። ከዚያም ትዕዛዙ ውድቅ ሆነ።

1. የባዳሽት ጉባዔ ዓላማ ምን ነበር?__________________________________________________

2. የባዳሽት ጉባዔ መቼ ተደረገ? _________________________

3. ጉባዔው ለስንት ቀናት ተደረገ? _________________________

4. በጉባዔው ስንት የባብ ተከታዮች ተካፈሉ? _________________________

5. ዋነኛዎቹ ተሳታፊዎች እነማን ነበሩ? _________________________

6. በጉባዔው ከተገኙት ከሁሉም በላይ ከፍተኛ ደረጃ የነበረው ሰው ማን ነበር? __________________

7. “ታሂሬ” የሚለው የማዕረግ ስም ምን ማለት ነው? _________________________

8. “ቅዱስ” የሚለው ስም ምን ማለት ነው? _________________________

9. ታሂሬ ዓይነ እርግቧን እና ክንብንቧን ገልጣ በጓደኞቿ ፊት የቀረበችበትን በጉባዔው ቀን የተፈጠሩትን ሁኔታዎች በራስዎ ቃላት ይተርኩ።

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

________________

10. የታሂሬ በጉባዔው ፊት ያሳየችው ድፍረት የተሞላበት ተግባር ምንን ያሳያል?

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

__________

11. የባዳሽቱ ጉባዔ ዜና ሲደርሰው መንግስት ምን አደረገ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

____

12. ባሃኡላህ እንዲያዝ መንግሥት ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ የሆነውን ነገር ያብራሩ።

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

__________

## ምዕራፍ 8

በባዳሽቱ ጉባዔ የአሮጌው ውድቅ መሆንና የአዲሱን መጀመር ያበሰረ ነበር። ከአብዱል-ባሃ ፅሁፎች የተገኘው የሚቀጥለው ምንባብ በየዘመናቱ የአምላክ ሃይማኖት በየጊዜው እንዴት እንደሚታደስ ይገልፃል። ስለ ባዳሽቱ ጉባዔ ያጠኑትን መሠረት በማድረግ በንባቡ ላይ ያሰላስሉ።

> **"የሃይማኖት እውነታ ዘር፣ ቅጠሎች እና ቅርንጫፎች፣ አበቦች እና ፍሬዎች ወደ ሚያስገኝ ዛፍነት አደገ። ከጊዜ በኋላ ይህ ዛፍ ወደ ብስባሽነት ሁኔታ ተለወጠ። ቅጠሎቹ እና አበቦቹ ጠወለጉ እና ጠፉ፣ ዛፉ አረጀ እና ፍሬ ቢስ ሆነ። ሕይወት የሚሰጡት ኃይሎቹ ገና አልቀነሱም፣ ፍሬውንም የሚወዳደረው የለም፣ የሚኖረውም ለዘለዓለም ነው፣ በማለት በአሮጌው ዛፍ ላይ የሙጥኝ ማለት ከአመክንዮ አንፃር ለሰው ትክክል አይደለም። አዲስ ዛፍ ያድግ ዘንድ እናም ዓለምን በአዲስ መለኮታዊ ፍሬዎች እንዲያድሷት በሰው ልቦች ውስጥ የእውነታ ዘር እንደገና መዘራት አለበት። በዚህ መንገድ አሁን በሃይማኖት የሚለያዩት አገሮች እና ሕዝቦች ወደ አንድነት ይመጣሉ፤ በጭፍን መከተል ይቀራል፣ እንዲሁም በራሱ በእውነታው ላይ ሁሉን አቀፍ ወንድማማችነት ይመሠረታል። በሰው ልጆች መካከል ጦርነት እና ውዝግብ ያከትማል፣ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደመሆናቸው ሁሉም እርቅ ያደርጋሉ። ምክንያቱም በአምላካዊው ጥበቃ እና ምህረቱ ዛፍ ጥላ ሥር ሁሉም ተጠልለዋል። አምላክ ለሁሉም ደግ ነው፤ ለሁሉም ሳይለይ በረከትን ሰጪ ነው። እየሱስ ክርስቶስም እንኳን እንዳለው እግዚአብሔር "በፍትህ አድራጊውም ሆነ ፍትሕን በሚያጓድለውም ላይ እኩል ዝናቡን ያዘንባል።" ይህም የእግዚአብሔር ምህረት ሁሉን ዓቀፍ ነው ለማለት ነው። መላው የሰው ዘር በእርሱ ፍቅር እና በቸሮታው ጥበቃ ሥር ነው፣ እርሱ ለሁሉም የመርሆንና የእድገትን መንገድ አሳይቷል።"[22]**

## ምዕራፍ 9

እ.ኤ.አ በ1848 በዙፋን ላይ የወጣው ንጉሥ ናስረዲን ሻህ ከቀድሞው ንጉሥ ከአባቱ በጣም የባሰ ጨካኝ ነበር። ዙፋን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የባቢዎች ጭቆና (ስቃይ) በአስገራሚ ፍጥነት ጨመረ። ባብ እራሱ እ.ኤ.አ በጁላይ ወር 1850 በታብሪዝ ከተማ ሰማዕት ሆነ። በሺህዎች የሚቆጠሩት የአማኝ ጓደኞቻቸውን አስከፊ ሞት የተመለከቱ የተጨቆኑ ተከታዮቹ፣ አሁን ደግሞ የልቦቻቸውን እጅግ ተወዳጅን አጡ። በእነኝህ ሁሉ ዓመታት የተጫነባቸው ጭካኔ በንጉሡ ምክንያት ነው ብለው ብዙዎች ያስቡ ነበር። እንደዚህ ዓይነት ስሜት ቢኖራቸውም እንኳን ለመንግሥትና ለሕዝብ መልካም ተመኚዎች መሆናቸውን ቀጠሉ። በመልካም ተግባሮች ኃይል እና በሚያሳምኑ ክርክሮች አማካኝነት ጉልበታቸው አዲሱን እምነት ለማሰራጨት ይውል ነበር። ሆኖም በከፍተኛ ቁጣ የተነሱ እና አደገኛ ሐሳብ የሚያውጠነጥኑ ጥቂት ምዕመናኖችን የያዘ አንድ ቡድን ነበር። ተስፋ በመቁረጥም እነኝህ ጥቂት ማመዛዘን የጎደላቸው ምዕመኖች ጭቆናን ከሥሩ በመመንገል የባቢ ኅብረተሰብን ሁኔታ መቀየር እንችላለን ብለው ያምኑ ነበር። እነዚህም ሰዎች ንጉሡን ለመግደል ማሴር ጀመሩ።

የቡድኑን ሐሳብ ከመሪዎቹ አንዱ ለባሃኡላህ ነገረው። ባሃኡላህም በጣም ግልፅ በሆነ ቋንቋ እቅዳቸውን እንዲሰርዙ መከረ። እንደዚህ ዓይነቱ ተግባር ሐዘን ባጎሳቆላቸው በባብ ተከታዮች ላይ ተጨማሪ አደጋዎችን እንደሚያመጣ አስጠነቀቃቸው። ነገር ግን ሴረኞቹ ልቦናቸው በጣም ከመሻከሩ እና የበቀል እሳት በውስጣቸው በኃይል ከመንደዱ የተነሳ የባሃኡላህ ምክሮች እንኳን ሊያቆሟቸው አልቻሉም። ንፁህ ከግለኝነት ነፃ እና ጀግንነት በተሞሉ ተግባሮች በስተቀር በሌላ ያላጌጠውን የባቢን ታሪክ ገፆች ለዘለዓለም አሳድፏል ተብሎ የሚታሰበውን ተግባር ለመፈፀም ገፉበት።

እ.ኤ.አ ኦገስት 15 ቀን 1852 ንጉሡ ከቴህራን አቅራቢያ ከሚገኘው የበጋ ወቅት መኖሪያው ጠዋት ጠዋት ለሚያደርገው የፈረስ ግልቢያ ወጣ። የግል ጠባቂው ከፊት ለፊቱ ጥቂት እርምጃዎችን ራቅ ብሎ ይጓዝ ነበር። አየሩ የተረጋጋ እና ሁሉም ነገር ደህና ይመስል ነበር። ከዚያም፣ ሁሉንም ባስገረመ መልኩ፣ ለንጉሡ ማመልከቻ ለማቅረብ የተዘጋጀ የሚመስል ከመንገዱ ዳር የቆመ አንድ ወጣት፣ ሊገድለው ሞከረ። ንጉሡን እገድላለሁ ብሎ የተነሳው ይህ ሰው እጅግ ማስተዋል የተሳነው ስለነበር የተጠቀመበት ሽጉጥ ያጎረሳቸው ጥይቶች ለታለመለት ዓላማ ፈፅሞ በቂ ያልሆኑ ነበሩ። ንጉሡ በጥቂቱ ብቻ ቆሰለ፤ ነገር ግን በሕይወቱ ላይ የተደረገው ሙከራ የፈጠረው ቁጣ ሊታሰቡ የማይቻሉ ዓይነት የጭካኔ ተግባሮች በባቢዎች ላይ እንዲፈፀሙ ሕዝቡን ለማነሳሳት ለእምነቱ ጠላቶች እድል ሰጣቸው።

ይህ እድለቢስ ወጣት ያኔውኑ ተገደለ፤ ሬሣውም ከበቅሎ ጭራ ላይ ታስሮ እስከ ቴህራን ድረስ እየተጎተተ ተወሰደ፤ ከዚያም ለሁለት ቦታ ተቆርጦ ሕዝቡ እንዲመለከተው ተሰቀለ። ሌላውን ተባባሪውን የሌሎቹን ጓዶቹን ስም እንዲሰጣቸው ቢጠይቁትም አሻፈረኝ ስላለ ያለምህረት ካሰቃዩት በኋላ የቀለጠ መዳብ በጉሮሮው አንቆረቆሩበት። ሦስተኛውን አጋራቸውን ልብሱን አውልቀው እና አካሉን በየቦታው ቦርቡረው የሚነዱ ሻማዎችን ከሸጎጡበት በኋላ በሕዝቡ ፊት እያዞሩ የስድብ እና የእርግማን መዓት እንዲወርድበት አደረጉ።

ከዚህ በኋላ ተከትሎ የመጣውን ነገር በቃላት ሊገለፅ አይችልም። መንግሥት፣ ካህናትና ደንቆሮ ደጋፊዎቻቸው ባቢዎችን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ተነሱ። የከተማው ደጃፎች ተዘግተው፣ ማንም ሳይፈተሽ እንዳይወጣ ተከለከለ። ባቢዎች ከቤት ለቤት እየታደኑ ተያዙ፣ በነዚህ ገፆች ለመግለፅ በሚዘገንን ሁኔታ ተገደሉ።

ንጉሡን ለመግደል ሙከራ በተደረገበት ቀን ባሃኡላህ በቴህራን አቅራቢያ በምትገኝ አንዲት መንደር የጠቅላይ ሚኒስትሩ ወንድም እንግዳ ነበር። የመዓቱ ዜና ደረሰው፣ ችግሩም እስኪያልፍ እንዲደበቅ

ተመከረ። የንጉሡ እናት ልጇን ለመግደል በተደረገው ሙከራ ባሃኡላህን ተወቃሽ አደረገች እናም በቁጥጥር ስር እንዲውል ወተወተች። ነገር ግን ባሃኡላህ አልደበቅም አለ። እንዲያውም በሚቀጥለው ቀን በፈረሱ ላይ ሆኖ ወደ ንጉሡ ዋና መስሪያ ቤት ሄደ። ንጉሱ እና ሸንጎው የባሃኡላህን መምጣት ሲሰሙ ተደነቁ። እንደዚህ ዓይነት አስከፊ ወንጀል ሠርቷል የተባለው ሰው ማምለጥ ንቆ በልበ ሙሉነት እንዴት ወደ አደጋው ሊመጣ ቻለ? ንጉሡ ባሃኡላህ እንዲታሰር ወዲያው አዘዘ። አንዳንድ ወዳጆች በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቤት መጠጊያ እንዲያገኝ ቢጥሩም አልተሳካም። ከዋናው ከተማ ሰላሳ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት በነበረችው በሺሚራን መንደር ተይዞ ታሰረ።

በእግሩ ሆኖ፣ በበጋ ለምትወጣው የከረረ ፀሐይ ተጋልጦ፣ ባሃኡላህ ከሺምራን ወደ ቴህራን ተወሰደ። በመንገዱ ሁሉ የንጉሣቸው ጠላት ነው ተብሎ የተነገራቸው በቁጥር የበዙ ሰዎች የስድብ ናዳ አወረዱበት። በባሃኡላህ ላይ ድንጋይ ለመወርወር ከፍተኛ ጥረት ያደረገችው አሮጊት ታሪክ በዚያን ቀን የተሰበሰበውን ሕዝብ እብደት እና የእርሱንም በእጅግ አሰቃቂ መዓት መካከል የደረሰበትን ስቃይ ተጋፍጦ በልቡ ውስጥ ያለውን ፍቅር ያሳየበት ሁኔታ ነው።

ባሃኡላህ ወደሚታሰርበት ወደ ጨለማው እስር ቤት እየተጠጋ ሲመጣ አንድ በእድሜ የገፋች እና ደካማ አሮጊት በእጇ ድንጋይ ይዛ በሕዝቡ መካከል እያቆራረጠች መጣች። በእርሷ እድሜ ያሉ ጥቂት ሴቶች ብቻ ሊኖራቸው የሚችል ዓይነት ቆራጥነትና አክራሪነት በፊቷ ላይ ይታይ ነበር። ጠቅላላ ሰውነቷ በንዴት ይርገፈገፍ ነበር። ወደፊት በመራመድ ባሃኡላህን ወደ ጨለማው እስር ቤት ለማስገባት እየወሰዱ የነበሩትን በመከተል ድንጋዩን ለመወርወር እጇን ስታነሳ "እባካችሁ ድንጋዩን እፊቱ ላይ እንደወረውር እድል ስጡኝ" በማለት ለመነቻቸው። ወደ እርሱ እየተንደረደረች ስትመጣ ሲያይ፣ ባሃኡ ላህ ለጠባቂዎቹ እንዲህ አላቸው፦ "በአምላክ ዘንድ እጅግ አስመስጋኝ ሥራ ነው ብላ ለገመተችው ተግ ባር እባካችሁ እድል አትንፈጓት፣" የሚል ቃላት ነበር።

1. እ.ኤ.አ በ1848 ፋርስ ላይ ወደ ዙፋን የመጣው ንጉሥ ስም ማን ነበር?

______________________

2. ናሲረዲን ሻህ ወደ ዙፋን ከመጣ በኋላ ባቢዎቹ ላይ የነበረው ሁኔታ እንዴት ነበር?

_______________________________________

3. ባብ ሰማዕትነትን ከተቀበለ በኋላ በአጠቃላይ ባቢዎች ምን ተሰማቸው?

_______________________

4. ንጉሡን ለመግደል የወሰኑት ባቢዎች የስነ-ልቡና ሁኔታ እንዴት ነበር?

_______________________

5. ባሃኡላህ ሐሳባቸውን ሲረዳ ለቡድኑ መሪ ምን ነገረው?

____________________________________

6. ንጉሡን ለመግደል ሙከራ የተደረገው መቼ ነበር? ____________________________________

7. የግድያውን ሙከራ ያደረጉት ሰዎች እጣ ፈንታ ምን ሆነ? ____________________________

8. የግድያው ሙከራው በባቢ ማህበረሰብ ላይ ምን ጦስ አስከተለ? ________________________

9. በንጉሡ ላይ የተደረገውን የግድያ ሙከራ በሰማበት ጊዜ ባሃኡላህ የት ነበር? _______________

10. የግድያ ሙከራውን ዜና በሰማ ጊዜ ባሃኡላህ ምን አደረገ?

_______________________________

11. ባሃኡላህ የተያዘው በየትኛው መንደር ውስጥ ነው? _________________

12. ባሃኡላህ በጠላቶቹ ፊት ኃይል አልባ እንዳልሆነ እና ራሱን የሚጥልበትን አደጋ እያወቀ

እንዲታሰር የፈቀደው ለምን ይመስላችኋል?

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

______

13. በምን ዓይነት ሁኔታ ነበር ባሃኡላህ ከሺምራን ወደ ቴህራን የተወሰደው?

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

___________

14. ጠባቂዎቹ ወደ ጨለማው የእስር ቤት ጉድጓድ ሲወስዱት በባሃኡላህ ላይ ድንጋይ ለመወርወር ስለፈለጉት አሮጊት ታሪክ በራስዎ አባባል ይተርኩ። ይህ ታሪክ ምንን ያሳያል?

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

___________

## ምዕራፍ 10

*በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ባሃኡላህ የኖረው፣ ሊጎዱት በሚፈልጉ ጠላቶቹ ተከብቦ ነው። ነገር ግን ፈፅሞ ራሱን ለመደበቅ ሞክሮ አያውቅም፣ ራሱንም ተከላክሎ አያውቅም። እንዲያውም ሁልጊዜ ለሰዎች በግልፅ ይታይ እና የተቃዋሚዎቹን ጥቃት በእርጋታ እና ሳይረበሽ ይቋቋም ነበር። ምንም እንኳን ብር ሐኑንን ለማጥፋት ቆርጠው ቢነሱም ሊያጠፉት ግን አልቻሉም፣ እንዲያውም ከቀን ወደ ቀን ድምቀቱ ይበልጥ እያንፀባረቀ ሔደ።*

> **“ይህ በደል የተፈፀመበት ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ራሱን ደብቆ አያውቅም። እንዲያውም በሁሉም ጊዜያቶች በሰዎች ሁሉ እይታ ፊት ፅኑ እና ግልፅ ሆኖ ቆይቷል። አፈግፍገንም ሆነ ለመሸሽ ፍላጎት አድሮብን አያውቅም፣ እንደ እውነቱ ከሆነ የሚሸሹት እነዚያ ማስታዋል የጎደላቸው ሰዎች ናቸው . . . ለአምላክ ምስጋና ይድረሰው! ይህ በደል የተፈፀመበት መልእክ ተኛ ሆኖ ያመጣው እምነት እንደሰማይ ከፍ ብሎ ያለ ነው። እንደ ፀሐይም በማንፀባረቅ ያበ ራል። መደበቅ ወደ እዚህ ደረጃ አያደርስም፣ ለፍርሐት እና ለዝምታም አጋጣሚዎች የሉም።”[24]**

> **“ይህ በደል የተፈፀመበት ሳይሸፈን እና ሳይደበቅ፣ በሁሉም ጊዜያቶች ያንን የሣይንሶችን፣ የስነ-ጥበባትን፣ የእውቀትን፣ የደህንነትን፣ የብልፅግናንና የሐብትን በሮች ለመክፈት እንደቁልፍ የሚያገለግለውን በሁሉም የዓለም ሕዝቦች ፊት አውጇል። በጨቋኞች የተፈፀሙትን በደሎች የእጅግ በጣም ከፍተኛውን ብዕር፣ የሚሠነጥቅ ድምፅ፣ ፀጥ ለማድረግ ያልተሳካላቸው መሆኑ ብቻ ሳይሆን የብልሹዎች ወይንም የአመፀኞች ጥርጣሬዎች፣ እጅግ በጣም የላቀውን ቃል ከመግለፅ አልገቱትም።”[25]**

*ችግሮችን በመጋፈጥ የባሃኡላህን ሃይማኖት ድል ለማጎናፀፍ በምናከናውነው ሥራ ምን ማድረግ እንዳለብን፣ በራሳችሁ ቃላት አብራሩ።*

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

_______________

## ምዕራፍ 11

በዚያ በ1852 እጅግ ክፉ ቀን ባሃኡላህ በ“ሲያህ-ቻል”፦ ትርጉሙ “ጥቁር ጉርጓድ” ማለት ነው፣ እስር ቤት እንዲታሰር ተወሰደ። በመጀመሪያ አሠራሩ በቴህራን ለሚገኙ የሕዝብ መታጠቢያ ቤቶች

ለአንዱ ውኃ ማጠራቀሚያ የነበረው ሲያሁ-ቻል፣ ከጊዜ በኋላ ግ አደገኛ ወንጀለኞች የሚታሰሩበት ከመሬት በታች ያለ እስር ቤት ሆነ።

ወደ እስር ቤቱ ለመድረስ ድቅድቅ ጨለማ በተላበሰ መተላለፊያ ውስጥ ካለፉ በኋላ ወደታች ሦስት እርከን ያላቸው ደረጃዎችን ቁልቁል መውረድ ያስፈልግ ነበር። ድቅድቅ ባለ ጨለማ ተሸፍኗል፣ እንደ በረዶ ይቀዘቅዛል፣ እናም ወለሉ በሚተነፍግ ቆሻሻ እና በሚርመሰመሱ ተባዮች የተሞላ ነበር። ባሃኡላህ እራሱ የታሰረበትን ወህኒ ሁኔታ እንዲህ በማለት ገልጾታል:–

> **"እዚያ ስንደርስ በመጀመሪያ በአንድ በጣም ጥቁር በሆነ መተላለፊያ እንድናልፍ ተደረገ፣ ከዚያም ሦስት እርከን ያላቸው ደረጃዎችን ከወረድን በኋላ ወደ ተመደበልን የእስር ስፍራ ደረስን። ጉድጓዱ ድቅድቅ ጨለማ ለብሶ ነበር፤ በእስር ቤቱ አብረውን የነበሩት እስረኞችም ወደ መቶ ሃምሳ የሚጠጉ ሌቦች፣ ነፍሰ ገዳዮች እና ዘራፊዎች ነበሩ። እስር ቤቱ ምንም እንኳ (በሰው ብዛት) ቢተፋፈግም ከገባንበት መተላለፊያ በስተቀር ሌላ መውጫ አልነበረውም። ያንን ቦታ ሊገልፅ የሚችል ብዕር፣ ወይም የሚዘገንን ክርፋቱን ሊገልፅ የሚችል ልሳን አይገኝም። ከእነኚህ ሰዎች አብዛኞቹ የሚለብሱትም ልብስ ሆነ፣ የሚተኙበት ምንጣፍ አልነበራቸውም። በዚያ እጅግ ክርፋታማ እና ጨለማ ቦታ የደረሰብንን የሚያውቅ አምላክ ብቻ ነው።"[26]**

በእንደዚህ ዓይነት አስከፊ ሁኔታ ንጉሡ ባሃኡላህንና ብዙ ባቢዎችን አሰረ። የባሃኡላህ እግሮች በእግረ-ሙቅ ተጠፈሩ፣ ሃምሳ ኪሎ ግራም የሚመዝን ከባድ ሠንሠለት በአንገቱ ዙሪያ ተደረገ። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት እና ሌሊቶች የሚበላም ሆነ የሚጠጣ አልተሰጣቸውም። የባሃኡላህ ቤተሰቦች ምግብ አዘጋጅተው ወስደው ጠባቂዎቹን እንዲሰጡት ጠይቀው ነበር። በመጀመሪያ አሻፈረን ቢሉም ቀስ በቀስ ግን ልመናቸውን ተቀበሉ። ነገር ግን፣ ምግቡ ለእርሱ ይድረሰው አይድረሰው፣ ወይንም አብረውት ያሉ እስረኞች እየተራቡ እርሱ እንዲበላ ምግቡን ይቀበል አይቀበል እርግጠኛ ለመሆን ማንም አልቻለም።

ባሃኡላህ እና ከእርሱ ጋር አብረው የነበሩት፣ በማነቆ እና በሠንሠለት ታስረው የታጨቁት አንዲት ክፍል ውስጥ ነበር። የተቀመጡት እርስ በእርስ ትይዩ ሆነው በመደዳ ነበር። ደጋግመው እንዲያዜሙት ባሃኡላህ አንዳንድ ጥቅሶችን አስተማራቸው። እነኚህን ጥቅሶች በየእለቱ ማታ ማታ በታላቅ ስሜት ያዜሟቸው ነበር። አንዱ ረድፍ:– **"እግዚአብሔር አርኪዬ ነው፣ እርሱ በእውነቱ ሁሉንም ያረካል።"** ብሎ ሲያዜም ሌላው ረድፍ ደግሞ፣ **"የሚተማመኑ በእርሱ ይታማመኑ።"** ብሎ ይመልስ ነበር። እስከ ንጋት ድረስ ደስታ የተሞላው ሕብረ ድምፃቸው እስከ ቤተ-መንግሥት ይሰማ ነበር። ጥዑመ ዜማቸው እጅግ ኃያል ከመሆኑ የተነሳ ንጉሥ ጆሮዎች ዘንድ ደረሰ። ንጉሡ "ይህ ድምፅ ምንድነው ነው?" ብሎ እንደጠየቀ ይነገራል። "እነርሱ በእስር ቤት ውስጥ የሚያዜሙት የባቢዎች መዝሙር ነው።"[27] ነበር የተሰጠው መልስ። ንጉሡም ዝም አለ።

የእስር ቤቱ ጠባቂዎች ወደ ክፍሉ በመግባት የአንድ ባቢ ስም ይጠሩና ተነስቶ ወደ መሰቀያ ቦታ እንዲከተላቸው ያዙታል። የተጠራው ሰው በጉጉት ለጥሪው ምላሽ ይሰጣል። ሠንሠለቱ ሲፈታለት በፍጥነት ይቆምና ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ሐሴት ወደ ባሃኡላህ ቀርቦ ያቅፈዋል። ከዚያም አብረውት የታሰሩትን እያንዳንዳቸውን አቅፎ ይስማል፣ ተስፋና ደስታ በተሞላው ልብም የሚጠብቀውን ሞት ለመጋፈጥ ይሄዳል። እነኚህ ጀግና ነፍሶች ሰማዕት ከሆኑ በኋላ የሞት ፍርድ አስፈፃሚው የባሃኡላህ አድናቂ ሆኖ ስለነበር መጥቶ ስለ እያንዳንዳቸው የአሟሟት ሁኔታ ይነግረው ነበር። እያንዳንዱ ሰማዕት የወረደበትን ስቃይ እስከመጨረሻው ድረስ በምን ዓይነት ሐሴት እንደቻለው ያሳውቀው ነበር።

1. ባሃኡላህ የታሰረበት እስር ቤት ምን ይባል ነበር?

_______________________________

2. "ሲያህ-ቻል" ማለት ምን ማለት ነው?

______________________________________

3. ሲያህ-ቻል አስቀድሞ ለምን ማጠቀሚያ ይውል ነበር?

____________________________

4. የሲያህ-ቻል እስር ቤት ሁኔታን ይግለፁ፡፡

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

___________

5. ባሃኡላህ ሲያህ-ቻል ሲደርስ በአንገቱ ዙሪያ ምን ተደረገ? ________________

6. እግሩንስ በምን እንዲጠፈር ተደረገ? ________________

7. ባሃኡላህ እና አብረውት የነበሩት በእስር ቤቱ ክፍል ውስጥ የተቀመጡት እንዴት ነበር?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

_____

8. ባሃኡላህ ምን አስተማራቸው? ________________

9. ሌሊቱን ሙሉ በአንደኛው ረድፍ የተደረደሩት ባቢዎች የሚያዜሙት ምን ነበር?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

_______

10. ሌላው ረድፍ ምን ብሎ ይመልስ ነበር? ____________________________________

11. ዜማቸው በንጉሡ ላይ ምን ውጤት አመጣ?

_____________________________________________________________________

___

12. በየቀኑ የእስር ቤቱ ጠባቂዎች ወደ ክፍሉ በመግባት የአንድ ባቢ ስም ይጠራሉ። ከዚያ በኋላ የሚሆነውን በእራስዎ አባባል ይግለፁ።

_____________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

__________________

13. የታሰሩበት ሁኔታ እጅግ አስከፊ ሆኖ ሳለ ባቢዎቹ እጅግ ደስተኛ የሆኑት ለምን ይመስሎታል?

_____________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

_________

## ምዕራፍ 12

የባሃኢን ታሪክ የሚያጠና ማንም ተማሪ ሊረዳው የሚገባው አንድ ጥልቅ ሐሳብ አለ። ይኸውም የአምላክ ሃይማኖት እያደገ የሚሄደው በተከታታይ በሚፈራረቁበት የተቃውሞ(የቀውስ) ሁኔታዎች እና ድል ነው። የድንቁርና ኃይሎች፣ ኢፍትሐዊነት፣ ጭካኔና አክራሪነት፣ ለተቃውሞ መንገድ ሲከፍቱ፣ አፍራሽ ኃይሉንም መቋቋም ይቻል ዘንድ በቂ የሆነ የታመቀ ኃይል ይለቀቃል። ከዚያም ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ አዲስ የተቃውሞ ትንኮሳን ይቀሰቀሳል፣ እምነቱም አዳዲስ ድሎችን እንዲጎናጸፍል፣ ብዙም ሳይዘገይ፣ በምንም ላልተገመቱ፣ ለአዳዲስ የተቃውሞ ወረርሽኝ ይዳረጋል ከዚያም በተራው እንደገና ሌላ ተመጣጣኝ መለኮታዊ ኃይል መለቀቅን ያስከትላል። እምነቱ ከችግር

ወደ ድል ከዚያም ወደ ችግር እንደገናም ወደ ድል እያለ የሚያደርገውን የግስጋሴ ጉዞውን በምድር ላይ ያለ ምንም ዓይነት ኃይል ሊያስቆመው አይችልም።

የባብ አጭር የተልዕኮ ዘመንም ይህን የመሰለ ሁኔታን የተከተለ ነበር። ነገር ግን ተራው ተመልካች በመጨረሻ የደረሰው ውድቀት (የባብ ሰማዕትነት) አማኞቹ ሊወጡት የማይችሉት እንደሆነ አድርጎ ተገንዝቦት ነበር። ሊነገር በማይቻል የጭካኔ ጭፍጨፋ በሺህዎች የሚቆጠሩ ተከታዮቹ ተገድለዋል። የላቁ ደቀ-መዛሙርቱ ሰማዕታት ሆነዋል፣ ተስፋው እንዲያንሰራራ ሊያደርግ የሚችለው ብቸኛውም በሰንሰለት ታስሮ ከሁሉ በከፋው ጨለማው ጉድጓድ ውስጥ ተጥሏል። ውድቀቱ በእርግጥ ከፍተኛ ቢሆንም፣ ነገር ግን ይህንን ሁኔታ ተከትሎ የመጣውም ድል እጅግ የላቀ ነበር።

በሲያህ-ቻል አምላክ ለባሃኡላህ የእርሱን (የባሃኡላህን) ታላቅ ደረጃ ገለፀለት። በጨለማ ተውጦ፣ ሽታው እጅግ አስከፊ የሆነውን ዓየር እየተነፈሰ፣ እግሮቹ በእግረ-ሙቅ ታስረው፣ አንገቱም በክብደቱ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ሠንሠለት ጎብጦ ሳለ የመጀመሪያውን አንቀሳቃሽ የሆነውን የአምላክን ግልፀት በነፍሱ ውስጥ ተቀበለ። ይህን በመሰለው እጅግ አስፈሪ እና ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ውስጥ፣ "ከሁሉ በላይ ታላቁ መንፈስ" እንዲነሳና የአምላክን ቃል እንዲናገር እያዘዘ ራሱን ገለፀለት።

ልክ ከከፍተኛ ተራራ ላይ ወደ መሬት እንደሚፈስ ኃይለኛ ፏፏቴ አንዳች ነገር ከራሱ ላይ ወደ ደረቱ እንደሚፈስ ይሰማው ነበር። የሰማይ አገልጋይት በፊቱ በማደግደግ፣ ከውስጣዊና ውጫዊ እሱነቱ ጋር ስትዋጋ የዓለማት ከፍተኛ ተወዳጅ፣ የአምላክ ውበት፣ የአምላክ ልዕልና ኃይል እንደሆነ ስትገልፅለት አየ። በእራሱ እና በብዕሩ፣ እንዲያውም በእነዚያ አምላክ በሚያስነሳቸው አማካኝነት አሸናፊ እንደሚሆን ተረጋገጠለት።

በመሆኑም፣ ከጥቁሩ ጉደጓድ በስተጀርባ የእውነት ፀሐይ ነጋ። የባብ ትንቢት ተፈፀመ። የባሃኢ ግልፀት ተወለደ። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ባሃኡላህ ስለተከሰተው ሁኔታ ለማንም አልገለፀም። ተልዕኮውን ለማሳወቅ በአምላክ የታዘዘውን፣ የተወሰነውን ሰዓት ይጠብቅ ነበር።

1. ባሃኡላህ በታሰረበት ወቅት የባቢ ማህበረሰብ የደረሰበትን ውድቀት ምን ያህል እንደነበር በራሳችሁ ቋንቋ ግለፁ።

   ________________________________________________________________________

   ________________________________________________________________________

   ________________________________________________________________________

   ________________________________________________________________________

   ____________

2. ከዚህ ችግር እና ውድቀት በኋላ የተከተለው ድል ምን ነበር?

   ________________________________________________________________________

   ________________________________________________________________________

   _____

## ምዕራፍ 13

በሰው ልጅ ሃይማኖት ታሪክ ውስጥ ይህን እጅግ አስፈላጊ ክስተት ባሃኡላህ በራሱ ቃል ስለዘገበው ዕድለኛ ነን። ከዚህ በታች ያለውን የእርሱን ጽሑፍ በማንበብ፣ ቀጥሎ ያለውን ባዶ ቦታዎች ይሙሉ።

የእርሱን ነፍስ የአምላክ ግልፀት እንዴት እንደሞላት፣ ባሃኡላህ እንዲህ አለ:–

> **"አንድ ምሽት በሕልሜ እነዚህ እጅግ የተወደሱ ቃላትን ከሁሉም አቅጣጫ ተሰሙኝ፣ በእርግጥ በእራስህና በብዕርህ ድልን እንድትጎናፀፍ እናስችልሃለን። በደረሰብህ ነገር አትዘን፣ አትፍራም፣ በጥበቃ ስር ነህና። ብዙም ሳይዘገይ አምላክ የምድር ሃብት የሆኑትን በራስህና እግዚአብሔር በእነዚያ እርሱን ባወቁት ሰዎች ልቦች ነፍስ በዘራበት ስምህ አማካኝነት የሚረዱህን ሰዎች ያስነሣል።"[28]**

በዚህ ምንባብ፣ ባሃኡላህ እንደሚነግረን አንድ ሌሊት፣ በሕልሙ፣ እነዚህ ቃላትን ከሁሉም አቅጣጫ ሰማቸው:–

"በእርግጥ ______________________ና ________________________

________________________ እንድትጎናፀፍ እናስችልሃለን። ______________________ ነገር

_________________________፣ ___________________________፣ በጥበቃ ስር ነህና። ብዙም

ሳይዘገይ _______________________ የምድር ___________________ የሆኑትን

______________________ና ______________________ በእነዚያ ____________ ባወቁት ሰዎች

ልቦች ነፍስ በዘራበት ስምህ አማካኝነት _________________ ሰዎች

_________________________።"

በሌላ ምንባብ ባሃኡላህ የአምላክ ግልፀት በእርሱ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ እንዲህ ገልፆታል:–

> **"በቴህራን እስር ቤት ታስሬ በነበርሁባቸው ቀናት ምንም እንኳ የሠንሰለቶቹ የከፋ ክብደት እና ክርፋት የተሞላው አየር እንቅልፍ ነስቶኝ የነበረ ቢሆንም፣ በእነዚያ በተቆራረጡ የሽለብታ ጊዜያት ልክ ከከፍተኛ ተራራ ጫፍ ላይ ወደ መሬት እንደሚወረወር ዶፍ አንድ ነገር ከራሴ አናት ላይ ወደ ደረቴ እንደሚፈስ ሆኖ ይሰማኝ ነበር። በዚህ ምክንያት የአካሌ እያንዳንዱ ክፍል ይቀጣጠል ነበር። በእንደዚህ ዓይነቱ ጊዜያት ከልሳኔ ማንም ሰው ሰምቶ ሊቋቋመው የማይችል ለው ነገር ይወጣ ነበር።"[29]**

ባሃኡላህ እንዳለው፣ “በ ______________________________ ታስሬ በነበርሁባቸው ቀናት

ምንም እንኳ የሠንሰለቶቹ ______________________እና

____________________________ እንቅልፍ ነስቶኝ የነበረ ቢሆንም፣ በእነዚያ በተቆራረጡ

የሸለብታ ጊዜያት ልክ ________________________ ላይ ወደ መሬት እንደሚወረወር

____________ አንድ ነገር __________________________________________________

ነበር። በዚህ ምክንያት ____________________________________________________

ነበር። በእንደዚህ ዓይነቱ ጊዜያት ከልሳኔ

_________________________________________ ይወጣ ነበር።”

እንደገና በሌላ ምንባብ ባሃኡላህ “እጅግ ታላቁን መንፈስ” የምትወክለውን እንዴት ለእርሱ እንደ ታየች በአንዲህ መልክ አብራርቶታል:–

> **“በመከራ ውስጥ ተውጬ ሳለሁ፣ ከራሴ በላይ ድንቅ፣ ከሁሉም በላይ ጣፋጭ ድምፅ ሲጠራ ሰማሁ። ፊቴን በመመለስ የጌታዬን ስም ትውስታ መገለጫ የሆነችውን አገልጋይት ከፊቴ በአየር ላይ ሆና ተመለከትኩ። ነፍሷ እጅግ ተደስታ፣ ገፅታዋ በአምላክ መልካም ፈቃድ ጌጥ አብርቶ፣ በሁሉን ይቅርባዩ ብርሃን ጉንጮቿ ፍም መስለው ነበር። የሰዎችን ልቦች እና አእምሮዎችን ለመማረክ የቻለ ጥሪ በምድር እና በሰማይ መካከል እያሰማች ነበር። ነፍሴንና፣ በአምላክ የተወደሱትን አገልጋዮችንም ነፍሶች የሚያሰስት ዜና ለውስጣዊና ውጫዊ እኔነቴ ታካፍለኝ ነበር። ወደ እኔ በጣቷ በመጠቆም፤ እንዲህ በማለት በምድር እና በሰማይ ለሚገኙት ሁሉ ተናገረች:– ‘በአምላክ! ይህ የዓለማት እጅግ ተወዳጅ ነው፣ ሆኖም እናንተ ልትገነዘቡት አትችሉም። ልትረዱ ብትችሉ ይህ በመካከላችሁ ያለ የእግዚአብሔር ውበት፣ በእናንተም ውስጥ የእርሱ ልዕልና ኃይል ነው። ከእነዚያ ከሚገነዘቡት ብትሆኑ ይህ የአምላክ ምስጢር እና የእርሱ ሐበት ነው፤ ለእናንተ በግልፀቱ እና በፍጥረቱ መንግስት ውስጥ ለምትኖሩ ሁሉ የአምላክ እምነት እና ክብሩ ነው’”**[30]

ባሃኡላህ እንደሚነግረን “በመከራ ውስጥ ተውጬ ሳለሁ ከጭንቅላቴ በላይ ድንቅ፣ ከሁሉም በላይ

_______________________________________________ ሰማሁ። ፊቱን በመመለስ የ

_____________ ትውስታ መገለጫ የሆነችውን አገልጋይት ከፊቱ _______________________

ሆና ተመለከተ። ______________________________ ገፅታዋ

__________________________________ አብርቶ፣

_____________________________________ ጉንጮቿ ፍም መስለው ነበር። የሰዎችን ልቦች እና

አእምሮዎችን ________________________________________ በምድር እና በሰማይ መካከል

እያሰማች ነበር። ነፍሴንና፣ በአምላክ _________________________________ የሚያስደስት ዜና

ለውስጣዊና ውጫዊ እኔነቴ ታካፍለኝ ነበር፡፡ ወደ ጭንቅላቴ በጣቷ በመጠቆም፤ እንዲህ በማለት ________________________ ለሚገኙት ሁሉ ተናገረች፡– በአምላክ! ይህ ________________________ ነው፣ ሆኖም እናንተ ልትገነዘቡት አትችሉም፡፡ ልትረዱ ብትችሉ ይህ በመካከላችሁ ያለ ________________________፣ በእናንተም ውስጥ የእርሱ ________________________ ነው፡፡ ከእነዚያ ከሚገነዘቡት ብትሆኑ ይህ ________________________ እና የእርሱ ________________________ ነው፤ ለእናንተ በግልፀቱ እና በፍጥረቱ መንግስት ውስጥ ለምትኖሩ ሁሉ የአምላክ ________________________ እና ________________________ ነው፡፡"

## ምዕራፍ 14

የውድቀት እና የድል ፅንሰ-ሃሳብ እጅግ ዋና ጉዳይ ስለሆነ በመንገዱ የገጠሙትን መሰናክሎች ሁሉ በድል ስለሚወጣው ስለእምነቱ ኃይል እዚህ ላይ ቆም ብሎ ማሰላሰል ይጠቅማችኋል፡፡ ይህንን ለማድረግ ያስችላችሁ ዘንድ ከዚህ በታች የሰፈሩትን አንድ ከባሃኡላህ ፅሑፍ እና ሌላው ደግሞ በሾጊ ኤፌንዲ ስም ከተፃፈ ደብዳቤ የተወሰዱ ጥቅሶችን እንድታነቡና የሚከተሉትን መልመጃዎች እንድትሰሩ ተጠቁሟል፡፡

> **"በዚህ ግልጸት ዑደት ዋጋ ቢሶችና ሞኞቹ ግድያ፥ ዝርፍያና ግዞት በመሳሰሉት ዘዴዎች፥ የመለኮታዊው እጅ ያበራውን መብራት ለማጥፋት ወይም የዘለዓለማዊውን ደማቅ ብርሃን የቀኑን ኮከብ ለመጋረድ የሚችሉ መስሎአቸው፥ እንዴት በጋለ ምኞት እንደሚያስቡ ተመል ከቱ፡፡ እንዲህ ያለው መከራ የዚህን መብራት ነበልባል የሚመግብ ዘይት የመሆኑን እውነት እን ዴት ያልተረዱ ይመስላሉ! የእግዚአብሔር የመለወጥ ኃይል እንዲህ ያለ ነው፡፡ እርሱ የሚፈል ገውን ማንኛውንም ነገር ይለውጣል፤ እርሱ በእውነት በሁሉ ነገሮች ላይ ሥልጣን አለው...፡፡"[31]**

> **"ይህ እምነት እንደማንኛውም መለኮታዊ እምነት ሊያጠቁት የተነሱትን የተቃውሞ ኃይላት ሁሉ ጀግንነት በተሞላው ሁኔታ ድል ካላደረገ በጠነከረ ሁኔታ ሊመሠረት አይችልም፡፡ ለዚህ የእ ምነቱ ታሪክ በራሱ በቂ ማረጋገጫ ነው፡፡ ፈተናዎች እና ስቃዮች የአምላክ ምርጦች ዕጣ ፋንታ ነው ይህ አሁንም ወደፊትም ይኖራሉ፡፡ በዚህ አማካኝነት እምነታቸው ሕይወት ይዘራበታል፤ ይነፃል እንዲሁም ይጠነክራል፤ ስለሆነም እነሱ ሁኔታውን እንደስውር ቡራኬ ሊወስዱት ይገባል፡፡ ባሃኡላህ እነዚህን የመሳሰሉትን ስቃይ የተሞሉ ፈተናዎች የአምላክን እምነት መብራት ከሚመግብ ነዳጅ ዘይት ጋር ያነፃፅረዋል፡፡"[32]**

እምነቱ በተከታታይ ቀውሶች እና ድሎች እንደሚያድግ ማወቃችሁ፣ በአገልግሎት መንገድ በመ ራመድ እምነቱንና የሰው ልጆችን ለማገልገል በምታደርጉት ቁርጠኝነት እንዴት ይረዳችኋል?

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_________

## ምዕራፍ 15

ባሃኡላህ በሠንሠለት በሲያህ-ቻል ታስሮ በነበረበት ወቅት ጠላቶቹ ከንጉሡ ዘንድ የሞት ፍርድ ሊያስፈርዱበት በመሯሯጥ ተጠምደው ነበር። ነገር ግን ባሃኡላህ በኅብረተሰቡ፣ በሹማምንቱ ሆነ በተራ ሰዎች ዘንድ እጅግ የተወደደ ስለነበር በቀላሉ የሞት ፍርድ ሊበየንበት አልቻለም ነበር። በንጉሡ ሕይወት ላይ ለደረሰው የግድያ ሙከራ እርሱ በቀጥታ ግንኙነት እንዳለው ማረጋገጫ ያስፈልግ ነበር። ነገር ግን ለዚህ ማረጋገጫ ለማግኘት ጥረት ባደረጉ ቁጥር ይልቁን በነገሩ ፈፅሞ እንዳልነበረበት ይበልጥ እየተረጋጋጠ መጣ። የእርሱን ወንጀለኛነት ለማረጋገጥ ሳይችሉ ሲቀሩ እነዚህ ጨካኝ ጠላቶቹ ምግቡን ሊመርዙበት ወሰኑ። መርዙ በጣም ኃይለኛ ስለነበር የመጀመሪያ ምልክቱ (ጉዳቱ) በቶሎ ስለታወቀ ባሃኡላህ የሰጡትን የተመረዘ ምግብ መብላት አቆመ። በመጨረሻም ባለስልጣናቱ እርሱን ነፃ አድርጎ ከመልቀቅ ሌላ ምንም አማራጭ አልነበራቸውም። ይህንን ለማድረግ የተስማሙት ግን ባሃኡላህ ከተለቀቀ በኋላ ሃገሩን ለቅቆ በግዞት እንዲሄድ በማድረግ ነበር።

ባሃኡላህ በእስር ቤት ለአራት ወራት ቆይቷል። ኃይሉ ሁሉ ተሟጥጦ በጣም ታምሞ ነበር። ፈፅሞ ሰብዓዊነት የሌለበት የእስር ቤቱ ሁኔታ፣ በአንገቱ ዙሪያ የነበረው ወደ 50 ኪ.ግ የሚመዝነው ሠንሠለት እና በመጨረሻም መርዙ ተደማምረው ይህን በመሰለ ጉስቁልናና ድክመት በአልጋ ውስጥ በልዩ ጥበቃ እንዲቆይ አድርጎት ነበር። የሠንሠለቶቹ መገጣጠሚያ በአንገቱ ላይ የከፋ ቁስል ፈጥረውበታል፤ ምንም እንኳ ቁስሉ በጊዜ ሂደት ቢደርቅም ጠባሳው ግን እስከ ህይወቱ ፍፃሜ አብሮት ነበር። በዚህ ሁሉ መሃል ቤተሰቡ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሚያደርጉት አስቸጋሪ ጉዞ መዘጋጀት ነበረባቸው። ባሃኡላህ የስደት ቦታውን እንዲመርጥ ነፃነት ተሰጥቶት ነበር። በዚያን ወቅት በኦቶማን ግዛት ሥር የነበረችውን አሁን የኢራቅ ዋና ከተማ የሆነችውን ባግዳድን መረጠ።

ጉዞው እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 12 1853 ጀምሮ በዚያው ዓመት ኤፕሪል 8 ተጠናቀቀ። ወቅቱ የክረምት ወቅት ነበር። እናም ባሃኡላህና ቤተሰቡ የክረምቱ ቅዝቃዜ እጅግ የከፋ በሆነበት በኢራን ምዕራባዊ ክፍል መጓዝ ነበረባቸው። ነገር ግን የነበራቸው አቅርቦት እጅግ ውሱን ስለነበር በጥቂት ምግብ ራሳቸውን ማብቃቃት ነበረባቸው። ነገር ግን የእነዚህ የአነስተኛ ስብስብ ተጓዦች ጠባቂ እርሱ ፍፁም ኃያሉ አምላክ በመሆኑ፣ በእርሱ ስህተት በሌለው ጥበቃ ባግዳድ በሰላም ደረሱ።

ኢራን ባሃኡላህን ከሃገሯ በማባረርዋ፣ ወደ ትውልድ ስፍራውም ፈፅሞ እንዳይመለስ በማድረጓ፣ ከባሃኡላህ መኖር የተነሳ ልታገኝ ከነበረው ፀጋ ተነፈገች። ኢራቅም በዚህ ምድር ላይ ካሉት ሁሉ የላቀው ድንቅ መኖሪያ ለመሆን በቃች። እጅግ ታዋቂው የባሃኢ ታሪክ ምሁር ስለ ባሃኡላህ ከኢራን መጋዝ እንዲህ ብሏል:–

> "ባሃኡላህ ወደ ድንበሩ ሲደርስ፣ አንድ የታሪክ ወቅት ተገባደደ። የኢራን ሕዝቦች በራሳቸው ላይ ያመጡትን ኪሳራ አውቀውት ይሆንን? በድንቁርና ተውጠው፣ በግትርነት ሰጥመው፣

በጭፍን ጥላቻ ታውረው፣ ራሳቸውን ከፍ ከፍ በሚያደርጉ ሰዎች እየተመሩ፤ በሐሰት ተታለው ይህንን መረዳት አልተቻላቸውም፡፡ እናም የዓለም አዳኝ ከመሃከላቸው ወጥቶ በአንድ ወቅት በሃብታሞ ችና በድኾች፣ በተከበሩት እና በተናቁት፣ በልዑላንና በገበሬዎች ሳይለይ ይወደድ እና ይከበር የነበረው፣ በሁሉም ጊዜያት ምህረትን፣ ፍቅርን፣ ፍትህን እና ችሮታን ሲያጎርፍላቸው የነበረው፣ አሁን በእነዚሁ ሰዎች ተከዳ፡፡ ኢራን የባሃኡላህን የመኖር ቡራኬ አጥታለች፣ ነገር ግን የእርሱ መንፈስ ከዚያም ሆነ ከየትኛውም ምድር ሊለይ ይችላልን?”[33]

1. የባሃኡላህ ጠላቶች የእርሱን የሞት ፍርድ ለምን ለማስበየን ሳይችሉ ቀሩ?________________

 ________________________________________________________________________

 ___

2. የባሃኡላህ ጠላቶች በንጉሡ ሕይወት ላይ ለደረሰው የግድያ ሙከራ እርሱን በቀጥታ ለማገናኘት ያሴሩት ሴራ አልተሳካላቸውም፡፡ ከዚህ በኋላ ምን አደረጉ?

 ______________________________

3. ባሃኡላህ በሲያህ-ቻል ለምን ያህል ወር ታሰረ?

________________________________________

4. ባሃኡላህ ከእስር የተለቀቀው በምን ሁኔታ ነበር?

_____________________________________

5. ባሃኡላህ ለግዞቱ የመረጠው ከተማ ማን ይባላል?

_____________________________________

6. በዚያን ጊዜ፣ የባግዳድ ከተማ የየትኛው ሥርወ-መንግሥት አካል ነበረች? አሁን የየትኛው አገር ዋና ከተማ ነች?

 ________________________________________________________________

7. ባሃኡላህ እና ቤተሰቡ ወደ ባግዳድ ጉዞ የጀመሩት በምን ቀን ነበር? ጉዟቸው ያበቃው፣ ከሦስት ወር በኋላ በየትኛው ቀን ነበር?

 _____________________________________________________

8. የገዞውን ሁኔታ ግለፁ?

__________________________________________________________

_________________________________________________________________________

___

_________________________________________________________________________

___

_________________________________________________________________________

___

## ምዕራፍ 16

ከዚህ ቀጥሎ የሰፈረው በባሃኡላህ የተገለፀው ፀሎት እርሱ በሲያህ-ቻል ያሳለፈውን ስቃይ እንዲሁም ከዚሁ ቀጥሎ በነበሩበት ወራት የደረሰበትን መከራ የጭላንጭል እይታ እንድናገኝ ያስችለ ናል።

> **"አምላኬ፣ ጌታዬ ፍላጎቴ ሆይ! . . . አንተ ይህንን የአቧራ ቅንጣት በታላቅነትህ ፍፁም በሆነ ኃይል ፈጠርከው፤ ማንም አስሮ ሊያቆየው በማይችለው እጅህም ተንከባከብከው . . . ለእርሱም አንደበት ሊያወሳቸው፣ እና የትኛውም የአንተ ፅላቶች በተገቢው መልክ ሊገልጿቸው የማይችሉትን፣ ፈተናዎችንና ችግሮችን እድል ፈንታው አደረግኸው። በሐር ክሳድ እንዲያጌጥ ያስለመድከውን አንገት በመጨረሻ በጠንካራ ሠንሠለቶች ተጠፍሮ እንዲታሰር አደረግኸው፣ በአጥላስ እና በረቀቀ ጉንጉን በተሰሩ ልብሶች የአሸበረቅከውን ገላ በመጨረሻ ለእስር ቤት ዳረግኸው። የአንተ ፍርድ (ድንጋጌ) ስፍር ቁጥር በሌላቸው እግር ብረት አሰረኝ፤ ማንም ሊበጥሳቸው የማይችላቸውን የሠንሠለቶች ሸክም በአንገቴ ላይ አሳረፈ። እነዚህ ጥቃቶች ልክ እንደ ምህረት ዝናብ በላዬ ላይ ሲዘንቡ አያሌ ዓመታት አለፉ . . . የሠንሠለቱ እና የእግር ብረቱ ክብደት እረፍትን የነሱኝ ስንት እና ስንት ሌሊቶችን ናቸው፣ እንዲሁም የሰዎች እጆች እና አንደበቶች ባደረሱብኝ ጥቃት ምክንያት ሰላምንና እርጋታን የተከለከልኩባቸው ምን ያህል የበዙ ቀናት ናቸው! አንተ ሁሉን በሚያቅፈው ምህረትህ ለምድር አራዊት እንኳ ያዘዝክላቸውን ምግብ እና ውኃ፣ በአንድ ወቅት ከዚህ አገልጋይህ ተነፍገውት ነበር፣ ከእምነትህ በሸሹት ላይ እንኳን ሊያደርጉ ያልፈለጉትን በእኔ ላይ አደረሱብኝ። በአንተም ትዕዛዝ በደካማ ሰዎች እና በለግላጋነት እድሜ ባሉ ልጆች ታጅቤ ማንንም ሰው ለመናገር እንኳን በማያስችለው ቅዝቃዜ፣ እንዲሁም ለማንቀሳቀስ እስኪያስቸግር ድረስ በበዛው በረዶ እና ውሽንፍር ፋርስን እንዲለቅ ይህን አገልጋይ በመጨረሻም ድንጋጌህ በማይሻር ሁኔታ ተወሰነ። "[34]**

1. ከላይ ያለውን ፀሎት ምናልባት በቃላችሁ ልታጠኑት ትሹ ይሆናል። ይህም ባይሆን እንኳን

   በተ ደጋጋሚ ስታነቡት ስለባሃኡላህ ስቃይ ብዙ ሐሳቦች በአእምሯችሁ ሊቀረፅ ይችላል።

ከእነዚህ ጥቂቶቹ የትኞቹ ናቸው?

______________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

__________

______________________________________________________________

___

## ምዕራፍ 17

በባግዳድ በከተማው አሮጌ ሠፈር ውስጥ ባሃኡላህ ቤት ተከራየ። እርሱ እዚያ በደረሰበት ተከታይ ወራት ብዛት ያላቸው ባቢዎች ወደ ባግዳድ መጡ። ይህም ሆኖ ግን ብዙዎች በአሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ሰጥመው፣ ግራ ተጋብተው እና መንገዳቸውን ስተው ነበር። የአንዳንዶቹም ተግባር የባብ ተከተይነታቸውን ደረጃ የማይመጥን ነበር። ባሃኡላህም፣ እዚያ የደረሱትን ሁሉ ወሰን በሌለው ፍቅር እንዲሁም ልባቸውን በማንፃት እና መንፈሳቸውን በማነቃቃት እየረዳ ይቀበላቸው ነበር። በእርሱም ተፅዕኖ የባቢ ማህበረሰብ እጣ ፈንታ እንደገና መለወጥ እና ተስፋቸውም መለምለም ጀመረ። ነገር ግን ያሳዝናል አዲስ አደጋ ተጋርጦ ነበር። በዚህ ወቅት የአደጋው ምንጭ ከሌላ ሳይሆን ከዚያው ከማህበረሰቡ ውስጥ ነበር፤ የአሳዛኙ እድል ምክንያት ማንም ሳይሆን የባሃኡላህ የራሱ ወንድም (የአባቱ ልጅ) የባብ ቀጣይ እኔ ነኝ ብሎ እራሱን ያስቀመጠው ሚርዛ ያህያ ነበር።

በእርግጥ ባብ ተተኪውን የማስቀመጥ አስፈላጊነት አልታየውም፣ ምክንያቱም በሁሉም ዘመናት ቃል የተገባለት በቶሎ እንደሚከሰት ያውቅ ነበር። ያደረገው ነገር ቢኖር በባሃኡላህ እና በአንድ ሌላ ደቀ-መዝሙር ምክክር ሚርዛ ያህያህን የክብር ቦታ እንዲኖረው ማድረግ ነበር። ይህ ባሃኡላህ እምነቱን በአንፃራዊ ደህንነት እንዲያራምድ አስችሎታል። ሚርዛ ያህያ በሕይወቱ ሙሉ ከባሃኡላህ ብዙ ፍቅር እና ድጋፍ ቢያገኝም በጣም በምኞት የተሞላ እና ፈሪም ነበር። የባብ ሰማዕትነት እምነቱን ለመካድ እስኪደርስ ድረስ አስደንግጦት ነበር። በማዚንዳራን ተራሮች ላይ ለጥቂት ጊዜ ደርቡሽ በመምሰል ተዘዋውሯል፤ በጣም አሳፋሪ በሆነ ባህሪውም የአካባቢውን ባቢዎች ከእምነቱ አርቋቸዋል። የተለያዩ ማሳሳቻዎችን ሲጠቀም ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ወደ ባግዳድ መጣ። ከዚያም ከባሃኡላህ ለንግድ ሥራ መንቀሳቀሻ የሚሆነውን ገንዘብ ካገኘ በኋላ በከተማው አቅራቢያ በአዲስ ስም (ስሙን ቀይሮ) ይኖር ነበር።

ባሃኡላህ በባብ ተከታዮች ዘንድ ያለው ክብር እና ፍቅር እያደር እየጨመረ መሄድ፣ እንዲሁም በከተማው ባለሥልጣናት ፊት ያለው ሞገስ ከፍ ማለት በሚርዛ ያህያ ላይ በጣም መጥፎ ውጤት አስከተለ። ቅናቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ እና በጣም በመቀጣጠሉ የተነሳ፣ በውስጡ የነበረውን

ጨዋነት እና ክብር አጠፋበት። ከእርሱ በበለጠ እፍረት ከሌለው ተባባሪ ጋር በመሆን፣ ሚርዛ ያህያ በባቢዎች ውስጥ በባሃኡላህ ዓላማ ላይ የጥርጣሬ ዘር መዝራት ጀመረ። በባቢ ማህብረሰብ ላይ አሁንም እንደገና የጥርጣሬ፣ የፍራቻ እና የአጉል ምኞት ደመናዎች ያንዣብቡ ጀመር። ለአጭር ጊዜ የነበረው መረጋጋት እና ሰላም እየተሟጠጠ፣ የባሃኡላህ ስቃይም ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መጣ።

እ.ኤ.አ ኤፕሪል 10 ቀን 1854 ጠዋት ላይ የባሃኡላህ ቤተሰቦች ከእንቅልፋቸው ሲነቁ፣ ባሃኡላህ ከአካባቢው ተለይቶ መሄዱን አወቁ። ከተማውን ለቅቆ የሄደው ዓላማውን እና መድረሻውን ለማንም ሳይናገር ነበር። የሚርዛ ያህያ ድርጊቶች ወዴት እንደሚያመሩ ስለተመለከተ፣ ባሃኡላህ ከባግዳድ ሰሜናዊ ምስራቅ ወደሚገኙት የኩርዲስታን ተራሮች ላይ ተገልሎ ለመቆየት መረጠ። እራሱ በኂላ እንደተናገረው፤ **"የመገላላችን ብቸኛው ምክንያት በታማኞች መካከል የፀብ ምክንያት፣ ለአጋሮቻችን የመበጣበጥ መነሾ፣ ለማንኛውም ነፍስ የመጎዳት ምክንያት፣ ወይም ለየትኛውም ልብ የሐዘን መነሾ ላለመሆን ነበር።"**[35]

ከሱሌይማኒህ ከተማ ወጣ ብሎ በዱር፣ ባሃኡላህ ብቻውን ከአምላክ ጋር በመቋረብ ኖረ። ጥቂት ምግብ ብቻም ይመገብ ነበር። አንዳንድ ጊዜ በአካባቢው ከሚገኙ እረኞች ወተት ያገኝ ነበር፣ እንዲሁም አልፎ አልፎ በሕይወት ለመቆየት የሚያስፈልገውን አነስተኛ ነገር ለማግኘት ወደ ከተማ ይሄድ ነበር። ይህም ሆኖ ግን ለቅፅበት ከአካባቢው ሰዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የባሃኡላህን ታላቅነት ሊሰወርባቸው አልቻለም። የነበረው ፍቅር እና ጥበብ የሱሌይማኒህን ነዋሪዎችን መሳብ ጀመረ፣ የስሙም ገናናነት በአቅራቢያው በሚገኙት አካባቢዎች መሠራጨት ቀጠለ። የአንድ እጅግ ድንቅ ጥበብ እና አንደበተ-ርዕቱነት ያለው ሰው በዚያ የኩርዲስታን ክልል የመኖር ዜና በመጨረሻ በባግዳድ ተሰማ። የባሃኡላህ ቤተሰብም ይህን የመሰለ ሰው ከባሃኡላህ በስተቀር ሌላ እንደማይሆን ስለተገነዘቡ አንድ ታማኝ የሆነ ምዕመን በመላክ እንዲመለስ ለመኑት። ባሃኡላህ ጥያቄያቸውን በመቀበል በገዛ ፈቃዱ ያደረገውን የሁለት ዓመት መገለል አቋረጠ።

1. የባሃኡላህን ባግዳድ መግባት ተከትለው ወደ ከተማዋ የመጡት ባቢዎች በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ ነበሩ?

   ______________________________________________________________________

2. በእንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ለምን ወደቁ?

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

   _____

3. ከባሃኡላህ ተፅዕኖ ፈጣሪነት የተነሳ በባቢ ኅብረተሰብ ውስጥ ምን እየተከሰተ መጣ?

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

   _____

4. ባብ እርሱን የሚተካ መርጦ ነበርን? ለምን?

_______________________________________________

5. ባብ በኅብረተሰቡ ውስጥ የክብር ቦታ እንዲኖረው የመረጠው ማንን ነበር?

____________________

6. ሚርዛ ያህያ ከባሃኡላህ ጋር የነበረው ዝምድና ምን ነበር?

__________________________________

7. የሚርዛ ያህያን ባህርይ ይግለፁ? _______________________________________________________

8. ከባብ ሰማዕትነት በኋላ ሚርዛ ያህያ ምን አደረገ?

_____________________________________________________________________________________

_____________________________________________________________________________________

_____

9. የከተማው መኳንንትን ጨምሮ በባብ ተከታዮች ለባሃኡላህ በሚያሳዩት ማክበር እና ፍቅር እያደገ መሄድ የተነሳ፣ በሚርዛ ያህያ ላይ ምንን አስከተለ?

__________________________________________

10. የሚርዛ ያህያ ድርጊት ወዴት እያመራ መሆኑን ሲያውቅ ባሃኡላህ ምን አደረገ?

________________

11. ባሃኡላህ ወደየት አካባቢ ተገልሎ ሄደ?

__________________________________________________

12. ባሃኡላህ እንደተናገረው የእርሱ መገለል ምክንያት በታማኞች መካከል

____________________________ ምክንያት፣ ለአጋሮቹ ________________________________

መነሾ፣ ለማንኛውም ነፍስ _______________________ምክንያት፣ ወይም ለየትኛውም ልብ

_____________________________________መነሾ ላለመሆን ነበር።

13. በኩርዲስታን ዱር በነበረ ጊዜ ባሃኡላህ ምን አደረገ? ____________________________________

14. ባሃኡሳህ ከባግዳድ ወጥቶ የቆየው ለምን ያህል ጊዜ ነው? ___________________________

15. እንዲመለስ ያደረጉት ሁኔታዎች ምንድን ነበሩ?

_________________________________________________________________________

_________________________________________________________________________

_____

## ምዕራፍ 18

እያንዳንዱ የአምላክ ክስተት ከተከታዮቹ ጋር ቃል-ኪዳን ይገባል። የባብ ተከታዮች ከባብ ጋር እርሱን አምላክ የሚከስተውን ለመፈለግ እና ለመቀበል እንዲሁም ትዕዛዙን አክባሪዎች በመሆን ለመኖር ቃል ገብተው ነበር። ምንም እንኳ ባሃኡላህ፣ በባብ ቃል የተገባለት መሆኑን ባይገልፅላቸውም ቀናት ባለፉ ቁጥር ታላቅነቱ ይበልጥ ግልፅ እየሆነ በመምጣቱ ጥቂቶች ደረጃውን መረዳት ጀምረው ነበር። ለባሃኡላህ ግርማ እና ክብር እውር ያልሆነው ሚርዛ ያህያ፣ በባቢዎች መካከል ጥርጣሬ መዝራቱን አላቋረጠም። በቀጣዮቹ ዓመታት፣ በባሃኡላህ ላይ የሚያውጠነጥነው ደባ ከቀን ወደ ቀን በመጠኑ እያደገ በመምጣት፣ በመጨረሻም የባብን ቃል-ኪዳን በግልፅ እስከማፈርስ አድርሶታል። የሚጠብቃቸውን የብጥብጥ እና የፈተና ጊዜዎች አስመልክቶ ባሃኡላህ የእርሱን ታማኝ ወዳጆች እንዲህ ሲል አስጠንቅቋ ቸዋል:–

> **"የፈተና ቀናት አሁን መጥተዋል። የጠብ እና የፈተና ውቅያኖሶች እየሞገዱ ናቸው፣ የጥርጣሬ ሠንደቆችም፣ በእያንዳንዱ ቅርቃር እና ጥጋ ጥግ ተደብቀው፣ ክህደትን በማነሳሳት ሰዎችን ወደጥፋት እየመሩ ናቸው . . . በመካከላችሁ ጥርጣሬን በሚፈጥሩ የአሉታ ወታደሮች ድምፅ አትረበሹ፣ በሁሉም ግልፀቶች ይህን የመሰለ ተቃውሞ ተነስቶ ነበርና እርሱ እውነት ከሆነው ቸል በማለት ራሳችሁን አታግልሉ። ምንም እንኳ የፀብ ቆስቋሾች ቢፀየፉትም፣ ነገር ግን፣ አምላክ፣ የእርሱን እምነት ይመሠርታል፣ ብርሐኑንም ይከስታል . . . የአምላክን እምነት በየ ዕለቱ ጠብቁ . . . ሁሉም በመዳፉ ስር ምርኮኞቹ ናቸው። ለማንም የሚሸሸበት ቦታ የለም። የአምላክን ሃይማኖት ማንም የራሱን ምኞት የሚያረካበት በቀላሉ የሚታይ ነገር አድርጋችሁ አታስቡ። በተለያዩ አኗኗሮች፣ በአሁኑ ጊዜ፣ ብዙ ነፍሶች ይህንኑ እሳቤ ያራምዳሉ። እያዳንዳ ቸው የሚንከታኮቱበት እና የሚጠፉበት፣ ይህ ብቻም አይደለም የአቧራው ያክል እንኳን ምንም የሌለ እና ምንም የማይታወስ ነገር የሚሆኑበት ጊዜ እየተቃረበ ነው።"[36]**

1. ከዚህ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሟሉ:–

   ሀ. ባሃኡላህ ለእርሱ ወዳጆች በመካከላችሁ ___________________________________

   ___________________________________________________________________

   _፣ በማለት ነግሯቸዋል።

   ለ. ራሳቸውን ከ_______________________________________እንዳያገለሉ አስጠንቅቋቸዋል።

ሐ. ምንም እንኳ የፀብ ቆስቋሾች ቢፀየፉትም፣ ነገር ግን፣ አምላክ፣

__________________________ ይመሠርታል፣ __________________________

እንደሚገልፅ አረጋግጦላቸዋል።

መ. የአምላክን ሃይማኖት ማንም የራሱን __________________________________

የሚያረካበት ________________________________________ አድርገው ወዳጆች

ማሰብ የለባቸውም።

ሠ. እነዚያ እምነቱን የሚቃወሙት ሁሉ ____________________________ እና

______________________________፣ ይህ ብቻም አይደለም የአቧራው ያክል እንኳን

________________________________________________________ ነገር የሚሆኑበት

ጊዜ እየተቃረበ ነው።

2. ባሃኡላህ እነዚያ ጥርጣሬን ለመዝራት የሚፈልጉትን “የአሉታ ወታደሮች” በማለት ይጠራቸዋል፣ የሚቃወሙት ምንን ነው?

## ምዕራፍ 19

ባሃኡላህ ባልነበረበት የሁለት ዓመት ጊዜ የእምነቱ እጣ ፈንታ ከዚህ በፊት በታሪኩ ውስጥ ባልታየ ሁኔታ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። እንደተጠበቀው ሁሉ ሚርዛ ያህያ በባግዳድ የነበረውን አናሳ ማህበረሰብ ለመምራት እንዳልቻለ አሳይቶ ነበር። በተለያዩ ቦታዎች ብዙ ባቢዎች የባብን በዋጋ የማይተመን እምነት፣ እፍረት ባላበሱ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተጠምደው ነበር። ስለዚህ ማህበረሰቡን እንደገና የማነቃቃቱን ሥራ ባሃኡላህ ተያያዘው። እ.ኤ.አ ማርች ወር 1856 ወደ ባግዳድ መመለሱ ለአማኞች ተነገራቸው። እውነትን ለሚናፍቁትም ሁሉ በሩ ክፍት ሆነ። ከቤተሰቡ ጋር ይኖርበት የነበረው አነስተኛ መኖሪያ ቤት እውነት ፈላጊዎች እና ጎብኚዎች የሚገናኙበት ማዕከል ሆነ። እርሱ ፊት የቀረበ እያንዳንዱ ሰው በጥዑምና አፍቃሪ ቃላቶቹ ኃይል ይለወጥ ነበር። እርሱ በሚኖርበት አቅራቢያ የመኖርን ፀጋ ያገኙት በገነት ውስጥ እንደሆኑ ይሰማቸው ነበር። ከዚህ ዓለም ነገሮች ፈፅመው የተላቀቁ አዲስ ፍጡሮች ሆኑ። የባሃኢን ዘመን የመጀመሪያዎቹን ዓመታት ታሪክ የፃፈው ታላቁ ታሪክ ፀሐፊ ናቢል የእነዚያን ነፍሶች ሁኔታ እንዲህ በማለት ነበር የገለፃቸው:–

> “ብዙ ምሽቶች ከአስር ያላነሱ ሰዎች ከአንድ ሳንቲም የማይበልጥ ዋጋ በሚያወጣ ቴምር ያድሩ ነበር። በቤቶቻቸው የሚገኙት ጫማዎች፣ ካባዎች፣ ወይም መጎናፀፊያዎች የማን ንብረት እንደ ሆኑ የሚያውቅ ሰው አልነበረም። ከእነርሱ መካከል ማናቸውም ወደ ገበያ ሲሄድ፣ ያደረግሁት ጫማ የራሴ ነው ለማለት ይችል ነበር፤ እንዲሁም እያንዳንዱ ባሃኡላህ ፊት የቀረበ የለበሰውን ካባ እና መጎናፀፊያ የራሱ እንደሆነ ማረጋገጥ አይችልም ነበር። ተወዳጃቸውን ከማፍቀር እና ከማምለክ የተነሳ፣ ስማቸውን እስከመርሳት እና ልባቸውም

> ከሌሎች ነገሮች ሁሉ የፀዳ ሆኖ ነበር። . . . አቤት የእነኛ ቀናት ደስታና የእነኛ ሰዓታት ግርምት እንዴት ያለ ነበር?"[37]

ባሃኡላህ ከሱለይማኒህ ከተመለሰ በኋላ በባግዳድ ሰባት ዓመታት ቆየ። በዚህ ወቅት ደረጃውን ማለትም የዚህ ዘመን የአምላክ ክስተት እርሱ ራሱ መሆኑን አልገለፀም ነበር። ሆኖም መለኮታዊ ፍቅር ከእርሱ በመጉረፉ ምክንያት ያልተነኩ ንፁህ ልቦች አልነበሩም። በንግግሮቹ፣ በጽሑፎቹ እና በፀሎቶቹ ለብዙ ዓመታት ያለእረኛ ሲባዝኑ የነበሩትን የባቢዎች ባህርይ ለወጠ። እነዚህ ዓመታት 'የእርግጠኝነት መፅሐፉ'ን የገለፀባቸው ሲሆኑ፣ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ የአለፉት ዘመናት ሰው ሰራሽ ቀኖናዎች መሠረቶችን በሚንድ መንገድ የአምላክን ግልፀት ምንነት በማያሳስት ቋንቋ አብራርቷል። ሁላችንም የመንፈሳዊ እድገት መመሪያ ነው ብለን የምናወድሰውን 'ኅቡዓተ ቃላት' በጢግሮስ ወንዝ አካባቢ እየተዘዋወረ በተመስጦ የገለፀውም በዚሁ ወቅት ነበር። ይገልፃቸው የነበሩት ጥቅሶች ከብዕሩ ይንቆርቆሩ የነበሩበት ፍጥነት በጣም የሚያስገርም (የሚደንቅ) ነበር። ያንን እጅግ ኃይል የተሞላ ወቅት እርሱ ራሱ እንዲህ በማለት ገልፆት ነበር:–

> **" . . . ጥቅሶቻችንን በአምላክ እርዳታ እና በመለኮታዊ ፀጋውንና ምህረቱ እንደ ዶፍ ዝናብ አወረድን፣ ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍሎችም ላክናቸው። ጥበብ በተሞሉ ምክሮቻችንና ፍቅር በተ ሞሉ ተግሳፆቻችን ሰዎችን ሁሉ፣ በተለይም እነኝህን ሰዎች በጥብቅ መከርን፤ በአመፅ፣ በጥል፣ በጭቅጭቅ እና በግጭትም እንዳይጠመዱ ከለከልናቸው። በዚህ ምክንያትና በአምላክ ፀጋ፣ አመ ፀኝነትና ስህተት ወደ ቅድስናና ግንዛቤ ተለወጡ፤ የጦር መሳሪያዎችም ወደ ሰላም መሳሪያዎች ተቀየሩ።"**[38]

ባሃኡላህ በባግዳድ የኖረባቸው ሰባት ዓመታት አስደናቂ ድሎች የተገኙበት ወቅት ነበር። ስለሆነም የበለጠ ድል የሚከተለው ችግር (ውድቀት) ቶሎ ወይም ዘግይቶ እንደሚከሰት ይጠበቅ ነበር። እያደገ የሄደው የባሃኡላህ ዝና በእምነቱ ጠላቶች ዘንድም ሳይታወቅ አልቀረም። ከእነዚህ ጠላቶች መካከል ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲያደርግ የነበረው አንድ ሼይክ ሲሆን፣ ይህ ሼይክ የፋርስ እና የኦቶማንን መንግሥታት እንዲሁም ካህናትን እንዲነሱበት ለማሳመን ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም።

ለዓመታት፣ የሼይኩ ጥረቶች በባሃኡላህ ቃላት እና ሥራዎች ጥበብ፣ ጨዋነት እና ታላቅነት ሊመክኑ ችለዋል። በክልሉ በአንድ ወቅት ይህ ሼይክ ዋና ዋና ቀሣውስቱን ጠርቶ ሙሉ በሙሉ በአንድ ድምፅ ተስማምተው ለማስውገዝ ዓላማ ነበረው። እምነቱን ከሥሩ ለማጥፋት በባግዳድ ይኖሩ በነበሩት ጥቂት ስደተኞች(ባቢዎች) ላይ ጥቃት ለመሰንዘር ሁሉም በመሰባሰብ ተዘጋጅተው ነበር። ሆኖም፣ ያልጠበቁት ነገር ተከሰተ፣ አንድ በደረጃው ከሁላቸውም ይበልጥ የነበረ እንዲሁም በቅድስናው እና በፍትሕ አድራጊነቱ የታወቀው በመካከላቸው ያለ ሰው በባቢዎቹ ላይ ለመፍረድ አሻፈረኝ አለ። እርሱ እስከሚያውቀው ድረስ የባቢ ማኅበረሰብ ሊያስፈርድባቸው የሚያስችል ነገር ያልሠሩ መሆናቸውን ከተናገረ በኋላ ስብሰባውን ጥሎ ሄደ።

የሼይኩ መጀመሪያው እቅዱ ሳይሳካ በመቅረቱ ተሰብሳቢዎቹ ጥያቄዎችን አስይዘው አንድ የተማረ ሰው ወደ ባሃኡላህ በመላክ የእርሱን እውቀት ለመፈተሽ ወሰኑ። ባሃኡላህም ሁሉንም ጥያቄ ዎች መልሰ፣ መልዕክተኛው በተሰብሳቢዎቹ ስም የባሃኡላህ እውቀት ሰፊ እና ተወዳዳሪ የሌለው መሆኑን መሰከረ። ነገር ግን የመልእክቱ እውነተኝነት ለሁሉም አጥጋቢ ይሆን ዘንድ ተዓምር እንዲሠራ ባሃኡላህን ጠየቀው። ባሃኡላህም እንዲህ ሲል መለሰለት:– "ምንም እንኳን ይህን ለመጠየቅ መብት የሌላችሁ ቢሆንም ይህን ጥያቄ ፈቅጄ ተቀብዬአለሁ፤ አምላክ ፍጡሮቹን ይፈትናል እንጂ ፍጡሮቹ አም ላክን መፈተን አይገባቸውም።"[39] ሆኖም ካህናቱ አንድ ተዓምር መምረጥ እና ያንን መፃፍ እንዳለባቸው እና ተዓምሩ ከተሠራ በኋላ ከእንግዲህ ስለ እርሱ ምንም ጥርጣሬ ሳያሳድሩ ማንነቱን አውቀው የእም ነቱን እውነተኝነት መቀበል እንዳለባቸው ለመልዕክተኛው ነገረው። ይህንንም ፅሑፍ በማህተም አትመው ወደ እርሱ ማምጣት እንዳለባቸው አሳወቀው።

ይህ ግልፅ እና ተፈታታኝ መልስ መልዕክተኛውን እጅግ ነካው። ወዲያው ብድግ ብሎ የባሃኡላ ህን ጉልበት ከሳመ በኋላ ሔደ። የባሃኡላህን መልዕክትም ለካህናቱ ስብስብ ሰጠ። ለሦስት ቀናት ተከራከ ሩበት። ነገር ግን ውሳኔ ላይ መድረስ አልቻሉም። በመጨረሻም ነገሩን እርግፍ አድርገው ከመተው ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም።

ነገር ግን እነኝህ ጨካኝ ጠላቶች በባሃኡላህ ላይ መዶለታቸውን አልተውም። በመጨረሻም ጥረ ታቸው ፍሬ አፍርቶ ቀጣዩ ችግር (ውድቀት) እስከተከሰተበት እ.ኤ.አ ፀደይ ወቅት 1863 ድረስ ተንኮል መሸረባቸውን እና ዓለማውን በተሳሳተ መልኩ ለባለስልጣናቱ ማቅረብ ቀጠሉ።

1. ባሃኡላህ ወደ ባግዳድ ሲመለስ የባቢ ማኅበረሰብ በምን ሁኔታ ላይ ነበር? __________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

______

2. ሚርዛ ያህያ የባቢን ማኅበረሰብ መምራት እንደሚችል አሳይቶ ነበርን?

___________________

3. የባሃኡላህ ወደ ባግዳድ መመለስ በባቢዎች ላይ ምን ውጤት አስከተለ?

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

_____

4. ከናቢል ትረካ በመነሳት፣ በባሃኡላህ አቅራቢያ ስለነበሩ ሰዎች ሁኔታ የገለፀውን በጥቂቱ ያብራሩ።

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

___________

5. ባሃኡላህ ከሱሌይማኒህ ከተመለሰ በኋላ በባግዳድ ስንት ዓመት ቆየ? ______________________

6. ባሃኡላህ ባግዳድ በቆየባቸው ሰባት ዓመታት ከገለፃቸው ሥራዎቹ (መፃሕፍት) ሁለቱን ይጥቀሱ።

___________________________________________________________________

___

7. የእርግጠኝነት መፅሐፉ ዋናው ጭብጥ ምንድነው?

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

_____

8. በኀቡዓተ ቃላት የተነሱት ምን ምን ጉዳዮች ናቸው? ________________________________

9. ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች ያሟሉ:–

ሀ. ጥቅሶቻችንን በአምላክ ___________________________ እና __________________________ና _____________________________ገልፀን፣ ባሃኡላህ ይነግረናል።

ለ. እነኝህን ጥቅሶች ወደ __________________________________________ላካቸው።

ሐ. በእነኝህ ጥቅሶች____________________________________________ሰዎችን ሁሉ___________________________።

መ. በ ____________________________፣ በ ______________________________፣ በ__________________________ እና በ ____________________________ ከለከላቸው።

ሠ. በዚህ ምክንያት እና በአምላክ ፀጋ ________________________________________ እና ___________________ ተለወጡ፣_____________________________ ወደ ____________________________ተቀየሩ።

10. እያደገ የመጣው የባሃኡላህ ዝና በእምነቱ ጠላቶች ላይ ምን ውጤት አስከተለ?

___________________________________________________________________

____________________________________________________________

____

11. "በአንድ ድምፅ ማውገዝ" የሚለው ሐረግ ምን ማለት ነው? ______________________

12. ተሰብስበው የነበሩትን ካህናት እና ወደ ባግዳድ የላኩትን መልዕክተኛቸውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይተርኩ:–

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

______

## ምዕራፍ 20

እምነቱን በሚያጠኑበት ጊዜ የእርግጠኝነትን መፅሐፍ (ኪታቢ ኢቃንን) ማንበብዎ አይቀርም፣ በዚህ መፅሐፍ የሚገኙትን ብዛት ያላቸውን ጭብጦች ጥልቅ ትርጉም ላይም ያሰላስሉ። በእርግጥ እስካሁን ድረስ ለ"ኅቡዓተ ቃላት" አዲስ አይደሉም። ይህ መፅሐፍ በሕይወትዎ ሁሉ የማይለይዎት ጓደኛ ይሆናል፣ በውስጡ የሚገኘውን መለኮታዊ መመሪያም ለመንፈሳዊ እድገትዎ ታላቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። እዚህ ላይ እነኝህ ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ሁለት መፃሕፍት የተገለፁበትን ባሃኡላህ በባግዳድ የኖረበትን ወቅት ሲያሰላስሉ የሁለቱን መፃሕፍት መግቢያ ምንባቦች በቃልዎ ለመያዝ ይፈልጉ ይሆናል። የእርግጠኝነት መፅሐፍ እንዲህ ሲል ይጀምራል:–

> **"ከዚያ በሰማይ ውስጥ እና በምድር ላይ ካለው ሁሉ ካልተላቀቀ በስተቀር ማንም ሰው የእው ነተኛ ግንዛቤ ውቅያኖስ ዳርቻዎችን ሊደርስባቸው አይችልም። እናንተ የዓለም ሕዝቦች ሆይ! እግዚአብሔር ለእናንተ የወሰነውን ደረጃ በደስታ ትገናፀፏቸው እና በችሮታው ግልፀቶች መሠ ረት በባያን ሰማይ ውስጥ ከፍ የተደረገው ድንኳን ውስጥ ትገቡ ዘንድ ነፍሶቻችሁን ቀድሱ።"**[40]

የ "ኅቡዓተ ቃላት" የመግቢያ ምንባብ ደግሞ እንዲህ ይነበባል:–

> **"ይህ ከክብር ግዛት የወረደው በሥልጣንና በኃይል አንደበት የተነገረው፣ ለአለፉትም ነብያት የተገለፀው ነው። ለአምላክ ቃልኪዳን በታማኝነት ይፀኑ ዘንድ፣ በሕይወታቸው የእርሱን አደራ ያሟሉ ዘንድ በመንፈስ ግዛትም የመለኮታዊ ባህርይን እንቁ ያገኙ ዘንድ፣ ለፃድቃን የፀጋ ምልክት እንዲሆን፣ እኛ ውስጣዊ ፍሬ ነገሩን ወስደን በምጥንነት ልብስ አለበስነው።"**[41]

## ምዕራፍ 21

በባግዳድ በኖረባቸው የመጨረሻዎቹ ቀናት ወደፊት ስለሚመጡት ፈተናዎች እና ችግሮች ባሃኡላህ አልፎ አልፎ ማመላከት እና መናገር ጀምሮ ነበር። አንድ ጊዜ ለወዳጆቹ የነገራቸው ሕልም እጅግ አስጨነቃቸው። በአንድ ፅላት ላይ እንዲህ በማለት ፅፎ ነበር። **"ነብያት እና መልእክተኞች በዙሪያዬ ተሰብስበው እየተንስቀሰቁ፣ ሲያነቡ አየሁ። በመገረም ምክንያቱን ጠየቅኋቸው፣ በዚህን ጊዜ ለቅሷቸውና ማንባታቸው የበለጠ ጨምሮ እንዲህም አሉኝ፦ 'አንተ እጅግ ታላቅ ምስጢር፣ አንተ የዘለዓለማዊ ሕይወት ድንኳን ሆይ, የምናለቅሰው ለአንተ ነው!' በጣም ከማልቀሳቸው የተነሳ እኔም አብሬአቸው አለቀስሁ፣ በዚህን ጊዜ የሰማዩ ሠራዊት እንዲህ አሉኝ፦ '. . . ብዙ ሳይቆይ ማንም ነብይ ያላየውን በገዛ ራስህ ዓይን ታያለህ። ታገስ፣ ታገስ።' . . . ጎህ እስኪቀድ ድረስ ሌሊቱን ሁሉ እኔን ማናገራቸውን አላቋረጡም።"**[42]

እ.ኤ.አ በ1863፣ በመጀመሪያዎቹ የፀደይ ቀናት የ"ቅዱሱ መርከበኛ" ፅላትን ገለፀ፣ በዚህ ፅላት ምስጢር በተላበሰ ቋንቋ፣ ወደፊት የሚመጡትን ሁኔታዎች ተንብዮ ነበር፣ ስለ ክህደትና ስለመለያየትም ተናግሮ ነበር። ይህ ፅላት ወዳጆች በፊቱ ተሰባስበው ባሉበት ተነበበላቸው። ባሃኡላህ ሊለያቸው እንደሆነ በመረዳታቸው በልቦቻቸው ውስጥ የሐዘን ውቅያኖስ ተንሰራፋ። በዚያኑ ዕለት የባግዳዱን አገረ-ገዢ እንዲያነጋግር የሚጠይቅ መልእክት ባሃኡላህ ከአንድ መልዕክተኛ ተቀበለ። በሚቀጥለው ቀን በጨዋ ቋንቋ የተፃፈ እና ባሃኡላህን ወደ ኦቶማን ግዛት ዋና ከተማ ቁስጥንጥንያ እንዲጓዝ የሚጋብዘውን ደብዳቤ ከኦቶማን ግዛት ጠቅላይ ሚኒስትር ለአገረ-ገዢው የተፃፈው ደብዳቤ ለባሃኡላህ ቀረበለት። ለደህንነቱ ሲባልም ፈረሰኞች እንዲያጅቡት ታዘዘ። ባሃኡላህ ጥያቄውን ወዲያውኑ ተቀበለ፣ ነገር ግን ለጉዞው መንግስት ያቀረበውን ገንዘብ ከመቀበል ተቆጠበ። የአገረ-ገዢው ተወካይ ግን ገንዘቡን ካልተቀበለ ባለሥልጣኖቹ እንደሚከፉ በመናገር እንዲቀበል አጥብቆ ለመነው። በመጨረሻም ያንን ብዙ ገንዘብ ወስዶ ወዲያውኑ በከተማው ለሚገኙ ድኾች አከፋፈላቸው።

ባሃኡላህ ከባግዳድ የመጋዙ ዜና የባቢን ማኅበረሰብ አናወጠው። እነዚያ ልቦቻቸው ከእርሱ ብሩህ ቅርበት ጋር አቆራኝተው ያሉት ፅኑ አማኞች፣ በሐዘን ተዋጡ። በመጀመሪያ ለመተኛት ወይም ለመብላት የቻለ አንድም አልነበረም። ሆኖም ቀስ በቀስ በባሃኡላህ ደግነት እና ርህራሄ በተሞሉ ቃላት ተረጋግተው አብዛኞቹም በሚቀጥለው ግዞቱም አብረውት የመሄድን ፀጋ አለመካፈላቸውን ተቀበሉት። የፍቅሩ ምልክት ይሆን ዘንድ በከተማው ለሚኖሩ ለእያንዳንዳቸው ወዳጆች፣ ወንድ፣ ሴት፣እንዲሁም ልጅ በራሱ እጅ ፅሑፍ አንዳንድ ፅላት (ፅሁፍ) ፃፈላቸው።

በባግዳድ አቅራቢያ አንድ በፅጌረዳዎች የተሞላው አትክልት ቦታ ነበር፣ ፅጌረዳ ደግሞ የባሃኡላህ ተወዳጅ አበባ ናት። እ.ኤ.አ ኤፕሪል 22 ቀን 1863 በጠዋት ከከተማው ወጥቶ ወደዚህ የአትክልት ስፍራ ገባ። አማኞች እና ብዛት ያላቸው የባግዳድ ነዋሪዎች እጅግ አዘኑ። በባሃኡላህ ፍቅር የተሞላ እንክብካቤ እንደገና ሙሉ ለሙሉ ሕይወት የዘራው የባቢ ማኅበረሰብ ሌላ እክል አጋጠመው። ብቸኛ ተስፋው የሆነው ብዙሐኑ ተከታዮች ከሌሉበት እጅግ ወደ ራቀ ቦታ ሲጋዝ የዚህ ጨቅላ እምነት የወደ ፊት እድል ምን ሊሆን ይችላል? ሊሰናበቱት የተሰበሰቡትን እና በሐዘን የተቆራመዱትን ባቢዎች የጠበ ቃቸው መልስ እጅግ የላቀ ነበር። ባሃኡላህ እውነተኛ ደረጃውን የሸፈኑትን መጋረጃዎች ቀደዳቸው፣ በሁሉም ዘመናት ቃል የተገባለትም እርሱ ራሱ መሆኑን በግልፅ አወጀ።

ባሃኡላህ ወደ ቁስጥንጢኒያ ከመሄዱ በፊት፣ አሁን የ"ሪዝቫን አትክልት" ስፍራ በመባል በሚ ታወቀው ቦታ ለአስራ ሁለት ቀናት ተቀመጠ። ከብዙሐኑ አማኞች እርሱን ለመለየት እምነቱንም ለማ ጥፋት ጠላቶቹ ሞከሩ። ሆኖም አምላክ ሽኝቱን የከፍተኛ ደስታ ምክንያት አደረገው። ተልዕኮውን ማወጁ፣ በተወዳጆቹ ነፍስ ውስጥ አዲስ ሕይወትን ፈጠረ። ባብ ያዘጋጃቸው ለዚህ

የቀናት ሁሉ ቀን ለሆ ነው ነበር። ባሃኡላህ እራሱ እንደተናገረው:– **“የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ በመንፃት ባህር ውስጥ ሰጥመው ነበር”**[43]

በሪዝቫን የአትክልት ስፍራ ቦታ ሊጠይቁት ከሚጎርፉ ከነበሩት ብዛት ካለቸው ሰዎች ጋር ባሃኡላህ ስላደረጋቸው ንግግሮች በዝርዝር ብዙም የሚታወቅ ነገር የለም። የሚከተለው በታሪክ ምሁሩ ናቢል ቃላት የተጻፈው፣ የእነኛን ቀናት ክብር በጨረፍታ ያሳያሉ:–

> “ጎህ ከመቀደዱ በፊት አትክልተኞቹ በአትክልት ስፍራው በአራት መንገዶች ዳር ዳር ያሉትን የፅጌረዳ አበቦች ይሰበስቡ እና በተባረከው ድንኳን ወለል መካከል ይከምሩት ነበር። ክምሩ በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ ወዳጆቹ የጠዋት ሻያቸውን ለመጠጣት እፊቱ ሲሰበሰቡ ለመተያየት አይችሉም ነበር። እነኝህ ሁሉ ጽጌረዳዎች፣ በባሃኡላህ በራሱ እጅ በየጠዋቱ በሚሸኛቸው ሰዎች አማካይነት፣ በከተማው ላሉ የአረብ እና የፋርስ ወዳጆቹ እንደርሱ በመሆን እንዲያደርሱ በአደራ ይሰጥ ነበር። . . . ጨረቃ ሙሉ በምትሆንበት በዘጠነኛው አንድ ሌሊት፣ በድንኳኑ አጠገብ ጥበቃ ከሚያደርጉት አንዱ ነበርኩ። እኩለ ሌሊት ሲቃረብ ከድንኳኑ ሲወጣ አየሁት። ከወዳጆቹ ጥቂቶች የተኙበትን ቦታ አለፈ እና በጨረቃ በበራው እና በአበቦች በተከበበው የአትክልት ሥፍራ ውስጥ መዘዋወር ጀመረ። ከየአቅጣጫው የሚሰማው የዘማሪ ወፎች ድምፅ በጣም ከፍተኛ ስለነበር የእርሱን ድምፁን ሊሰሙ የሚችሉት አጠገቡ የነበሩት ብቻ ነበሩ። መራመዱን ቀጠለ። በኋላም ከመንገዶቹ በአንዱ መካከል ቆም አለና እንዲህ አለ:– **‘እነኝህን ዘማሪ ወፎችን ተመልከቱ። ለእነኝህ ጽጌረዳዎች ያላቸውን ፍቅር እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ ከምሽት እስከ ጎህ መቅደድ ያለ እንቅልፍ ጥዑመ ዝማሬያቸውን ያሰማሉ፣ ከሚያፈቅሩትም ነገር ጋር በሚነድ ስሜት ይቋረባሉ። ስለዚህ እንዴት ነው በተወዳጁ፣ በፅጌረዳ የሚመስል ውበት ነደናል የሚሉ ለመተኛት የሚመርጡት?’** ለሦስት ተከታታይ ሌሊቶች የተባረከውን ድንኳኑን ዙሪያውን እጠብቅ ነበር። ይተኛበት ወደ ነበረው መደብ በተጠጋሁ ቁጥር እንቅልፍ እንዳልወሰደው ተመለከትሁ። እንዲሁም በየቀኑ ከጠዋት እስከ ምሽት ከባግዳድ ይጎርፉ ከነበሩ ጎብኚዎች ጋር ሳያቋርጥ ሲነጋገር አየው ነበር። በሚናገራቸው ቃላት አንድም የመታቀብ ሁኔታን አላየሁበ ትም።”[44]

በዛሬ ጊዜ፣ የባሃኡላህን ግልፀት ተልዕኮ አስመልክቶ የሪዝቫን ክብረ በዓል በየዓመቱ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ይከበራል። ለአስራሁለት ቀናት የሚዘልቀው ይህ ዓመት በዓል፣ የተቀደሰ እና ከባሃኢ በዓ ላት እጅግ ታላቁ እና ዋነኛው ነው።

1. የባግዳድ ቆይታውን ሊጨርስ አካባቢ ባሃኡላህ ያየውን ህልም በራስዎ አባባል ይተርኩ?

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

2. የሕልሙ ትርጉም ምን ነበር?

3. የ'ቅዱስ መርከበኛ' ፅላትን ባሃኡላህ የገለፀው መቼ ነበር?

4. የ'ቅዱስ መርከበኛ' ፅላት ምንን ይተነብያል?

5. ፅላቱ ለወዳጆቹ በተነበበት ዕለት የመንግሥት መልዕክተኛ ለባሃኡላህ ምን ይዞ መጣ?

6. በሚቀጥለው ቀን ለባሃኡላህ ምን ቀረበለት?

7. መንግሥት ባሃኡላህን ሊሰደው የፈለገው ወዴት ነው? ______________________

8. ለጉዞው እንዲረዳው መንግሥት ያቀረበለትን ገንዘብ ባሃኡላህ ምን አደረገው?

9. የባሃኡላህ የመለየት ዜናን ምዕመናኖች በሰሙ ጊዜ ምን ዓይነት ሁኔታን አሳዩ?

10. ለወዳጆቹ ላለው ፍቅር ምልክት ይሆን ዘንድ ባሃኡላህ ምን አደረገ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

____

11. ባሃኡላህ ተልዕኮውን ያወጀበት የአትክልት ሥፍራ አሁን ምን ተብሎ ይጠራል?

__________

12. በዚህ ያትክልት ሥፍራ ምን ያህል ቀናትን ቆየ? ______________

13. እነዚያን ባሃኡላህ በሪዝቫን አትክልት ሥፍራ ያሳለፋቸውን ድንቅ ቀናት በመጥቀስ ናቢል እንዲህ ሲል ይነግረናል:–

ሀ. ጎህ ከመቅደዱ በፊት በየቀኑ አትክልተኞቹ

______________________________________ እና

____________________________________________ ነበሩ::

ለ. የጽጌረዳ ክምሩ በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ

_____________________________________

ሐ. እነኝህ ሁሉ ጽጌረዳዎች ባሃኡላህ በራሱ እጅ በየጠዋቱ ለሚሸኛቸው እየሰጠ፣

____________________________________________________________ እንደርሱ

በመሆን እንዲላክላቸው አደራ ይል ነበር::

መ. አንድ ሌሊት _______________________________________ ናቢል አንዱ ነበር::

ሠ. እኩለ ሌሊት ሲቃረብ ባሃኡላህ ከ ________________________________ ሲወጣ ናቢል

አየው:: ____________________________ አለፈና

____________________________ ጀመረ::

ረ. ___________________________________________በጣም ከፍተኛ ስለነበር ድምፁን

ሊሰሙ የሚችሉት አጠገቡ የነበሩ ብቻ ነበሩ::

ሰ. ባሃኡላህ መራመዱን ቀጠለ፡፡____________________________እንዲህ አለ:–

________________________ተመልከቱ፡፡ _____________________________________

እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ ________________________ እስከ

____________________________፣ ከሚያፈቅሩትም ነገር ጋር

____________________________________፡፡ ስለዚህ እንዴት ነው

____________________________________ የሚመርጡት?

ሸ. ለሦስት ተከታታይ ቀናት ናቢል

___________________________________________________፡፡

ቀ. ባሃኡላህ ይተኛበት ወደነበረው መደብ ናቢል በተጠጋ ቁጥር

____________________________፡፡ እንዲሁም በየቀኑ ከጠዋት እስከ ምሽት

___________________________________፡፡

በ. ባሃኡላህ ከሚናገራቸው ቃላት ናቢል እንድም ____________________________________

አላገኘም፡፡

14. ባሃኡላህን ከብዙሐኑ አማኞች በመለየት የእምነቱ ጠላቶች ምን ለማድረግ ሞከሩ? በምትኩስ የአምላክ ፈቃድ ምን ሆነ? _____________________________________________________

______________________________________________________________________________

___

15. የባሃኡላህን ተልዕኮ የታወጀበትን ቀን በማስመልከት የምናከብረው ክብረ በዓል ምን ይባላል?

___________________________________________________________________________

16. የ"ሪዝቫን በዓል" መቼ ይከበራል? ለምን ያህል ጊዜስ ይቆያል? __________________________

17. አሁን ከኢራን ወደ ባግዳድ የተደረገውን የባሃኡላህን ግዞት አጥንተው ስላጠናቀቁ ያንን ሁኔታ በተመለከተ አጭር ንግግር አዘጋጅተው ያቅርቡ፡፡

## ምዕራፍ 22

ባሃኡላህ ከገለፀው አንድ ፅላት የተወሰዱ ምንባቦች ከዚህ በታች ተሰጥተዋል። ለቡድናችሁ ጮክ ብለው በስሜት ያንብቧቸው። ይህን ሲያደርጉ ባሃኡላህ በሪዝቫን የአትክልት ስፍራ ያደረገውን እወጃ ያስታውሱ እናም ቃላቶችዎ ልብዎን በደስታ እንዲሞሉት ይፍቀዱ።

**"መለኮታዊው የፀደይ ወቅት መጥቷል፣ እጅግ በጣም የተከበርከው ብዕር ሆይ! የፍፁም መሐሪው በዓል በፍጥነት እየተቃረበ ነው። ራስህን አንቀሳቅስ፣ የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ እንደገና ሕይወት በሚዘሩባቸው እና በሚታደሱበት ሁኔታ በመላው ፍጥረት ፊት የአምላክን ስም አጉላ፣ ምስጋናውንም አክብር። ተናገር ፀጥ አትበል። የእግዚአብሔር ስም መንግሥት በጌታህ፣ በሰማያት ፈጣሪ ስም ጌጥ ስለተጌጠ የፍፁም ደስታ የቀኑ ኮከብ ደስተኛው ከሚለው ስማችን አድማስ በላይ ያበራል። በምድር ሕዝቦች ፊት ተነሳ፣ በዚህ እጅግ ታላቅ ስም ኃይል ራስህን አስታጥቅ፣ ከእነዚያ ከሚዘገዩትም አትሁን። . . .**

**"ብዕር ሆይ! በዚህ ቀን ከእኔ በስተቀር ሌላ ለማወቅ ትችላለህን? ፍጥረትና ክስተቶቿ እምን ደረሱ? ስሞች እና ግዛታቸውስ ምን ሆኑ?የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ የሚታይቱም የማይታይትም ወዴት ደረሱ? ሁለንተን ዓለም የተደበቁ ምስጢራት እና ግልፀታቸውስ? እነሆ መላው ፍጥረት በፊቴ አለፈ! ከዘለዓለም ነዋሪው፣ ከአንፀባራቂው፣ ከንዑዱ በስተቀር የቀረ የለም።**

**"ይህ ቀን፣ ከጌታህ፣ ፀጋ ከተሞላው፣ ከፍፁም ለጋሱ ፊት ከሚያበራው የብርሃን ድምቀት በስተቀር ሌላ ምንም ሊታይ የማይችልበት ቀን ነው። በእውነቱ በማይገታው እና ሁሉን ድል በሚነሳው ሉዓላዊነታችን እያንዳንዱ ነፍስ እንዲያልፍ አድርገናል። ከዚያም በሰዎች የፀጋችን ምልክት ይሆን ዘንድ አዲስ ፍጥረት ወደ መኖር ጠርተናል። እኔ በእውነቱ ፍፁም ለጋሱ፣ የቀናት ቀደምቱ ነኝ።**

**"በል:– ይህ፣ በቅጠሎቹ ላይ የንግግር ወይን ጠጅ፣ 'እርሱ ከሰዎች ዓይኖች ተሰውሮ የነበረው፣ ልዕልናና ሥልጣን ተገልፆአል!' የሚለው ምስክርነት የታተመበት ገነት ነው። ይህ የቅጠሎቹ እንቅስቃሴዎች ድምፅ:– 'እናንተ በሰማይ እና በምድር የምትኖሩ ሆይ! ከዚህ በፊት ከቶ ያልታየው ታይቷል። እርሱ ከእምቅድመ ዓለም ጀምሮ ፊቱን ከፍጥረት ዓይን ሰውሮ የነበረው አሁን መጥቷል' በማለት የሚያውጀው ገነት ነው። በቅርንጫፎቹ መካከል ከሚነፍሰው የሚያንኮሻኩሽ ልዝብ ነፋስ:– 'እርሱ የሁሉ ሉዓላዊ ጌታ ተከስቷል። መንግሥት የእግዚአብሔር ነው!' የሚለው ጩኸት ይመጣል፣ ከወራጅ ውኃው ደግሞ 'ዓይኖች ሁሉ እንዲደሰቱ ተደርገዋል፣ እርሱ ማንም ያላየው፣ ምስጢሩንም ያላገኘው፣ የክብር መጋረጃን ከፍቶ የውበትን ገፅታ ገልጧል' የሚለውን ንግግር ይሰማል።'**

**"በዚህ ገነት ውስጥ እና ከእጅግ በጣም ከፍተኛች ክፍሎቿ ከፍታዎች የመንግሥተ ሰማይ ድንግሎች:– 'የላይኛው ግዛት ነዋሪዎች ሆይ! ደስ ይበላችሁ፣ የቀናት ቀደምቱ ጣቶች በእርሱ፣ በንዑዱ ስም፣ እጅግ በጣም ታላቁን ደወል በሰማይ ማዕከላዊ እንብርት ውስጥ እየደወሉ በማሰማት ላይ ናቸውና። የቸርነት እጆች የዘለዓለማዊ ሕይወትን ፅዋ አድለዋል። እናንተ የናፍቆት የራሷ ሕልውናዎች፣ እናንተ የጥልቅ ፍላጎት ምሳሌዎች የሆናችሁ ሆይ! 'ቀርባችሁ የተሞላላችሁን ተጎንጩ። በጤናማ ደስተኝነትም ጠጡ፤' በማለት ጮኸው ተናግረዋል።"[45]**

# ምዕራፍ 23

ባሃኡላህ፣ ቤተሰቡ እና አብረዋቸው የነበሩት ጥቂት አማኞች በቁስጥንጥኒያ ለአራት ወራት ብቻ ቆዩ። በርቀት ያለው የፋርስ መንግስት፣ እያደገ የመጣውን የእርሱን (የባሃኡላህን) ተፅዕኖ ፈጣሪነት እንደስጋት መቁጠሩን አላቋረጠም። በኦቶማን ሥርወ መንግስት ውስጥ የሥልጣኑ ችሎት የፋርስ አምባሳደር የሆነው፣ በባሃኡላህ ላይ ስልታዊ ዘመቻ ማድረጉን እየቀጠለበት መጣ። ሱልጣኑ፣ ሚንስትሮቹ እና አብረዋቸው የነበሩት ሁሉ ኑሯቸውን በክህደት፣ በምስጢር በመዶለት እና በግብዝነት የተሞላ ነበር። ባሃኡላህ ከእነኝህ ዋጋ ቢስ እና ዓላማ ቢስ ሰዎች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር አልፈቀደም። የባሃኡላህ ገለልተኝነት ለፋርሱ አምባሳደር የባለሥልጣኖቹን አእምሮ በወቀሳ እና በውሸት ለመሙላት ቀላል አደረገለት። ሳያቋርጥ ያደረገው ጥረት ተሳካለት፣ በመጨረሻም ባሃኡላህ ከፋርስ ድንበር በጣም ወደራቀችው አድሪያኖፕል እንዲጋዝ ትዕዛዝ ወጣ።

ለትዕዛዙ ባሃኡላህ የሰጠው ምላሽ እጅግ የተለየ ጀግንነት የተሞላበት ድርጊት ነበር። ወዲያውኑ አንድ ረዥም ፅላት ለሡልጣኑ ለእራሱ ገለፀ። በፅላቱ ሱልጣኑን እና ሚንስትሮቹን ያልበሰሉ እና ብቃት የሌላቸው መሆናቸውን በመጥቀስ ወቀሳቸው። ፅላቱ በታሸገ ፖስታ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ተሰጠ። ደብዳቤውን ከፍቶ ማንበብ ሲጀምር ፊቱ ገረጣ እንዲህም አለ፦ **"የነገሥታት ንጉሥ የሆነው፣ የእርሱን ሥራ ከሚቆጣጠረው እጅግ ዝቅተኛ ከሆነው ሎሌው ትዕዛዝን እንደመቀበል ነው። "**[46] በማለት ሲናገር ተሰምቷል።

አሁን ለሦስተኛ ጊዜ የተጋዙበት ከቁስጥንጥኒያ እስከ አድሪያኖፐል የተደረገው የአሥራሁለት ቀናት ጉዞ ለባሃኡላህ እና ለቤተሰቡ እጅግ በጣም ከባድ ነበር። ወሩ ታህሳስ እንደመሆኑ መጠን የዓየር ንብረቱ እጅግ አስመራሪ ቀዝቃዛ ክረምት ነበር። በመንገዳቸው ላይ ከምንጭ ውሃ የሚያገኙት በረዶውን በእሳት በሚሚት ብቻ ነበር። የከፋ ቅዝቃዜውን ለመከላከል አብዛኞቹ የተጋዙት ስደተኞች አስፈላጊው ልብስ ስንኳ አልነበራቸውም።

ባሃኡላህ እ.ኤ.አ ዴሴምበር 12 ቀን 1863 አድርያኖፐል ከተማ ደረሰ፤ በዚያች ከተማ አራት ዓመት ከመንፈቅ ተቀመጠ። እንደበፊቱ ሁሉ ይህም ወቅት ስቃይ የሞላበት፣ ችግሮች እና የላቁ ድሎ ችም የተመዘገቡበት ወቅት ነበር። የባሃኡላህ ተሰሚነት እያደገ ሲሄድ በጣም አስፈሪ የቅናት እሳት በሚርዛ ያህያ ልብ ውስጥ ነደደ። የመቃወም ድፍረቱም እየጨመረ ሄደ። የዚህን ቀን የአምላክ ክስተት የሆነው ባቢዎች እንዳይቀበሉት ለማድረግ የተቻለውን ሁሉ አደረገ። የተቀሰቀሰው ችግር ማኅብረሰቡን ከመጥቃቱ ባሻገር ለእምነቱ የውጭ ጠላቶች፣ ባሃኡላህ ላይ እና ተከታዮቹ ላይ ተጨማሪ ጥቃት ለመክፈት የሚጠቀሙበትን መሣሪያ ሰጣቸው። የሚርዛ ያህያ ክህደት ወሰን ያለው አይመስልም ነበር። ለባሃኡላህም መርዝ ለማጠጣት ወሰነ፤ ይህን ዓላማውን እስኪያሟላ ድረስም ማሴሩንና መልፋቱን አላቆመም። መርዙ በባሃኡላህ ላይ እጅግ የከፋ ውጤት አስከትሏል፣ ምንም እንኳ ከመርዙ ቢተርፍም እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ድረስ እጁ ይንቀጠቀጥ ነበር።

በእርግጥ አድሪያኖፐል የምትታወሰው በሚርዛ ያህያ አሳፋሪ ድርጊቶች ሳይሆን ባሃኡላህ በዚያች ከተማ በተጎናፀፋቸው ታላላቅ ድሎች ነው። ባሃኡላህ ለነገሥታት እና ለዓለም መሪዎች ብዙዎቹን ፅላቶች የላከው እና የእርሱን ሃይማኖት በቅርብም በሩቅም ያወጀው ከዚህች ከተማ ነበር።

የእሱ ህዝባዊ አዋጅ፣ ተልእኮው ለሰው ልጆች የተገለጸበትን ቀጣይነት ያለው ሂደት ሦስተኛውን ደረጃ ይወክላል። የመጀመሪያው ደረጃ፣ በቴህራን በሲያህ-ቻል ጉድጓድ እስር ቤት ውስጥ መለኮታዊው መንፈስ እራሱን ለባሃኡላህ ሲገልጽለት እና የዘመኑ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ እንደሆነ ሲያውጅ ይጀምራል። ምንም እንኳ የግልፀቱ መወለድ ለአስር ዓመታት ሳይታወቅ ቢቀርም ልክ እንደጎህ መቅደድ ያንቀላፉትን ነፍሳት ቀስቅሶ ነበር። ቀስ በቀስ ዝግጁ የነበሩትን ነፍሶች በማንቃት ባሃኡላህን እንዲቀበሉ አዘጋጃቸው። ሁለተኛው ደረጃ፣ ሊሰናበቱት ተሰብስበው ለነበሩት

አማኞች ተልዕኮውን ባወጀላቸው በሪዝ ቫን የአትክልት ስፍራ ተጀመረ። ጥቂት ቁጥር ያላቸው እድለኞች ነፍሶች የእርሱን ደረጃ ተገንዝበው ነበር። ሦስተኛው ደረጃ የተልዕኮው ዓለም ዓቀፍ እወጃ ነበር። በቁስጠንጥንያ ተጀምሮ፣ በአድሪያኖፒል እጅግ ጎልብቶ፣ቀጣይና የመጨረሻ የግዞቱ ቦታ በሆነችው አቆር ደግሞ እጅግ ከፍተኛ ኃይልን ተጎናፀፈ።

1. ባሃኡላህ በቁስጥንጥኒያ ለምን ያህል ጊዜ ቆየ? ____________________________

2. በቁስጥንጥኒያ የቆየበት ጊዜ ለምን አጭር ሆነ?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

____

3. ባሃኡላህ በዋናው ከተማ በቆየበት ወቅት ከሡልጣኑ ችሎት ጋር ግንኙነት ያልፈጠረው ለምንድን ነው?

___________________________________________________________________________

4. የፋርሱ አምባሳደር፣ ባሃኡላህ ከችሎቱ አባላቶች ጋር እና በምንም ዓይነት ጉዳዮች ላይ ከፍሬቢስ ዓላማዎቻቸው ጋር አለመተባበሩን እንደመጠቀሚያ አድርጎ የወሰደው እንዴት ነው?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

___

5. ቀጥሎ ወደ የት ተሰደደ? __________________________

6. የፋርስ መንግሥት ባሃኡላህን ከወሰኑ (ከድንበሩ) አርቆ እንዲሰደድ የፈለገው ለምንድነው?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______

7. ባሃኡላህ ወደ ቁስጥንጥኒያ የመጋዙን ዜና ሲሰማ ምን አደረገ?

_____________________________

8. የሡልጣኑ ጠቅላይ ሚኒስትር የባሃኡላህን ደብዳቤ ካነበበ በኋላ ምን አለ?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

___

9. ባሃኡላህ አድሪያኖፕል መቼ ደረሰ? ____________________________________

10. በዚያች ከተማ ለምን ያህል ጊዜ ቆየ? ____________________________________

11. በወቅቱ በአድሪያኖፕል ከተከናወኑት ነገሮች በጣም ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነገር ምንድን ነው?

______________________________________________________________________________

__

12. የባሃኡላህ ተልዕኮ ለሰው ልጅ ሲታወጅ በስንት ደረጃዎች ውስጥ አለፈ?

____________________

13. የመጀመሪያው ደረጃ ምን ነበር?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

_______

14. ሁለተኛው ደረጃ ምን ነበር?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______

15. ሦስተኛው ደረጃ ምን ነበር?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

___

## ምዕራፍ 24

በአድሪያኖፕል ሚርዛ ያህያ ባሃኡላህን በግልፅ በመቃወሙ ምክንያት በአማኞች መካከል ታላቅ ብጥብጥ ተነሳ። ምክንያቱም ከእነኝህ አማኞች አብዛኛዎቹ የባሃኡላህን ደረጃ በጨረፍታ ማየት ከመጀመራቸው የተነሳ ነበር። ይህ ሁኔታ ከጀርባቸው የሁለቱ የፋርስ እና የኦቶማን መንግስታት ድጋፍ ለነበራቸው ለእምነቱ ጠላቶች አዲስ በተወለደው በእግዚአብሔር እምነት ላይ ሌላ ጥቃት ለመሰንዘር እድል ሰጣቸው። አንድ ቀን በጠዋት የባሃኡላህ ቤት በድንገት በወታደሮች ተከበበ። ምንም ሳይዘገዩም ቦታውን ለቀው ለመሄድ እንዲዘጋጁ ለሁሉም ተነገረ። ለተወሰነ ጊዜ ዕጣ ፋንታቸው ምን እንደሚሆን የሚያውቅ አንድም ሰው አልነበረም። ባሃኡላህ እና ቤተሰቡ ወደ አንድ ቦታ እንደሚጋዙ እና ሌሎቹ ደግሞ ለመበታተን እንደሚገደዱ ወሬ ተናፍሶ ስለነበር የአብዛኞቹ ፍርሐት ከተወዳጃቸው መለየት ነበር። በመጨረሻም ባሃኡላህ የእስር ከተማ ወደ ሆነችው አቆር፣ ሚርዛ ያህያ ደግሞ ወደ ቆጵሮስ ደሴት እንደሚጋዙ ግልፅ ሆነ። ወደ ሰባ የሚጠጉ ምዕመናኖች እና ሁለቱ እጅግ በክፋት የተሞላው የሚርዛ ያህያ ደጋፊዎች ወደ አቆር ተላኩ። በሌላ በኩል አራት የባሃኡላህ አጋሮች ከሚርዛ ያህያ ጋር ወደ ቆጵሮስ ተጋዙ።

ባሃኡላህ እና ቤተሰቡ እ.ኤ.አ ኦገስት 12 ቀን 1868 አድሪያኖፕልን ለቀቁ፣ በመሬትና በባህር ላይ አስቸጋሪ የሆነ ጉዞ ካደረጉም በኋላ ኦገስት 31 ቀን አቆር ደረሱ። ለአቆር ነዋሪዎች ግን የእስረኞች መምጣት እንግዳ ነገር አልነበረም፣ ምክንያቱም ኦቶማኖች ከተማይቱን ወንጀለኞችንና በጥባጮችን ለማ ጋዝ ይጠቀሙበት ስለነበር ነው። አሁን የመጡት እስረኞች የመንግሥት፣ የእግዚአብሔር እና የሃይማ ኖቱ ጠላቶች ናቸው ተብሎ ተነገራቸው። በጥብቅ እንዲታሰሩም ሱልጣኑ ትዕዛዝ ሰጠ። እርሱ እና ሚኒስትሮቹም የአቆር አስከፊ ሁኔታዎች በመጨረሻ እንደሚያጠፋቸው ተስፋቸውን ገልፀው ነበር። የሡልጣኑ ትዕዛዝ በመስጊድ ውስጥ ለሕዝቡ ተነበበ፣ በመሆኑም እነኝህ የፋርስ ሰዎች ለእድሜ ይፍ ታህ እንደታሰሩ እና ከእነርሱ ጋር ግንኙነት መፍጠር በጥብቅ የተከለከለ መሆኑን ሁሉም ተረዱ።

አቆር ሲደርሱ ከጀልባ ከወረዱ በኋላ ግዞተኞቹ እስር ቤታቸው ወደ ሚሆነው ወደ ወታደሮች መኖሪያ ተወሰዱ። በመጀመሪው ሌሊት ምግብ እና ውኃ ተነፈጋቸው፣ በኋላም ለእያንዳንዳቸው በቀን ሦስት ጥራት የሌላቸው የዳቦዎች ተመደበላቸው። ብዙም ሳይቆዩ ከሁለቱ በስተቀር ሁሉም ታመሙ። ከዚያም በአጭር ጊዜ ውስጥ ሦስቱ ሞቱ። አስፈላጊው ወጪ ካልተከፈላቸው በስተቀር የሞቱትን ለመቅበር ዘበኞቹ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። ባሃኡላህ ይጠቀምበት የነበረ አንድ ትንሽ የፀሎት ምንጣፍ ተሸ ጠና ገንዘቡ ለዘበኞቹ ተሰጣቸው። የኋላ ኋላ ዘበኞቹ ቃላቸውን ማጠፋቸው እና አስከሬኖቹ ሳይታጠቡ፣ በጨርቅ ሳይጠቀለሉ እና ያለሳጥን እንደቀበሯቸው ተደረሰበት። እንደእውነቱ ከሆነ ግን የተሰጣቸው ገን ዘብ፣ ለቀብሩ ከሚያስፈልገው በላይ እጥፍ ነበር።

ምንም እንኳ የእስሩ ሁኔታ ቀስ በቀስ እየተሻሻለ ቢመጣም በአቆር የኖሩባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ለባሃኡላህ የአስከፊ ስቃይ ወቅት ነበር። በሲያህ-ቻል የተቀበለው መከራ ሙሉ ለሙሉ የእምነቱ የውጭ ጠላቶች ያደረሱበት ነበር። በአድሪያኖፕል የተነሳው ብጥብጥ በባህሪው ውስጣዊ

ችግሮች የቆሰቆሱት ሁኔታ ነበረው። ነገር ግን አቆር በነበሩባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የታዩት ችግሮች የውጪ እና የውስጥ ኃይሎች ግፊት ውጤት ነበር። ይህንን ወቅት ባሃኡላህ እራሱ በሚከተ ሉት ቃላት ገልፆታል:–

> **"እዚህ ቦታ ላይ በደረስን ጊዜ እጅግ በጣም 'ታላቁ እስር ቤት' የሚለውን ስም እንደመረጥንለት እወቅ። ምንም እንኳን አስቀድመን በሌላ አገር በሠንሠለቶች እና በእግር ብረቶች ብንሰቃይም በዚያ ስም ልንጠራው አልፈለግንም። በሉ:– እናንተ ግንዛቤ የተቸራችሁ ሆይ! በዚህ ላይ አሰላ ስሉ።"[47]**

ከባሃኡላህ እና ከቤተሰቡ ጋር ማንም ሰው እንዳይገናኝ የሚከለክለው የሡልጣኑ ትዕዛዝ ቢኖርም እንኳ፣ ባሃኡላህ ፊት እንቀርባለን በሚል ተስፋ ብዙ አማኞች ከፋርስ ወደ አቆር በእግራቸው ረዥም ጉዞ ያደርጉ ነበር። እነኝህ ጥልቅ ፍቅር የነበራቸው ነፍሶች አቆር ሲደርሱ ወደ እርሱ ለመጠጋት ባለመ ቻላቸው ከሩቅ ቆመው እስር ቤቱን በመመልከት፣ በብረት በታጠረው መስኮቱ ውስጥ በጨልቅታም (በጨረፍታም) ቢሆን እርሱን ማየቱ ብቻ ያረካቸው ነበር። ለወራት ለተጓዙት ጉዞ እጁን በማውዛወዝ የሚሰጣቸው ሰላምታ ለእነርሱ በቂ ወሮታ ነበር። አብዛኞቹም ለተቀበሉት ፀጋ አመስጋኝ በመሆን ወደ ቤታቸው ይመለሱ ነበር።

የዚህ ወቅት እጅግ አሳዛኝ ሁኔታ የባሃኡላህ ልጅ እጅግ በጣም ንጹሁ ቅርንጫፍ በመባል የሚ ታወቀው ሚርዛ ምህዲ ድንገተኛ ሞት ነበር። አንድ ምሽት በእስር ቤቱ ጣራ ላይ፣ በፀሎት እና በማሰ ላሰል ተመስጦ እየተረማመደ ሳለ፣ ብርሃን እንዲያስገባ በተሠራ ቀዳዳ ተሰናክሎ ወደ ታች ወለሉ ላይ ባለ የእንጨት ሣጥን ላይ ወደቀ። ጎድኖቹ ተሰባበሩ። ከመሞቱ በፊት ባሃኡላህ እጅግ በጣም ንጹሑን ቅርንጫፍ ምን እንደሚመኝ ጠየቀው፣ እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ:– "የባሃ ሰዎች እፊትህ ለመቅረብ እንዲችሉ እመኛለሁ።" ባሃኡላህም:– "እንደዚያ ይሆናል፣ አምላክ ፍላጎትህን ያሟላልሃል።"[48] አለው።

በእጅግ በጣም ታላቁ እስር ቤት የባሃኡላህ መከራ እጅግ አስከፊ ቢሆንም ወደ አቆር መጋዙ ያለፉትን ዘመናት ትንቢቶችን ያሟላ መሆኑ መረሳት የለበትም። የእውነት ፀሐይ በሙሉ ነፀብራቋ ለሃያ አራት ዓመታት ያበራቸው በአቆር ነበር። በዚህ ወቅት ነበር ባሃኡላህ በሃይፋ አጠገብ ያለውን የቀርሜሊዮስ ተራራን በጎበኘበት ጊዜ የባብ መካነ መቃብር የሚገነባበትን ቦታ ለአብዱል-ባሃ ያመለከተው። ከአካ ወጣ ብሎ በሚገኝ ቦታ፣ በባህጂ የሚገኘው የእርሱ የእራሱ መካነ መቃብር፣ በምድር ካሉ ቦታዎች ሁሉ እጅግ የተቀደሰ እና በዓለም ዙሪያ ለሚገኙት የእርሱ ተከታዮች በየቀኑ በሚያደርጉት ፀሎት ፊታቸውን የሚያዞሩበት ነው። ከባብ የተቀደሰ መካነ መቃብር አቅራቢያ የዓለም ዓቀፍ ቤተ ፍትሕ መንበር (መቀመጫ) እየተመሠረተ ይገኛል። መንትያ የሆኑት የሃይፋ እና የአቆር ከተሞች የባሃኢ እምነት መንፈሳዊ እና አስተዳደራዊ ማዕከሎች እየሆኑ ነው። ባሃኡላህ በአድሪያኖፕል ውስጥ ባሳለፈው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ወደ አቆር እንደሚጋዝ አስመልክቶ በጽላቶቹ በአንዱ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡-

> **"ስንደርስ በብርሃን ሰንደቆች ተቀበሉን፤ ከዚያም የመንፈስ ድምፅ እንዲህ ሲል ጮኸ:– 'በቅርቡ በምድር ላይ የሚኖሩ ሁሉ በእነዚህ ሰንደቅ ዓላማዎች ስር ይሰበሰባሉ።' "[49]**

1. በሚርዛ ያህያ የተነሳውን ችግር የእምነቱ ጠላቶች እንዴት አድርገው ነው ለራሳቸው ዓላማ የተጠቀሙበት?

________________________________________________

2. ባሃኡላህ በመቀጠል የተሰደደው ወዴት ነው?

__________________________________________

3. ሚርዛ ያህያ የተላከው ወዴት ነው? ____________________________

4. ከባሃኡላህ ጋር ወደ አቆር የተጋዙት ስንት ነበሩ? ______________

5. ጥቂት የባሃኡላህ ተከታዮች ከሚርዛ ያህያ ጋር ወደ ቆጵሮስ ሁለት የሚርዛ ያህያ ደጋፊዎች ደግሞ ወደ አቆር የተላኩት ለምን ይመስልዎታል?

____________________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

6. ባሃኡላህ ከአድርያኖፕል የለቀቀው በምን ቀንና ዓመት ነበር?

_____________________________

7. አቆር የደረሰው መቼ ነበር?____________________________________

8. የባሃኡላህን እና አብረውት የነበሩትን አማኞች በተመለከተ ሡልጣኑ የሰጠው ትዕዛዝ ምን ነበር?

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

___________________________________

9. የአቆር ነዋሪዎች ስለትዕዛዙ እንዴት አወቁ?

__________________________________________

10. ባሃኡላህ እና አብረውት የነበሩት አቆር ሲደርሱ የተወሰዱት ወዴት ነበር?

___________________

11. በጥቂት ቃላቶች በእስር ቤቱ ውስጥ የቆዩባቸውን የመጀመሪያዎቹን ጥቂት ቀናት ሁኔታዎች ያብራሩ:

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

_______________________________________________________

12. ባሃኡላህ አቆርን ምን ብሎ ሰየማት?

_____________________________________________

13. በአቆር ቆይታቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የተከሰተው እጅግ አሳዛኝ የነበረው ሁኔታ ምን ነበር?_________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______

14. የመጀመሪዎቹ ባሃኡላህን ለማየት ወደ አቆር የሚጓዙት ምዕመናኖች በምን ሁኔታ ውስጥ ነበር?

______________________________________________________________________

___

15. የእጅግ በጣም ንፁሁ ቅርንጫፍ ሞት ሁኔታዎች በራስዎ አባባል ይግለፁ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

___________________________________________________________

16. በአቆር እና በአካባቢዋ ባሃኡላህ ለስንት ዓመታት ቆየ?

_______________________________

17. ባሃኡላህ በሃይፋ የሚገኘውን ቀርሜሊዮስ ተራራን በጎበኘት ወቅት ለአብዱል-ባሃ ያመለከተው ምንድን ነው? _____________________________________

18. በምድር ላይ እጅግ በጣም ቅዱሱ ስፍራ ምንድነው? የትስ ይገኛል?

______________________

19. የዓለም ዓቀፍ ቤተ-ፍትህ መንበር (መቀመጫ) የሚገኘው የት ነው?

______________________

20. የባሃኢ እምነት የመንፈሳዊ እና አስተዳዳራዊ ማዕከል የሚገኘው የት ነው?

________________

21. በዛሬው ጊዜ መንፈሳዊ ተጓዦች ሃይፋንና አቆርን ሲጎበኙ ምን እንደሚያደርጉ ያውቃሉ? በማኅበረሰ ብዎ ውስጥ ቅድስት አገርን የጎበኘ አማኝ ካለ ስለጉብኝቱ ጠይቀው ለመረዳት ይሹ ይሆናል።

## ምዕራፍ 25

ባሃኡላህ በአቆር ዓለም ዓቀፋዊ እወጃውን ቀጥሎ ነበር። ከአድሪያኖፐል እና ከአቆር ለነገሥታት እና ዓለም ላይ ላሉ መሪዎች ባሃኡላህ ከላካቸው መልእክቶች ጥቂት ምንባቦች እዚህ ቀርበዋል:–

ለፈረንሣይ ንጉሠ ነገሥት ለናፖሊዮን ሳልሳዊ:–

> **"የፓሪስ ንጉሥ ሆይ! ካህኑ ደውሎቹን ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይደውል ንገረው። በአምላክ፣ በእውነተኛው! እጅግ በጣም ኃያሉ ደወል ከሁሉም በላይ ታላቅ በሆነው ስም አማካኝነት ተከስቷልና . . ."**[50]

ለሩሲያው ዛር (ንጉሥ) ኒኮላቪች አሌክሳንደር ዳግማዊ:–

> **"በዚህ፣ ሁሉን አስገዳጅ በሆነው እምነት ስም በሰዎች መካከል ተነሳና፣ ከዚያም አገሮችን ወደ ተከበረው ወደ ታላቁ አምላክ ጥራቸው።"**[51]

ለእንግሊዟ ንግሥት ቪክቶሪያ:–

> **"ፍላጎትሽን ተዪ፣ ከዚያም ልብሽን የቀናት ቀደምቱ ወደ ሆነው ጌታሽ አቅኚ። ለአምላክ ስንል ስለአንቺ እናወሳለን፣ የምድር እና የሰማይ ፈጣሪ የሆነው አምላክን በማስታወስሽም አማካኝነት ስምሽ ከፍ እንዲል እንፈልጋለን።"**[52]

ለፕሩሲያው ንጉሥ ዊልያም ቀዳማዊ:–

> **"ትዕቢት የመለኮታዊው ግልፀት ጎህን ማወቅ እንዳይከለክልህ፣ ምድራዊ ፍላጎቶች እንደ መጋረጃ ሆነው የሰማዩን ዙፋንና የዝቅተኛው ምድር ጌታ ከሆነው እንዳይሸፍንህ ተጠንቀቅ። "**[53]

ለኦስትሪያው ንጉሥ ነገሥት ፍራንሲስ ጆሴፍ:–

**"ይህን ንውድ ራዕይ እንድታይ እና በቀንና በማታ የምትማፀነውን ታውቅ ዘንድ፣ እንዲሁም ከዚህ ብሩህ አድማስ በላይ በሚያበራው ብርሃን ላይ ታተኩር ዘንድ ዓይኖችህን ክፈት።"[54]**

ለኦቶማኑ ግዛት ሡልጣን አብዱል አዚዝ:–

**"ፈሪሃ እግዚአብሔርን ገሸሽ አታድርግ፣ ከእነዚያ በቀናነት ከሚሠሩትም ሁን። እነዚያን ከላያቸው የእምነትንና የፍትሕን መዓዛ ልታሸትባቸው የምትችለውን ሚኒስትሮች በዙሪያህ ሰብስብ እና ከእነርሱ ጋር ተመካከር፤ ማንኛውንም የተሻለ ሆኖ የታየህን ምረጥ፣ ከእነዚያ በቸርነት ከሚሠሩትም ሁን።"[55]**

ለፋርሱ ናስረዲን ሻህ:–

**"እርሱ ይክበር እና ከፀጋው የተነሳ በዚህ እስር አማካኝነት የሰዎች አንገቶች ከሠንሠለቶች እና ከእግር ብረቶች ነፃ እንዲወጡ እና ወደ እርሱ፣ ወደ ኃያሉ፣ በረከት ወደ ተሞላው ኃያል የእርሱ ገፅ ፊቶቻቸውን በቅንነት እንዲያዞሩ ያደርጋቸው ዘንድ እንፀልያለን። እርሱን ለሚጠራ ለማ ንኛውም (ሰው) መልስ ለመስጠት ዝግጁ ነው፤ ለእነዚያም ከእርሱ ጋር ለሚቋረቡት ቅርብ ነው።"[56]**

ለአሜሪካ ገገሮች እና ለሪፖብሊኮቹ ፕሬዚዳንቶች:–

**"የተሰበሩትን በፍትህ እጆች ጠግኑ፤ የተንሰራፉትንም ጨቋኞች በጌታችሁ፣ በአዛዡ በጠቢቡ ትዕዛዛት በትር ሰባብሩ።"[57]**

ለፓየስ ዘጠነኛ የሮማው ጳጳስ:–

**"ወልድ የሰወረው ቃል እንዲከሰት ተደርጓል። በዚህ ቀን በሰው አካል አምሳያ ተልኳል (ወር ዷል)፣ አባት የሆነው ጌታ የተባረከ ይሁን! እርሱ በእርግጥ፣ ይበልጥ ታላቅ በሆነው ግርማው ወደ ሕዝቦች መጥቷል።"[58]**

ለአብያተ ክርስቲያን ለሚገኙት መነኮሳት በሙሉ:–

**"የመነኮሳት ጉባዔ ሆይ! በአብያተ ክርስቲያነት እና በገዳማት ራሳችሁን አታግልሉ። በእኔ ፈቃድ ውጡ እና ነፍሶቻችሁን እና የሰዎችን ነፍሶች የሚጠቅም ሥራ ያዙ።"[59]**

## ምዕራፍ 26

ከእጅግ በጣም ንፁሁ ቅርንጫፍ ድንገተኛ ሞት አራት ወራት ካለፉ በኋላ ለጦር ሠራዊት አባላት ቦታ ለመስጠት ሲባል፣ ባሃኡላህ እና አብረውት የነበሩት ከወታደሮቹ መኖሪያ መዛወር ነበረባቸው። እርሱ እና ቤተሰቡ ለአጭር ጊዜ በተለያዩ ቤቶች ተቀመጡ፣ በመጨረሻም ዛሬ የአቡድ ቤት በመባል ወደሚጣወቀው ቤት ተዛወሩ። በዚህም ጊዜ ቢሆን በጥበቃ ስር ነበሩ። እንዲሁም በሡልጣኑ ትዕዛዝ ምክንያት በዙሪያቸው ያለው ሕዝብ በክፉ ዓይን የሚያያቸው እና በጠላትነት ስሜት የተሞላ ነበር።

ሆኖም ጊዜ እያለፈ ሲሄድ የአቆር ሕዝብ እነዚህ ከፋርስ የመጡ ጥቂት ግዞተኞች፣ ወንጀለኞች እንዳልሆኑ መገንዘብ ጀመረ፣ የእስር ሁኔታዎቻቸውም ቀለል አሉ። አብዛኛዎቹ ለውጦች ከከተማው ነዋሪዎች ጋር ብዙ ግንኙነት በነበረው እና የባሃኢዎቹን እውነተኛ ዓላማ እና የአባቱን ትምህርቶች መንፈስ ለሕዝቡ በግልፅ ለማሳየት ችሎ በነበረው በአብዱል-ባሃ ምክንያት የመጡ ነበሩ። በመጨረሻም ባሃኡላህ ከከተማው ወጥቶ በአቅራቢያው ያሉትን ቦታዎች ለመጎብኘት ችሎ ነበር። ለብቻዋ ተነጥላ በነበረች ከተማ ቅጥር ውስጥ ለረዥም ጊዜ ከታሠረ በኋላ አንዳንድ ጊዜውን በገጠር ለማሳለፍ እና እጅግ ይወደው በነበረው የተፈጥሮ አረንጓዴነት እና ውበት ለመደሰት ችሎ ነበር።

ባሃኡላህ የሕይወቱን የመጨረሻ ዓመታት ከአቆር ከተማ ውጭ በነበረው የባህጂ መኖሪያው (እልፍኙ) አሳለፈ። እርሱ በከተማ ቅጥር እስር ውስጥ እያለ የተሠራው ይህ ቤት በቦታው ወረርሽኝ በሽታ ሲነሳ ባለቤቱ ጥሎት ሸሸ። ይህን ቤት አብዱል-ባሃ ለተወዳጅ አባቱ መጀመሪያ በኪራይ በኋላም በግዢ ለማግኘት በቃ።

በዚህን ጊዜ የአቆር ብቻ ሳይሆን በቅርብ የሚገኙት የሶሪያ እና የሊባኖስ ሕዝቦች ስለ ባሃኡላህ እና ተከታዮቹ የነበራቸው አስተሳሰብ ፈፅሞ ተለውጦ ነበር። ምንም እንኳ የሡልጣኑ ተእዛዝ ገና ያልተሻረ የነበረ እና በጥብቅ ቁጥጥር ሥር የዋለ እስረኛ የነበረ ቢሆንም እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እንደ ንጉሥ በጥልቅ የተከበረ ነበር። የአካባቢው ባለሥልጣኖች እንኳን ምክሩን በመሻት ወደ እርሱ ይመጡ ነበር። የባሃኡላህ ግልጸት የሰዎችን ልቦች ለመለወጥ ያለው ኃይል ይህን ይመስላል።

አቆር እና ባህጂ በኖረባቸው ዓመታት የባሃኡላህ ብዕር የሰው ልጅ አስደናቂ የሆነ የዓለም ስልጣኔ ለመገንባት የሚያስችለውን መመሪያ የያዙ እጅግ ብዙ ፅሑፎችን (ጥራዞችን) ገለፀ። ከብዕሩ ከመነጩት ፅሑፎቹ ሁሉ እጅግ በጣም ኃያል የነበረው እ.ኤ.አ በ1873 በአቡድ ቤት የተገለፀው የሃይማኖቱ እጅግ በጣም ቅዱስ መፅሐፍ የሆነው 'ኪታቢ አቅዳስ' ነው። ሾጊ ኤፌንዲ፣ ባሃኡላህ በቅድስት ሀገር ስለገለፃቸው ፅሑፎቹ ሲጠቅስ እንዲህ ብሎ ነበር፦

> **"በዚህ ወቅት የተፃፉት የባሃኡላህ ፅሑፎች፣ የሚያካልሉትን ሰፊ መስክ በአጠቃላይ መልኩ ስናይ በሦስት የተለያዩ ክፍሎች የተከፈሉ ይመስላሉ። የመጀመሪያው በአድሪያኖፕል ያደረገውን የተልዕኮውን እወጃ ተከታይ ፅሑፎችን የያዘ ነው። ሁለተኛው የግልጸት ዘመኑን ሕግጋትን እና ትዕዛዛትን የሚጨምር ሲሆን እነኝህን አብዛኞቹን የእርሱ እጅግ በጣም ቅዱስ መፅሐፍ በሆነው በኪታቢ አቅዳስ ውስጥ ሰፍረዋል። በሦስተኛው ክፍል የሚመደቡት ደግሞ ለዚያ የግልፀት ዘመን መሠረት የሆኑትን መሠረታዊ እምነቶች እና መርሆዎችን በከፊል የሚገልፁ እና በከፊል ደግሞ እንደገና የሚያረጋግጡ ጽሳቶች ናቸው።"[60]**

የባሃኡላህ እምነት ወደ ምዕራቡ ዓለም ያደረገው መስፋፋት እርሱ በሕይወት እያለ ያልጀመረ ሲሆን የአብዱል-ባሃን የአገልግሎት ዘመን መጠበቅ ነበረበት። ሆኖም ትምህርቶቹ በምዕራብ አገሮች ታውቀው፣ እንዲያውም ጥቂቶቹ ወደ እርሱ ፊት የሚቀርቡትን ሁሉ እስከሚያስደንቅ ድረስ ተፅዕኖ ያሳደረባቸው የአቆር እስረኛ መሆኑን አውቀው ነበር። እ.ኤ.አ በ1890 በፀደይ ወቅት የባሃኡላህ ሕይወት ዘመን ማብቂያ አካባቢ፣ በኢንግላንድ የካምብሪጅ ታዋቂ ምሁር የነበሩት ኤድዋርድ ግራንቪል ብራውን እርሱን ለማግኘት መጥተው ነበር። የሚቀጥሉት ምንባቦች ከዚያ ታሪካዊ ቃለ-መጠይቅ መዝገብ የተገኙ ናቸው፦

> "*. . . ጫማዬን እስካወልቅ ድረስ አስተናባሪው ለጥቂት ጊዜ ቆሞ ጠበቀኝ። በተለመደው የአቀባበል ባህል መጋረጃውን ገልጦ ካስገባኝ በኋላ መጋረጃው መልሶ ጋርዶ ሄደ። እኔም በአንድ በኩል በአጭር ሶፋ በተከበበና ከመዝጊያው ፊት ለፊት ካለው ወገን ደግሞ ሁለት ወይም ሦስት ወንበሮች የተቀመጡበት ሰፊ ክፍል ውስጥ ገብቼ ቆምሁ። በቅድሚያ የተሰጠኝ ማብራሪያ ስላልነበር ምንም እንኳ የት እንደምሄድ እና ማንን እንደማይ ትንሽ ጋራ የተጋባሁ ቢሆንም አድናቆት እና ፍርሐት ከተሞላበት ድንጋጤ ጋር ክፍሉ ውስጥ ሰው ስለመኖሩ ሳልረዳ አንድ ወይም ሁለት ሴኮንዶች አለፉ። ግድግዳውን ይዞ ወደ ማዕዘኑ በተጠጋው ቦታ ላይ የተቀመጠ፣ በታችኛው ጠርዙ ዙሪያ ትንሽ ነጭ መጠምጠሚያ ያለበት እና በደርቡሾች 'ታጅ' ተብሎ የሚጠራ ነገር ግን ያልተለመደ ከፍታ እና አሠራር ያለው የራስ ቆብ የደፋ በጣም ግሩም እና የተከበረ ሰው ተቀምጦ ነበር። እርሱን፣ እይታዬን ያተኮርኩበትን ገፅታ፣ ምንም እንኳ ልገልፀው ባይቻለኝም በፍፁም ልረሳው አልችልም። እነዚያ ጠልቀው የሚያዩ ዓይኖቹ የሰውን ነፍስ የሚያነቡ ይመስላሉ። ኃይል እና ስልጣን በሰፊው ግንባሩ ላይ ይታዩበታል። በግንባሩ እና በፊቱ ላይ ያሉት ጥልቅ መስመሮች እስከ ወገቡ ተንጣሎ የተኛው ጥቁር ሐር ፀጉሩ እና ፂህሙ ሊደብቁ የሞከሩትን እድሜ ያሳይ*

ነበር። ነገሥታት ቢቀኑበት፣ ንጉሠ ነገሥቶች ቢሹት ሊያገኙ የማይችሉትን የታማኝነት እና የፍቅር ባለቤት ከሆነው ፊት አጎንብሼ ቀና ስል ከማን ፊት እንደቆምሁ መጠየቅ አላሻኝም።"

ለዘብ ያለ እና ክብር የተጎናፀፈ ድምፅ እንድቀመጥ ከጋበዘኝ በኋላ ንግግሩን ቀጠል በማድረግ:–

**"ለዚህ ስለበቃህ ለአምላክ ምስጋና ይድረሰው! ... እስረኛ እና ስደተኛን ለማየት መጥተሃል ...ፍላጎታችን ለዓለም ደህንነት እና ለግዛቶቹዋም ደስታ ብቻ ነው፤ ነገር ግን እስራት እና ከሀገር መባረር እንደሚገባው የጠብ ቆስቋሽ እና አነሳሽ እንደሆነ ሰው አድርገው ገመቱን... አገራት ሁሉ በእምነት አንድ እንዲሆኑ እና በሰዎች ዘንድ ወንድማማችነት እንዲፈጠር፣ የፍቅር ሠን ሠለት እና አንድነት በሰዎች ልጆች መካከል እንዲጠነክር፣ የሃይማኖት መከፋፈል እንዲወገድ እና የዘር ልዩነት ፈፅሞ እንዲጠፋ ዓላማችን ነው፤ ይህ ምን ጉዳት ያስከትላል?... ሆኖም ይህ ሁሉ ይፈፀማል፣ እነዚህ ፍሬቢስ ብጥብጦች እና ጦርነቶች አልፈው እጅግ ታላቁ ሰላም ይመሠረታል... እናንተስ በአውሮፓ ይህ አያስፈልጋችሁምን? ...ነገር ግን ነገሥታቶቻችሁ እና ገዢዎቻችሁ ሐብታቸውን ለሰው ልጅ ደስታን በሚጨምሩ ነገሮች ፋንታ የሰው ልጅ መጥፊያ በሚሆን ነገር ላይ ሲያባክኑ እናያቸዋለን። እነዚህ ብጥብጦች፣ አለመግባባት እና ደም መፋሰስ ይወገዱ፣ ሰዎችም እንደ አንድ ወገን እና አንድ ቤተሰብ ይሁኑ። ...አንድ ሰው አገሩን በመውደድ አይመካ፣ ይልቁንም መሰሉን [የሰው ልጅን] በመውደድ እንጂ።"[61]**

1. ባሃኡላህ እና አብረውት የነበሩት ከወታደሮቹ መኖሪያ እንዲለቁ የተደረጉት ምን ሁኔታዎች ስለተፈጠሩ ነበር?

___________________________________________________________________________

_

2. በአቆር የሚገኘው ባሃኡላህና ቤተሰቡ በመጨረሻ የተዘወሩበት ቤት ማን ተብሎ ይጠራል?

__________________

3. በአቆር የነበረው የአኗኗር ሁኔታቸው እንዴት ሊቀየር ቻለ?

___________________________________________________________________________

_____________________________________________

4. የዚህ ለውጥ ምክንያት ምን ነበር? ______________________________________

5. ባሃኡላህ የህይወቱን የመጨረሻ ዓመታት ያሳለፈበት መኖሪያ (እልፍኝ) ማን ተብሎ ይጠራል?

__________________________

6. አብዱል-ባሃ በባሕጂ የሚገኘውን ቤት ያገኘው በምን ሁኔታ ነበር?

_________________________

7. ባሃኡላህ በአቆር በነበረበት ወቅት ከገለፃቸው ፅሑፎች ሁሉ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው የትኛውን ነው? _______________________________________

8. የትና መቼ ነው የተገለፀው? ________________________________

9. ሾጊ ኤፌንዲ ባብራራው መሠረት በዚህ ወቅት ባሃኡላህ የገለፃቸው ፅሑፎች የሚከፈሉበት ሦስት ክፍሎች ምን ምን ናቸው?

ሀ. __________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

__

__________________________________________________________________________

__

ለ. __________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

__

__________________________________________________________________________

__

ሐ.

__________________________________________________________________________

___

__________________________________________________________________________

__

___________________________________________________________________

__

10. የባሃኡላህ የግልፅት ዘመን አንዳንድ ሕግጋት ምን ምን ናቸው?

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

________________

11. የግልፀት ዘመኑ አንዳንድ መርሆዎች (tenets) እና አስተምርሆቶች ምን ምን ናቸው?

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

________

12. ኤድዋርድ ግራንቪል ብራውን ማን ናቸው?

__________________________________

13. ኤድዋርድ ግራንቪል ብራውን በባሃኡላህ ፊት እጅ እየነሱ ሳለ ሁኔታውን ለማብራራት ምን ዓይነት ቃላትን ተጠቀሙ፣ ከእርሱ ፊት መቅረብስ የሚሰማ ስሜትስ እንዴት ያለ ነው?

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

14. በተዘገበው በኤድዋርድ ግራንቪል ብራውን አገላለጽ መሠረት:–

– ባሃኡላህ የእርሱ ፍላጎት ምንድነው አለ?

– ሁሉም ሀገሮች ምን መሆን አለባቸው አለ?

– ምን ዓይነት ነገር ተጠናክሮ እንዲያይ ፈለገ?

– ምን እንዲቆም ጥሪ አቀረበ?

– ምን እንዲያበቃ ጥሪ አቀረበ?

– ምን እንደሚያልፍ ተነበየ?

– ባሃኡላህ እያንዳንዳችን ክብርን በምን እናገኛለን አለ?

## ምዕራፍ 27

ኪታቢህ አቅዳስ ትልቅ መፅሐፍ አይደለም፤ የያዘው 190 አንቀፆችን ብቻ ነው። ሆኖም ግን ይህ መፅሐፍ የወደፊቱ የዓለም ስልጣኔን መሠረታዊ ሕግጋትና ትእዛዛትን ይዟል። ሾጊ ኤፌንዲ የባሃኡላህ የግልፀት ዘመን እናት መፅሐፍ እና የአዲሱ የዓለም ስርዓት መመሪያ ነው ብሎታል። ሐሳብዎንና ተግባርዎን ከአምላክ ትዕዛዛት ጋር ለማስተካከል ጥረት ሲያደርጉ በሕይወት ዘመንዎ ሁሉ ከኪታቢህ አቅዳስ ምንባቦችን በተደጋጋሚ ያጠናሉ። ለአሁኑ የመክፈቺያዎቹን አምስት አንቀፆች በቃልዎ እንዲይዙ ቢሆን ይመከራል።

> **“ለአገልጋዮቹ በአምላክ የታዘዘው የመጀመሪያው ተግባር እርሱን የግልፀቱ ንጋት እና የሕግጋቱ ምንጭ የሆነውን በእምነቱ መንግሥት እና በፍጥረተ ዓለም አምላክ የሚወክለውን ማወቅ ነው። ይህን ተግባር የፈፀመ ሁሉ መልካሙን ሁሉ ተቀዳጅቷል፤ ከዚያም የተነፈገ ሁሉ እያንዳንዱን የፅድቅ ሥራ ያከናወነ ቢሆንም እንኳ ከትክክለኛው መንገድ ርቋል። ወደ እዚህ እጅግ በጣም ቅዱስ ወደ ሆነው ደረጃ፣ ወደ እዚህ ወደ ላቀው ክብር የመጨረሻ ከፍታ የሚደርስ እያንዳንዱም ሰው የእርሱን የዓለማት እሾት የሆነውን እያንዳንዱን ትእዛዝ ማክበር አለበት። እነዚህ መንታ ተግባራት አይነጣጠሉም። አንዱ ያለሌላው ተቀባይነት የለውም። በእርሱ የመለኮታዊ የመንፈስ መነቃቃት ምንጭ በሆነው እንዲህ ታዟል።**
>
> **“እነዚያ አምላክ ማስተዋል ያጎናፀፋቸው ሰዎች፣ በአምላክ ከተሰጡት ሕግጋቶች በዓለም ውስጥ ሥርዓት እንዲከበር ለማድረግ ብሎም ለሕዝቦችዋ ደህንነት ከሁሉ የላቁ መሣሪያዎች**

*እንደሆኑ በቀላሉ ይገነዘባሉ። ከእነርሱም ፊቱን የሚያዞር ከወራዶች እና ከሞኞች ጋር ይቆጠራል። እኛ ክፉ ፍላጎቶቻችሁን እና የእርኩስ ምኞቶቻችሁን ግፊቶች እንዳትከተሉ፣ እንዲሁም እነዚህ እጅግ በጣም ከፍተኛው ብዕር የወሰናቸውን ገደቦች ለተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ የሕይወት እስትንፋስ ስለሆኑ ወሰናቸውን እንዳታልፉ አዘናችኋል። በመለኮታዊ ጥበብ እና በመለኮታዊ አንደበት የተነገሩት ቃላት ባሕሮች በፍፁም መሐሪው ልዝብ ንፋስ እስትንፋስ ስር ተዘርግተዋል። የመረዳት ችሎታ ያላችሁ ሰዎች ሆይ! እስክትረኩ ለመጠጣት ፍጠኑ። እነዚያ የእርሱን ትዕዛዛት በመተላለፍ የአምላክን ቃል ኪዳን የጣሱትን እና ጀርባቸውን የሰጡትን እነዚህ የሁሉ ባለቤት በሆነው፣ ከሁሉም በላይ ከፍተኛ በሆነው በአምላክ ፊት በአሳዛኝ ሁኔታ ተሳስተዋል።*

*"እናንተ የዓለም ሕዝቦች ሆይ! ትዕዛዛቱ በአገልጋዮቹ መካከል የፍቅራዊ ጥበቃዬ መብራቶች፣ ለፍጡራኔም የምሕረቴ ቁልፎች እንደሆኑ በእርግጥ እወቁ። የግልፀት ጌታ ከሆነው ከጌታችሁ ፈቃድ ሰማይ በዚህ ዓይነት ተልከዋል። ማንም ሰው የፍፁም መሐሪው ከናፍር ለመናገር የፈቀዱትን ቃላት ጣፋጭነት ቢቀምስ፣ በረከት ከተመላበት ጥበቃው እና ከፍቅራዊ ደግነቱ የቀኑ ምንጭ በላይ ከሚያበሩት የእርሱ ትዕዛዛት መካከል የአንዱን እንኳን እውነተኝነት ለማስረዳት ሲል፣ የምድር ሐብቶች ሁሉ በእጆቹ ውስጥ ቢሆኑም እንኳ አንዱንም ሳያስቀር ሁሉንም ይተዋል።*


*"በል፦ ከሕግጋቴ ጣፋጭ ሽታ ያለው የልብሴ መዓዛ ሊሸተት ይችላል፣ በእነርሱም እርዳታ የድል አርማዎች እጅግ በጣም ከፍተኞቹ ተራሮች ጫፎች ላይ ይተከላሉ። የኃይሌ አንደበት ምንም ከማይሳነው ከክብሬ ሰማይ እነዚህ ቃላት ለፍጥረቴ ተነግሯል፦ 'ለውበቴ ፍቅር ስትሉ ትእዛዛቴን አክብሩ' ምንም አንደበት ሊገልፀው የማይችለውን የፀጋ ሽቶ ከተመሉት ከእነዚህ ቃላት ከሁሉም ተወዳጁን መለኮታዊ መዓዛ ያሸተተ አፍቃሪ ደስተኛ ነው። በሕይወቴ! እርሱ በረከት ከተሞላበት የችሮታዬ እጅ የትክክለኝነት ምርጥ የወይን ጠጅ የጠጣ ከፍጥረቴ ጎህ በላይ የሆነው በሚያበሩት ትዕዛዞቼ ዙሪያ ይዞራል።*

*"ተራ ዝርዝር ሕግጋትን ብቻ የገለፅንላችሁ አይምሰላችሁ። አይደለም፤ ይልቁንም የምርጡን የወይን ጠጅ እሽግ በኃያልነት እና በሥልጣን ጣቶች ከፈትን እንጂ። ይህንንም ያ የግልፀት ብዕር የገለፀው ይመሠክራል። የማስተዋል ሰዎች ሆይ! ይህን አሰላስሉ።"*[62]

## ምዕራፍ 28

ምንም እንኳ የባሃኡላህ ተከታታይ ግዞቶች በሙስና ከዘቀጡ የሃይማኖት መሪዎች ጋር በመተባበር በሁለቱ ምድራዊ ባለሥልጣናት ትዕዛዝ የተፈፀሙ ቢመስሉም፣ ነገር ግን በእርግጥ የታዘዘው በእራሱ በፍፁም ኃያሉ አምላክ ነበር። በመጨረሻም የእምነቱ መንፈሳዊ እና አስተዳደራዊ ማዕከል ወደ ተመሠረተበት ወደ ቅድስት ሀገር እስኪደርስ ድረስ የአምላክ ክስተት የሆነው ባሃኡላህ ከትውልድ ስፍራው አንስቶ እስከ አቆር ዳርቻ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር የተለቀቁትን ኃይል አቅሞች ለማስላት አይቻልም። በመፅሐፍ ሁለት ጥናታችሁ የምታውቁት ከዚህ በታች ያለው ካራታ፣ እርሱ በግዞት የተጓዘባቸውን መንገዶች ያሳያል። በዚህ ክፍል ባካበታችሁት እይታ ላይ በመመርኮዝ፣ በእያን ዳንዱ በተጠቀሙት ቦታዎች ላይ መንፈሳዊ ጠቀሜታውን አስመልክቶ ምን ተከስቶ እንደነበር ለማሰላሰል ጥቂት ጊዜን ውሰዱ። ከእርሱ ሕይወት ጋር በተያያዘ ቁጥር ስፍር በሌላቸው ኩነቶች ላይ እያሰላሰላችሁ ሳለ፣ የእርሱን ታላቅነት እና ክብር፣ ኃያልነት እና ግርማ፣ በማስታዎስ እነዚህን የእርሱን ቃላት፦ "እርሱ እስከመጨረሻው ከሰዎች ዓይኖች የተደበቀው በክስተቱ አማካይነት

በስተቀር ሊታወቅ ከቶ አይቻልም፤ ክስተቱም ስለተልዕኮው እውነትነት ከራሱ ስብዕና የበለጠ ማስረጃ ሊያቀርብ አይችልም።” የሚለውን በአእምሯችሁ አሰላስሉ።




## ምዕራፍ 29

የአምላክ ክስተት በሰዎች መካከል በሚቆይበት ዓመታት እጅግ በጣም ልዩ የሆኑ ኃይሎችን በዓለም ሁሉ ላይ በመናኘት፣ በተፈጠሩት ነገሮች ምንነት ሁሉ ላይ ጥልቅ ለውጦችን ያመጣል። በዚህ ክብር የተመላ ቀን፣ ባሃኡላህ ለአርባ ዓመታት ያህል መገለፃቸው ሊታሰብ የማይችል ውብ የሆኑና ሥልጣኔን የሚፈጥሩ፣ የፍጠረት ዓለምን ወሰን በሌለው እምቅ ኃይሎች የሚያላብስ የአምላክን ቃል ለሰው ልጆች ገለፀ። እነኝህ ተከታታይ የአርባ ዓመታት ግልጸቶች እ.ኤ.አ ሜይ 29 ቀን 1892 ተቋጨ።

ከእርገቱ ዘጠኝ ወራት አስቀድሞ፣ ባሃኡላህ ከዚህ ዓለም ለመለየት እንደሚፈልግ ገልፆ ነበር። ከዚያን ጊዜ አንስቶ በዚህ ምድር ላይ የሕይወቱ መጨረሻ እየተቃረበ መሆኑ ከንግገሮቹ አፅንዖት ይበልጥ ግልፅ እየሆነ መጥቶ ነበር። እ.ኤ.አ ሜይ 8 ቀን 1892 ማታ በትንሹ ትኩሳት ያዘው። በሚቀጥለው ቀን ትኩሳቱ ጨመረ፤ በኋላ ደግሞ የቀነሰ መሰለ። ከወዳጆች እና መንፈሳዊ ተጓዦች አንዳንዶቹን ፊቱ እንዲቀርቡ መፍቀዱን ቀጠለ፣ ይሁንና ደህና እንዳልሆነ ወዲያው ግልፅ እየሆነ መጣ። ከበፊቱ ይበልጥ ትኩሳቱ ተጠናክሮ ተመለሰ፣ ሁኔታውም ቀስ በቀስ እየተባባሰ መጣ። እ.ኤ.አ ሜይ 29 ቀን ንጋት ላይ በ75 ዓመቱ መንፈሱ ከዚህ ዓለም ዐረገ።

ከህልፈቱ ስድስት ቀናት አስቀድሞ በባህጂ ተሰብስበው የነበሩትን ሁሉንም አማኞች እፊቱ እንዲቀርቡ ለመጨረሻ ጊዜ ጠራቸው። ከወንድ ልጆቹ በአንዱ ላይ ተደግፎ በአልጋ ላይ እንዲህ አላቸው፦ “በሁላችሁም በጣም ተደስቻለሁ። ብዙ ግልጋሎቶች ሰጥታችኋል፤ በሥራችሁም በጣም ትጋት አሳይታችኋል። በየጠዋቱ እና ምሽቱ እዚህ ተገኝታችኋል። አንድነታችሁን ይዛችሁ

እንድትቆዩ አምላክ ይርዳችሁ። የፍጥረት ጌታ እምነቱን እንድታራምዱ እርሱ ያግዛችሁ።"[63] በእርሱ ዙሪያ ከተሰባ ሰቡት ዓይኖች እንባዎች ጎረፉ።

የሕልፈቱ ዜና ወዲያው በቴሌግራም ለሱልጣኑ ተላለፈ። ቴሌግራሙ በእነኝህ ቃላት ይጀምራል፤ "የባሃ ፀሐይ ጠለቀች" ከዚያም ቅዱስ አስከሬኑን በእልፍኙ አቅራቢያ (ባህጂ) ለመቅበር እንደታቀደ በመግለፅ ይቀጥላል። ከእልፍኙ በስተምዕራብ በሚገኝ ቤት ውስጥ ያለች አንዲት ትንሽ ክፍል ተመረጠች፤ በአረገበትም ዕለት ከፀሐይ መጥለቅ ትንሽ ከቆየ በኋላ አካሉ እንዲያርፍ ተደረገ። የእነዚያን ቀናት ሐዘን ናቢል በሚቀጥሉት ቃላት ገልፆ ነበር፦ "እኔ እንደመሰለኝ በትቢያው ዓለም የተቀሰቀሰው መንፈሳዊው ሁካታ የአምላክን ዓለማት እንዲንቀጠቀጡ አደረጋቸው። …የነበርንበትን ሁኔታ ለመግለፅ ውስጣዊና ውጫዊ ልሳኔ ኃይል አልባ ናቸው …በነገሰው ግራ መጋባት መካከል እልፍኙንና በዙሪያው ያሉትን ሜዳዎች የሞሉት የአቆር እና የአጎራባች መንደሮች ነዋሪዎች ሲያለቅሱ፣ ራሳቸውን ሲደልቁ እና ሐዘናቸውን በከፍተኛ ድምፅ ሲገልፁ ይታዩ ነበር።"[64]

ለአንድ ሙሉ ሳምንት፣ ለባሃኡላህ ቤተሰብ ሐዘናቸውን ለመግለጽ የሚመጡ የማያቋርጥ የሐዘንተኞች ጎርፍ ነበር። ከሁሉም ዓይነት የኅብረተሰብ ክፍል የተገኙ ታዋቂ ሰዎች፣ ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖች፣ አይሁዶች፣ የቅኔ ሊቆች፣ ካህናት እና የመንግሥት ባለሥልጣናት እርሱ በመታጣቱ የመጣውን ሐዘን ለመካፈል እና ምግባሩን እና ታላቅነቱን ለማሞገስ ተሰባሰቡ። እንዲያውም ከመካከላቸው አንዳንዶቹ የፅሑፍ ውዳሴ አቅርበው ነበር። ተመሳሳይ የሆኑ የሐዝን መግለጫ ጽሑፎች በአካባቢው ካሉ ከተሞች ሁሉ ደረሱ። ሁሉም የተሰጡት አሁን የባሃኡላህን እምነት ለሚወክለው አብዱል-ባሃ ነበር። ሆኖም ግን እነዚህ የሐዘን መግለጫዎች በሞግዚቱ ቃላት እንዲህ በሚል ተገልፆ አል፦ "የእርሱን እምነት የተቀበሉ እና ሰንደቁን በፋርስ፣ በሕንድ፣ በሩሲያ፣ በቱርክ፣ በፍልስጤም፣ በግብፅ እና በሶርያ ከፍ ለማድረግ በቁርጠኝነት ከተነሱት ከአሃዝ በላይ ከሆኑ ሺህዎች ልቦች፣ የእውነት ፀሐይ በጠለቀች ሰዓት የፈሰሰው የሐዘን ውቅያኖስ እና ያልተገደበ ፅናት ተቆጥረው ከማያልቁ ማስረጃ ዎች ጋር ሲወዳደሩ እንደ አንድ ጠብታ ናቸው።"

አሁን፣ ከላይ በቀረቡት አንቀፆች ላይ ከሰላሰሉ በኋላ፣ ከቡድን አባላቶቻችሁ ጋር በመጣመር ተራ በተራ የባሃኡላህ እርገትን ታሪክ በራሳችሁ ቃላት ተርኩ።

## ምዕራፍ 30

ከባሃኡላህ ህልፈት በኋላ በጉብኝት መልዕክት የተካተቱትን ምንባቦችን እንዲመርጥ ናቢል በአብዱል-ባሃ ተመረጠ። ይህ መልዕክት በአሁኑ ወቅት በባብ እና በባሃኡላህ መካ-ነመቃብራት ላይ ይደገማል። እንዲሁም አብዛኛውን ጊዜም በየዓውደ ዓመቶቻቸው ለመዘከር ይውላል። የባሃኡላህ እርገት ሜይ 29 ከንጋት በፊት (ከምሽቱ 9 ሰዓት) ይከበራል። በማህበረሰብዎ በሚካሄዱ መሰል ስብሰባዎች በንቃት እየተሳተፉ ሲሄዱ፣ ከፅሑፉ ጋር እየተዋወቁ በመሄድ የፅላቱን ውበት እየተረዱ ይመጣሉ። በመሆኑም፣ በባሃኡላህ ሕይወት ላይ ያተኮረውን ይህንን ኮርስ ለማጠናቀቅ በዚህ ፅላት ላይ ማንበብ እና ማሰላሰል ተገቢ ይሆናል።

> **"አቤቱ አንተ የታላቅነት ክስተት፣ የዘለዓለም ንጉሥና በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ ጌታ ሆይ! ከሁሉም በላይ ከተከበረው ሕልውናህ ጎሕ የቀደደው ምስጋና፣ ከሁሉም በላይ አንፀባራቂ ከሆነው ውበትህ ያበራው ክብር በአንተ ላይ ይረፍ! በአንተ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ገዥነቱ፣ የአምላክ ግርማና ታላቅነቱ የተገለፁ መሆናቸውንና የጥንታዊ ጮራ የቀን ከዋክብት በማይሻረው ትዕዛዝህ ሰማይ ብርሃናቸውን መፈንጠቃቸውን፣ ያልታየውም ውበት ከፍጥረት አድማስ በላይ ማብራቱን እመሠክራለሁ። በብዕርህም እንቅስቃሴ ብቻ**

“ሁን” የሚለው ትዕ ዛዝህ እንዲከበር መደረጉን፣ የተደበቀውም የአምላክ ምስጢር መገለፁን፣ የተፈጠሩት ነገሮችም ሁሉ መፈጠራቸውን ግልፀቶችም ሁሉ መገለፃቸውን እመሰክራለሁ።

ከዚህም በላይ በአንተ ውበት የተወዳጁ ውበት መገለጹን፣ በገጽታህም የተናፈቀው ገጽታ ማብራቱን፣ ከአንተም በመነጨ አንድ ቃል ብቻ ለአንተ ታማኝ የሆኑት ወደ ከፍተኛው የክብር ጫፍ እንዲመጥቁ ከሐዲዎች ግን ወደ መጨረሻው ጥልቅ አዘቅት እንዲወርዱ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ መካከል መወሰንህን እመሠክራለሁ።

አንተን ያወቀ አምላክን ማወቁን ወደ አንተ ዘንድ መቅረብን የተቀዳጀውም እግዚአብሔር ፊት የቀረበ መሆኑን እመሠክራለሁ። ስለዚህ በአንተና በምልክቶችህ ያመነ በሉዓላዊንነትህም ፊት ራሱን ዝቅ ያደረገ፣ አንተንም የማየት ክብር ያገኘ፣ ለፈቃድህም ታዛዥ የሆነ፣ በአንተም ዙሪያ የዞረ፣ በዙፋንህም ፊት የቆመ ቡራኬው ታላቅ ነው። በአንተ ላይ በደል የፈፀመ፤ አንተን የካደ፣ በምልክቶችህ ያላመነ ሉዓላዊነትህን ያቃለለ፣ በአንተም ላይ ያመፀ፣ በአንተ ላይ እብሪተኛ የሆነ፣ ማስረጃዎችህን የተከራከረ ከግዛትህና ከመንግስትህ የሸሸ፣ አንተ ስሞቻቸውን ለይተህ በተቀደሱ መልእክቶችህ ላይ በትዕዛዝህ ጣቶች ካሠፈርካቸው ከሐዲዎች ጋር የተቆጠረ ወዮለት።

አምላኬና ተወዳጄ ሆይ፣ እንግዲህ፣ ከራሴና ከዓለም አርቀው ወደ ቅርበትህና አንተ ወደምትገኝ በት መንበሮች ያቀርቡኝ ዘንድ ከምሕረትህና ከፍቅራዊ ደግነትህ ቀኝ እጅ የችሮታዎችህን ቅዱስ እስትንፋሶች አርብብብኝ። የሚያስደስትህን ለመፈፀም ኃይል አለህ። በእውነቱ አንተ በሁሉም ነገሮች ላይ የበላይ ነህ።

አንተ የእርሱ ውበት የሆንክ ሆይ! የአግዚአብሔር ምስጋናና አስታዋሽነት፣ የአምላክ ክብርና የእርሱ ግርማ በአንተ ላይ ይረፍ። የፍጥረት ዓይን እንደ አንተ በደል የደረሰበትን ፍጹም አይቶ እንደማያውቅ እመሠክራለሁ። የሕይወትህን ቀናት ሁሉ በስቃይ ውቅያኖስ ውስጥ እንድትሰጥም ተደርገሃል። በአንድ ወቅት በእግር ብረትና በሠንሰለት ታስረሃል፤ በሌላው ደግሞ የጠላቶችህ ሰይፍ ማስፈራሪያ ደርሶብሃል። ይህም ሁሉ ሆኖ ግን አንተ በሁሉን አዋቂው በፍጹም ጠቢቡ የታዘዝከውን ሰዎች ሁሉ እንዲያከብሩ አዘሃል።

ስለደረሱብህ በደሎች መንፈሴ መስዋዕት ይሁን፣ ስለተቀበልካቸውም መከራዎች ነፍሴ ቤዛ ትሁን። በአንተና በፍጡራንህ መካከል የተጋረደውን ግርዶሽ እንዲያስወግድ፣ የዚህኛውንና የመጪውንም ዓለም መልካም ነገር እንዲለግለሰኝ፣ በአንተና በእነዚያ ፊቶቻቸው በገጽህ ብርሃን ድምቀት በበሩት፣ ለአንተም ፍቅር ሲሉ የታዘዙትን ሁሉ በፈፀሙት እግዚአብሔርን እማፀነ ዋለሁ። በእውነቱ አንተ ፍጹም ኃያሉ፣ ከሁሉም በላይ የተከበረው፣ ፍጹም ክብር የተመላው፣ ዘለዓለም ይቅር-ባዩ፣ ከሁሉም በላይ ሩኅሩኅ ነህና።

ጌታ አምላኬ ሆይ፣ ከሁሉም በላይ የላቁት ስያሜዎችህ እስካሉና ከሁሉም በላይ የተከበሩት ባህርያትህ እስከሚኖሩበት ጊዜ ድረስ፣ መለኮታዊውን የሎጥ ዛፍ ከነቅጠሎቹ፣ ከነቅርንጫፎቹ ከነቀንበጦቹ፣ ከነግንዶቹ ከነውልዶቹ ባርከው እንግዲህ ከጠብ አጫሪው ተንኮልና ከጭቆና ሠራዊት ጠብቀው። በእውነቱ አንተ ፍጹም ኃያሉ፣ ከሁሉም በላይ ኃይል የተመላው ነህና። ጌታ አምላኬ ሆይ ወደ አንተ የቀረቡትንም አገልጋዮችህንና ሴት አገልጋዮችህን ባርካቸው፣ አንተ በእውነቱ ፍፁም ለጋሱ፣ ፀጋው ወሰን የሌለው ነህና። ከአንተ ከዘላለም ይቅር-ባዩ ከሁሉም በላይ ለጋሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም።”[65]

## ምዕራፍ 31


ከእራስዎ ልምድ በመነሳት፣ እንደሚያውቁት በሚመጡት ብዙ ዓመታት የባሃኡላህን ታሪክ ለመተረክ ብዙ እድሎች እንደሚያጋጥሞት ይረዳሉ። መፅሐፍ ሁለትን ካጠኑ በኋላ፣ እንደአንድ የጥልቀት ትምህርት ጭብጥ የጓደኞችዎን እና የጎረቤቶችዎን ቤቶች በጎበኙበት ጊዜ የእርሱን ሕይወት በአጭሩ እና በደምሳሳው ለመተረክ እና ታሪኩን ለመጋራት ያለጥርጥር ብዙ አጋጣሚዎችን ተጠቅመዋል። አሁን እያጠኑ ያሉት ታሪክ በመፅሐፍ ሁለት ካጠኑት የበለጠ ዘርዝር ያለ እና ለውይይትዎ ብዙ መወያያ ነጥቦችን የሚያነሳ እና ስለ ባሃኡላህ ሰብዕና፣ እና የእርሱን ህይወት ኩነቶች በተመለከተ ብዙ አዳዲስ እውቀቶችን እንዲያካብቱ ረድቶታል። ከዚህም በላይ፣ የእርሱን ግልፀት፣ የእርሱን ተልዕኮ ባህርይ፣ በእርሱ መከሰት ምክንያት ስለተለቀቁት ኃይሎች፣ እና በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የዚህን ጊዜ አስፈላጊነትን በተመለከተ እይታን አግኝተዋል። በመጨረሻም፣ ምንም ይሁን ምን፣ ለእምነቱ አዲስ ከሆነ ሰው ጋር በሚደረግ አጭር ውይይት ወይም በመንደርዎ ወይም በሰፈርዎ ውስጥ ያለ ቤተሰብን በሚጎበኙበት ጊዜ፣ ስለባሃኡላህ ስብዕና የተናገራችሁት እና ለአድማጩ ያስተላለፋችሁት አቀራረብ፣ ተፅዕኖ ማሳደሩ እና ስሜትን መንካቱ ነው ቁም ነገሩ። አዎን፣ አንዳንዴ ቀለል ያለ አቀራረብ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። በዚህ ጉዳይ የሚቀጥሉት ገፆች ሊረድዎት ይችላል።

# ባሃኡላህ

## የአምላክ ክብር




ባሃኡላህ የኢራን ዋና ከተማ በሆነችው በቴህራን ኖቬበር 12 ቀን 1817 ተወለደ። ከልጅነቱ ጀምሮ፣ የታላቅነት ምልክቶችን ይታይበት ነበር። በቤት ውስጥ የተወሰነ ትምህርት አግኝቷል ነገር ግን ትምህርት ቤት መግባት አላስፈለገውም፣ ምክንያቱም በተፈጥሮ እውቀት አምላክ ለግሶታል።



አንድ ቀን ምሽት አባቱ፣ ባሃኡላህ በውቅያኖስ ውስጥ ሲዋኝ ህልም አዩ። ከአካሉ የሚወጣው ብርሃን ውሃውን አበር ቶታል። ረጅም ጥቁር ጸጉሩ በየአቅጣጫው ተንሳራፍቷል፣ ብዙ ዓሣዎችም ተከተሉት፣ እያንዳንዳቸው የአንድን ፀጉር ጫፍ ይዘዋል። በነፃነት እና ያለ ምንም እንቅፋት ይንቀሳቀስ ነበር። ይህ ህልም ባሃኡላህ ታላቅ እጣ ፈንታ እንደሚ ጠብቀው ከሚያሳዩ ብዙ ማስረጃዎች አንዱ ነበር።



ባሃኡላህ ወጣት ሳለ፣ በንጉሡ ቤተ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ተሰጠው፣ እሱ ግን እምቢ አለ። የተጨቆኑትን፣ የታመሙትን፣ ድሆችን ለመርዳትና ለፍትህ ዘብ በመቆም ጊዜውን ለማሳለፍ ፈለገ።



ባሃኡላህ 27 ዓመት ሲሆነው፣ መምጣቱ ለዘመናት ሁሉ የተስፋ ቃል የተገባለትን የአምላክ መልዕክተኛ እንዲቀበሉ ሰዎችን ሲያዘጋጅ ከነበረው ከባብ የተጠቀለለ ጽሑፍ ተቀበለ፡፡ መልዕክቱን ከተቀበለ በኂላም ከጽኑ ተከታዮቹ አንዱ ሆነ፡፡



ባለሥልጣናቱ ባብ ያወጀውን እውነት ለመቀበል ፈቃደኛ ሳላልሆኑ በእርሱ የሚያምኑትን ለማሰቃየት ተነሱ፣ የባሃኡላህ መከራም ጀመረ። እ.ኤ.አ. በ1852፣ ተይዞ በሰንሰለት ታስሮ እጅግ አስፈሪ በሆነው የቴህራን እስር ቤት ውስጥ ተጣለ።



በዚህ እስር ቤት ውስጥ፣ በባብ እና ባለፉት ነቢያት ሁሉ ቃል የተገባለት እርሱ መሆኑን አምላክ ለባሃኡላህ ገለጸለት፡፡ ከዚህ ጨለማ እስር ቤት የእውነት ፀሀይ ወጥታ ዓለምን እያበራች በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ አዲስ ቀንን ወለደች፡፡



ከአራት ወራት እስራት በኋላ መንግስት ባሃኡላህን ከትውልድ አገሩ አባረረው። በክረምቱ ከባድ ቅዝቃዜ፣ ባሃኡላህ እና ቤተሰቡ ከቴህራን ወደ ባግዳድ ረጅም ጉዞ አደረጉ።



በባግዳድ የባሃኡላህ ጥበብ እና ዝና በሁሉም አቅጣጫ ተስፋፋ። የእርሱን እርዳታ እና ምክር በሚፈልጉ ሁሉም ዓይነት ሰዎች ቤቱ ተጨናነቀ። የባሃኡላህን ተጽእኖ የፈራው መንግስት እሱን ከትውልድ አገሩ የበለጠ ለማራቅ ወሰነ።



# የሪዝቫን አትክልት ሥፍራ
## ኤፕሪል 1863

ባግዳድን ከመልቀቁ በፊት ባሃኡላህ ከከተማው ውጭ ባለ የአትክልት ስፍራ ውስጥ አስራ ሁለት ቀናት አሳልፏል፣ እርሱን ለመሰናበት ብዙ ጎብኚዎች ይመጡ ነበር። በዚህ የአትክልት ስፍራ፣ ባሃኡላህ ለዚህ ቀን የአምላክ መልዕክተኛ መሆኑን አውጀ። ለመጪዎቹ ዘመናት፣ ይህ የኤፕሪል ወር የአስራ ሁለት ቀናት ጊዜ የሪዝቫን በዓል ተብሎ ይከበራል። ባሃኡላህ ዓለም አቀፍ ተልእኮውን ያወጀበት ቀን ክብረ በዓል።



ሱልታን አብዱ አል-አዚዝ
የኦቶማን ኢምፓየር



ኒኮላቪች አሌክሳንደር II ፣ የሩሲያ
ንጉስ



ፍራንዝ-ጆሴፍ,
የኦስትሪያ ንጉሠ
ነገሥት



ናፖሊዮን III, የፈረንሳይ
ንጉሠ ነገሥት




የፋርስ ናስረዲን
ሻህ



ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፒዮስ ዘጠነኛ




የእንግሊዝ ንግስት
ቪክቶሪያ



ዊሊያም I,

የፕሩሲያ ንጉስ

**የባሃኡላህ ቀጣይ የግዞት ቦታ ቁስጥንጥንያ ከዛ ደግሞ አድሪያኖፕል ሲሆን ሁለቱም ዛሬ የቱርክ ከተሞች ናቸው:: እስረኛ እና ግዞተኛ የሆነው ባሃኦላህ፣ ከአድሪያኖፕል ለዓለም ነገሥታትና ገዥዎች መልዕክት ላከ:: ፍትህን እንዲያስከብሩ እና ስልጣናቸውን ተጠቅመው መከራን እና ጦርነትን እንዲያቆሙ መከራቸው::**



በአድሪያኖፕልም ልክ እንደበፊቱ የባሃኡላህ ዝና በክልሉ ነዋሪዎች መካከል ተስፋፋ፣ መንግሥትም እሱን ወደ 'አካ የእስር ከተማ አርቆ ሊያባርረው ወሰነ። ይህ የእስር ከተማ ወንጀለኞች እና የአገሪቷ ነገር ቆስቋሾች ዳግመኛ ድምጻቸው እንዳይሰማ የሚላኩበት ነበር።



የእስር ሁኔታው በጣም ከባድ ነበር፡፡ አንዳንድ የባሃኡላህ ተከታዮች ወደ ‘አካ ብዙ ርቀት ተጉዘዋል፣ ነገር ግን ወደ እርሱ እንዲገቡ አልተፈቀደላቸውም፡፡ ሊያዩት የቻሉትም፣ ከሩቅ ሆነው፣ ከእስር ቤቱ መስኮት ወደ እነርሱ ሲያውለበልብ ብቻ ነበር፡፡



በክልሉ ውስጥ ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣ ሰዎች የባሃኡላህን ኃይል እና ግርማ ሲገነዘቡ ሁኔታዎች ቀስ በቀስ ተሻሻሉ። በመጨረሻዎቹ የህይወት ዘመኑ ከከተማው ቅጥር ውጭ በሚገኘው ባህጂ በሚባለው ትልቅ ቤት ውስጥ ኖረ። በአካ፣ ባሃኡላህ ኪታብ-ኢ-አቅዳስ የተባለውን እጅግ ቅዱስ መፅሐፉን ጨምሮ ለሰው ልጅ ብዙ መመሪያዎችን ገልጿል።



ሜይ 1892 ባሃኡላህ አረፈ። በአሁኑ ጊዜ በሚያማምሩ የአትክልት ስፍራዎች የተከበበው ባህጂ ውስጥ ያለው መካነ-መቃብሩ በምድር ላይ ካሉት ሁሉ የተቀደሰ ቦታ ነው። በየዓመቱ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ከዓለም ዙሪያ የሚመጡ ሰዎች አክብሮታቸውን ለመግለጽ እና ጸጥ ባለ አከባቢ ውስጥ ለመጸለይ እና ለማሰላሰል የመካነ-መቃብሩን ቦታ ይጎበኛሉ።

**ማጣቀሻዎች**


1. በ18 ኤፕሪል 1912 ከተሠጠ ንግግር፣ በፕሮሙልጌሽን ኦፍ ዩኒቨርሳል ፒስ:– በ1912 በተባበሩት አሜሪካ እና በካናዳ በአብዱል-ባሃ የተሰጠ ንግግር (ዊልሜት፤ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 2012)፣ አንቀፅ 2፣ ገፅ 34
2. ዘ ሰመንስ ኦፍ ዘ ሎርድ ኦፍ ሆስትስ:– የባሃኡላህ ፅላቶች (ዊልሜት፤ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 2006)፣ ቁ 3. 14–15፣ ገፅ፣ 248.
3. ዝኒ ከማሁ፣ ቁ. 3. 16-17፣ ገፅ 248–49
4. ዘ ዶውን ብሬከርስ:– ናቢልስ ናሬቲቭ ኦፍ ዘ ኧርሊ ዴይስ ኦፍ ዘ ባሃኢ ሬቬሌሽን ((ዊልሜት፤ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 1932፣ 2018 የታተመ)፣ ገፅ 119
5. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 119–20
6. ባሃኡላህ ይድረስ ለተኩላው ልጅ (ዊልሜት፤ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 1988፣ 2016 የታተመ)፣ ገፅ 11.
7. አብዱል-ባሃ ኦን ዲቫይን ፊሎዞፊ (ቦስተን:– ዘ ቱዶር ህትመት፣ 1918) ገፅ፣ 53
8. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ፣ 96
9. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 104
10. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 104–05
11. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 105–06
12. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 106
13. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 107
14. ዝኒ ከማሁ
15. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 107–108
16. ሰሌክሽንስ ፍሮም ዘራይቲንግስ ኦፍ ዘ ባብ (ዊልሜት፤ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 2006፣ 2014 የታተመ)፣ ቁ፣ 3፡8.1፣ ገፅ 106–7
17. ዝኒ ከማሁ፣ ቁ፣ 3፡27.1፣ ገፅ፣ 126–27
18. ዝኒ ከማሁ፣ ቁ፣5፡21.3፣ ገፅ፣ 193
19. ዘ ዶውን ብሬረከርስ፣ ገፅ፣ 113.
20. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 116
21. ግሊኒንግስ ፈሮም ዘ ራይቲንግስ ኦፍ ባሃኡላህ (ዊልሜት፤ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 1983፣ 2017 የታተመ)፣ CXXIX, አንቀፅ፣1–2፣ 316–17
22. ፍሮም ኤ ቶክ ባይ አብዱል-ባሃ ኦን 22 ሜይ 1912፣ በፕሮሙልጌሽን ኦፍ ዩኒቨርሳል ፒስ የታተመ፣ አንቀፅ፣ 6፣ ገፅ 193–94.
23. ዘ ዶውን ብሬከርስ፣ ገፅ፣ 607–8
24. ታብሌትስ ኦፍ ባሃኡላህ ሪቪልድ አፍተር ዘ ኪታቢህ-አቅዳስ (ዊልሜት፤ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 1988፣ 2005 የታተመ)፣ ቁ፣ 4.22፣ ገፅ፣ 40.
25. ዝኒ ከማሁ፣ ቁ. 7.40፣ ገፅ 96.
26. ኢፒስቲል ቱ ዘ ሰን ኦፍ ዘ ዎልፍ፣ ገፅ. 20–21.

27. ዘ ዶውን ብሬክርስ፣ ገፅ፣ 632

28. ኢፕስቲል ቱ ዘ ሰን ኦፍ ዘ ዎልፍ፣ ገፅ. 21

29. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 22

30. ዘ ሰመንስ ኦፍ ዘ ሎርድ ኦፍ ሆስትስ፣ ቁ፣ 1.6፣ ገፅ 6–7

31. ግሊኒንግስ ፊሮም ዘ ራይቲንግስ ኦፍ ባሃኡላህ፣ XXIX, አንቀፅ፣ 5፣ ገፅ. 80.

32. እንደ ሾጊ ኤፌንዲ በጁን 24 ቀን 1936 ከተፃፈ ደብዳቤ፣ ኢን "ክራይሲስ ኤንድ ቪክትሪ፡ ከባሃኢ ፅሑፎች የተውጣጣ፣" የዓለም ዓቀፍ ቤተ ፍትሕ የምርምር ተቋም፣ የኮምፓይሌሽን ኮምፓይሌሽን (ሜሪቦሮው፡ ባሃኢ ህትመት ኡስትራሊያ፣ 1991) ቮልዩም.1፣ ቁ. 287፣ ገፅ. 148)

33. ኤች. ኤም፣ ባልዩዚ፣ ባሃኡላህ፡ ዘ ኪንግ ኦፍ ግሎሪ (ኦክስፎርድ፡ ጆርጅ ሮናልድ፣ 1991፣ 2018 ህትመት)፣ ገፅ. 106.

34. ባሃኡላህ፣ በሾጊ ኤፌንዲ እንደቀረበው፣ ጎድ ፓስስ ባይ (ዊልሜት፤ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 1974፣ 2019 የታተመ)፣ ገፅ. 169–70

35. ባሃኡላህ፣ የእርግጠኝነት መፅሐፍ፣ ዘ ኪታቢ ኢቃን (ዊልሜት፤ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 2003፣ 2018 የታተመ)፣ አንቀፅ፣ 278፣ ገፅ፣ 231.

36. ባሃኡላህ፣ በሾጊ ኤፌንዲ እንደቀረበው፣ ጎድ ፓስስ ባይ፣ ገፅ 178–79

37. ናቢል-ኢ-አዛም፣ በጎድ ፓስስ ባይ እንደተጠቀሰው፣ ገፅ 215–16.

38. ኢፕስቲል ቱ ዘ ሰን ኦፍ ዘ ዎልፍ፣ ገፅ፣ 22.

39. ባሃኡላህ፣ በሾጊ ኤፌንዲ እንደቀረበው፣ ጎድ ፓስስ ባይ፣ ገፅ፣ 226.

40. ዘ ኪታቢ ኢቃን፣ አንቀፅ 1. ገፅ፣ 3.

41. ባሃኡላህ፣ ህቡዓተ ቃላት (ዊልሜት፤ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 2003፣ 2012 የታተመ)፣ ገፅ. 3

42. ባሃኡላህ፣ በሾጊ ኤፌንዲ እንደቀረበው፣ ጎድ ፓስስ ባይ፣ ገፅ፣ 147

43. ባሃኡላህ፣ ኪታቢህ-አቅዳስ፡ ዘ ሞስት ሆሊ ቡክ (ዊልሜት፤ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 2003፣ 2012 የታተመ)፣ አንቀፅ፣ 75፣ ገፅ. 48.

44. ናቢል-ኢ-አዛም፣ በጎድ ፓስስ ባይ እንደተጠቀሰው፣ ገፅ፣ 240–241

45. ግሊኒንግስ ፊሮም ዘ ራይቲንግስ ኦፍ ባሃኡላህ፣ XIV፣ አንቀፅ፣ 1፣ 4–5፣ 11–12፣ ገፅ፣ 29–34.

46. ጎድ ፓስስ ባይ፣ ገፅ፣ 252

47. ባሃኡላህ፣ በጎድ ፓስስ ባይ እንደቀረበው፣ ገፅ፣ 292–93

48. ኤች. ኤም. ባልዩዚ፣ ባሃኡላህ፡ ዘ ኪንግ ኦፍ ግሎሪ፣ ገፅ 317–19

49. ባሃኡላህ፣ በጎድ ፓስስ ባይ እንደቀረበው፣ ገፅ፣ 292.

50. ዘ ፐሮክላሜሽን ኦፍ ባሃኡላህ ቱ ዘ ኪንግ ኤንድ ሊደርስ ኦፍ ዘ ዎርልድ (ሃይፋ፡ የባሃኢ ዓለም ማእከል፣ 1967፣ 1972 ህትመት) ገፅ፣ 17.

51. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 28

52. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 33

53. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 39

54. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 43

55. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 47

56. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 60

57. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 63

58. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 84

59. ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ፣ 95

60. ጎድ ፓስስ ባይ፣ ገፅ፣ 325

61. ኤድዋርድ ግራንቪል ብራውኒ፣ ሪኮርዲንግ ዘ ምርደስ ኦፍ ባሃኡላህ፣ በኤች.ኤም. ባልዩዚ፣ ባሃኡላህ፤ ዘ ኪንግ ኦፍ ግሎሪ፣ ገፅ 378–80.

62. ባሃኡላህ፣ በኪታቢህ አቅዳስ፡ አንቀፅ 1–5፣ ገፅ፣ 21–23

63. ባሃኡላህ፣ በጎድ ፓስስ ባይ እንደቀረበው፣ ገፅ፣ 350–51

64. ናቢል-ኢ-አዛም፣ በጎድ ፓስስ ባይ እንደተጠቀሰው፣ ገፅ፣ 351–52

65. ባሃኡላህ፣ በባሃኢ ፀሎቶች ውስጥ፣ ኤ ሴሌክሽን ኦፍ ፕሬየርስ ሪቪልድ ባይ ባሃኡላህ፣ ዘ ባብ ኤንድ አብዱል-ባሃ (ዊልሜት፤ የባሃኢ አሳታሚ ድርጅት፣ 2002፣ 2017 የታተመ) ገፅ፣ 323–27